# የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሴት



# የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሴት

መሰረታዊ መመሪያ መጽሀፍ ለሴቶች፣ ክፍል ሀ

እንደገና የታተመ
በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ታተመ
ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ

© 2000 by Intellectual Reserve, Inc.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
በዩ. ኤስ. ኤ. ታተመ
እንግሊዝኛው የፀደቀበት፣ 1998
ትርጉሙ የፀደቀበት፣ 1999
Translation of *Latter-day Saint Woman: Basic Manual for Women, Part A*
Amharic

# ማውጫ

መግቢያ .......................................v
የትምህርት ቁጥር እና ርዕስ

**ክፍል 1፥ የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች እና ትምህርቶች**

1. በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን .......................1
2. ንስሃ .......................................11
3. ጥምቀት፣ ምንጊዜም የሚኖር ቃልኪዳን ..............21
4. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ .........................28
5. ምስክርነት .................................35
6. ጾም .......................................41
7. አክብሮት ...................................46
8. ፍቅር፣ ደግነት፣ እና አገልግሎት .................52
9. ንጽህና እና ትህትና ............................56
10. ዘለዓለማዊ ጋብቻ .............................62

**ክፍል 2፥ ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ**

11. የክህነት አስፈላጊነት ..........................71
12. የክህነት ሥነ ሥርዓቶች ........................77
13. ሴቶች እና የክህነት ሥልጣን .....................85
14. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሴት .......................90
15. ከቤተሰቦቻችን ጋር መማከር .....................100
16. የቤተሰብ የቤት ምሽት ........................107
17. የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች .....................113
18. የሚሲዮናዊነት ሥራ እና ጓደኝነት ..................121
19. ሚስዮናውያንን ማዘጋጀት እና ማበረታታት ...........128

**ክፍል 3፤ ባልትና**

20. ቤቶቻችንን በሚገባ ማስተዳደር ....................135
21. የቤተሰብን ገንዘብ አያያዝን ማስተዳደር ..............141
22. የቤተሰብ የአመጋገብ ዘዴ .......................148
23. ለእናትና ለሕፃኑ አልሚ ምግብ .....................153
24. በሽታን መከላከል ...............................157
25. የጓሮ አትክልትን መትከል .........................164
26. የቤት ምርት ...................................175

## ክፍል 4፡ የቤተሰቡ እና የግል እድገት

27. ተሰጥዎአችንን ማጎልበት ....................................185
28. የቀጥር ሙያዎችን ማዳበር ..................................193
29. የሥራን ጥቅም እና ኃላፊነትን ለቤተሰቦች ማስተማር ....................202
30. ራስን መግዛትን ማስተማርና ማጎልበት ..........................210
31. በቤታችን በጎና አበረታች ሁኔታን መፍጠር ........................216
32. በቤታችን ውስጥ ወንጌልን መማር ............................227
33. ለማስተማር መዘጋጀት ......................................235
34. ከቅዱሳን መጽሐፍት ማስተማር ...............................243
35. በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ተፅዕኖ ማስተማር .........................251
የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንቶች ...................................257
የተጠቀሱ ምንጮች ..........................................260
ሥዕሎች .................................................265

# መግቢያ

ይህ የሴቶች እና የልጃገረዶች መመሪያ መፅሐፍ ለቤተክርስቲያኑ አዲስ አባላት እና ለሌሎች መሰረታዊ የወንጌል ህጎችን መማርን ለሚፈልጉ ሰዎች የተዘጋጀ ነው። ትምህርቶቹ የታለሙት የወንጌልን ህጎች እና ትምህርቶችን ለማስተማር ብቻ ሳይሆን የቤተክርስቲያኑ ሴቶች (1) ወንጌልን እንዲያፈቅሩ፣ (2) በትምህርቱ መኖርን እንዲፈልጉ፣ (3) የተሻለ ጥሩ የባልትና አዋቂ እንዲሆኑ፣ እና (4) ጊዜያቸውን፣ ችሎታቸውን፣ እና ሐብታቸውን ቤተሰባቸውን ለመባረክ እና የእግዚአብሔር መንግስትን ለመገንባት በበለጠ ጥበብ እንዲጠቀሙበት ለማበረታታት ጭምር የተዘጋጀ ነው።

አንድ ቅርንጫፍ በተቋቋመበት አካባቢ፣ ይህ በሰንበት ስብሰባ ጊዜ ለሴቶች እና ለልጃገረዶች እንደ የትምህርት መመሪያ መፅሐፍ ሆኖ ያገለግላል። ይህ ስብሰባ ወንድሞች በክህነት ስብሰባ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ይከናወናል። የሴቶች መረዳጃ ማኅበር ፕሬዝዳንቷ ስብሰባውን ትመራለች እንዲሁም ለቅርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ሴቶቹ ትምህርት እንዲያስተምሩ እንዲጠራቸው ስማቸውን ትጠቁማለች።

### የግል ጥናት

በሳምንቱ ውስጥ እያንዳንዷ እህት የራሷን መመሪያ መፅሐፍ ቅጂ ማጥናት አለባት፣ ወደ ክፍሉ ስትመጣ መመሪያ መፅሀፍዋን እና ቅዱሳን መጻሕፍቶቿን ማምጣት አለባት፣ እንዲሁም በውይይቱ ውስጥ ለመሳተፍ መዘጋጀት አለባት። ከትምህርቶቹ የምታገኛቸውን እውቀቶች በቤትዋ ውስጥ ልትጠቀምባቸው ትችላለች፣ እንዲሁም በቤትዋ ውስጥ የተሻለ የቤተሰብ አባል እና መምህር እንድትሆን ይረዳታል። በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ የተጠቀሱት መልመጃዎች ከትምህርቱ ያገኙትን ዕውቀት ተግባር ላይ እንዲያውሉት መርዳት አለባቸው።

### የመምህር ድጋፎች

የመምህሯን መመሪያ በትምህርቶቹ መጨረሻ ላይ በ "የመምህር ዝግጅት" በሚለው ርዕስ ሥር ተካተዋል። የወንጌል መሰረታዊ ደንቦችን (መመሪያ መጽሐፍ) ከዚህኛው መመሪያ መጽሐፍ ጋር አንድ ላይ አጥኑ፣ በተለይ "የመምህር ዝግጅት" በሚለው ርዕስ ሥር ያሉትን ትምህርቶች መምህሩ የክፍሉ አባላትን ከወንጌል መሰረታዊ ደንቦች የተማሪ ማመልከቻ እንድያቀርቡ ሊመድቧቸው ይችላሉ። ለበቂ ዝግጅት ምደባው በትክክል ከጊዜው ቀደም ብሎ መደረግ አለበት።

በአብዛኛው ትምህርቶች ውስጥ ስዕላዊ መግለጫዎች ተካተዋል።

ለመምህሯ መመሪያ እና ለክፍሉ ተማሪዎች መወያያ ጥያቄዎች መምህሯ በቀላሉ መለየት እንዲችሉ በትንንሽ ፊደላት ተለይተው ተጽፈዋል። መምህሯን ክፍሉ የተሻለ ትርጉም ያለው እንዲሆን ሌሎች ዘዴዎች እና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ።

በተቻለ መጠን በክፍሉ ውስጥ በጣም ወጣት የሆኑ አባላት በክፍል ውይይት እንዲሳተፉ ያድርጉ። ትምህርቶቹ ለባልትና እና የእግዚአብሔርን መንግስት ለመገንባት እንዲዘጋጁ ይረዷቸዋል።

**ትምህርቶች**

በዚህ መምሪያ መፅሐፍ ውስጥ ሰላሳ አምስት ትምህርቶች ብቻ ተካተዋል። ይህም በዓመቱ ውስጥ ለተጨማሪ ትምህርት የሚሆን የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲኖር ይረዳል። አስተማሪው ተጨማሪ ጥናት ለማያስፈልጋቸው ትምህርቶች ከአንድ በላይ ክፍለ ጊዜ ሊጠቀም ይችላል። የትምህርት ክፍለ ጊዜዎቹ አንዳንድ ጊዜ ለክፍል ውስጥ ሰርቶ ማሳያ ለተጋባዥ ተናጋሪ፣ ለምስክርነት ስብሰባ፣ ወይም መምህርዋ እና የክፍሉ ተማሪዎች ጠቃሚ ነው ብለው ላሰቡት ሌላ ነገር ሊመደቡ ይችላሉ።

ቢሆንም በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ትምህርቶች በሙሉ መሰጠት አለባቸው። አብዛኛው ትምህርቶች ሁሉንም እህቶች ይመለከታሉ፣ ነገር ግን መምህርዋ የባልትና ትምህርቱን ፍላጎታቸውን እንደሚያረካ አድርጋ ማቅረብ አለባት።

በአራቱ ክፍሎች ያሉትን ትምህርቶች በቀደም ተከተል ማጥናቱ በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን፣ መምህርዋ ወቅታዊ ትምህርቶችን በተገቢው ጊዜ ማስተማር አለባት። ትምህርት 25 ስለ ጓሮ አትክልት የሚያስተምረው ትምህርት አንዱ ምሳሌ ነው፣ ይኸውም ከዘር መዝሪያ ወቅት ቀደም ብሎ በደንብ መሰጠት አለበት።

የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንቶች ስዕል እና የሕይወት ታሪክ መረጃ ለጠቀላላ ዕውቀት በዚህ መምሪያ መፅሐፍ ተካተዋል። ከነዚህ ወንድሞች እና ከሌሎች የበላይ ባለስልጣኖች ጥቅሶች በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተዋል።

# በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን

ትምህርት 1

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን እምነት ለማጠንከር እንዲረዳን ነው።

---

“እምነት ማለት ስለ ነገሮች ፍፁም የሆነ እውቀት መያዝ አይደለም፤ ስለዚህ ዕምነት ካላችሁ የማይታዩት ነገሮች እውነት እንደሆኑ ተስፋ ታደርጋላችሁ” (አልማ 32፥21)።

እምነት ምንድን ነው? እምነትን ዛሬ እንዴት ነው በተግባር ላይ የምታውሉት?

**መጀመሪያ፤ እውነትን መማር ይገባናል**

በኢየሱስ ክርስቶስ እምነትን ለማሳደግ፤ በትክክል ማን እንደሆነ ማወቅ ይገባናል። ስለእርሱ ምንም የማናውቅ ከሆነ በእርሱ እምነት ሊኖረን አይችልም። ስለእርሱ የምናውቀው ነገር እውነት ካልሆነ በስተቀር በእርሱ እምነት ሊኖረን አይችልም።

አዳኛችንን በምድር ላይ ያዩት ጥቂት ሰዎች ናቸው። አብዛኞቻችን በዚህ ሥጋዊ ሕይወታችን እሱን የማየት አጋጣሚ አናገኝም፤ ግን ስለ እርሱ እውነታ ማወቅ የእኛ ተግባር እና ልዩ መብት ነው። በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ስለ እርሱ ትክክለኛ ዕውቀት ሊኖረን ይገባል። ስለ እርሱ እውነትን ማወቅ እሱን እንድናምነው፤ እንድንታዘዘው፤ እራሳችንን ለመርዳት ከአቅማችን በላይ ለሆኑ ነገሮች እንደሚረዳን ለመተማመን ይረዳናል።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሳሳተ አስተሳሰብን ማስወገድ ለምንድነው የሚያስፈልገው?

“ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።” (ወደ አብራውያን ሰዎች 11፥6)።

ከዚህ ጥቀስ እግዚአብሔርን ለማስደሰት በእሱ እምነት ሊኖረን እንደሚገባን እንማራለን። እምነት እንዲኖረን ከተፈለገ (1) እርሱ እንዳለ ማመን፤ እና (2) እርሱን ለማወቅ እና ከእርሱ ዕርዳታ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ስናደርግ መልሱን እንደሚሰጠን ማመን አለብን። እነዚህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሁለቱ በጣም ጠቃሚ እውነታዎች ናቸው።

እምነት በእውነት ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት። ምንም ያህል በተሳሳተ ዛሳብ ብናምንም፤ በፍፁም እውነት ሊሆን አይችልም፤ እንዲሁም፤ በውስጡ ለእምነት የሚሆን ምንም መሰረት የለም።

እህቶችን ከድሮው የተሳሳተ ሀሳብ ይልቅ እውነተኛውን የወንጌል መሰረታዊ ዛሳቦች ማወቃቸው ያመጣላቸውን ከፍተኛ ደስታ እንዲያነፃፅሩ ይጠይቁዋቸው።

ስዕል 1-ሀ፤ አንዲት በዕድሜ የገፉ ሴት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማወቅ ቅዱሳን መፃሕፍትን ሲያጠኑ፤ 1-ለ፤ ወንጌላውያን በዓለም ዙሪያ ወንጌልን ለሰዎች ሲያስተምሩ፤ እና 1-ሐ፤ አንድ ቤተሰብ ቅዱሳን መፅሐፍትን በሕብረት ሲያጠኑ የሚያሳዩትን፤ ስዕሎች እንዲመለከቱ ያድርጉ።

1-ሀ፤ አንዲት በዕድሜ የገፉ ሴት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማወቅ ቅዱሳን መጻሕፍትን ሲያጠኑ።
ፎቶግራፍ በሐሮልድ ኤም ላምበርት።
1-ለ፤ ሚሲዮናዊያን በዓለም ዙሪያ ወንጌልን ለሰዎች ሲያስተምሩ።



1-U



1-ለ



ቅዱሳን መፃሕፍትን ማጥናት እና በምድር ላይ ያሉ የጌታ አገልጋዮችን ምስክርነት መስማት አለብን። ከዚያም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ስለ ወንጌሉ እውነታ ልንማር እንችላለን። ትሁት፣ ታማኝ፣ እና ፀሎተኛ ከሆንን፣ እርሱ የሰማይ አባታችን አንድያ ልጅ እንደሆነ፣ ዛሬም እንደሚኖር፣ ምንም እንኳን ፍፁማን ባንሆንም፣ እያንዳንዳችንን እንደሚወደን ለራሳችን ማወቅ እንችላለን። እሱ ሁሉንም እውነት እንደሚያውቅ መማር እንችላለን። ይህን እውነት ለማግኘት በጣም ለሚጥሩ ይገለፅላቸዋል። ክፉዎችን የሚቀጣ ፍትሀዊ አምላክ እንደሆነ፣ ነገር ግን ንስኃ ለሚገቡ ይቅርታ አድራጊ አምላክ እንደሆነ ልንማር እንችላለን። ስለ ኃጢያታችን እንደከፈለ እና ሁላችንንም ለትንሳኤ እንዳቀረበን ማወቅ እንጀምራለን። ይህ እውነት በልባችን ሲያድር እና ሲያድግ፣ ጥርጣሬ እና ፍርሐት ሚምተው መጥፋት ሲጀምሩ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለን እምነት በእኛ ውስጥ ያድጋል።

ቅዱሳን መፃሕፍቶችን ማጥናት ጥርጣሬ እና ፍርሀት በእምነት እንዲቀየሩ እንዴት ይረዳናል? እምነታችንን ለመገንባት ሌሎች ምን ነገሮች ሊረዱን ይችላሉ?

በኢየሱስ ክርስቶስ የነበራቸውን እምነት እንዴት ማዳበር እንደቻሉ በአጭሩ እንዲናገሩ የተወሰኑትን እህቶች ይጠይቋቸው።

## እምነታችንን በተግባር ላይ ማዋል አለብን

ቅዱሳን መጻሕፍትን በማጥናት፣ በፆም፣ በፀሎት፣ እና የሌሎችን ምስክርነት በመስማት እውነትን ልናውቅ እንችላለን። ነገር ግን፣ እውነትን ማመን ብቻ በእምነት እየተጠቀምን ነው ማለት አይደለም። ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ እና ወንጌል እውነተኛ መሆኑን የሚያውቁ ሰዎች አሉ፣ ነገር ግን የእርሱን ትዕዛዛት አይጠብቁም። እነዚህ ሰዎች እምነትን በተግባር ላይ እያዋሉ አይደሉም። እምነት በእንቅስቃሴ ያለ ኃይል ነው። እምነት ካለን ኢየሱስ ክርስቶስ በትዕዛዙ መኖር እንድንችል መንገድ እንድንፈልግ እንደሚረዳን እናምናለን።

ቅዱሳን መፅሐፍት እንደሚከተለው ያስተምሩናል፥

"በፍፁም ልብህ በእግዚአብሄር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ።

"በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል።" (ምሳሌ 3፥5-6።)

ኔፊ እምነት የነበረው እና ጌታ ትዕዛዛቱን እንዲጠብቅ እንዲረዳው በጌታ የታመነ ላመጹ ሰዎች የወጣት ልጅ ምሳሌ ነበር። በጌታ ትዕዛዝ፣ አባቱ እሱን እና ወንድሙን ሀይለኛ እና ኃጢያተኛ ከሆነ ሰው የህዝባቸውን መዝገብ እንዲያመጡ አዘዛቸው። ይህን ሰው በጣም ፈሩት። ቢሆንም ይህን አስቸጋሪ ትዕዛዝ እንዲፈፅሙ ስለታዘዙ፣ ኔፊ በጌታ ያለውን እምነት ገለፀ። እንዲህም አለ፥

"ጌታ ያዘዘውን ሄጄ እፈፅማለሁ፣ ጌታ የሰው ልጆች ትዕዛዛቱን እንዲፈፅሙ መንገድ ካላዘጋጀ በስተቀር ትዕዛዛት እንደማይሰጥ አውቃለሁና እርሱ ያዘዛቸውን እንዲያከናውኑም መንገድ ያዘጋጅላቸዋል፣" (1 ኔፊ 3፥7)።

ኔፊ ጌታን ለመታዘዝ ፈቃደኛ የነበረው ለምንድን ነው?

ዛሬ እንደዚህ ዓይነት እምነት ያላቸው በርካታ የቤተክርስቲያን አባል የሆኑ ከወጣቶችም ከሽማግሌዎችም አሉ። እህት ሳቺኮ ሆታ ከናጎያ፣ ጃፓን የሚከተለውን ታሪክ ተናግራ ነበር፥

1-ሐ፣ አንድ ቤተሰብ ቅዱሳን መፃሕፍትን በህብረት ሲያጠኑ።

“እኔ እና ባለቤቴ ከመጋባታችን በፊት፣ ቤተክርስቲያኑ የሕይወታችን አንዱ ጠቃሚ ነገር እንደሆነ እና ጊዜያችንን እንዲሁም ያለንን ተሰጥዎኦች በሙሉ ቤተክርስቲያኑን ለማገልገል እንደምንጠቀምበት ተስማምተን ነበር። ነገር ግን ይህን መናገሩ ከማድረጉ በጣም እንደሚቀል ተረዳን።

“ከተጋባን በኋላ፣ እኔ እና ባለቤቴ ከቤተክርስቲያኑ ራቅ ወዳለ አፓርታማ ሄደን ለመኖር ተገደድን። ብስክሌቴን ወደ ባቡር ጣቢያው በመንዳት፣ ወደሚቀጥለው ከተማ የሚወስደውን ባቡር በመያዝ፣ እና ከዚያም ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚወስድ አውቶብስን ለመያዝ፣ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ይወስዳል፣ እናም፣ በእርግጥ የመጀመሪያው ባቡር ካመለጠኝ የሚቀጥለውን ባቡር መጠበቅ ካለብኝ ጉዞው ከሁለት ሰዓት በላይ ይወስድብኝ ነበር። ይህ የቅርንጫፉ ፕሬዚዳንቱ የሚሰሩ ሥራዎች እንዳይሰጠን እንቅፋት ሆነበት። ከዚህም በተጨማሪ፣ ከተጋባን ከሶስት ወር በኋላ፣ ባለቤቴ በጠና ስለታመመ ሆስፒታል ገብቶ መታከም ነበረበት፣ ስለዚህ ራሳችንን ለመርዳት ሥራ መስራት ነበረብኝ። ሁልጊዜ ከሥራ በኋላ ባለቤቴን ሆስፒታል ሄጄ መጎብኘት አለብኝ ከዚያም በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ እሞክር ነበር ነገር ግን ሁሉንም ነገር በቀን ውስጥ ለማከናወን በቂ ሰዓት አልነበረኝም።

“ይህ አስቸግሮኛል፣ እናም ቀርብ አካባቢ የምኖር ቢሆን ኖሮ፣ የቤተክርስቲያን ጥሪ ሊኖረኝ እንደሚችል አውቅ ነበር። ሆኖም፣ በቤተክርስቲያኑ አካባቢ የነበረው መሬት በጣም ውድ ነበር፣ እናም እንደዚህ በመሰለ ቀንጆ አካባቢ ቤት ለመከራየት አልቻልንም በመሆኑም ቤትን መግዛት የተሻለ ነው። በምክንያታዊ አስተያየት፣ ይህ ነገር እንደማይቻል አውቅ ነበር፣ ነገር ግን (ቅዱሳን መጻሕፍት ዘወትር ከፀለይን፣ ፀሎታችን እንደሚሰማ ያስተምራሉ) (የሉቃስ ወንጌል 18፡1–5 ይመልከቱ።) ስለዚህ ባለማቋረጥ ፀለይኩኝ። ጌታ ለእንደዚህ ዓይነት የማይቻል ጥያቄ እንዴት መልስ እንደሚሰጥ አላውቅም ነበር፣ ብቻ ዝምብዬ ፀለይኩኝ። ወዲያውኑ መኖሪያ ቤቱ ከቤተክርስቲያኑ 13 ደቂቃ ብቻ የሚርቀው አጎቴ፣ በድንገት ለመልቀቅ ስለወሰነ፣ ቀንጆ ቤቱን ሰጠን። ፀሎቴ እንደተሰማ አወቀሁኝ። በመጨረሻ በቤተክርስቲያን ውስጥ መሥራት በመቻላችን በጣም ነበር የተደሰትነው። በዚህ ጊዜ ባለቤቴ ከሆስፒታል ወጣ፣ ከዚያም ስብሰባችንን እንደ አንድ ቤተሰብ መካፈል ቻልን።

“ቤት ከቀየርን በኋላ፣ ቤተክርስቲያኑ በናጉዋያ አዲስ ቤተክርስቲያን ለመገንባት ያለውን ዕቅድ አስታወቀ፣ እናም ሁሉም ሰው ለሕንፃው ማሰሪያ የሚሆን ገንዘብ ለማሰባሰብ ጠንክሮ መስራት ጀመረ። ይህ ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ ባለቤቴ የራሱ የሆነ ሥራ . . . ዳቦ ጋጋሪነት ለመጀመር ወሰነ። አሁንም የነበረን ገንዘብ በጣም ትንሽ ነበር፣ የቀጠብነውን ገንዘብ በሙሉ ሥራውን ለመጀመር አዋልነው፣ እናም የእኔን ወርሀዊ ገቢ ለዕለት ተዕለት መጪያችን ማዋል ጀመርን። ለሕንፃው ማሰሪያ ገንዘብ እንዴት እንደምንረዳ የምናውቀው ነገር አልነበረም፣ በተለይም እርጉዝ ስለነበርኩኝ ሥራ መስራት አልችልም ነበር። ምንም እንኳን የባለቤቴ ሥራ እያደገ ቢሆንም፣ የዕለት ተዕለት ወጪያችንን ለመሸፈን፣ ለሕንፃው ማሰሪያ መዋጮ ለመክፈል፣ እና አዲስ ለሚወለደው ልጃችን ለመዘጋጀት በቂ ገንዘብ አልነበረንም። ዓመታዊ ጉርሻ ለማግኘት ለረጅም ጊዜ እሰራ ስለነበር ይህንኑ ለልጃችን ወጪ እንዲሆን ቀጥቤ አስቀምጬው ነበር። ይህ ገንዘብ ብቻ ነበር የነበረን።

“አንድ ቀን ምሽት የቅርንጫፉ ፕሬዚዳንት ጠራን እና ለሕንፃው ማሰሪያ ማሟያ ትንሽ ገንዘብ እንዳጠራቸው ነገረን፣ እናም ይህን መሸፈን እንችል እንደሆነ ጠየቀን። የነበረን ገንዘብ በቅርቡ ለሚወለደው ልጃችን ብለን ያስቀመጥነው ብቻ ነበር፣ እናም የነበረን ገንዘብ ይህ

ብቻ ስለነበር፣ ለመስጠት የምንችለውም ያንኑ ነበር። በዚያኑ ምሽት ገንዘቡን ወደ ቅርንጫፍ ፕሬዚዳንት ወሰድነው። አዲሱን ቤተክርስቲያን ለመገንባት የቅርንጫፉን የዋጋ ተመን ለመሙላት በቂ ነበር።

“ከዚያ በኋላ ለልጆችን የሚሆነውን ወጪ ከየት እንደምናገኝ አልተጨነቀንም፤ ጌታ እንደሚያስብልን እናውቅ ነበር። እኔ በእርግጥ በመጠኑ ተጨንቄ ነበር፤ ነገር ግን ስለ ነገሩ ባሰብኩበት ቁጥር፤ ሁልጊዜ ሰላም ይሰማኝ ነበር።

“በቀጣዩ ወር፣ ባለቤቴ በናጎዋያ አካባቢ የሙሉ ጊዜ ሥራ አገኘ። ይህ ሥራ መኖሩንም አናውቅም ነበር። በዚህ አዲስ ደሞዝ አዲስ ለሚወለደው ልጃችን የሆስፒታል ወጪ ለመሸፈን ያስችለን ነበር። እግዚአብሔር የምንችለውን ያህል መጣር እንዳለብን እና ከዚያም የቀረውን ለእርሱ መተው እንዳለብን ይነግረናል። ይህም እውነት እንደሆነ አውቃለሁ።” (“Two Hours from the Chapel,” *Ensign,* Aug. 1975, pp. 64–65.)

እህት ሆታ ቤተክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ተችል ዘንድ በእምነት ከፀለየች በኋላ ጌታ ቤተሰባቸውን እንዴት ነበር የባረከው?

ወንድም እና እህት ሆታ ለልጃቸው የቀጠቡትን ገንዘብ ለቅርንጫፉ ፕሬዚዳንት በመስጠታቸው ጌታ እንዴት ነበር ውለታቸውን የመለሰላቸው?

እህት ሆታ ስለ እምነት ጥሩ የሆነ ገለፃ ሰጥታለች። እምነት አለን ሲባል (ምንም እንኳን በምክንያታዊ አስተያየት ሊታይ የማይቻል እንኳን ቢመስልም) የወንጌል ህጎችን ለማክበር ማድረግ የሚቻለንን ነገር ሁሉ ማድረግ ነው። ከዚያም እራሳችንን ለመርዳት ከአቀማችን በላይ የሆኑ ነገሮችን ጌታ እንዲረዳን በእርሱ ላይ እምነታችንን መጣል እንችላለን።

## እምነት በመታዘዝ ሕይወት ይኖረዋል

እምነታችን ያለ ጥረት በህይወት ሊቆይ አይችልም። እምነት ልክ እንደ አንድ ተክል ነው፤ ካልተንከባከብነው እና ካልጠበቅነው ይጠወልግና ይሞታል።

እምነታችን በህይወት እንዲቆይ የምናደርግበት መንገድ የወንጌል ሕጎችን ልክ እንደተማርናቸው ስንጠብቃቸው ነው። “እምነት ለግል ፅድቅ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ሽልማት ነው።” (Bruce R. McConkie, *Mormon Doctrine,* p. 214.) የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጣስ ከጀመርን፤ እምነታችንን እናደክመዋለን። ሰይጣን የእግዚአብሄርን ትዕዛዛት እንድንንቅ እና እምነታችንን ለማዳከም የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል።

ስዕል 1-መ፤ ኔፊ ታላቅ ወንድሞቹን ኃጢያት ለተሞላው መንገዳቸው ሲገስጻቸው የሚያሳየውን ያሳዩዋቸው።

በ1ኛ ኔፊ ስለ ላማን እና ሌሙኤል የተባሉ የኔፊ ወንድሞች እናነባለን። በአባታቸው፤ በኔፊ፤ እንዲሁም በመላአክ ጭምር ብዙ እውነተኛ ህጎችን ተምረው ነበር፤ ነገር ግን እምነትን ሊያዳብሩ አልቻሉም ነበር ምክንያቱም ካልተገደዱ በስተቀር እነዚህን እውነተኛ ህጎችን አይቀበሉም እንዲሁም በእነሱ አይኖሩም። ትዕዛዛቶችን ለመጠበቅ በጣም ከባድ ናቸው እያሉ ያጉረመርሙ ነበር። አባታቸውን እና ወንድማቸውን ይተቹ ነበር። በዚህ ምክንያት፤ እንደታዘዙት ለመፈፀም አይፈልጉም ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ ኃጢያት ላይ ወደቁ።

በተቃራኒው፤ ኔፊ እንዲያደርግ የተጠየቀውን ሁሉ የሚያደርግ እና በጌታም ያምን ነበር። እግዚአብሔር ስለ እምነቱ ሸለመው፤ እንዲሁም በኔፊ ሕይወት ውስጥ ብዙ ተአምራት ተከናውነው ነበር። ስለ መርከብ አሰራር ምንም ነገር ባያውቅም መርከብ ለመገንባት ችሎ



1-00

ነበር። ከሰው ችሎታ በላይ የሆነ ሐይል ተሰጥቶት ነበር እናም የወንድሞቹን ክፉ ዕቀድ ለማሸነፍ ችሎ ነበር። ራዕይ የማየት እና የእግዚአብሔር መልአክን የማናገር ልዩ መብት ተሰጥቶት ነበር። በታዛዥነቱ ምክንያት፣ በእምነትም ተባርኮ ነበር።

እኛም ታዛዦች በመሆን እምነታችን ሕይወት እንዲኖረው ማድረግ እንችላለን። በፆም እና በፀሎት፣ ቅዱስ ፅሁፎችን በማንበብ፣ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን በመሳተፍ፣ እና በቤተክርስቲያን መሪዎቻችን የታዘዝነውን ነገር በመፈፀም እምነታችንን ለመንከባከብ እንችላለን። ባለመተቸት ባለማጉረምረም እምነታችንን መከላከል እንችላለን።

ትችት እና ማጉረምረም እምነታችንን ለምን ያዳክመዋል?

አያንዳንዳችን እምነታችን እንዲፈተን እናደርጋለን። ምናልባት ጌታ እምነታችንን እና ታዛዥነታችንን አያስተውልም የሚል እምነት ሊኖረን ይችላል። ምናልባት እርሱ በጣም ርቆ እንዳለ፣ ፈተናችንን እንደማያይ፣ እና ለፀሎታችን መልስ እንደማይሰጥ ሊሰማን ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ እምነታችን እየተፈተነ መሆኑን መገንዘቡ ይረዳል። በትዕግስት ከቀየን እና ትክክለኛ የሆኑ ነገሮችን ማድረግ ከቀጠልን፣ ፈተናው ወደ ፍፃሜው ይቀርባል። ለእምነታችን እና ለታዛዥነታችን እንሸለማለን።

ሞሮናይ “እምነት ተስፋ የምናደርገው ነገር እንጂ የምናየው አይደለም፣ ስለዚህ ስለሚታዩ አትከራከሩ፣ ምክንያቱም እምነታችሁ ካልተፈተነ በስተቀር ምንም ምስክርነት አታገኙምና” ብሎ አስተምሮናል። (ኢተር 12:6)

እንዲሁም ጌታ “የእኔ ህዝብ በሁሉም ነገሮች መፈተን አለባቸው፣ ስለዚህ ለእነርሱ ያዘጋጀሁላቸውን የፅዮንን ክብር እንዲያገኙ ይዘጋጁ ዘንድ። ቀጣትን የማይቋቋም ለመንግስቱ ብቁ አይደለም።” ይላል (ት እና ቃ 136፥31።)

በጾም እና በፀሎት፣ ለእግዚአብሄር ትዕዛዛት ታዛዥ በመሆን፣ ቅዱስ ፅሁፍን በማንበብ፣ እና ስብሰባዎችን በመሳተፍ እምነታችንን መንከባከብ ጠቃሚ ነገር ነው።

## ሙከራ

እምነታችሁን እንዴት ማጠንከር እንደምትችሉ ወስኑ። ውሳኔያችሁን በማስታወሻ ትንሽ ወረቀት ላይ ፃፉ። (አልማ 32፥17–43 እና ሞሮናይ 7፥33–39 በሳምንቱ ውስጥ አንብቡ።)

## ተጨማሪ ጥቅሶች

የማቴዎስ ወንጌል 8፥5–10 (በእምነት መፈወስ)
የማቴዎስ ወንጌል 17፥20 (በእምነት የማይቻል ምንም ነገር የለም)
ማርቆስ 9፥23 (በእምነት ሁሉም ነገር ይቻላል)
ሉቃስ 8፥43–48 (በእምነት መፈወስ)
ዮሐንስ 20፥24–29 (የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው)
ሮሜ 10፥13–17 (እምነት እንዲኖረን የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አለብን)
2ኛ ቆሮንቶስ 5፥6–7 (በእምነት እንመላለስ)
1ኛ ኔፊ 3 (የኔፊ እምነት)
1ኛ ኔፊ 4 (ሐይል በእምነት)

1-መ፣ ኔፊ ታላቅ ወንድሞቹን በኃጢያት ስለተሞላው መንገዳቸው ሲገስጻቸው።

አልማ 32፥17–43 (ስለ እምነት የአልማ ንግግር)
ኢተር 12፥6 (የሞሮናይ የእምነት ትርጓሜ)
ሞሮናይ 7፥33–39 (እምነት ለተአምራት አስፈላጊ ነው)

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. የወንጌል *መሰረተ ሃሳቦች*፤ ምዕራፍ 18፤ "እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ፤" የሚለውን ያጥኑ።
2. የወንጌል *መሰረተ ሃሳቦች*፤ ምዕራፍ 11፤ "የክርስቶስ ሕይወት" የሚለውን ያጥኑ።
3. ተማሪዎቹ ቅዱሳን መፅሐፍቶቻቸውን ወደ ትምህርት ክፍል እንዲያመጡ ያስታውሱአቸው።
4. አልማ 32፥17–43 ያንብቡ።
5. 1ኛ ኔፊ ምዕራፍ 3 እና 4ን ያንብቡ
6. የክፍሉ ተማሪዎች ታሪኮችን እና ቅዱሳን መጸሐፎችን በትምህርቱ ውስጥ እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

# ንስኃ

ትምህርት 2

የዚህ ትምህርት ዓላማ የንስኃን መሰረታዊ ሐሳብ ተረድተን መጠቀም እንድንችል ለመርዳት ነው።

**ንስኃ መግባት ማለት ምን ማለት ነው?**

እያንዳንዳችን በሕይወት ጉዞ ላይ ነን። እያንዳንዳችን በዘለዓለማዊ ሕይወት አቀጣጫ እየተጓዝን ነው። ስንጓዝ፣ የሚጠሩንን ድምፆች እንሰማለን። አንደኛው ወደ ሰማይ ግዛት የሚጠራን፣ የጌታ ድምፅ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ክፉ ነገር እንድናደርግ የሚገፋፉን የሰይጣን ድምፅ ነው። ከሁለቱ አንዱን መርጠን እርምጃ ለመውሰድ ነፃ ነን።

2ኛ. ኔፊ 2፥16፣ 27–29 ያንብቡ።

እውነትን እስክናውቀ ድረስ፣ በቀላሉ በእነዚህ ሁለት ድምፆች እንወናበዳለን። በገሐድ እየተታለልን ሳለን፣ ትክክለኛ ነገር እያከናወንን ያለን ሊመስለን ይችላል። የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ስንማር፣ ምንጊዜም ቢሆን ትክክለኛ ምርጫ እንዳላደረግን እንገነዘባለን። በትክክለኛው መንገድ ላይም እንዳልሆንን እንገነዘባለን። በተሳሳተው መንገድ መጓዝ ብንቀጥል፣ ወደ ጉዞዋችን መጨረሻ እንደርሳለን፣ ነገር ግን ወደ ሰለስቲያል መንግሥት እንዳልደረስን እንገነዘባለን። ትክክለኛ መንገዳችንን መሳት ኃጢያት ይባላል። መንገዳችንን አስተካክለን ዳግም ወደ ሰለስቲያል መንግሥት ማምራት ንስኃ ይባላል።

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚከተለውን ቃል ገብቶልናል፥

“ማንኛውም ነፍስ ኃጢያትን ትቶ ወደኔ የሚመጣ፣ ስሜን የሚጠራ፣ ድምጼን የሚያከብር፣ ትዕዛዜን የሚጠብቀ፣ ፊቴን ያያል እናም እኔንም ያውቃል፣

“እናም ወደ ዓለም የመጣ ለማንኛውም ሰው የሚያበራ እውነተኛ ብርሃን እኔ ነኝ” (ት እና ቃ 93፥1–2)።

“እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፥ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይኖረዋል እንጂ በጨለማ አይመላለስም።” (ዮሐንስ 8፥12።)

“በጨለማ” መመላለስ ምን ማለት ነው? “በብርሃን” መመላለስስ?

ስዕል 2-ሀ፣ ልክ በጨለማ ውስጥ ትክክለኛውን መንገድ እንደሚያሳይ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰለስቲያል መንግስት የሚወሰደውን መንገድ ያሳየናል የሚለውን አሳይ። ይህን ስዕል እንዲመለከቱ ያድርጉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንግስተ ሰማይ የምንገባበትን እና ከሰማያዊ አባታችን ጋር አብረን የምንሆንበትን መንገድ አሳይቶናል። እርሱ በጨለማ ውስጥ ትክክለኛውን መንገድ እንደሚያሳየን ብርሃን ነው። በትክክለኛው መንገድ ስንሆን በብርሃን እንመላለሳለን። (ዮሐንስ 8፥12 ይመልከቱ)። ልንከተለው የሚገባንን ትክክለኛ መንገድ ማየት እንችላለን። ከትክክለኛው መንገድ ስናፈነግጥ፣ በሚናወጥ ውሃ ውስጥ እና በአደገኛ አለት አካባቢ እንደሚባክን መርከብ እንሆናለን። እነዚህ ሰይጣን ያጠመደልን የኃጢያት ወጥመዶች ናቸው። እርሱ



ወደ ጉዞዋችን መድረሻ እንዳንደርስ ሊገድበን ይፈልጋል። ነገር ግን የኃጢያት ሕይወት በጉዞአችን መጨረሻ ላይ ወደ ደስታ አያመራንም። ወደ ኃጢያት በበለጠ በሰጠምን ጊዜ ሰይጣን የበለጠ ኃይል በእኛ ላይ ይኖረዋል። ስለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ “ኃጢያት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢያት ባሪያ ነው” (ዮሐንስ 8፥34) ብሎ የተናገረው።

ሰይጣን ኃጢያት በምንፈፅምበት ጊዜ ደስ ይለዋል። በእርሱ ኃይል ቁጥጥር ስር እንድንሆን ይፈልጋል። የእርሱ ድምፅ የፈፀምነው ነገር ትክክል እንደነበር ይነግረናል። ይህን ለመፈፀም በቂ ምክንያት እንደነበረን፣ ማለትም ኃጢያት በመፈፀማችን ፍትሐዊ እንደሆንን ይነግረናል። (2 ኔፊ 28፥21-22 ይመልከቱ)። የፈፀምነው ኃጢያት ያን ያህል ከባድ እንዳልሆነ ለራሳችን እንድንነግር ይፈልጋል። ለሰራነው ኃጢያት የምናመካኝ እስከሆነ ድረስ፣ በፍፁም ንሰኃ እንደማንገባ ያውቃል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣን በዚህ መንገድ እንደሚጠቀም ያውቃል። ስለዚህ ነው የእርሱ ድምፅ ለምንሰራው ኃጢአት ምቸት እንዳይሰማን የሚያደርገው። የእርሱ ድምፅ እንድንሰማ እና ወደ እውነተኛው መንገድ እንድንመለስ በማስጠንቀቀ ይገፋፋናል።

ያዕቆብ፣ በእግዚአብሔር ኃይል በመናገር፣ ሰዎቹን እንዲነቁ ለማድረግ ፈልጎ ነበር። በእነዚህ ቃላቶች ስለ ኃጢያታቸው ነግሯቸዋል፥

“የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ከኃጢአታችሁ ተመለሱ፣ አጥብቀ ያሰራችሁን የሰይጣንን ሰንሰለት በጥሳችሁ ጣሉ፣ ለመዳናችሁ የመሰረተ ድንጋይ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ።

“ነፍሳችሁን ለፍርድ ቀን አዘጋጁ፣ እናም በአስከፊ ፍርሃት አትሸማቀቁም እንዲሁም ጥፋታችሁን በግልፅ አታስውሱትም፣ በዚያን ጊዜ፣ ፍርዶችህ ቀዱስ ቀዱስ ናቸው . . . ነገር ግን ጥፋቴን አውቃለሁኝ፣ ህግህን ጥሻለሁኝ፣ ህግህንም የጣስኩት በራሴ ድክመት ነው፣ እናም ዲያብሎስም አገኘኝ፣ የእርሱም መከራ ሰለባ ሆንኩኝ እያላችሁ ለመናገር ተገደዳላችሁ፣

“አስታውሱ ወንድሞቼ፣ ከዚህ አስከፊ ሐቀ እንድትነቁ ማድረጌ ጠቃሚ አይደለምን? አዕምሮዋችሁ ንፁህ ሆኖ ቢሆን ኖሮ፣ ነፍሳችሁን አሳዝነው አልነበረምን፣ ከኃጢአት የነፃችሁ ብትሆኑ እንደ ሐቁ ግልፅነት ግልፅ እሆንላችሁ አልነበር።

“እነሆ፣ ቀዱስ ብትሆኑ ነበር ስለ ቀዱስነታችሁ እነግራችሁ ነበር፣ ነገር ግን ቀዱሳን ስላልሆናችሁ፣ እንደ መምህራችሁ ስለምታዩኝ የኃጢአት ውጤት ምን እንደሆነ ላስተምራችሁ ግዴታዬ ነው።” (2 ኔፊ 9፥45–48)

ስለ ኃጢያታችን አስከፊነት ስንገነዘብ፣ ወደፊት እንቀጥልበታለን አለዚያም ስህተታችንን በድፍረት ለመቀበል እና ለማስተካከል እንወሰናለን። ኃጢያት በማድረጉ ለመቀጠል ከመረጥን፣ ሰይጣን በመጨረሻ የንሰሐ መግባት ፍላጎታችን እስኪጠፋ ድረስ ይተበትበናል። ንሰኃ ለመግባት እስክንሞት ድረስ ከጠበቅን፣ በጣም ልንዘገይ እንችላለን።

አልማ 34፥32–35 አንብቡ።

ንስኃችንን ማዘግየት ጥበብ ያልሆነው ለምንድነው?

2-ሀ፣ ልክ በጨለማ ውስጥ ትክክለኛውን መንገድ እንደሚያሳይ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንግስተ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ ያሳየናል።

## ሁላችንም ንሰሐ መግባት ይገባናል

ኃጢያታችን እንደ ኔፊ ወንድሞች ኃጢያት ከባድ ላይሆን ይችላል። ቢሆንም፣ ሁላችንም ንስኃ መግባት ይገባናል።

ሮሜ 3፥23 አንብቡ።

ማድረግ ለማይገቡን ነገሮች፣ እንደ ውሸት መናገር፣ ሐሜት፣ የጌታን ስም በሐሰት መጠቀም ለመሳሰሉት ንስኃ መግባት አለብን። በተጨማሪም ማድረግ የሚገባን፣ እንደ አስራት መክፈል፣ ሁልጊዜ መፀለይ፣ የሰንበትን ቀን ማክበር፣ የጎረቤት ወዳጅ መሆን፣ ወይም የተሰጠንን ሥራ መፈፀም የመሳሰሉትን ሳናደርግ ብንቀር ንስኃ መግባት አለብን። በህሊናችን ክብደት ከምንሰጠው ጀምረን ንስኃ መግባት ጠቃሚ ነው። የጌታ መንፈስ ስህተታችንን መቋቋም እንድንችል እንደሚገፋፋን መገንዘብ አለብን።

“አንድ ወጣት የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥቷል፥ ‘ኃጢያት ደስታን እንደማያመጣ ባለመገንዘቤ በቤተሰቦቼ እና በራሴ ላይ የፈጠርኩትን ስቃይ አስባለሁኝ። ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴ በኋላ ከቤት ወጣሁኝ እናም መጠጣት፣ ማጨስ፣ እና አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም ጀመርኩኝ። ጥሩ የደስታ ጊዜ ያሳለፍኩኝ መስሎኝ ነበር፣ ነገር ግን፣ አሁን በትክክል የመከራ ጊዜ እንዳሳለፍኩ አውቃለሁ።

“ ‘ከዚያም አንድ ቀን ቆምኩኝ እና እንዲህ ስል አሰብኩኝ “አሁን ቤተሰቦቼ ቢያዩኝስ? ምን ይሰማቸው ይሆን?”

“ ‘በዚህ ጊዜ ነበር ሕይወቴን መቀየር የጀመርኩት . . . ያለ ጥሩ አዲስ ጓደኞች እና የሰው ችግር በሚገባው ጳጳስ . . . እንዲሁም ያለ መንፈስ ቀዱስ እርዳታ ይህን ማድረግ ባልቻልኩኝ ነበር። ነገር ግን በእነርሱ እርዳታ ንስኃ መግባት ቻልኩኝ። እንዲሁም አሁን ምን ያህል ደስተኛ እንዳልነበርኩኝ ተረዳሁ። ንስኃ እና የፅድቅ ሕይወት ደስታ እንደሚያመጣ እመሰክራለሁ። እናም በተሞክሮዬ ጌታ እኛ ከፈቀድንለት ሕይወታችንን ለመቀየር ሁሌም ከእኛ ጋር እንደሆነ አውቃለሁ።’ ” (Jay A. Parry, “Miracles Today” *Ensign,* Jan. 1978, p. 56.)

ንስኃ ስንገባ፣ ወደ እውነተኛ መንገድ እየቀረብን እንመጣለን። በእውነተኛው መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማይ እያመራን ከሆንን፣ ሁሉም የእግዚአብሄር ህጎች ጠቃሚ እንደሆኑ ይገባናል። ኃጢያት ተቀባይነት አለው ብለን ለማሰብ አንችልም። ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየሆንን እንመጣለን እንዲሁም ኃጢያትን እርሱ እንደሚመለከተው መመልከት እንጀምራለን። በሌላ አባባል፣ ማንኛውንም ኃጢያት ለመቀበል አንችልም። ይህ ግባችን ነው። ምንም እንኳን እስከአሁን ግባችንን ባንመታም፣ ግባችንን እና እርሱን ለማግኘት የምንሰራውን ሥራ ማስታወስ አለብን። ጌታ ድክመታችንን እና ኃጢያታችንን እንዲያሳየን በፀሎታችን ትሁት ሆነን ከፀለይን፣ እርሱ ይፈፅመዋል።

ኢተር 12፥27 ያንብቡ።

## እውነተኛ ንስኃ ይቀርታን ያስገኛል

ኃጢአቶቻችን በጌታ ፊት የተጠሉ መሆናቸውን በተገነዘብን ጊዜ፣ ጥልቅ የሐዘን ስሜት ይሰማናል (2ኛ ቆሮንቶስ 7፥10 ይመልከቱ)። ጥልቅ የጥፋተኝነት ስሜት እና ፀፀት ሳይሰማን ልናስታውሳቸው አንችልም። እንድንጨነቀ ያደርጉናል እንዲሁም ትልቀ ሸክም ይሆኑብናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ተሰቃይቶ በሞተበት ጊዜ የተሰማውን ታላቀ ሐዘን እኛም በትንሹ ሊሰማን ይጀምራል። (አልማ 36፥12–13 ይመልከቱ)

ስዕል 2-ለ፣ ክርስቶስ በጌቴሴማኒ ሲፀልይ የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩዋቸው።

ይህን ሸክም ሁልጊዜ መሸከም ስለማንገደድ ምን ያህል በምስጋና የተሞላን መሆን ይገባናል። በንስኃ አማካኝነት ይህን ሸክም ማስወገድ እንችላለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ባለው ታላቅ ፍቅር ምክንያት ለእኛ ኃጢያት ሲል ተሰቃይቷል፣ ደምቷል፣ እንዲሁም ሞቷል ስለዚህ ንስኃ ከገባን ሙሉ ለሙሉ አንሰቃይም። (*የወንጌል መሰረቶች*፣ ምዕራፍ 12፣ "የኃጢያት ክፍያ" ይመልከቱ።)

ስዕል 2-ሀ፣ ንስኃ እንገባ ዘንድ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ተሰቃይቷል። የሚለውን ስዕል ያሳዩዋቸው።

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣

"እነሆ ንስኃ ቢገቡ፣ እንዳይሰቃዩ እኔ አምላካቸው ይህን ሁሉ ለሁሉም ስል ተሰቃይቻለሁ፣

"ነገር ግን ንስኃ የማይገቡ ከሆነ እኔ እንደ ተሰቃየሁት እነርሱም ይሰቃያሉ፣

"ይህም ስቃይ እኔ ታላቅ አምላክ የሆንኩትን እንኳን ለመንቀጥቀጥ—በእያንዳንዱ የሰውነት ቀዳዳ ለመድማት እንዲሁም በስጋ እና በመንፈስ ለመሰቃየት ዳርጎኛል። (ት እና ቃ 19፥16–18።)

ንስኃ ለመግባት የተወሰነ ዘዴ መጠቀም አለብን። ይህ ዘዴ በወንጌል መሰረቶች፣ ምዕራፍ 19 ተገልጿል።

ስዕል 2-መ፣ የንስኃ እርምጃዎች ከጥልቀ ሐዘን ትዕዛዛትን በመጠበቅ ወደምናገኘው ደስታ ይወስዱናል። የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው።

ስለ ሰባቱ የንስኃ ክፍሎች ተወያዩ። ከተቻለ፣ ብዙ እህቶች እንዲሳተፉ ያድርጉ።

በምትወያዩበት ጊዜ ሰባቱን የንሰኃ ክፍሎች የሚያሳይ ቻርት ያሳዩአቸው።

ሰባቱ የንስኃ ክፍሎች (1) ኃጢያት እንደሰራን ማመን፣ (2) በሰራነው ኃጢያት ማዘን (3) ኃጢያት መስራትን ማቆም፣ (4) ኃጢያትን መናዘዝ፣ (5) ካሳ ማድረግ፣ (6) ሌሎችን ይቀር ማለት፣ እና (7) የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ ናቸው። እነዚህን ዘዴዎች በምንጠቀምበት ጊዜ፣ አዳኛችን ኃጢያታችን ሙሉ በሙሉ ይቀር እንደሚባልልን ቃል ገብቶልናል። እንደገና አያስታውሳቸውም ምክንያቱም ለሐጢያታችን ቤዛ ስለሆነ፣ ይቀርታ የማድረግ ሀይል አለው።

ት እና ቃ 58፥42 ያንብቡ።

በንስኃ አማካኝነት እንደገና ንፁሕ እና የፀዳ እንሆናለን። ስለ ድሮው ማንነታችን እና ኃጢያታችን ማስታወስ እንችላለን፣ ነገር ግን ምንም ስቃይ አይሰማንም። ይልቁንም ሰላም ይሰማናል። ስሙ እንዲገለፅ ያልፈለገ አንድ ወንጌላዊ አንድ እንግዳ የሆነ ታሪክ ተናግረዋል። ይህ ታሪክ ንስኃ ስንገባ የምናገኘው የተሟላ ይቀርታን ይገልፃል።

ልትጠመቅ የነበረች አንዲት ወጣት ሴት በወጣትነቷ ለፈፀመችው ኃጢያት የምትገባውን ንስኃ በጌታ ያለውን ተቀባይነት ተጠራጥራ ነበር። ይቀር መባልዋን ለማረጋገጥ መፀለይዋን ቀጠለች። ልክ እንደተጠመቀች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጣት፣ ሽማግሌው እንዲህ አለ፣

2-ለ፣ ክርስቶስ በጌቴሴማኒ ሲጸልይ።

2-ሐ፣ ክርስቶስ ንስኃ የምንገባ እስከሆነ ድረስ ለእኛ ኃጢያት ተሰቃይቷል።



2-ለ



2-ሐ



“እጄ በራሷዋ ላይ በነበረበት ጊዜ እና መንፈስ ቅዱስን እንድትቀበል በምነግራት ጊዜ፣ በሰውነቷ ውስጥ ልክ እንደ ኤሌክትሪክ ንዝረት ወይም መንዘፍዘፍ የመሰለ ነገር ሲገባ ተሰማኝ። ለጥቂት ጊዜ ተደናግሬ ነበር ከዚያም በኋላ እራሴን ሳውቅ ፀሎቱን ጨረስኩኝ። እናም፣ በቤተክርስቲያኑ እንደተለመደው፣ እንኳን ደስ አለሽ ልላት ወደ እርስዋ ስዞር እራሷን ስታ ነበር ያገኘኋት። አይኗ ተሸፍኖ ነበር፣ እንዲሁም እንባዋ በፊትዋ ይፈስ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለአምስት ደቂቃ ያህል ቀይታ ነበር፣ በኋላ ግን በድንገት እራሷን አንቀሳቀሰች ቀመች እና ወደ መቀመጫዋ ሄዳ ተቀመጠች።

“ማረጋገጫ በተሰጣት ጊዜ በሳየቸው ሁኔታ በእርግጥ ስለሁኔታው ለማወቅ ጓጉቼ ነበር፣ ስለዚህ ከዚያ በኋላ ስለሁኔታው ጠየቅኩኝ። ከሰውነትዋ የወጣው በጣም ቀንጆ፣ ንፁህ፣ ጣፋጭ ስሜት ነገረኝ . . . በሕይወቷ ሙሉ ገጥሟት የማታውቀው ቀንጆ፣ አዝናኝ፣ የሚያነፃ መንፈስ።”

የዚህ ተሞክሮ ውጤት አስገራሚ ነበር። በሶስት ቀን ጊዜ ውስጥ የፊቷ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተቀየረ። መልኳም እየጠራ እና ለስላሳ እየሆነ መጣ፣ እንዲሁም አይኖችዋ ለስላሳ ሆኑ። ሽማግሌው እንዲህ አለ፥

“ይህ ለእኔ እና ለአጋሬ የጌታ መንፈስ በእውነት ንስኃ ለሚገባ ሰው በመንፈስም በሥጋም ወደ በጣም ተፈቃሪ እና ቀንጆ ወደሆነ ሰውነት እንዴት እንደሚቀይር ማየታችን ታላቅ ምስክርነት ነበር፡ በጥምቀት ጊዜ የማንፃት ኃይል ያለው መንፈስ ቅዱስ በጣም እውነተኛ ነው።” (Margie Calhoun Jensen, *When Faith Writes the Story,* pp. 18–19.)

ይህ የጌታ መንፈስ እኛን ለማንፃት ስላለው ኃይል አስገራሚ ታሪክ ነው። ምንም እንኳ ጥቂቶቻችን ብቻ እንደዚህ ዓይነት ተመክሮ የገጠመን ቢሆንም ሌሎቻችንም ተመሳሳይ ጣፋጭ ንፁሕ ስሜት ልናገኝ እንችላለን። ምንም እንኳን አንዴ ብቻ የተጠመቅን ቢሆንም፣ በህይወታችን ሙሉ እራሳችንን ለማራቅ እና መንገዳችን ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲያመራ የንስኃ ህጎችን መጠቀም እንችላለን። በእውነት ንስኃ ስንገባ ጌታ ይቅር እንደሚለን እና ኃጢያታችን እንደሚረሳ ማወቅ እንዴት ያለ ታላቅ በረከት ነው።

## ሙከራ

በሚቀጥለው ሳምንት እንዴት ንስኃ እንደምትገቡ ሕይወታችሁን መርምሩ። ሞዛያ ምዕራፍ 17፣ አልማ ምዕራፍ 36፣ አንብቡ። የወንጌል መሰረቶች ምዕራፍ 19 ከልሱ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

2ኛ ቆሮንቶስ 7፥8–11 (ጥልቀ ሐዘን ንሰሐን ያስገኛል)
1 ዮሐንስ 1፥8–9 (ሁላችንም ኃጢያተኞች ነን)
ኢኖስ 1፥1–8 (ኃጢያት በእምነት ይቀር ይባላል)
ሞዛያ 26፥29–31 (ኃጢያታችሁን ተናዘዙ እንዲሁም እርስ በራሳችሁ ይቀር ተባባሉ)
ት እና ቃ 42፥18–29 (ትዕዛዛትን ጠብቁ)

2-መ፣ የንስኃ እርምጃዎች ከጥልቀ ሐዘን ትዕዛዛት በመጠበቅ ወደ ሚገኘው ደስታ ይወስዱናል።

**የአስተማሪ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. የወንጌል መሰረቶች፣ ምዕራፍ 12፣ “የኃጢያት ክፍያ” ያጥኑ።
2. የወንጌል ህጎች፣ ምዕራፍ 19፣ “ንስኃ” ያጥኑ።
3. ሞዛያ 27 እና አልማ 36 ያጥኑ።
4. ሰባቱን የንስኃ ክፍሎች የሚያሳይ ቻርት ያዘጋጁ።
5. የክፍሉ ተማሪዎች ለትምህርቱ የሚሆን ታሪኮች እና ቅዱስ ፅሁፎች እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

# ጥምቀት፤ ምንጊዜም የሚኖር ቃል ኪዳን

ትምህርት 3

የዚህ ትምህርት ዓላማ በጥምቀት ጊዜ በገባነው ቃል ኪዳን መኖር እንድንቀጥል ማበረታታት ነው።

**መግቢያ**

የሰማይ አባታችን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምን እና ለሐጢአታችን ንስኃ እንድንገባ ይፈልጋል። ንስኃ ከገባን በኋላ፣ በክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንጠመቃለን። ወደ መዳን የሚመራውን ሕግ ለመታዘዝ መጠመቅ ይገባናል። ነገር ግን መጠመቅ ብቻ አይበቃም። በጥምቀት ጊዜ አዲስ የሕይወት መንገድ እንጀምራለን፣ ነገር ግን ሁልጊዜ ወደ ፍፅምና ለማደግ መጣር አለብን።

ነቢዩ አልማ ህዝቦቹ ከተጠመቁ በኋላ እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፥ "በመንፈስ ከእግዚአብሔር ተወልዳችኋልን? በፊታችሁ የእሱን ምስል ተቀብላቹሃልን? ይህ መለኮታዊ ለውጥ በልባችሁ ተሰምቷችኋልን?" (አልማ 5፥14) ሁላችንም ልባችን ሲቀየር እና መንፈሳችን እንደገና ሲወለድ ተሰምቶናልን? በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ስንጠመቅ እነዚህ ስሜቶች ሊኖሩን ይገባል።

በምትጠመቁበት ጊዜ ምን እንደተሰማችሁ ቆም ብላችሁ ለተወሰነ ጊዜ አስቡ። ጥምቀት አልማ እንደገለፀው "የታላቅ ለውጥ" መጀመሪያ ነበር። ወዲያው እንደ ተጠመቅን ለውጥ አልተሰማንም ይሆናል። ነገር ግን ሕይወታችን እየተሻሻለ ሲመጣ፣ ለውጡን ማየት እንችላለን። ጥምቀት ለሁላችንም አዲስ ጅምር ይሆንልናል። እኛ እንደ ክርስቶስ በጥምቀት ጊዜ በውኃ ውስጥ "ተቀብረናል"። ከዚያም ወደ አዲስ ሕይወት ተነስተናል። (ሮሜ 6፥3–4 ተመልከት።) በታዛዥነት ምክንያት ይህ አዲስ ሕይወት ከሰማዩ አባታችን ጋር ለዘለዓለም ወደ መኖር ግባችን ይመራናል።

ብዙ ሰዎች በጥምቀታቸው ጊዜ በሚሰማቸው መንፈሳዊ ስሜት ደስ ይላቸዋል። አንድ አባል እንዲህ ሲል ስለ ሁኔታው ገልጿል፥ "በነፍሴ ውስጥ የተሰማኝን ስሜት በፍፁም አልረሳውም፣ ንፁህ መሆን፣ እንደ አንድ የእግዚአብሔር አዲስ ልጅ መሆን መጀመር . . .በጣም ልዩ ስሜት ነበር!"። (Hartman and Connie Rector, *No More Strangers,* 3፥17.)

ጥምቀታችን በእኛ ውስጥ የተከናወነውን ጠቃሚ ለውጥን ይወክላል። ንስኃ የገባን ስለሆንን ነጽተናል እናም አዲስ ሕይወት እንድንጀምር ዕድል ተሰጥቶናል። በጥምቀት ጊዜ የነበረንን ንፁህ እና የመዳን ስሜት ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን።

አንድ ወይም ሁለት እህቶች ሲጠመቁ የተሰማቸውን ስሜት እንዲገልፁ ይጠይቁ። ከጥምቀት ወዲህ ሕይወታቸው እንዴት እንደተለወጠ ይጠይቁ። በዚህ ውይይት ወጣት ሴቶቹ እንዲሳተፉ ያድርጉ።

## የጥምቀት ቃል ኪዳናችን

ስዕል 3-ሀ፣ አንዲት ወጣት ሴት ስትጠመቅ የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩ

ቃልኪዳን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ክፍሎች የሚደረግ ስምምነት ነው። ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እንዳሉት፥ “መጠመቀ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ፅድቀን. . . . ለማድረግ፣. . .ለመሥራት፣ እንዲሁም ክፋትን ለማስወገድ ቃልኪዳን መግባት ነው” (*The Miracle of Forgiveness,* p. 94)።

የክፍሉ አባላት ት እና ቃ 20፥37 እንዲያነቡ እና ምልክት እንዲያደርጉ ያድርጉ።

በዚህ ጥቅስ ለጥምቀት ምን መመዘኛዎች ተሰጥተዋል? ሰሌዳው ላይ ጻፋዋቸው።

1. ትሁት ሁኑ
2. የተሰበረ ልብ እና ትሁት መንፈስ ይኑራችሁ።
3. የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ለመቀበል ፈቃደኛ መሆናችሁን መስክሩ።
4. እስከመጨረሻው ኢየሱስ ክርስቶስን ለማገልገል ወስኑ።

የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መቀበል ምን ማለት ነው?

የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መቀበል ማለት የክርስቶስ ልጆች ተብሎ መጠራት ነው። (ሞዛያ 5፥7–8 ይመልከቱ)። የአንድን ሰው ስም ስንቀበል ኃላፊነት አለብን ማለት ነው። ልክ ከቤተሰባችን ለተቀበልነው ስም ኃላፊነት እንዳለብን ሁሉ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ስንቀበልም ኃላፊነት አለብን። እሱ እንደኖረው ለመኖር መጣር አለብን።

ስዕል 3-ለ፣ አንዲት ወጣት ሴት ቅዱስ ቁርባንን በመካፈል የጥምቀት ቃል ኪዳንዋን ስታድስ። የሚያሳየውን ስዕል አሳዩአቸው።

ት እና ቃ 20፥77 የክፍሉ አባላት እንዲያነቡ ይጠይቋቸው።

ቅዱስ ቁርባን ስንወስድ የምንገባው ቃል ኪዳን ስንጠመቅ ከገባነው ቃል ኪዳን ጋር አንድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስታወስ እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ የገባነው ቃል ኪዳን ስንጠብቅ፣ በረከት እንደሚሰጠን ቃል ተገብቶልናል።

የሰማይ አባታችን ይህን ቃል ኪዳን ለሚጠብቁ ምን ቃል ገብቷል? (መንፈሱ ከእነሱ ጋር እንዲሆን)

መንፈሱ ከእኛ ጋር መሆኑ እርሱን እንድናገለግለው እና ትዕዛዛቱን እንድንጠብቅ እንዴት ይረዳናል?

## ከጥምቀት በኋላ ያለን መሻሻል

አንዳንድ ሰዎች መዳን በመጠመቀ ብቻ ይመጣል ብለው ያስባሉ። እንደ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነታችን፣ ጥምቀት ጅምር ብቻ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህም በቤተክርስቲያኑ መዝገብ ስማችን ሲፃፍ ነው። ነገር ግን መጠመቀ ብቻ በቂ አይደለም። ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ከጥምቀት በኋላ ብዙ ነገሮችን ማድረግ አለብን።

ከጥምቀት በኋላ ምን ግዴታዎች አሉብን? ሞሮናይ 6፥4–9 የክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡ ይጠይቋቸው። በሰሌዳው ላይ ጌታ እንድናደርግ ያዘዘንን ነገሮች ይጻፉ፥

1. ወደ ሰማይ አባታችን መፀለይ።
2. ለተለዩ ችግሮች መፆም።
3. በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች መገኘት እና መሳተፍ።
4. ቅዱስ ቁርባንን ሁልጊዜ መካፈል።
5. ለእያንዳንዳችን ደህንነት ማሰብ።
6. ለኃጢያታችን ንስኃ መግባት።
7. የመንፈስ ቅዱስ መመሪያን መከተል።

3-ሀ፣ አንዲት ወጣት ሴት ስትጠመቅ፥


3-U



የክፍሉ አባላት ዝርዝሮችን በሰሌዳው ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ይጠይቋቸው።

የጥምቀት ቃልኪዳኔን ምን ላይ ማሻሻል ይገባኛል?

በጥምቀት ጊዜ በመንፈስ እንደገና መወለድ እንጀምራለን። ሞሮናይ የዘረዘራቸውን ነገሮች በማድረግ በዚህ አዲስ ሕይወት መቀጠል አለብን። ግን ለሐላፊነታችን ለቤተሰባችን እና ለቤታችን ስንጨነቀ፣ ትምህርት ስንማር፣ የዕለት ተዕለት ኃላፊነታችንን ለማሟላት ስንጥር በዓለማዊ ችግሮች ውስጥ እንገባና አንዳንድ ጊዜ ቃል ኪዳናችንን እንረሳለን።

መንፈሳዊነታችንን መጨመር እና የጥምቀት ቃልኪዳናችን እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

አንዳንድ ጊዜ ስህተት እንሰራለን። ከዚያም የጥምቀት ቃል ኪዳናችንን ለመጠበቅ ንስኃ መግባት አለብን፣ በግልፅ ኃጢያት እንደሰራን ስናምን እና ንስኃ ስንገባ (የዚህ መምሪያ መፅሐፍ ትምህርት 2 ይመልከቱ)፣ ወደ ፍፁምነት እንደገና እናድጋለን። በፀሎት ከመንፈስ ቅዱስ በታማኝነት መመሪያ ስንሻ፣ በሰማይ ያለውን አባታችንን እናስደስተዋለን።

## የፍፁምነት መንገድ

የጥምቀት ቃል ኪዳናችንን ሁልጊዜ እናሟላለን? ምናልባት በዚህ ሕይወት ሊሆን አይችልም፣ ነገር ግን፣ መጥፎ ልማዶችን በጥሩዎቹ በመቀየር፣ ሕይወታችንን ፍፁም ለማድረግ መቀጠል አለብን። ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እንዲህ ብለው ነበር፥

"የፍፁምነት መንገድ ሕይወትን መቀየርን ይመስላል፥ በሁሉም ነገር ክፉውን በጥሩ መቀየር ነው። አንድን ነገር ብቻ በአንድ ግዜ ስንወስድ የበለጠ ለውጥ ሊመጣ ይችላል። አንድ ሰው የዓመት ገቢውን አንድ አስረኛ ቢከፍል፣ በአስራት ፍጹም ነው ማለት ነው። የመማል ፀባይ በማስወገድ ፍፁም መሆን ከባድ አይደለም፣ አንድ ሰው አፉን ከክፉ ቃላት እና እርግማን እስከቀለፈ ድረስ፣ በዚህ ጉዳይ ወደ ፍፁምነት ጉዞ ላይ ነው። አንድ ሰው ቅዱስ ጽሑፎችን ምክንያታዊ በሆነ መስዋዕትነት እየከፈለ ካጠና፣ በዚህ ጉዳይ ላይም ወደ ፍፁምነት ተዳርሷል ማለት ነው። ("Be Ye Therefore Perfect," Salt Lake Institute of Religion devotional, 10 Jan. 1975, p. 11.)

ነብዩ ኔፊ ከጥምቀት በኋላ ሁሉም ነገር አይፈፀምም ብሎ ነበር። "ወደፊት መግፋት" እና "እስከመጨረሻው መፅናት" እንዳለብን ነግሮናል። ጌታ ፍቀራችንን እሱን በመታዘዝ ስናሳየው ዘለአለማዊ ሕይወትን ሊሰጠን ቃል ገብቶልናል። (2 ኔፊ 3፥19–21 ይመልከቱ።) እውነተኛ ደስታ በምድር ላይ እና ዘለዓለማዊ ደስታ ከዚህ ሕይወት በኋላ ከጌታ ጋር የገባነውን የጥምቀት ቃል ኪዳን በመኖር ይመጣል።

ፕሬዚዳንት ዮሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ በዚህ መንገድ ገልጸውታል፥

"አንዱ የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ታላቀ ዓላማ ሰዎች የወንጌልን የተሟላ በረከት እንዲያገኙ ከጥምቀት በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማስተማር ነው . . .

"እስከመጨረሻው መጽናት አለብን፣ ከጥምቀት በኋላ ትዕዛዛትን መጠበቅ አለብን፣. . . . ስለዚህ የአማኝነት ባሕሪ እንዲኖረን እና በሰለስቲያል መንግስት ክብር የሚደሰቱ እና የሚደነቁ ሰዎች ሆነን መኖር አለብን።" ("The Plan of Salvation," *Ensign,* Nov. 1971, p. 5.)

3-ሉ፣ አንዲት ወጣት ሴት ቅዱስ ቁርባን በመካፈል የጥምቀት ቃል ኪዳንዋን ስታድስ።

ወደ ቤተክርስቲያኑ የተቀየረች የቀድሞ የካቶሊክ መነኩሲት ጥምቀትዋ ለእሷ ምን ማለት እንደሆነ እንዲህ ስትል ገልፃ ነበር፡

“በቤተክርስቲያኑ ያየኋቸው እና የሰማኋቸው ነገሮች በሙሉ አስደነቁኝ፣ እያንዳንዱ አባል ለሌሎች አባላት ያላቸው ሞቀ ያለ ፍቀር እና እንዲሁም ተቀርቋሪነት፣ ይህ ሐይማኖት አንድ ልዩ ነገር እንዳለው እንድገነዘብ አደረገኝ . . .

“ከዚያም በተሳሳተ ቤተክርስቲያን እንደነበርኩኝ እና የኋለኛው ቀን ቀዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ብቸኛው እውነተኛ ቤተክርስቲያን መሆኑን ተረዳሁ። አባል መሆን. . . . እንዳለብኝም አወቀኩኝ. . . .

“ከቀድሞው ሕይወት ወደ አሁኑ ሕይወት መሸጋገሩ ቀላል አልነበረም፣ ነገር ግን በሁሉም ገጠመኞቼ እንድፀና ያደረገኝ በቀዱስ ቁርባን ስብሰባ በየሳምንቱ የጥምቀት ቃል ኪዳኔን ማደሴ ነበር—የአዳኛችንን ስም ለመቀበል፣ እሱን ምንጊዜም ለማስታወስ፣ እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቀ የገባሁት ቃል ኪዳን፣ እንዲሁም የጌታ ቃል ኪዳን በተራው፣ ቃሌን ካከበርኩኝ መንፈሱ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ይሆናል . . .።

“ቀጥሎ ጥምቀቴን እና ሙሉ ለሙሉ በውኃ ውስጥ መጥለቅን አስታውሳለሁ። ለእኔ ለራስ ወዳድነት እና ለሐጢያት መሞት እንዲሁም ለአዲሱ እንደ አንድ የእግዚአብሄር ልጅነት ሕይወት ምልክት ነው። ይህ የጥምቀት ሥራ፣ እኔ እንደማስበው የሰማዩ አባታችን ራስ ወዳድነትን ተቋቁመን እና ፈተናን ታግለን እንድንኖር የሚፈልግበት መንገድ ምልክትም ጭምር ነው። በዚህ ሁኔታ ለራሳችን እና ለሐጢያት ሞተናል። እንዲሁም ተነስተን አባታችን ወደ አለበት በሚወስደው መንገድ በየቀኑ በመሻሻል ላይ ነን።

“ከዚያም በጸጥታ የክርስቶስን ስም ለመውሰድ የገባሁትን ቃልኪዳን እንደገና አደስኩኝ፣ እሱን፣ የወንጌሉን መሰረቶች፣ የእሱን ትምህርት ለመቀበል የገባሁትን ቃልኪዳን እንደገና ማደሴን ለእሱ በመንገር፣ ቤተክርስቲያኑን ለመቀበል እና ነቢዩን እና በእግዚአብሔር ስም እኛን ለመምራት በመለኮት የታዘዙት ብቸኞቹ ሌሎች የቤተክርስቲያኑ የበላይ ባለስልጣኖች ለመደገፍ የገባሁትን ቃልኪዳን አድሳለሁ። በጸጥታ ፀሎቴ ሁልጊዜ እሱን ለማስታወስ የገባሁትን ቃል ኪዳን እንደገና አስባለሁ፣ ለምሳሌ፣ በተለይም ፈተና እና መሰላቸት በሚኖርበት ቀን እሱ እንዳለ አስታውሳለሁኝ። በመጨረሻ ትዕዛዛቱን ለመጠበቀ የገባሁትን ቃል ኪዳን እንደገና አድሳለሁ፣ ይህን በታማኝነት ካደረግኩኝ መንፈሱ ከእኔ ጋር እንደሚሆን አውቃለሁ።” (*No More Strangers,* 3:154, 157, 159.)

### ማጠቃለያ

በጥምቀታችን ጊዜ፣ በውስጣችን “ልባችን መለወጥ” ይጀምራል። የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ለመቀበል እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቀ ቃል ኪዳን ገብተናል እነዚህን ነገሮች በእያንዳንዱ ቀን ለመፈፀም ስንጥር፣ መንፈሱ ከእኛ ጋር ይሆናል። መንፈሱ እንደ እርሱ እንድንሆን ይረዳናል።

### ሙከራ

ከጥምቀት ጊዜ ወዲህ በሕይወታችሁ ውስጥ ምን እንዳደረጋችሁ መርምሩ። በአልማ 5፥26–31 የተጠየቀውን ጥያቄ መርምሩ። መሻሻል የምትፈልጉ ከሆነ ዛሬ ንስኃ በመግባት እና ስህተተ የሆኑትን ነገሮች በማረም ጀምሩ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

ገላትያ 3፥27–29 (በጥምቀት፣ በክርስቶስ አንድ መሆን)
1ኛ ጴጥሮስ 3፥21 (ጥምቀት እና ትንሳኤ)
ት እና ቃ 27፥2 (ቅዱስ ቁርባን መካፈል)

### የመምህሩ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረተ ሀሳቦች*፣ ምዕራፍ 20፣ "ጥምቀት" ያንብቡ።
2. ሰሌዳና ጠመኔ እንዲኖርዎ ያድርጉ ወይም (እንደ አማራጭ) የጥምቀት መመዘኛዎች እና የሞርሞንን 6፥4–9 ምክር የሚያሳይ ፖስተር ያዘጋጁ።
3. ለትምህርቱ የሚሆኑ ታሪኮች እና ጥቅሶች እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ

ትምህርት 4

የዚህ ትምህርት ዓላማ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚገኝን ታላቅ በረከት እንድንገነዘብ ለመርዳት ነው።

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለምን ያስፈልገናል

የቤተክርስቲያኑ አባል ከመሆናችን በፊት፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ ጊዜ ወደ እኛ መጥቷል። ወንጌላዊያንን በምንሰማበት ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ስለ ወንጌል ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ ወንጌል እንዲገባን እና እንድንቀበለው ረድቶናል። ነገር ግን እስከ ተጠመቅንበት እና አባልነታችን እስከፀደቀበት ጊዜ ድረስ የመንፈስ ቅዱስ አጋርነት በቋሚነት የማግኘት አጋጣሚ አልነበረንም። በዚያን ጊዜ በመልከጼዴቅ ክህነት አማካኝነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጥቶናል።

መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጅ በምድር ከሚደሰትበት አንዱ ታላቅ ስጦታ ነው። ፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖው እንዲህ ብለው ነበር፥ “መንፈስ ቅዱስን . . . ከተቀበልንበት ጊዜ ጀምሮ፣ አንድ ጓደኛ አለን።” (In Conference Report, Oct. 1899, p. 52; cited in *Family Home Evening,* 1975, p. 54.)

መንፈስ ቅዱስ በምን መንገድ ነው መልካም ጓደኛ የሆነው?

ስዕላዊ መግለጫ 4–11፣ አንዲት ወጣት ሴት እጅ በመጫን የቤተክርስቲያኑ አባል ሆና ስትፀና እና መንፈስ ቅዱስን ስትቀበል የሚያሳየውን ስዕል አሳዩአቸው። የክፍሉ አባላት የዮሐንስ ወንጌል 14፥16–17 እና ዮሐንስ 16፥13 እንዲያነቡ ያድርጉ።

መንፈስ ቅዱስ የእኛ ጓደኛ እንዲሆን የምንፈልግበት አንዳንድ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

መልሶቹን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ። የሚከተሉት መልስ ሊሆኑ ከሚችሉት ጥቂቶቹ ናቸው፥

1. ወንጌልን እንድናስተምር ይረዳናል።
2. ነገሮችን እንድናስታውስ ይረዳናል።
3. ከክፉ ነገር ይጠብቀናል።
4. የተሻለ ንግግር እንድናደርግ እና ትምህርት እንድንሰጥ ይገፋፋናል።
5. አደጋ ላይ ስንሆን ያስጠነቅቀናል።
6. ማድረግ የሚገባንን ሁሉ ይነግረናል።
7. የማንፃት እና ቅዱስ የማድረግ ኃይል አለው።

2ኛ ኔፊ 32፥5 ያንብቡ።

ቄስ ለግራንድ ሪቻርድ የሚከተለውን ንግግር አድርጎ ነበር፥ “በአለም ውስጥ ካሉ ሌሎች ጓደኝነቶች ይልቅ ልጆቼ እና የልጅ ልጆቼ የመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነት እንዲኖራቸው እመርጣለሁ፣ ምክንያቱም የዚህን መንፈስ ግፊት ከተቀበሉ ወደ እውነት ይመራቸዋል። እንዲሁም ወደ ሰማይ ወዳለ አባታችን በሰላም ይመራቸዋል።” (in Conference Report, Apr. 1966, p. 112; or *Improvement Era,* June 1966, p. 540.)

4-ሀ፣ አንዲት ወጣት ሴት እጅ በመጫን የቤተክርስቲያኑ አባል ሆና ስትፀና እና መንፈስ ቅዱስ ስትቀበል።



መንፈስ ቅዱስ በጣም ተፈላጊ ጓደኛ ነው። እሱ ጓደኛችን እንዲሆን ለማድረግ የሚገባንን ሁሉ ማድረግ አለብን።

**መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር እንዲቀይ እንዴት እንደምናደርግ**

ትዕዛዛትን መጠበቅ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር እንዲቀይ ለማድረግ ይረዳናል። ቅዱስ ቁርባን በምንካፈልበት በእያንዳንዱ ጊዜ፣ የጌታ ትዕዛዛትን ለመጠበቅ ቃል እንገባለን። ቃላችንን ከጠበቅን፣ ጌታ "መንፈሱ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር" እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል። (ት እና ቃ 20፥77 ይመልከቱ)

ጌታ በግብረገብ በኩል እራሳችንን ንጹህ አድርገን እንድንጠብቅ አዞናል። ሰውነታችን ልክ እንደ ቤተመቀደስ እንደሆነ ነግሮናል። ሰውነታችንን በአስተሳሰብ፣ በአነጋገር፣ በአለባበስ፣ እና በድርጊት ንፁህ አድርገን ከጠበቅነው፣ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ይሆናል። (1ኛ ቆሮንቶስ 3፥16–17 ይመልከቱ።) ከማንኛውም ክፋት ወይም የክፋት ምንጮቹ መወገድ አለብን።

እኛ "ትንሽ ነገር" ነች ብለን በምናስብበት ነገር እንኳን መንፈስ ቅዱስ ሊከፋ ይችላል። በ3ኛ ኔፊ 11፥29 ጸብ ከሰይጣን እንደሚመጣ እንማራለን። ጸብ ማለት አንድነት ወይም ስምምነት የለንም ማለት ነው። የምንከራከር እና የምንጨቃጨቅ ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ ይርቀናል። ምንም እንኳን ከባል፣ ከልጅ፣ ወይም ከወንድም እና እህት ጋር መጨቃጨቅ ከባድ ኃጢያት ባይሆንም፣ መንፈስ ቅዱስን ግን ያርቃል።

ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ ለሁሉም ሰው ትክክለኛ የሆነ አመለካከት ባይኖረው ኖሮ መገለፅን ባላገኘ ነበር። አንድ ቀን ጠዋት ሚስቱ ባደረገችው አንድ ነገር ተበሳጨ። ከዚያም ዮሴፍ የመጽሐፈ ሞርሞንን የተወሰነውን ክፍል ለመተርጎም ሞከረ፣ ግን አልቻለም። ከዚያም ወደ አትክልት ሥፍራው ሄዶ ፀለየ። ከዚያም በኋላ ተመለሰና ኤማን ይቅርታ ጠየቀ። ይህን ካደረገ በኋላ ነበር መተርጎም የቻለው። (See statement by David Whitmer, 15 Sept. 1882, in B. H. Roberts, *Comprehensive History of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints,* 1:131; quoted by Henry D. Taylor, "Thou Shalt Love Thy Wife with All Thy Heart," *Ensign,* Jan. 1974, p. 37.)

ልጆቻችን ስህተት በሚፈፅሙበት ጊዜ፣ መቆጣት የለብንም። መንፈስ ቅዱስ ልጆቻችንን እንድናርም እንዲመራን ማድረግ አለብን። (ት እና ቃ 121፥43 ይመልከቱ)

መንፈስ ቅዱስ የእኛ ጓደኛ እንዳይሆን የምናደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው? የእሱ ጓደኝነት እንዲኖረን ምን ማድረግ አለብን? መልሶቹን በሁለት ሰንጠረዥ በመክፈል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ።

ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ እንዲህ ብለው ነበር፣

"የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለማክበር እና ለመጠበቅ ፈቃደኛ ባልሆነ ሰው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አይኖርም. . . . እንዲህ በመሰለች ነፍስ መንፈስ ቅዱስ ሊገባ አይችልም።

"ይህ ታላቅ ስጦታ በትህትና እና በእምነት እንዲሁም በታዛዥነት ብቻ ወደ እኛ ይመጣል. . . .

"የፈጣሪ አንዱ ክፍል የሆነው እንደ ጓደኛ አብሮን መኖሩ ምን ያህል ትልቅ መብት መሆኑን ቆም ብላችሁ አስባችሁበት ታውቃላችሁን? በዚህ መንገድ አስባችሁበት ታውቃላችሁን? ይህ

ትዕዛዛትን ከጠበቅን፣ ጌታ የሰጠን ልዩ መብት ነው።” (“Fundamental Gospel Truths Balance Education, . . .” *Church News,* 4 Nov. 1961, p. 14.)

**መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚረዳን**

መንፈስ ቅዱስ እንደ እኛ ጓደኛ እንዲሆነን በእምነታችን ካሳየን፣ በብዙ መንገዶች ይረዳናል።

ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖረን ይረዳናል

መንፈስ ቅዱስ “ጥሩ ምግባር፣ ደግነት፣ መልካምነት፣ ርህራሄ፣ ጨዋነት፣ እና በጎ አድራጊነት እንዲኖር ያደርጋል” (Parley P. Pratt, *Key to the Science of Theology,* 9th ed., p. 101) ቤተሰቦቻችን እነዚህን ፀባዮች ሲያዳብሩ፣ በቤት ውስጥ የበለጠ መስማማት ይኖረናል።

ምን ማድረግ እንዳለብን ያሳየናል

መንፈስ ቅዱስ ጠቃሚ ውሳኔዎችን እንድናደርግ እና ምን ማድረግ እንዳለብን እንድናውቅ ይረዳናል።

ት እና ቃ 8፡2 እና 6፡15 የክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ።

መንፈስ ቅዱስ ምን ማድረግ እንዳለብን እንዴት ያሳየናል?

በቤተክርስቲያን ውስጥ እንድናድግ ይረዳናል

ቄስ ፍራንክሊን ዲ ሪቻርድስ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደመራው እንዲህ ብሎ ነበር፥ “ወንድሞቼ እና እህቶቼ ከእናንተ ጋር በምማከርበት ጊዜ፣ ክህነትን በወንዶች በማፀናበት ጊዜ፣ ወንዶች እና ሴቶችን ለቤተክርስቲያን ሥራ በምባርክበት ጊዜ፣ ለህሙማን በረከት በምሰጥበት ጊዜ፣ አባላት ላልሆኑ እና እንዲሁም ለሆኑት፣ ምስክርነቴን በምሰጥበት ጊዜ፣ ንግግር በማደርግበት ጊዜ፣ እና በሌሎች በተለያዩ ጊዜያቶች፣ የመንፈስ ሽውታ ድምፅ ወይም ሹክሹክታ ተሰምቶኛል።” (“The Continuing Power of the Holy Ghost,” *Ensign,* July 1973, p. 117.)

ያስጠነቅቀናል

አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከአደጋ እና ከፈተና ያስጠነቅቀናል። ቄስ ፍራንክሊን ዲ. ሪቻርደስ የአንድ ወጣት አባላትን ተሞክሮ ይነግረናል።

“አንድ ምሽት ከእንቅልፋ ተነስቶ ወደ ታችኛው ክፍል እንዲሄድ አንድ ድምፅ በግልፅ ነገረው። ማስጠንቀቂያውን ተቀብሎ ወደ ማእድ ቤት ሲሄድ አንዱ ግድግዳ በእሳት ተሸፍኖ አገኘው። በፍጥነት ቤተሰቦቹን በሙሉ ቀሰቀሰ፣ ለእሳት አደጋ ጥሪ አደረገ፣ ከዚያም እሳት አደጋ ተከላካይ መጥቶ እስኪያጠፋው ድረስ ከቤተሰቦቹ ጋር ሆኖ እሳቱን ለመቀነስ ጥረት አደረገ።

“ይህ መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን ከመንፈሱ ጋር አስማምተው ለሚኖሩ ሰዎች የሚሰጠውን ጥበቃ እያየ መሆኑን በአዕምሮው ውስጥ ምንም ጥያቄ አልነበረውም።” (“The Continuing Power of the Holy Ghost,” *Ensign,* July 1973, p. 117.)

የቤተክርስቲያኑ አባል ከሆናችሁበት ጊዜ ጀምሮ፣ መንፈስ ቅዱስ ከፈተና እና ከአደጋ እንድትጠነቀቁ ያደረገበት አጋጣሚ ነበርን?

ሊያጽናናን ይችላል

ብዙ ሰዎች በስቃይ ወይም በሐዘን ጊዜ የተሰማቸውን የመንፈስ ማጽናናት መስክረዋል። መንፈስ ቅዱስ ሰላም እና መረዳትን እንዲያገኙ ረድቷቸዋል።

ቄስ ፍራንክሊን ዲ ሪቻርደስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተሞክሮ ነግረውናል፥

"ባሎቻቸው በጣም አሳዛኝ በሆነ የአውሮፕላን አደጋ የሞቱባቸው ሁለት የቀርብ ጓደኞች የሆኑ ሴቶች ጋር መተዋወቀ በመቻሌ ለእኔ ልዩ አጋጣሚ ነበር። በተስፋ መቁረጥ እና በጥልቀ ሐዘን ውስጥ ሆነው ያገኘኋቸው ይመስላችኋልን? በፍፁም አልነበረም። እንደዚህ ያለ ታላቀ ብርታት እና ጥንካሬ አይቼ አላውቀም። ሁለቱም የመንፈስ ማፅናኛ እንዳገኙ መስክረዋል . . . እናም ለቤተክርስቲያኑ በቀረቡ እና የጌታን ትዕዛዛት በጠበቁ ጊዜ ድረስ እነሱ እና ቤተሰባቸው ማረጋገጫ አግኘተው ነበር።" ("The Continuing Power of the Holy Ghost," *Ensign,* July 1973, p. 117.)

ከክፍሉ ተማሪዎች አንዱ የሚከተለውን ታሪክ እንዲያቀርብ ያድርጉ።

ፕሬዚዳንት ሄበር ጄይ፣ ግራንት ለቤተሰቦቹ መንፈስ ቅዱስ ዕውቀት እና መፅናናትን እንዴት እንደሰጣቸው ይነግሩናል፥

"ሚስቴ ከመሞቷ አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ፣ ልጆቼን ወደ ክፍሏ ጠራኋቸው እና እናታቸው ልትሞት ስለሆነ እንዲሰናበቷት ነገርኳቸው። እድሚዋ አስራ ሁለት ዓመት የሆናት ትንሽዋ ሴት ልጅ እንዲህ አለችን፥ "አባባ እናቴ እንድትሞት አልፈልግም። ለስድስት ወር ያህል . . . ከአንተ ጋር ሆስፒታል ነበርኩኝ፣ እማዬ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጭንቀት ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ ትባርካት እና ከስቃይዋ ድና እንቅልፍ ይወስዳት ነበር። እማዬ ላይ እጅህን ጭነህ የክህነት በረከት አድርገህላት እንድታድናት እፈልጋለሁኝ።'

"ለትንሽዋ ልጄ አንድ ቀን ሁላችን የምንሞትበት ጊዜ እንደሚመጣ ነገርኳት፣ እናም እናትዋ የምትሞትበት ጊዜ መድረሱን በልቤ እንደተሰማኝ ገለፅኩላት እሷ እና የቀሩት ልጆች ክፍሉን ለቀው ሄዱ።

"ከዚያም ከሚስቴ አልጋ ስር ተንበረከኩኝ (በዚህ ጊዜ ህሊናዋን ስታ ነበር) ለጌታ በህይወት፣ በሞት፣ በደስታ፣ በሐዘን፣ በብልፅግና፣ ወይም በችግር ጊዜ ያለውን ስልጣን እንዳደነቅኩኝ ነገርኩት ሚስቴ ለዘለዓለም የእኔ መሆንዋን በማወቄ አመሰገንኩ። . . . ግን የሚስቴን ሞት ማየት እና የትንሽዋ ልጄ እምነት በመነካቱ ጥንካሬዬን በማጣቴ ለጌታ ነገርኩት . . . ባለኝ ጥንካሬ ሁሉ ጌታን ለመንኩ . . . ትንሿ ልጄን የእናትዋ መሞት የእሱ ሐሳብ እና ፈቃድ መሆኑን እንድታውቀ እንዲያደርጋት ለመንኩት።

"በአንድ ሰዓት ውስጥ ሚስቴ አረፈች፣ እናም ልጆቹን ወደ ክፍል ጠራኋቸው። እድሚው አምስት ዓመት ተኩል የሚሆነው ልጄ አምርሮ ሲያለቅስ ነበር፣ የአስራ ሁለት ዓመቷ ልጄ በእጇ ይዛው እንዲህ አለችው፥ "ሄበር፣ አታልቅስ፣ አታንባ፣ ከዚህ ክፍል በወጣን ጊዜ የጌታ ድምፅ ከገነት እንዲህ ብሎኝ ነበር፥ በእናትሽ ሞት የጌታ ፈቃድ ይፈጸማል።" (*Gospel Standards,* p. 316.)

ስለ እውነት ይመሰክራል

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው የወንጌል ምስክርነት የምናገኘው።

የሚከተለውን ታሪክ ከክፍሉ ተማሪዎች አንዱ እንዲያቀርብ ያድርጉ።

አንዲት አይሁዳዊት ሴት ስለ ቤተክርስቲያኑ ለማወቅ ፍላጎት ስላደረባት ወደ ህዝብ ቤተመፅሐፍ ሄደች እና የጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ *የወንጌል መሰረተ ሐሳቦች*የተባለውን መፅሐፍ መረመረች። በምታነብበት ጊዜ በጣም ለማወቅ ፍላጎት አደረባት። የሞርሞኖችን ቤተክርስቲያን ለመጎብኘት ወሰነች። እንዲህ አለች፧

“በዚያን ጊዜ ካገባሁኝ በኋላ፣ ባለቤቴን ወደ ሞርሞኖች ቤተክርስቲያን እንዲወስደኝ ጠየቅኩት። የክርስቶስ መስቀል አይ ይሆናል በሚል ፍርሃት በቤተክርስቲያኑ በር ላይ ለመግባት ፈራ ተባ ማለቴን አስታውሳለሁ። ቤተክርስቲያኑ ሞቀ ባለ የጓደኝነት ስሜት ሰዎችን በሚቀርቡ ሰዎች ተሞልቶ በማየቴ ሰውነቴ በደስታ ተወረረ። የሰንበት ትምህርት አገልግሎቶች በሙሉ ከረዥም ጉዞ ወደ ቤቴ እንደተመለስኩኝ እንዲሰማኝ አድርገዋል።

“ከአገልግሎቱ በኋላ ለሁሉም የሚሆን ትምህርት መኖሩን ተነገረን፣ በዚህም ክፍል ማለትም ከጊዜ በኋላ የመማሪያዎች ክፍል መሆኑን የተገነዘብኩት ሄደን እንድንሳተፍ ተጋበዝን። በዚያ ሰንበት ይሰጥ የነበረው ትምህርት ስለ ቤተክርስቲያኑ አደረጃጀት ነበር። ስለ ጳጳስ ኃላፊነት በተነሳ ጊዜ ጳጳስ ማለት ራቢ ነው የሚል ግምት አደረብኝ። ከዚያም በኋላ መምህሩ የመሰብሰቢያውን አዳራሽ አካባቢ በሚያሳየን ጊዜ እንዲህ አልኩት፣ ‘በመጀመሪያ እንዲህ ብዬ ስናገር ቀር እንደማትሰኝ ተስፋ አደርጋለሁ፣ ግን በቤተክርስቲያናችሁ አንድ ጳጳስ ልክ እንደ ራቢ አይደለም። አንድ ራቢ ተራ መምህር ነው፣ ግን የእናንተ ጳጳስ ከእግዚአብሔር ስልጣን ያለው ነው።’

“ለራሴ ይህን ነገር ስናገር መስማቴ በጣም አስደነቀኝ። ይህም ገና ጅምሩ ብቻ ነበር። በዚያን ጊዜ ስለነዚህ ነገሮች ዕውቀት እንዴት እንደአገኘሁ ሐሳቡም አልነበረኝም። *ጎስፔል ዶክትሪን* የተባለውን መጽሐፍ መጨረሴ እርግጥ ነው፣ ግን የሁለት ቀን ንባብ 543 ገፆች አዳዲስ ሐሳቦችን የያዘ መፅሐፍ በዓዕምሮ ውስጥ ማስረፅ በቂ አልነበረም። ከጊዜ በኋላ ግን ይህ የልብ ማስተዋል . . .የመንፈስ ማረጋገጫ . . . ማለትም ዕውቀቴን ወደ መረዳት እየተቀየረ እንደመጣ ተረዳሁኝ። (Renጵe Pool Vorhaus, “The God of My Fathers,” *Ensign,* Feb. 1978, p. 20.)

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፣ የእግዚአብሄር ነብይ እውነትን በሚገልፅበት ጊዜ ሁሉም የቤተክርስቲያን አባል ሊረዳው ይችላል። ፕሬዚዳንት ብሪግሃም ያንግ እንዲህ ሲል ምክሩን ሰጥቶናል፣

“እኛ እራሳችን በመንፈስ ቅዱስ ስንገፋፋ ብቻ ተናጋሪው በመንፈስ ቅዱስ ተገፋፍቶ እንደተናገረ ልንረዳ እንችላለን። ስለዚህ፣ የቤተክርስቲያኑ አባላት ልክ እንደመሪዎቻቸው ትጉህ መሆናቸው አስፈላጊ ነው።” (Quoted by Henry D. Moyle, in Conference Report, Apr. 1962, p. 101: or *Improvement Era,* June 1962, p. 407.)

የመንፈስ ቅዱስ በረከቶች እውነተኛ ናቸው። እነዚህን በረከቶች እንደ የቤተክርስቲያኑ አባልነታችን በፅድቅ ከፈለግናቸው ልናገኛቸው እንችላለን።

ከክፍሉ ተማሪዎች አንድዋ የመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነት የተሰማትን ጊዜ ለተማሪዎቹ እንድትገልፅ ይጋብዙ። (ይህ በመዝሙሮች፣ በጸሎት፣ ወይም ከጌታ ጋር መነጋገር ወይም አብሮ የመሆን ስሜት በተሰማበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ወይም በትምህርቱ ከተገለፁት ተሞክሮዎች ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።)

## ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ ታላቅ በረከት ነው። እንደ ቤተክርስቲያኑ አባል ሆነው ለፀኑት ሰዎች የሚሰጥ ነው። ይህ መንፈስ በምድር ላይ ያለን ተልእኮ በተሳካ ሁኔታ እንድንፈፅም አስፈላጊ ነገር ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነት ብቁ እስከሆንን ድረስ፣ ለሁሉም የህይወታችን ክፍል ሊረዳን ይችላል።

## ሙከራ

በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ የመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነትን ፈልጉ። በሚከተሉት በማናቸውም መንገዶች ማሻሻል ትችላላችሁን?

1. ሁሉንም ትዕዛዛት ለመጠበቅ መሞከር።
2. ሁልጊዜ መፀለይ።
3. ለአዳኛችን ፍቅር ማሳየት።
4. ሌሎችን ማገልገል።
5. ሐሳባችንን እና ድርጊታችንን ንፁህ እንዲሆን ማድረግ።
6. ጌታን ለበረከቱ ማመስገን። ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ እሱን ማመስገን።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

የሐዋሪያት ሥራ 5፥32 (መንፈስ ቅዱስ፣ ምስክር ነው)
1ኛ ኔፊ 10፥17 (በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እዩ፣ አዳምጡ፣ እንዲሁም እወቁ)
2ኛ ኔፊ 31፥13 (በመላዕክት ልሳን ተናገሩ)
ት እና ቃ 107፥56 (በመንፈስ ቅዱስ የወደፊቱን መተንበይ)
ሙሴ 6፥61 (አጽናኝ)

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረቶች*፣ ምዕራፍ 21፣ “የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ” የሚለውን ያንብቡ።
2. የክፍሉ ተማሪዎች ቅዱስ ፅሑፎቻቸውን እንዲያመጡ ያስታውሷቸው።
3. ጥቁር ሰሌዳ እና ጠመኔ ያዘጋጁ (ወይም የተሰጡ ሐሳቦች ዝርዝሮች እና ፖስተር ያዘጋጁ)።
4. ተማሪዎቹ ለዚህ ትምህርት የሚሆን ቅዱስ ፅሑፍ እና ታሪክ እንዲያቀርቡ ይመድቧቸው።

# ምስክርነት

ትምህርት 5

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ የተመለሰውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ምስክርነት እንድንቀበል፣ እንድንገነባ፣ እንድንሰጥ ለመርዳት ነው።

---

**ምስክርነት ምንድነው?**

ምስክርነት ከእኛ ምክንያት የመስጠት ችሎታ ብቻ የሚመጣ መደምደሚያ አይደለም። ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እንዲህ ብለው ነበር፥ "ምስክርነቶች፣ የተጨባጭ ነገሮች ክምችት ብቻ ሳይሆኑ፣ ስሜቶች ናቸው" (Margaret Hoopes, "Community and Communing," *Ensign,* Jan. 1978, p. 50)።

የወንጌል ምስክርነትን "መንፈስ ቅዱስ (ውስጣችን) ላለው መንፈስ ሲነግረው እንቀበላለን፣ ፀጥ ያለ ትንሽ ድምፅ ተንሾካሽኮ ሲሰማ ይመጣል።" "በረጋ፣ እና በማያጠራጥር እርግጠኝነት" ይመጣል።

"በእያንዳንዱ ዋጋ ባላቸው ምስክርነት ሶስት ታላላቅ ሐቆች መካተት አለባቸው፥ 1. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እና የዓለም አዳኝ መሆኑ። (ት እና ቃ 46፥13)፣ 2. ዮሴፍ ስሚዝ በዚህ ዘመን ወንጌል በእሱ አማካኝነት እንዲመለስ ያደረገ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው፣ እና 3. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በመላው ምድር ብቸኛው እውነተኛ እና የሚኖር ቤተክርስቲያን መሆኑ ነው። (ት እና ቃ 1፥30) (Bruce R. McConkie, *Mormon Doctrine,* 2nd ed., pp. 785–86.)

ፕሬዚዳንት ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥተዋል፥

"ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ ምስክርነቴን ለእናንተ ልሰጥ እፈልጋለሁ፣ ምክንያቱም እኔነቴን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረኝ ዋስትና ስለተቀበልኩኝ ነው። በልቤ ውስጥ ሰርፀዋል፣ እያንዳንዱን የነፍሴን ስር ሞልቶታል፣ ስለዚህ እግዚአብሔር ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ፣ የህያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፣ የዓለም አዳኝ እንደሆነ እንደገለፀልኝ፣ ዮሴፍ ስሚዝ ይህን ዘመን እንዲመራ የተሾመ እና የተመረጠ የእግዚአብሔር ነብይ እንደሆነ፣ እንደነበር፣ እና ሁሌም እንደሚሆን እንደገለፀልኝ በዚህ ህዝብ ፊት መናገር እፈልጋለሁ። . . . በህይወት እስካለሁ ድረስ ይህ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፣ እናም ለእውነተኛነቱ ምስክርነቴን እሰጣለሁ . . . ይህ የእግዚአብሔር መንግስት እንደሆነ እና በእግዚአብሔርም እንደሚመራ አውቃለሁኝ። ህዝቦቹን ይመራል። የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንቶችን ይመራል፣ . . . እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ የቤተክርስቲያኑን መሪዎች ይመራል፣ ለሌላ ሕዝብ እንዲሰጥ አይፈቅድም፣ ለሰዎች ብቻ አይተውም።" (*Gospel Doctrine,* pp. 501–502.)

እነዚህ የእግዚአብሔር ነብይ ቀስቃሽ ቃላቶች ናቸው። ግን የምስክርነት ኃይል ለነብያት ብቻ የተሰጠ አይደለም። ፕሬዚዳንት ብሪግዛም ያንግ እንዲህ ብለዋል፣ "የኋለኛው ቀን ቅዱሳን

ሃይማኖታቸው እውነት እንደሆነ ማወቅ ኃላፊነታቸው እና ልዩ መብታቸው ነው (*Discourses of Brigham Young*, p. 429)።

እያንዳንዳችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የዮሴፍ ስሚዝ፣ እና የህያው ነቢያችን ምስክርነት የማግኘት መብት እና ኃላፊነት አለን። የመፅሐፈ ሞርሞን፣ የአስራት ሕግ፣ የጥበብ ቃላት፣ እና ስለ ሌሎች የወንጌል መሰረቶች ሁሉ ምስክርነት ልናገኝ እንችላለን።

እህቶች ወደ ቤተክርስቲያኑ ሲለወጡ ስለነበረው ሁኔታ ወደኋላ እንዲያስቡ ይጠይቁአቸው። ከመጠመቃቸው በፊት ስለ ወንጌል መሰረቶች ያገኙት ምስክርነት ካለ እንዲዘረዝሩ ያድርጉ።

## ምስክርነት እንዴት ይመጣል?

መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን፣ ለልባችን፣ እና ለአዕምሮአችን የወንጌልን እውነተኛነት ሲመሰክር ምስክርነትን እናገኛለን።

ትምህርት እና ቃልኪዳን 8፡2–3 ያንብቡ። መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚመሰክር ያብራሩ። *የወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 7 ንዑስ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ለምን አስፈላጊ ሆነ? የሚለውን ያጣቀሱ።

ለአንዳንዶች ምስክርነት ማግኘት ግልፅ የሆነ ተሞክሮ ነው። ይህ ለሄኒሬች ስቲልገር፣ በፍራንክፈርት፣ ጀርመን ለነበረው እውነት ነበር። በሽማግሌዎች ከተጎበኘ በኋላ ለመጠመቅ ወሰነ። ግን ቀኑ በቀረበ ቁጥር ውሳኔውን እንደገና መመርመር ጀመረ። ሲጋራ ማጨስ እና መጠጥ መጠጣት ማቆም እንደሚችል እና ማቆም እንዳለበት ሊያምን አልቻለም ነበር። ሚስዮናውያኑ ትዕግስተኞች ነበሩ፣ ግን የጥበብ ቃል እውነት እንደሆነ ሊያሳምኑት አልቻሉም ነበር። ሌላ ሚስዮናዊ መጣና ለምስክርነት እንዲፀልይ ጠየቀው። በመጨረሻ እንደተባለው አደረገ። ወንድም ስቲልገር ከዚያ በኋላ እንዲህ አለ፣

"በጣም የሚያበራ ምስል ተመለከተኩኝ እናም የጥበብ ቃል እና የአስራት ህግ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት እንደሆኑ የሚነግረኝን ድምፅ ሰማሁኝ፣" ("His Testimony Came through prayer," *Church News*, 17 Jan. 1970, p. 6)።

ለብዙ ሰዎች፣ ምስክርነት በጣም ግልፅ ባልሆነ መንገድ ይመጣል። *እነዚህ በጣም ግልፅ ያልሆኑ ምስክርነቶች ያነሰ ጥቅም እና ዋጋ ያላቸው ናቸው ሊባሉ አይችሉም*። የቤተክርስቲያኑ ነቢያት እና ሐዋሪያትም ቢሆኑ በጣም ግልፅ ባልሆነ መንገድ ምስክርነታቸውን ያገኙ አሉ። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ ምስክርነቱን እንዴት እንዳገኘ ይገልፅልናል፣

"ልጅ ሳለሁ ስለ ወንጌል መሰረቶች፣ ስለ ክህነት ኃይል፣ እና ስለዚህ ሥራ ክብር በተመለከተ ምስክርነት ሰምቼ ነበር። ከፀለይን ምስክርነትን እንደምናገኝ ሰምቼ ነበር፣ ግን ወጣት ሳለሁ መገለፅን ካላገኘን በስተቀር ምስክርነትን እንደማናገኝ ሃሳቡ ነበረኝ። የነብዩ ዮሴፍ ስሚዝን የመጀመሪያ ሕልም አንብቤያለሁ፣ እናም ያየው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር መሆኑን አውቄያለሁ፣ ድምጾችን ስለሰሙ ሽማግሌዎች ሰምቻለሁ፣ . . . እናም እነዚህ ነገሮች ምስክርነት እንደሆኑ በሆነ መልኩ ይታወቀኝ ነበር . . .

"አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ በኮረብታማ አካባቢ ፈረሴን ስጋልብ፣ ስለዚህ ነገር አስብ ነበር፣ እናም በዚህ ፀጥ ባለው ኮረብታ ምስክርነት ለማግኘት ከሁሉም የተሻለ ቦታ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደረስኩኝ ፈረሴን አቆምኩ . . .

“ተንበረከኩኝ እና በሙሉ ልቤ ወደ እግዚአብሔር በክብር ፀለይኩኝ፣ እናም ስለ ወንጌል ምስክርነት እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት። በአዕምሮዬ ውስጥ መገለፅ ማለትም በልቤ ውስጥ ምንም ጥርጣሬ እንዳይኖር የሚያደርግ ለውጥ መኖር እንዳለበት ይሰማኝ ነበር።

“ተነሳሁ እና ፈረሴ ላይ ወጣሁ፣ ፈረሱ መጋለብ ሲጀምር . . . ለራሴ እንዲህ አልኩ፣ ጌታው፣ ምንም ለውጥ የለም፣ ከመንበርከኬ በፊት እንደነበርኩት ነው አሁንም ያለሁት የተጠበቀው መገለጥ አልመጣም. . . .

“ይህ ሥራ መለኮታዊ እንደሆነ የሚመሰክረው ምስክርነት. . . . የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመታዘዝ፣ እና ክርስቶስ ከሰጠን ተስፋ ጋር የመጣ ነው፣ ፈቃዱን ሊያደረግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል። (ዮሐንስ 7፥17.)” (“A Personal Testimony,” *Improvement Era,* Sept. 1962, pp. 628–29.)

ፕሬዚዳንት ማሪዮን ጂ ሮምኒ እንዴት ምስክርነቱን እንዳገኘ ያብራራልናል፥

“አንዳንድ ጊዜ ለሰዎች ምስክርነት ቀስ በቀስ ከብዙ ጊዜ በኋላ ይመጣል። ምስክርነት ለእኔ በድንገት የመጣበትን ቀን አላስታውስም . . . ምስክርነት ያላገኘሁበትን ጊዜም አላስታውሰውም። በእርግጥ ከዓመት ወደ ዓመት እየጠነከረ መጥቶአል፣ ግን ያላመንኩበትን ጊዜ በፍፁም ላስታውስ አልችልም። ግን ምስክርነት በድንገት መጣም ደረጃ በደረጃ ቢመጣም ለግለሰቡ አንድ ትርጉም ይኖረዋል። አንድ ግለሰብ ምስክርነት ካገኘ በኋላ የተለየ ይሆናል።” (“How to Gain a Testimony,” *New Era,* May 1976, p. 11.)

ማናችንም ብንሆን ምስክርነታችን ተአምራዊ በሆነ መንገድ ስላልመጣ ከሁሉ ያነሰ ምስክርነት ነው ብለን ማሰብ የለብንም።

### ምስክርነት ለማግኘት እንዴት መዘጋጀት አለብን?

ምስክርነት ለማግኘት የሚጠቀሙ አምስቱ መንገዶችን የሚያሳይ ፖስተር አሳያቸው።

1. እምነትን መሻት
2. ቅዱሳን መጻሕፍትን መመርመር
3. የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈፀም
4. በክርስቶስ በማመን ማሰላሰል እና መጸለይ
5. ዘወትር መፆም እና መጸለይ

ስለ ፖስተሩ ሲወያዩ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ያብራሩ፥

እምነትን መሻት

የመጀመሪያ ደረጃ እርምጃ የሆነው እምነትን መሻት ጠቃሚ ነው።

አልማ 32፥26–27 አንብቡ። እውነትን ለማወቅ መሻት በፕሬዚዳንት ማኬይ እና ሄንሪቻ ስቲልገር ተመክሮ ላይ ምን ተፅዕኖ ነበረው? ይህ ተመሳሳይ ጉትት ዮሴፍ ስሚዝን እንዴት ይነካዋል?

ቅዱሳን መጽሐፍትን መመርመር

ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት ምስክርነትን እንድንቀበል ይረዳናል። ምስክርነት እንዲመጣ ካልጣርን በቀር እራሱ ዝምብሎ አይመጣም።

ት እና ቃ 9፥7–9 አንብብ።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈፀም

ይህ ነቢዩ ዴቪድ ኦ ማኬይ ምስክርነቱን ያገኘበት መንገድ ይህ ነው።

ዮሐንስ 7፥17 ያንብቡ።

በክርስቶስ በማመን ማሰላሰል እና መፀለይ

ከመንፈስ ቅዱስ እውቀትን ለመቀበል፣ መጠየቅ አለብን። በተጨማሪም እግዚአብሔር ስለሚያፈቅረን ሰይጣንም ሆነ ሌላ ሰው እንዲያታልለን እንደማይፈቅድ ማመን አለብን።

ሞሮናይ 10፥3–5 ያንብቡ።

ዘወትር መፆም እና መፀለይ

ፆም የፀሎትን ኃይል ይጨምራል። ፆም እና ፀሎት ምስክርነታችንን እንድናገኝ ይረዱናል።

አልማ 5፥45–46 ያንብቡ።

አኔት ፓርክንሰን የተባለች ልጃገረድ ፀሎት ብታደርግም፣ ቅዱስ ፅሑፎችንም ብታነብም፣ እንዲሁም ትዕዛዛትን ብትጠብቅም ምስክርነት የማግኘት ችግር ነበረባት እሷም እንዲህ ትላለች፥

"እታለል ይሆን በሚል ፍርሐት እጨነቅ ነበር፣ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ እውነተኛ ምስክርነት የተለየ ምስክርነት የተቀበልኩኝ መስሎኝ እራሴን አታልል ይሆን እያልኩ አስብ ነበር። መታለል ከማንኛውም ነገር ይልቅ የምፈራው እና የምጠላው ነገር ነው። በእግዚአብሔር የማመን ሀሳብ በአየር ላይ እንደመዝለል እና የሆነ ሰው ይይዘኛል ብሎ እንደመጠበቅ አስፈሪ ነበር። ቢሆንም ምስክርነት ለማግኘት የምፈልግ ከሆነ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ይገባኝ ነበር።

"እምነት ማግኘት በአንድ ጊዜ የሚሆን ነገር እንዳልሆነ ተገነዘብኩኝ። ግን በጌታ እንደማምን ለማሳየት ከልብ እጥር ነበር። ጊዜያት ባለፉ ቁጥር፣ በውስጤ በጣም አስደናቂ የሆነ ነገር መፈፀም ተጀመረ። አንድ ቀን አልጋዬ ላይ ቁጭ ብዬ ሳለሁ፣ ከዚህ በፊት አጋጥሞኝ የማያውቅ ስሜት ተሰማኝ፣ በእርግጥ ሙሉ በሙሉ አዲሱ ስሜት አልነበረም። በተቀመጥኩበት ለራሴ እንዲህ ማለቴን አስታውሳለሁ፣ ጌታ ፀሎቴን ሰምቶኛል፣ አሁን እሱ እንዳለ አወቅኩኝ። በእውነት እሱ እንዳለ አውቃለሁ!

"ስሜቱ ጥልቅ፣ ሰፊ፣ እናም ጣፋጭ እና ሰላማዊ ነበር። እግዚአብሔር እንዳለ አውቅ ነበር እናም ምን ያህል ደስተኛ ነበርኩ!

"በእርግጥ ይህ የትግሌ መጨረሻ አልነበረም፣ አሁንም ቢሆን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኜ መሆኑን፣ ዮሴፍ ስሚዝ ነብይ እንደነበር፣ የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ነብይ እንደሆነ ማወቅ እፈልግ ነበር . . .

"ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የወንጌል እውቀቴ መቶ እጥፍ ጨመረ፣ እናም በብዙ ነገሮች ላይ ምስክርነት አገኘሁ።" ("Trust, a Key to Testimony," *New Era,* Feb. 1978, p. 33.)

ለምንድነው አንዳንድ ጊዜ እምነትን ለማዳበር አስቸጋሪ የሚሆነው? ምስክርነት ለማግኘት ያለንን ፍላጎት ካገኘንም በኋላ ቢሆን ድርጊታችንን እንዴት ይለውጠዋል?

**ምስክርነትን ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?**

ቄስ ሔበር ሲ ኪምቦል እንዲህ ብሎ ነበር፥

“የሚመጡትን ችግሮች ለመቋቋም፣ ለራሳችን የዚህ ሥራ እውነተኛነት እውቀቱ እንዲኖረን አስፈላጊ ነው…

“ወንድም ሆነ ሴት በሌላው ሰው ምስክርነት የማይመኩበት ጊዜ ይመጣል። እያንዳንዱ ሰው በራሱብርሃንየሚመራበትጊዜ ይመጣል። ይህ የሌላችሁ እንደሆነ እንዴት ትቋቋሙታላችሁ?” (In Orson F. Whitney, *Life of Heber C. Kimball,* 3rd ed., p. 450.)

ፕሬዚዳንት ሐሮልድ ቢሊ እንዲህ ብለው ነበር፥

“ምስክርነት ዛሬ የምታገኙት ወይም ሁልጊዜ የሚኖራችሁ ነገር አይደለም። ምስክርነት ተሰባሪ ነው። እንደ ጨረቃ ጨረር ለመያዝ አስቸጋሪ ነው። ሁልጊዜ በህይወታችሁ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ያለባችሁ ነገር ነው።” (J. M. Heslop, President Harold B. Lee Directs Church; Led by the Sprit,” *Church News,* 15 July 1972, p. 4.)

ቄስ ጆርጅ ኪው ካኖን እንዲህ ሲል ጽፏል።

“የዚህ ሥራ እውነተኝነት ትናንትና ወይም ከትናንትና ወዲያ ወይም ከሳምንት በፊት ወይም ከወር በፊት ወይም ከዓመት በፊት ማወቁ በቂ አይደለም፣ ደስተኞች ለመሆን ዛሬ እውነት መሆኑን ማወቅ ይገባናል፣ እንዲሁም ማወቅ አለብን . . . ከእግዚአብሔር ጋር ቀርበን በመኖር ብቻ ነው እውነትን ማቆየት የምንችለው።” (*Gospel Truth,* 1:343.)

አልማ ምስክርነትን ተወዳጅ ዛፍ ሆኖ እንዲያድግ እንክብካቤ ከሚደረግለት ዘር ጋር አወዳድሮታል።

አልማ 32፥37–38 ያንብቡ። ምስክርነታችንን እንድናጣ የሚያደርጉን ምን ምን ነገሮችን ስንፈፅም ነው?

አልማ 32፥41 ያንብቡ። ምስክርነታችንን እንዴት ልንንከባከበው እንችላለን?

ምስክርነታችንን እና የሌሎችን ምስክርነት የምንገነባበት አንዱ መንገድ ዘወትር በመመስከር ነው። አባል ላልሆኑ ሰዎችም የመመስከር ኃላፊነት አለብን። በየወሩ በፆም እና ምስክርነት ስብሰባ ቀን፣ የተወሰኑ የወንጌል መሰረቶች እውነት እንደሆኑ እንደምናውቅ ለመመስከር እንችላለን። በተጨማሪም እንዴት እንዳወቅን ልናብራራ እንችላለን። ስለ አዳኛችን መለኮታዊ እና የኃጢያት ክፍያ፣ ስለ ዮሴፍ ስሚዝ እንደ ነብይ መጠራት፣ እና የአሁን ጊዜ ነብያችንን ጥሪ መመስከር እንችላለን። መመስከር ስሚታችን እንዲረዳ እና ግምት እንድንሰጠው ይረዳናል። ምስክርነታችን በእኛ ውስጥ እንዲያድግ ይረዳናል። ዘወትር መመስከር ምስክርነት እንዳለን እንድንገነዘብ ይረዳናል።

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንመሰክር፣ ሌሎች ከመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ሊያገኙ ይችላሉ። ከዚያም የምንናገረው ነገር እውነት እንደሆነ ያውቃሉ። በተጨማሪም ስህተታቸውን መቋቋም እንዲችሉ እና የተሻለ ሰው እንዲሆኑ ፍላጎት ሊያድርባቸው ይችላሉ። ጥሩ የሆነ የምስክርነት ስብሰባ የዋርድ ወይም የቀርንጫፍ አባላት በአንድ ላይ አንድ ትልቅ ቤተሰብ እንዲሆኑ ይስባቸዋል።

ምስክርነት የአንድ ግለሰብ በጣም ውድ የሆነ ሐብት ነው። የፅድቅ ሕይወት መኖር፣ ሌሎችን ማገልገል፣ እና መመስከር አለብን። ይህን ካደረግን፣ ምስክርነታችን ኃይል ያገኛል እናም ደስታን፣ ጥንካሬን፣ ሰላምን በሕይወታችን ውስጥ ያመጣል።

## ሙከራ

ምስክርነታችሁን ስጡ።

---

### የአስተማሪ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. የወንጌል መሰረቶች፣ ምዕራፍ 7፣ ንዑስ ምዕራፍ "መንፈስ ቅዱስ ለምንድነው አስፈላጊ የሆነው" የሚለውን ያጥኑ።
2. አልማ 32፥26–43፣ ኢተር 12፥6 ያጥኑ።
3. ምስክርነት የሚገኝባቸው አምስቱ ደረጃዎችን የሚያሳይ ፖስተር ያዘጋጁ (ወይም ሰሌዳ ላይ ይጻፉ)
4. ስብሰባውን "አዳኜ እንዳለ አውቃለሁኝ" በሚለው መዝሙር ለመክፈት ያቀዱ።
5. ለትምህርቱ የሚሆኑ ታሪኮችን እና ቅዱስ ፅሑፎችን ተማሪዎቹ እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# ጾም

ትምህርት 6

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ እራሳችንን እና ቤተሰቦቻችንን በፆም እንዴት ማጠንከር እንደምንችል ለማሳወቅ ነው።

---

## ትክክለኛው የአጿጿም መንገድ

የተመደበችው የክፍሉ ተማሪ *ከወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 25፣ "ጾም" የሚለውን ምዕራፍ ለሶስት ደቂቃ እንድትከልስ ያድርጉ።

## የጾማችንን መንፈሳዊነት መጨመር

ስንፆም እና ስንፀልይ፣ ከዓለማዊ ነገሮች እንርቃለን። መፆም በጌታ ያለን ጥገኝነት እንድንገናዘብ ይረዳናል። ፆም የፀሎታችን ቁምነገረኛነትን ያጎላል። እግዚአብሔር ለእኛ እና ለቤተሰባችን ያለውን ፈቃድ ለማወቅ እና ለመቀበል ልባችንን እንከፍታለን።

እንደ ሴትነታችን፣ በቤተሰባችን ውስጥ ያለውን ስሜት እና አስተሳሰብ ማሻሻል እንችላለን። ፍላጎቱ ካለን፣ እራሳችን እና ቤተሰባችን የፆማችንን መንፈሳዊነት መጨመር እንድንችል መርዳት እንችላለን።

የክፍሉን ተማሪዎች አልማ 32፥27 እንዲያነቡ ይጠይቁአቸው። የፆም ተሞክሮአችሁን እንዴት ማዳበር ትችላላችሁ? እህቶች ለመፆም ፍላጎት እንዲያድርባቸው እና ፆማቸውን ለማሻሻል እንዲያቀዱ ያበረታቱአቸው።

በህይወታችን ውስጥ አንድ ነገር ለመለወጥ ስንፈልግ፣ ለውጥ የሚያመጡትን ነገሮች ማቀድ፣ ማዘጋጀት፣ እና መለማመድ ይኖርብናል።

### ለአንድ ዓላማ መፆም

ለመጾም ምክንያት ሲኖረን፣ ፆማችን የተሻለ ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል። ብዙ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች በፀሎት መፆም ከመጀመራቸው በፊት ለምን ነገር መፆም እንዳለባቸው ያስቡታል። (1) የታመመን ሰው ለመባረክ (2 ሳሙኤል 12፥16 ተመልከቱ)፣ (2) ችግሮችን ለመቋቋም እንድንችል መንፈሳዊ ጥንካሬ ለመቀበል (ኦምኒ 1፥26)፣ (3) መገለፅ እና ራዕይ ለመቀበል (አልማ 17፥3 ተመልከቱ)፣ (4) እርዳታ እና መፅናናት ለመጠየቅ (ሂላማን 9፥10 ተመልከቱ)፣ (5) በቤተሰብ ውስጥ ፍቅር እና መስማማትን ለመጨመር በትክክለኛ መንገድ መፆም እንችላለን።

ቤተሰቦች የሚፆሙባቸው አንዳንድ ምክንያቶች ምንድናቸው? ለመፆም ዓላማ መያዝ ፆማችንን እንዴት ቀላል ያደርገዋል? ይህ ዓላማ የፆምን ትርጉም ይጨምረዋል።

### የቤተሰብ አባላትን እንዲፆሙ መርዳት

ልጆቻችን ትንንሽ ልጆች ከሆኑ፣ እንዲፆሙ ማስገደድ የለብንም። ስለ ፆም ዓላማ ከእነርሱ ጋር መነጋገር አለብን። ፆማችንን በምንጀምርበት ጊዜ ስንፀልይ በፀሎታችን እነርሱንም ማካተት አለብን። አንድ የምግብ ሰዓት እንዲፆሙ በማድረግ መፆምን እንዲማሩ ልንረዳቸው

እንችላለን። ለጥምቀት በሚደርሱበት ጊዜ ሙሉ ፆም ለመፆም በተሻለ ይዘጋጃሉ። የግለሰቦች የጤና ችግርን መገንዘብ እና የቤተሰብ አባላት የሚፆሙበት መንገድ ለመፈለግ መጣር አለብን።

ትንንሽ ልጆችን ለብቻቸው በመመገብ ለመፆም የሚሞክሩ የቤተሰብ አባላትን መርዳት እንችላለን። ቤተሰቡን ፈታኝ በሆነ የምግብ መዓዛ ከሚያስቸግር ምግብ ይልቅ የተለመደውን አመጋገብ መቀየር እና በቀላሉ ሊዘጋጁ የሚችሉ ምግቦችን ማቀረብ እንችላለን። እንደ ሚስት እና እናትነታችን፣ የሰንበትን ምግብ ቀዳሚ ማዘጋጀት እንችላለን። ይህ በሰንበት ቅዱስ ጽሑፎችን ለማጥናት፣ ለመፀለይ፣ እና ስለፆማችን ዓላማ ለማሰላሰል ጊዜ እንዲኖረን ያደርጋል። ጊዜውን ለልጆቻችን ቅዱስ ፅሑፎችን ለማንበብ፣ ከእነርሱ ጋር ለመወያየት፣ እና ስለ ወንጌል ያላቸውን ፍቀር ለመጨመር ልንጠቀምበት እንችላለን። በመመገብ የምናጠፋውን የተለመደውን ጊዜ ተስማሚ በሆኑ ስራዎች ከተሞላ፣ ስላልበላንበት የምግብ ጊዜ ብዙም አናስብም። በፆም ጊዜ ከራብን፣ ስለምግብ ላለማሰብ መሞከር አለብን። ይልቁንስ እራሳችንን በመንፈሳዊነት ስለ መንከባከብ ማሰብ አለብን። ይህንንም የክርስቶስን ቃል በማክበር ልንፈፅመው እንችላለን። ከመብላት ይልቅ ቀዱስ ፅሑፎችን ማጥናት፣ ማሰላሰል፣ እምነትን መጨመር፣ እና በጸሎት መትጋት አለብን።

ት እና ቃ 59፥13–15 አንብቡ። ፆማችንን ለመፈሰክ ምግብ ስናዘጋጅ አቋማችን ምን መሆን አለበት? በዚህ ጥቀስ የተፃፈውን ምክር መከተል መንፈሳዊነታችን እንዴት ይጨምረዋል?

በፀሎት መጾም

ሁልጊዜ ጾማችንን በፀሎት መጀመር አለብን። በዚህን ጊዜ የሰማይ አባታችንን ፆሙን በጥንካሬ እንድንፈፅም እንዲረዳን መጠየቅ እንችላለን። ፆም እንደፈለግን፣ የምንፆምበት ዓላማ፣ ጾሙ ለእኛ ያለውን ጥቅም መግለፅ አለብን። በተጨማሪም የተፈለገውን በረከት ለማግኘት እርዳታ እንዲያደርግልን መጠየቅ አለብን።

የፆማችንን ዓላማ በእምነት በመግለፅ፣ ፆማችን በጸሎት መፈሰክ አለብን። ሌሎች ከእኛ ጋር ለአንድ ዓላማ አብረውን የሚፆሙ ከሆነ፣ ሁላችንም በፀሎቱ መሳተፍ አለብን። ልጆቻችን በፆም በኩል የተሳካላቸው ከሆኑ፣ በፆም መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት ለሚፈልጉ ታዛዥ እና ጠንካራ ልጆች ምስጋናችንን መግለፅ አለብን።

ለሁሉም የቤተሰባችን አባላት የፆም መንፈሳዊነትን ለመጨመር በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እንችላለን?

ወጣት እና ያላገባችሁ ከሆናችሁ፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ለመፆም እንዲዘጋጁ እና በፆም እንዲጠቀሙ ለመርዳት ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

**ፆም የኃይል ምንጭ ነው**

ችግር በሚገጥመን ጊዜ ብዙውን ጊዜ ተጨማሪ ጥንካሬ ያስፈልገናል። የክህነት ስልጣን የያዙ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የክህነት ስልጣናቸውን የመጠቀም ችሎታቸውን ለመጨመር ይፆማሉ። ከክህነት ስልጣን በረከትን በምንፈልግበት ጊዜ፣ ይህን ተመሳሳይ ደንብ በመፆም መፈፀም እንችላለን። ቄስ ማትዩ ኩሌይ ስለ ወላጆች ፆም የሚከተለውን ታሪክ ተናግረው ነበር፦

"ከአንድ ዓመት ጥቂት ቀደም ብሎ ወደ ቢሮዬ ባል እና ሚስት ትንሽ ልጅ ይዘው መጡ። አባትየው እንዲህ አለኝ፦ እኔ እና ሚስቴ ለሁለት ቀን ያህል ጾመን ነበር፣ እናም ትንሹን ልጃችን ለቡራኬ አምጥተነዋል። ወደ አንተም ልከውናል።

"እኔም፣ ምን ሆነባችሁ?" 'አልኩ'

"እነርሱም ልጁ እውር ሆኖ እንደተወለደ፣ ደንቆሮ እና ዲዳ ፣ የሰውነቱ ጡንቻ የማይታዘዝለት፣ በአምስት ዓመቱ እንኳ መዳን እንደማይችል ነገሩኝ። ለራሴ እንዲህ አልኩ እንደዚህ ዓይነቱ በጾም እና በጸሎት ካልሆነ በስተቀር አይድንም ለእነዚህ ወላጆች ለመፃም እና ለመጸለይ ግልፅ የሆነ እምነት ነበረኝ። ልጁን ባረኩት፣ እናም ከጥቂት ሳምንት በኋላ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ፡ ወንድም ከሌይ፣ አሁን ትንሹ ልጃችንን ብታየው በወደድን ነበር። እየሄደ በወለሉ ላይ ኳስ ስንወረውርለት ወደ ኳሷ በእጅ እና በጉልበቱ ይሮጣል። ማየት ይችላል። እጃችንን ስናጨበጭብ ይዘላል። መስማት ይችላል። የህክምና ሳይንስ ተስፋ ሳይቆርጥ አይቀርም። እግዚአብሔር ቦታውን ወስዷል። ("Miracles," *Speeches of the Year,* 18 Feb. 1953, p. 8.)

ስዕል 6-9፣ አስቴር፣ ለህይወትዋ ባለማሰብ በንጉሱ ፊት ፆመች የሚለውን ስዕል አሳያቸው።

አንዲት ጻድቅ ሴት፣ በታዛዥነት ሕይወቷ፣ እርሷን እና ቤተሰቧን ብቻ ሳይሆን፣ አለምን በሙሉ ልትባርክ ትችላለች። እንዲህ አይነትዋ ቀንጆ ሴት አስቴር ነበረች፣ ታሪኳም በብሉይ ኪዳን ተነግሮላታል። አይሁዳዊቷ አስቴር በፋርስ ንጉስ በመወደድዋ፣ ሚስቱ ሆነች። በዚያው ዛገር ሃማን የተባለ ኃያል ሰው የአስቴር አጎት ልጅ መርዶክዮስ በጣም ጠላቱ ነበር። በፊቱ ተንበርክኮ ሊሰግድላት ባለመፍቀዱ፣ ሁሉን አይሁዶች ለመግደል ዕቀድ አወጣ። መርዶክዮስ ይህን አሳዛኝ ዜና በሰማ ጊዜ፣ ለአስቴር ወደ ንጉሱ ሄዳ ጥበቃ እንዲያደርግላቸው እንድትጠይቀው መልዕክት ላከባት አስቴርም ህጉን በማብራራት እንዲህ ብላ መለሰችለት፡ "የንጉሱ ባሪያዎችና በአገሮችም የሚኖሩ ሕዝብ ሁሉ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ሳይጠራ ወደ ንጉሱ ወደ ውስጠኛው ወለል የሚገባ ሁሉ በህይወት ይኖር ዘንድ ህግ እንዳለ ያውቃል፣ እኔ ግን ወደ ንጉሱ ለመግባት ይህን ሰላሳ ቀን አልተጠራሁም። (አስቴር 4፡11)። መርዶክዮስም አስቴር የተባለችውን ካላደረገች ቤተሰብዋን ጨምሮ ሁሉም ሰው ይገደላል ብሎ መለሰላት።

አስቴር ኃላፊነትዋን ተገነዘበች። እንዲህ ስትል መለሰች፡ "ሄደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስበህ፣ ለእኔም ፁሙ ሶስት ቀን ለሊቱን እና ቀኑን አትብሉም፣ አትጠጡም፣ እኔ እና ደንገጡሮቼ ደግሞ እንዲሁ እንፆማለን፣ ምንም እንኳን ያለ ህግ ቢሆን ወደ ንጉሱ እገባለሁኝ ብጠፋም እጠፋለሁ።" (አስቴር 4፡16) አስቴር ለህይወቷ ባለማሰብ በንጉሱ ፊት ፆመች። ንጉሱ ወደእርሱ እንድትቀርብ ዘንጉን አነሳ፣ ሕይወትዋን ማረላት። ሕይወትዋን እና ይህን ችግር በጌታ እጅ ላይ ስለጣለች፣ ሕይወትዋ ዳነ። ንጉሱም አይሁዶች እራሳቸውን ለማዳን መከላከል እንደሚችሉ አወጁ።

የአስቴር እና የሌሎች ጾም ጥንካሬ እና ድፍረት እንድታገኝ እንዴት ረዳት? በህይወታችሁ ምን ዓይነት ሁኔታዎች ጥንካሬ እና ድፍረትን ይፈልጋሉ? ፆም እንዴት ሊረዳችሁ ይችላል፧

በመፆም የሚመጣው መንፈሳዊ ጥንካሬ በታዛዥነት እና በእምነት ይመጣል። ስንፆም እና ስንፀልይ፣ እምነታችንን ስናከናውን፣ እንዲጨመርልን በምንፈልገው ኃይል እንባረካለን። ስንፆም፣ የምስክርነታችን ጥንካሬን ይጨምራል። በፆም እና ምስክርነት ቀን ለሌሎች ለመካፈል ፍላጎቱ ያድርብናል። ልጆቻችን ስለ ወንጌል ያለንን ፍቀር በሚሰሙበት ጊዜ፣ እነርሱም በመንፈሳዊነት ያድጋሉ።



6-U

## ሙከራ

ለጾም እንዴት እንደምትዘጋጁ እና በጾም ሰንበት ምን እንደምታደርጉ መርምሩ። በቤታችሁ ውስጥ መንፈሳዊነትን ለመጨመር ጣሩ። አስተሳሰባችን እና ዝግጅታችን ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ አስታውሱ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

2ኛ ሳሙኤል 12፥1 አስቴር ከንጉሱ አንደኛው ህግ ማንም ወንድ ሆነ ሴት ወደ ንጉሱ ክፍል ሳይጠራ የገባ እንደሆነ ንጉሱ ከወርቅ የተሰራውን ዘንጉን አንስቶ ካላሳየ በስተቀር ይገደላል ብላ ገለፀችላቸው። ግን አስቴር ለሰላሳ ቀናት ወደ ንጉሱ እንድትመጣ አልተጠራችም (አስቴር 4፥11 ተመልከቱ) 6 (ዳዊት ጾሟል)
ማቴዎስ 6፥16–18 (እንዴት መፀለይ እንዳለብን)
ሉቃስ 2፥37 (እግዚአብሄርን በፆም እና በጸሎት ማገልገል)
ሞዛያ 27፥22–23 (በመፆም እና በፀሎት መፈወስ)
አልማ 5፥46 (በፆም እና በፀሎት ራዕይ ማግኘት)

---

#### የመምህሩ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. *የወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 25 "ፆም" የሚለውን ያንብቡ።
2. *የወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 25፣ ለሶስት ደቂቃ ለመከለስ ከክፍሉ ተማሪዎች አንድዋን ይመድቡ።
3. በትምህርቱ ላይ ታሪክ እና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ የክፍሉን ተማሪዎች ይመድቡ።

6-ሀ አስቴር፣ ለህይወትዋ ባለማሰብ፣ በንጉሱ ፊት በጾም ቀረበች።
© 1999 by Intellectual Reserve, Inc.

# አክብሮት

ትምህርት 7

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ ለቤተሰባችን አባላት እንዴት አክብሮት እንደምናስተምር እና የራሳችንንም አክብሮት እንዴት እንደምናሻሽል ለመርዳት ነው።

---

**መግቢያ**

የዘመናችን ነቢያት ስለ አክብሮት መክረውናል። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ እንዲህ ብሎ ነበር፥ "አክብሮት ለነፍስ ዋና አስፈላጊ ነገር ነው ብዬ ነው የምመለከተው። (In Conference Report, Oct. 1951, pp. 179–80.)

የሚከተለው በፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ተፅፎ ወደ ቤተክርስቲያኑ በልዩ በራሪ ወረቀት በ1976 የተላከ ነበር፥

"እኛ በከፍተኛ ደረጃ የተባረክን ህዝቦች ነን። ጌታ ሁሉን ነገር ሰጥቶናል፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፣ ብርሃኑን፣ ክህነቱን፣ ኃይልን፣ ቃል ኪዳንን፣ ቤተመቅደሶችን፣ ቤተሰባችን፣ እውነትን ሰጥቶናል። በምድር ላይ ደስተኞች መሆን አለብን። በተጨማሪም ከፍተኛ አክብሮት ያለን ሰዎች መሆን አለብን፣ ግን እዚህ ላይ እያንዳንዱ ግለሰብ እና ቤተሰብ እራሱን መታዘብ እንዳለበት ይሰማኛል። አክብሮት ያለን ሰዎች ነን? በቤት እና በቤተክርስቲያን የምናደርገው ድርጊት ለፈጣሪያችን አክብሮት ያሳያልን?

"አንዳንድ ጊዜ ይገርመናል። ሕፃናት ልጆች ያለማንም ክልካይ በስብሰባ መተላለፊያዎች የሚዘዋወሩበት የቀዱስ ቁርባን ስብሰባ እና ኮንፍረንስ ተሳተፈናል፣ በአገልግሎት ጊዜ፣ አዋቂዎች አጠገባቸው ካለ ሰው ጋር ሲነጋገሩ፣ ሰዎች ሲያንቀላፉ፣ እና ወጣቶች በመግቢያ በሩ ላይ አንድ ላይ ተሰብስበው አስተውለናል። ቤተሰቦች ዘግይተው መጥተው ወደ ወንበራቸው በህውከት ሲራመዱ እና ከስብሰባ በኋላ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ በከፍተኛ ድምፅ ሲያውኩ አይተናል።

"ሐሳባችን ወደ ምስክርነታቸው በቀላሉ ወደ ሚሰባበር፣ እና ታዲጊ ተመራማሪዎች እና ጓደኞቻችን፣ እናዙር። ስብሰባዎቻችን የጌታ መንፈስ ልብን የሚገዛ እና የሚቦረቡር ጠንካራ ወንጌላዊ መሳሪያ ነውን? ወይስ ከመንፈስ ጋር ለመገናኘት አስፈላጊ ያልሆኑ እንቅፋቶችን ማስወገድ አለብን?

"በአክብሮት በኋለኛው ቀን ቅዱሳን ያለው ትርጉም እና ጥቅም ብቻ ሳይሆን፣ ለልጆቻችን አክብሮት የምናስተምርበት አንዳንድ መንገዶች እና የራሳችንን አቋም የምናሻሽልበት መንገድ እንመርምር።

**የአክብሮት ትርጉም እና ጥቅም**

“አክብሮት” ቀዱስ ለሆነ ነገር ያለን ጥልቀ ክብር፣ ፍቀር፣ እና አክብሮት” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። እራሳችንን ለእግዚአብሔር መሰዋት ሌላው አክብሮትን የመግለጫ መንገድ ነው።

“አብዛኛዎቹ መሪዎቻችን አክብሮትን በተመለከተ እንደ ነፍሳችን ከፍተኛ ጥራት፣ በእግዚአብሔር እና በፅድቁ እውነተኛ እምነት እንደሚያካተት በመጠቀም፣ እንደ ከፍተኛ ባሕል፣ እና በሕይወት ውስጥ በጣም ጥሩ ለሆኑ ነገሮች ፍቀር እንደማሳደር ነው ብለው ገልፀውታል።

ለእግዚአብሔር አክብሮት

“በዘመናችን ራዕይ ላይ ጌታ የአክብሮት ትርጉምን እና ጥቀም አስረድቶናል።

“አንደኛው ምሳሌ ለአብ እና ለወልድ ያለን አክብሮት ሰማያዊ መንግስት ለመግባት እንደ አንድ መመዘኛ ወይም መለያ ጠባይ ተደርጎ ይገልፃል። በት እና ቃ ምዕራፍ 76 ለዮሴፍ ስሚዝ እና ሲድኒ ሪግደን በሬቧሪ 1932 በተሰጣቸው ራዕይ ክፍል የሚከተለውን እናገኛለን፥

“እናም እግዚአብሔር፣ አብም ዙፋኑ ላይ ቁጭ ብሎ ለዘለዓለም የሚነግስበት—ክብሩ ከሁሉም ነገር በላይ በሚልቀው ሰማይ ላይ አየነው፣

‘በዙፋኑ ፊት ሁሉም ነገር ትህትና በተሞላ አክብሮት ይሰግዳሉ፣ እናም ክብርን ለዘለዓለም ይሰጡታል።

‘እሱ ወዳለበት የሚገቡት የቤተክርስቲያኑ የበኩር ልጆች ናቸው፣ እናም እንደታዩት እነሱም ያያሉ፣ እናም እንደታወቁት እነሱም ያውቃሉ፣ ሙሉነቱን እና ፀጋውን ይቀበላሉ፣

‘እናም በኃይል፣ በክብር፣ እና በሥልጣን እኩል ያደርጋቸዋል።” (ት እና ቃ 76፥92–95)

የእግዚአብሔርን ስም ማክበር

“ሌላ የዘመናችን ራዕይ የእግዚአብሔር ስም ቢሆንም እንኳን በክብር እንድንይዝ ያዘናል፣ የአብን ስም እንዳናረክስ እና እንዲሁም በተደጋጋሚ መጠቀሙን እንድናስወግድ ተነግሮናል። (ት እና ቃ 107፥2–4)

“እዚህ ላይ ከአስሩ ትዕዛዛት አንዱን እንደሚነበበው እራሳችንን ማስታወስ አለብን፥

‘የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነፃውምና።” (ዘፀአት 20፥7።)

“እግዚአብሔርን እና ስሙን ማክበር ልናዳብረው የሚገባን አንዱ ጠቃሚ ነገር ነው።

የጌታን ቤት ማክበር

“ሌላው በጣም ጠቃሚ የሆነው ክፍል ደግሞ፣ ጌታ በዘመናችን ራዕይ ለተቀደሰ ቤቱ ተገቢ የሆነ አክብሮት እንዲኖረን ያዘናል። ለኪርትላንድ ቤተመቅደስ፣ የመመረቂያ ፀሎት ተብሎ የሚታወቀው ለዮሴፍ ስሚዝ የተሰጠው ራዕይ ላይ ይህ፣ እና ሌሎች ለጌታ የቆሙ የተቀደሱ ቤተመቅደሶች፣ ለእርሱ የተከበሩ ቦታዎች መሆን እንዳለባቸው መመሪያ ተሰጥተዋል። (ት እና ቃ 109፥13፣ 16–21 ተመልከቱ)



“በእውነታውም ዓለም፣ ለቤተክርስቲያኑ የተቀደሱ ቤተመቀደሶች የተባለው ለሁሉም “የጌታ ቤቶች፣” ማለትም ቀዱሳን የሚያመልኩበት መሰብሰቢያ ወይም ማንኛውም ቦታ፣ ወይም በእርግጥ ማንኛውም የኋለኛው ቀን ቀዱሳን የሚሰሩት ቤት ነው።

አክብሮት ደስታንም ይጨምራል

“እንደ ሌሎች የወንጌል መሰረቶች፣ አክብሮት ወደ ደስታ ይመራል።

“አክብሮት የጨፈገገ ነገር፣ ማለትም በሰንበት ቀን ብቻ የምናደርገው ጊዜያዊ ነገር እንዳልሆነ ማስታወስ አለብን። እውነተኛ አክብሮት ደስታን ይጨምራል፣ እንዲሁም ፍቀርን፣ ክብርን፣ ምስጋናን፣ እና ፈርሐ እግዚአብሔርን ይጨምራል። አክብሮት የህይወታችን አንዱ ክፍል መሆን ያለበት ጥሩ ስነ ምግባር ነው። በእርግጥ፣ የኋለኛው ቀን ቀዱሳን በምድር ላይ አክብሮት ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው።

አክብሮት እና ቤት

“አክብሮት ከየት ይጀምራል፣ እናም እንዴት ልናዳብረው እንችላለን?

“ቤት አንዱ የአክብሮት ቁልፍ ነው፣ እንደ ሌሎች እግዚአብሔር የሚወዳቸው መልካም ጠባዮች።

“እስኪ ለልጆች ጸሎትን ስለማስተማር ጥቀም ልግለጽ። ሕፃናት የሰማዩ አባታችን ስሙ ሲጠራ፣ እራሳቸውን መድፋት፣ እጃቸውን ማጣመር፣ እና አይናቸውን መጨፈን የሚማሩት በግል እና በቤተሰብ ፀሎት ጊዜ ነው። በቤት ውስጥ የተማርናቸው ፀባዮች በቤተክርስቲያን የምናሳያቸውን ፀባዮች ይወሰናሉ። አንድ ህፃን እቤት ውስጥ መፀለይ የተማረ እንደሆነ በአገልግሎት ጊዜ ፀጥ ብሎ እና ረግቶ መቀመጥ እንዳለበት ይገነዘባል።

በተጨማሪም፣ የቤተሰብ ምሽት የቤታችን ሕይወት አንዱ ክፍል በሚሆንበት ጊዜ፣ ስለ ሰማዩ አባታችን የምንማርበት እና እያንዳንዱ ሰው መልካም ፀባይን የሚያሳይበት ልዩ ቀን በቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በቤት ውስጥም እንዳለ ያውቃሉ።

“መዝሙር ለልጆች ልዩ ልዩ አስደሳች ነገር ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ በተደጋጋሚ የሚዘመሩ መዝሙሮች በቤት ውስጥ እንዲማሩ ካደረጉዋቸው ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በዚህ መንገድ፣ ልጆች በቀዱስ ቁርባን እና ሌሎች ስብሰባዎች በጉጉት በመዘመር ይሳተፋሉ።

አክብሮት በቤተክርስቲያን

“እርግጥ፣ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር የሰንበት ስብሰባን መሳተፍ አለባቸው።

“አባት እና እናት ለስብሰባ መዘጋጀት የቤተሰቡ አስደሳች ተሞክሮ እንዲሆን አብረው መሥራት አለባቸው። በመጨረሻዋ ደቂቃ ልጆችን ለመሰብሰብ፣ ለማልበስ እና ወደ ስብሰባ ቦታ ለመሄድ መቻኮል ለአክብሮት አፍራሽ ጎን አለው።

“ቤተሰቦች በዚህ ሁኔታ በሚሆኑበት ጊዜ ብዙውን ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ለመምጣት ይዘገያሉ፣ ብዙውን ጊዜ ቃላት መወራወር እና አንዱ የአንዱን ስሜት መጉዳት ይጀምራሉ፣ ብዙውን ጊዜ ልጆች በአገልግሎት ጊዜ ቁጡዎች እና ቀብጥብጦች ይሆናሉ። ለስብሰባ ቀደም ብለው የሚዘጋጁ፣ ስብሰባው ከመጀመሩ ቀደም ብለው ቤተክርስቲያን የሚደርሱ፣ የመግቢያ

7-ሀ በቤተክርስቲያን ውስጥ አክብሮት ያለን እና ልጆቻችን አክብሮት እንዲኖራቸው ማስተማር አለብን።

መዝሙር ለማዳመጥ አብረው የሚቀመጡ እና አለማዊ ሐሳቦችን የሚያስወግዱ ቤተሰቦች ምን ያህል አክብሮት ያላቸው ናቸው።

“ትንንሽ ልጆች ያላቸው ወላጆች ልጆቻቸው ስብሰባዎችን እንዲወዱ ለማድረግ እና ረብሻ እንዳይፈጥሩ ለማድረግ በጣም ይቸገራሉ። ተስፋ ያለመቁረጥ፣ ፅኑነት፣ እና በቤት ውስጥ መዘጋጀት ለውጤት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ወጣት ወላጆች በቤተክርስቲያን ውስጥ ልጆቻቸውን እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ግራ ከገባቸው፣ በዋርዱ ብዙ ልምድ ያላቸው ጥንዶችን ምክር መጠየቀ ይችላሉ።

“ብዙ ጊዜ፣ ከስብሰባ በፊት እና በኋላ፣ የቤተክርስቲያኑ አባላት በቤተክርስቲያኑ ሰላምታ ለመለዋወጥ ይሰበሰባሉ። አንዳንዶቻችን፣ ወንድማዊነት ያለን ሰዎች ስለሆንን፣ እና ሰንበት ቀን ለመኅበኛኘት አመቺ ጊዜ ስለሆነ፣ እንዲሁም ጓደኛ ለማግኘት እና ከአዲስ ሰው ጋር ለመተዋወቀ አመቺ ስለሆነ አክብሮት የሌለን ሰዎች ለመምሰል እንገደዳለን። ወላጆች ሌሎች በበረንዳው ወይም ከቤተክርስቲያኑ ውጪ ሌላ ቦታ ከስብሰባው በኋላ ሌሎችን በመኅብኘት ምሳሌ መሆን አለባቸው። ከስብሰባው በኋላ፣ ወንዶች አቤት ውስጥ ስለ አንዳንድ ሐሳቦች በመወያየት፣ ስለመዝሙሮች፣ ወይም ሌሎች የስብሰባው በጎ ገፅታ ከልጆቻቸው ጋር በመነጋገር የአገልግሎቱ መንፈስ ወደቤት እንዲመጣ ማድረግ ይችላሉ።

## አክብሮትን ማሻሻል

“ስለ አክብሮት ጥቀም ተነጋግረናል እንዲሁም ትርጉሙን መርምረናል። በተጨማሪም በቤት እና በቤተክርስቲያን ውስጥ አክብሮት የምናበረታታበት መንገድ ጠቁመናል። ነገር ግን በሰዎች ድርጊት እውነተኛ መሻሻል የሚመጣው፣ የአካባቢው መሪዎች እና ቤተሰቦች አንድ የተወሰነ የአክብሮት ችግር ለመፍታት ጥረታቸውን ሲያስተባብሩ ነው። በመላው ቤተክርስቲያን አክብሮት ለማሻሻል ጥረት እንዲደረግ እንመኛለን . . .

“እውነተኛ አክብሮት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፣ ግን የክፋት ኃይል ተፅዕኖ እየሰፋ በመጣበት ጊዜ በዓለም ላይ በፍጥነት የሚጠፋ ነገር ሆኗል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባላት እንደ አክብሮት ሞዴል ሆነው የሚያገለግሉ ቢሆኑ ኖሮ የምናገኘው ሐይል ሙሉ ለሙሉ ሊገባን አይችልም ነበር። ሌሎች ብዙ ተጨማሪ ቁጥር ያላቸው የሰዎችን ህይወት ልንነካ የምንችለውን ማሰብ ባልቻልን ነበር። በጣም ጠቃሚው ነገር ደግሞ፣ መሆን የሚገባንን ያህል አክብሮት ካለን፣ በቤተሰባችን የሚኖረውን መንፈሳዊ ተፅዕኖ መገመት አንችልም። ታላቀ አክብሮት በህይወታችን እንዲኖር እንስራ ዘንድ ፀሎቴ ነው።” (*We Should Be a Reverent People,* 1976, pp. 1–4).

ወላጆች ልጆቻቸው በስብሰባዎች እንዲደሰቱ እና የተሻለ አክብሮት እንዲኖራቸው እንዴት ማድረግ ይችላሉ? የክፍሉ ተማሪዎች መልስ ከሰጡ በኋላ፣ አንድ ሰው የሚከተሉትን የቀረቡ ሐሳቦችን እንዲያነብ ያድርጉ።

## ለወላጆች አክብሮት ስለማስተማር ሐሳቦች

“ወላጆች ልጆቻቸው በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች እንዲደሰቱ በሚከተሉት መንገዶች ማድረግ ይችላሉ . . .

“1.በሰንበት ትምህርት እና በቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎች ከልጆቻቸው ጋር መሳተፍ።
“2.ለስብሰባዎች አስደሳች እና ያልተቻኮለ ዝግጅት ማድረግ።
“3.ስብሰባው ከሚጀምርበት አምስት ደቂቃ ቀደም ብሎ መድረስ።
“4.እንደ አንድ ቤተሰብ አብሮ መቀመጥ።
“5.ከስብሰባው በኋላ ስለ ንግግሮች፣ መልዕክቶች፣ ስለመዝሙሮች፣ ወይም ሌሎች የስብሰባው ጉዳዮች መነጋገር።”
(Spencer W. Kimball, *We Should Be a Reverent People,* p. 4.)

ለትንንሽ ልጆች አክብሮት እንዴት ማስተማር እንችላለን? የክፍሉ ተማሪዎች ከመለሱ በኋላ፣ ከክፍሉ ተማሪ አንዱ የሚከተሉትን ሐሳቦች እንዲያነብ ያድርጉ፥

"ህፃናት ልጆች ያላቸው ወላጆች የሚከተሉትን መሞከር አለባቸው—

"1. ልጆችን ምን እየተከሰተ እንደሆነ ማስረዳት

"ለትንንሽ ልጆች የከለር መፅሐፍ ወይም ደብተር በመስጠት ሳይረብሹ እንዲቀመጡ ማድረግ ይቻላል፣ ግን በተቻለ መጠን ስለስብሰባው ማስረዳት ጠቃሚ ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ ስለዋርዱ ጉዳዮች ወይም ስለተናጋሪዋ መልዕክት ለማብራራት ለልጆች ማንሾካሾክ፣ ልጆች ምን እየተደረገ እንዳለ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ለምሳሌ አባትየው እንዲህ ሲል ለልጁ ሊያንሾካሹክለት ይችላል፣ አሁን የሚናገረው የፀጋ አባት ነው። ስለ ፈር ቀዳጆች ነው የሚናገረው።

"2. መዝሙሮች ላይ ማተኮር።

"መዝሙር ለልጆች አንዱ አስደሳች የስብሰባው ክፍል ሊሆንላቸው ይችላል። አንድ ልጅ የመዝሙር ፍላጎት እንዲያድርበት መዝሙር ለልጁ በማስተማር ማበረታታት አለብን። የዋርዱ የሙዚቃ መሪ ለወደፊት ስብሰባ የሚዘመሩ መዝሙሮች ሊስት ሊያቀርብላችሁ ይችላል።

**"**3. በቤት ውስጥ፣ በልጆች ክፍል፣ እና በሰንበት ትምህርት ቤት የሚሰጡትን የሥነ ምግባር ትምህርቶችን ማጠናከር።

"ልጆች በጸሎት ጊዜ እጃቸውን እንዲያጣምሩ እና ራሳቸውን እንዲደፉ እርዷቸው እንዲሁም በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ፀጥ ብለው እንዲቀመጡ አድርጉ። ልጆች በመተላለፊያዎች ላይ መጫወት ወይም በስብሰባ ጊዜ ከቤተክርስቲያኑ ወደ ውስጥ እና ወደ ውጭ መራመድ ነውር መሆኑን መረዳት አለባቸው።

"4. ምሳሌ ማሳየት።

"ስለስብሰባው ፍላጎት በማሳደር፣ አስፈላጊ ብቻ ሲሆን በመንሾካሾክ በመነጋገር፣ ልጆች እንዲሁ እንዲያደርጉ በማበረታታት ጥሩ ምሳሌ ማሳየት ይገባል።

"5. ልጆች ለስብሰባዎች ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጡ።

"ወደ መፀዳጃ ቤት እና የሚጠጣ ውሃ ፍለጋ ከስብሰባ በፊት መከናወን አለበት።" (Spencer W. Kimball, *We Should Be a Reverent People,* 1976, pp. 4–5.)

## ሙከራ

### ሕይወታችሁን የተሻለ አክብሮት ያለው ለማድረግ እና ሌሎችን በተለይም ቤተሰባችሁን የተሻለ አክብሮት ያላቸው ለማድረግ ማድረግ፣ የሚገባችሁን ነገር ዘርዝሩ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. የክፍሉ ተማሪዎች ቅዱስ ፅሑፎቻቸውን እንዲያመጡ ያስታውሷቸው።

2. ጥቁር ሰሌዳ እና ጠመኔ ያዘጋጁ።

የክፍሉ ተማሪዎች ዘሌዋውያን 19፥30 እንዲያነቡ ያድርጉ። ይህን ጥቅስ በሰሌዳው ላይ ይጻፉ፥ "ሰንበትን ጠብቁ፣ መቅደሲንም አክብሩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።"

ስዕል 7-ሀ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ አክብሮት ያለን እና ልጆቻችን አክብሮት እንዲኖራቸው ማስተማር አለብን። የሚለውን ስዕል አሳያቸው።

# ፍቅር፣ ደግነት፣ እና አገልግሎት

ትምህርት 8

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ ሌሎችን እንድናፈቅር እና እንድናገለግል ለመርዳት ነው፡

---

## እግዚአብሔር በፍፁም ፍቅር ይወደናል

ፍፁም ፍቅር፣ "ደግነት" ተብሎ የሚታወቀው የክርስቶስ ንፁህ ፍቅር ነው። (ሞሮናይ 7፥47 ተመልከቱ)። ይህን ፍቅር የቀመሱ ሰዎች በቃላት ለመግለፅ ይቸገራሉ። እህት ኤርመብሩክ፣ ከዩናይትድ ስቴትስ፣ ስለ ባለቤቷ የእግዚአብሔር ፍቅር ልምድ ተነግረናለች፥

"በርት ብሩክ . . . የመፅሐፍ ቅዱስ ምክር፣ 'ለምኑ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል።' (ማቴዎስ 7፥7) . . . እንደ ግሉ የፀሎት ግብዣ ተጠቀሞበታል። . . .እግዚአብሔር በእውነት እንዳለ በጉጉት ለማወቅ ፈልጎ ነበር። ካለም፣ እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

"የተለያዩ ቤተክርስቲያኖችን መሳተፍ እና ቅዱስ ጽሑፎችን ማንበብ ጀመረ። በማቴዎስ ያሉት ቃላቶች እራሱን እንዲጠይቅ ገፋፉት፣ . . .እናም እውነቱን ለማወቅ ካለው ጥልቅ ፍላጎት፣ የመጀመሪያ ፀሎትን እንዲህ አቀረበ "እግዚአብሔር በእውነት ካለህ፣ እንዳውቅህ አድርገኝ፣ እናም እንድፈፅም የምትፈልገውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ።' እንዲሁም እንደተንበረከከ እንዲህ አለ፣ ታላቅ ሰላም ሰውነቴን ወረረው፣ ልቤ ነደደ፣ በሰውነቴ ተሰምቶኝ የማይታወቅ ደስታ ወረረኝ። በታላቅ መንፈሳዊ ንጥር ውስጥ እንደሰመጥኩኝ ተሰማኝ።

"ለሶስት ቀናት ይህ ስሜት አብሮት ነበር፣ በዚህ ሁሉ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፥ እግሮቼ መሬትን ሲረግጡ ይሰማኝ ነበር። የእግዚአብሔር ንፁህ ፍቅር የከበበኝ ይመስለኛል፣ በጣም አስደናቂ ነበር። በዚህ ጊዜ ሁሉንም ነገር አፈቀርኩኝ ለሕፃናት ልጆች ግድ አልነበረኝም፣ ግን አሁን ለእነሱ ታላቅ ፍቅር ከሰውነቴ መፍሰስ ጀመረ። ዝናብን አማርር ነበር፣ አሁን በዝናብ ብርስ፣ እያንዳንዷን ደቂቃ አፈቅራለሁኝ፣ ይህ የሰማዩ መንግስት የሞላው የእግዚአብሔር ፍቅር ትንሽ ቀምሻ ከሆነ፣ ጠቦት እና አንበሳ አብረው መተኛታቸው፣ እንዲሁም ምንም ስቃይ እና የሚያስፈራ ነገር አለመኖሩ ምንም አያስገርምም።" ("A Small Taste of Love," *Ensign,* Aug. 1976, p. 36.)

ከዚያም በርት ብሩክ ወደ ቤተክርስቲያኑ ገባ።

በፍቅር የተሞላችሁበትን ጊዜ አስታውሱ።

እግዚአብሔር እንደሚያፈቅረን በግላችን ማወቃችን ለምን ይጠቀመናል?

አዳኛችን እንዴት ማፍቀር እንዳለብን ምሳሌ ሰጥቶናል። ፍትሐዊ ያልሆነ በደል ደርሶበታል፣ በበደሉት ላይ ግን አልተነሳም። ተጠልቶ ነበር፣ ነገር ግን እርሱ ጥላቻን በፍቅር መልሷል። በእንጨት መስቀል ተሰቅሎ እንዲሞት ተደርጓል፣ ግን ለሮማ ወታደሮች እንዲህ ሲል ለምኖላቸው ነበር፣ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁም እና ይቅር በላቸው።" (ሉቃስ

23፥34) (See *Gospel Princples,* chapter 11.) ተልዕኮውን በትክክል ያልተረዱለትን ሐዋሪያትን ታግሷቸው ነበር። ለልጆች ታላቅ ፍቅር ነበረው። ልብን የሚነካው የአዳኛችን ፍቅር በ 3ኛ ኔፊ 17 ተመዝግቧል።

ከክፍሉ የተመደበችውን አንድዋን እህት ከ3ኛ ኔፊ 17 የአዳኛችንን ፍቅር ያሳየናል ያለችውን አንድ ጥቅስ እንድታነብ ያድርጉ።

## ፍቅር እንዲኖረን ታዘናል

አዳኛችን ከመሰቀሉ ጥቂት ሰዓታት ቀደም ብሎ፣ ደቀመዛሙርቱን እንዲህ ሲል አስተምሯቸው ነበር። "እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እኔ እንደ ወደድኳችሁ እናንተም ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። (ዮሐንስ 13፥34.)

ተከታዮቹን እንዳፈቀረ ሁሉ እርስ በርሳችን እንድንፋቀር አዞናል። እንዲህ ሲል አስተምሮናል። "ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፣ ለሚያሳድዷችሁም ፀልዩ፥

"በሰማይ ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ" (ማቴዎስ 5፥44-45)

ቄስ ማሪዮን ዲ. ሐንክስ አንዲት ሴት የክርስቶስን የመሰለ ፍቅር እንድታዳብር እንድትማር መደረጓን አንድ ታሪክ ይነግረናል፥

"በልጅነትዋ ስለገጠማት ሁኔታ ስለምትናገር አካለ ጎዶሎ ሆና የተወለደች አንዲት ሴት ሁሌም አስባለሁኝ። ጓደኞቿዋ እንድታዝን እና እንድታለቅስ የሚያደርጋት ስድብ ይሰድብዋት ነበር። እቤትዋ ስትገባ አባትዋ ጭኑ ላይ አስቀምጦ በጠንካራ እጆቹ አቀፏት ከእርሷ ጋር በማንባት ይህ ጉዳይ ለወደፊቱ እርሷን ሕይወቷን ፍሬ ያለው እና ደስተኛ እንደሚያደርግላት ይገልፅላት ነበር፥ እንዲህ ይላት ነበር፥ 'የእኔ ፍቅር በጀርባሽ ላይ እብጠት አለብሽ፣ እንዲሁም ሎሌች ከባድ ነገሮች አለብሽ። ግን ይህ የአንቺ ስህተት አይደለም። ይህ የወላጆችሽ ወይም የሰማይ አባታችን ስህተት አይደለም። . . .ወንዶች እና ሴቶች ልጆች የሚሉት እውነት ነው፣ ግን ተገቢ እና ርህራሔን ያዘለ አይደለም። በሕይወትሽ ለሌሎች ሩህሩህ የምትሆኚላቸው ከሆነ፣ ደስተኛ እና ሕይወትሽ የተሟላ እና ጠቃሚ ይሆናል።' " ("More Joy and Rejoicing," *Ensign,* Nov. 1976, p. 32.)

1ኛ ቆሮንቶስ 13፥2-7 አንድ ሰው እንዲያነብ ያድርጉ። የክፍሉ ተማሪዎች ይህን ጥቅስ እንዲያብራሩ ይጠይቁ። አንዲት ደግ የሆነች እህት የሌላ ዘር የሆኑ ሰዎች ላይ ፍርደ ገምድል ትሆናለችን? ህሙማንን፣ ድሆችን፣ ወይም የተራቡትን ቸል ማለት ትችላለችን? በሌሎች ውጤት መቀናት ትችላለችን? ሌሎችን ማማት ወይም መውቀስ ትችላለችን?

## እንደ ክርስቶስ ማገልገል ፍቅርን ይገነባል

ፕሬዚደንት ሐሮልድ ቢ. ሊ አንድ ምሽት እንዲህ የሚል "ራዕይ" ተመለከተ እንዲህ ተብሎም ተነገረው፣ "እግዚአብሔርን ለማፍቀር ከፈለግክ፣ ሰዎችን ማፍቀር እና መውደድ መማር አለብህ። ለእግዚአብሔር ያለብህን ፍቅር በዚህ መንገድ ማሳየት ትችላለህ።" (*Stand Ye in Holy Places,* p. 189.)

በትልቁም በትንሹም ስናገለግል፣ በጥልቀት ማፍቀርን እንማራለን። እህት ኮራ ሒል ኦርኖልድ፣ ከዩናይትድ ስቴትስ ምንም እንኳን ከማትወዳት ሴት አጠገብ ብትኖርም በአገልግሎት ፍቅርን መማር ችላለች፥

"በምትናገረው ነገሮች ሁሉ ስህተት አገኛለሁ።. . . . ከሌሎች ሰዎች እርስዋም ስለእኔ እንዲሁ እንደሚሰማት ሰምቻለሁ። ብዙውን ጊዜ ለሁሉም ሰው ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነች ለማሳየት እራሷን የምታስገድድ ትመስላለች። አንድ ነገር ሲሳካላት ማየት በጣም እወዳለሁ።

"ለእኔ የወዳጅነት ስሜት አልነበራትም፣ እንዲሁም እኔ ቀዝቀዝ ባለ ሰላምታ ወይም ረጋ ባለ አንደበት "ሄለው" ብያት አልፍ ነበር። . . . በዚህን ጊዜ ደስተኛ አልነበርኩም ምክንያቱም ሰውን መጥላት ደስተኛ ስለማያደርግ ነበር።

"አንድ ቀን መታመሟን ሰማሁ። እና ምን? የኔ ጭንቀ አልነበረም።

"ነገር ግን [የኔው ጭንቀት] ነበር፣ ልረሳው አልቻልኩም። ህሊና ስለነበረኝ በመጨረሻ ወደ ማዕድቤት ሄድኩኝ እና ከፍራፍሬ ሱጎ የተሰራ የኩባያ ኬኮች ጋገርኩኝ. . . .

"እናም ወደ እርስዋ ወሰድኳቸው!

"ፊትዋ በግርምታ እና በደስታ በራ፣ የቁጣ ፍርደ ገምድልነቴን በመጠራረግ ልቤ በደስታ አበራ። ወደ ቤቴ ስመለስ በፈገግታ ነበር እንዲሁም ቀኑም የበራ እና ቀንጆ ነበር።

"አሁን ከቀርብ ጓደኞቼ አንዷ ነች። . . .

"አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ነበር፣ "ጥላቻ ማለት ፍቀር ሲጠፋ ነው። ምናልባት የምናፈቅራቸውን ሰዎች ልንጠላ እንችላለን" ("Shall I Deem Her My Enemy?" *Relief Society Magazine,* Aug. 1970, p. 595.)።

እህቶች አንድን ሰው ማፍቀር የተማሩበትን ልምድ እንዲናገሩ ያድርጉ። በአገልግሎት ከቤተሰቦቻችን ጋርም ቢሆን የጠበቀ ዝምድና እንዴት መገንባት እንችላለን?

### እርስ በርሳችን ለመረዳዳት ቃል ገብተናል

ስንጠመቀ ከጌታ ጋር "የሌሎችን ሸክም ለመሸከም . . . ከሚያለቀሱ ጋር ለማልቀስ፣ . . . መፅናናት ለሚፈልጉ መፅናናትን ለመስጠት።" (ሞዛያ 18፥8-9) ቃል ገብተናል። የተቸገሩትን የመፈለግ ሐላፊነት አለብን። ከዚያም ያለምንም ጉትጎታ እና ትዕዛዝ የመርዳት ሐላፊነት አለብን። (ት እና ቃ 58፥26-29 ተመልከቱ።)

ክርስቶስ ተከታዮቹን እንዳገለገለ፣ እኛም የተቸገሩትን ለማገልገል ቃል ገብተናል። ልክ እንደ ክርስቶስ እንድናገለግል አንጠየቅም ይሆናል። መልሶ ሊከፍለን በማይችል እንግዳ ሰው፣ አገልግሎታችንን ይፈልግ ይሆናል። በእኛ በኩል የሚያስደስት እና ከፍተኛ ጥረት የሚያስፈልገው ሊሆን ይችላል። ለመስጠት አስቸጋሪ በሚሆንብን ጊዜ ልንጠየቅ እንችላለን። ምንም ምስጋና ወይም እውቀና አናገኝበትም ይሆናል። ግን እናገለግላለን፣ ምክንያቱም የሰማይ አባታችን ልጆች ስለምናፈቅር ከንፁህ ልባዊ ምኞት የተነሳ ልንረዳቸው እንፈልጋለን።

ኤማ ሰመርቪል መኮንኪ የቄስ ብሩስ፣ አር፣ መኮንኪ ሴት አያት፣ ከሞአብ ዩታ ባልዋ የሞተባት ነበረች። የቄስ መኮንኪ አባት በማስታወሻው የእናቱን ልምድ እንደሚከተለው ጽፎ ነበር፥

"እናቴ የሞአብ የሴቶች መረዳጃ ማኅበር ፕሬዚዳንት ነበረች። ጂ.______ ቢ.______ (ቤተክርስቲያኗን የሚቃወም አባል) የሞርሞንን ልጃገረድ አገባ። ብዙ ልጆች ነበራቸው፣ አሁን አዲስ ልጅ ወልደዋል። በጣም ድሐ ነበሩ እናቴ ልጆችን ለመንከባከብ እና ምግብ ለማቀረብ

ቀን በቀን ትጥር ነበር። እናቴ ህመምተኛ ነበረች፤ ከ ጄ ቢ ይ ቤት ሰርታ ስትመጣ አንድ ቀን ወደቤት በችግር ነበር የመጣችው።

“አንድ ቀን ወደ ቤት በጣም ደክማ መጣች። ወንበርዋ ላይ ተኛች። በህልሟ ክርስቶስን የመሰለ ህፃን ገላውን ስታጥብ ታየት። እንዲህ ስትል አሰበች እውነተኛውን ክርስቶስ ማገልገል እንዴት ያለ ክብር ነው። ህፃኑን ጭንዋ ላይ ስታስቀምጠው በስሜት ሰመጠች። እንዲህ ስትል አሰበች፤ ክርስቶስን በሕፃንነቱ ማን ይሆን ያቀፈው? በቃል ሊነገር የማይችል ደስታ መላ ሰውነትዋ በጌታ ክብር አንፀባረቀ፤ በአጽሟ ውስጥ ያለው መቅኒ የቀለጠ ይመስላል። ደስታዋ እስክትነቃ ድረስ ታላቅ ነበር። ስትነቃ፤ እነዚህ ቃላቶች ተነግሯት ነበር፡ “እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሰው ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁ ለእኔ አደረጋችሁት።” (Bruce R. McConkie, “Charity Which Never Faileth,” *Relief Society Magazine*, Mar. 1970, p. 169.)

ማቴዎስ 25፡34–40 የንብቡ።

እህቶች ለሌሎች አገልጋይ የሚሆኑበትን መንገድ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው (*የወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 28 “አገልግሎት” የሚለውን ተመልከቱ።)

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ መኬይ እንዲህ ብለዋል፡ “ከሌላው ጊዜ በበለጠ ለጎረቤቶቻችን ስምምነት፣ ፍቅር፣ የህብረተሰብ ኃላፊነት፣ ታማኝነት ከቤታችን እንዲመነጭ የማደረግ ኃላፊነት አለብን . . .

“እግዚአብሔር የቤተክርስቲያኑ አባላት . . . ፍቅር፤.. ደግነት . . . እና አገልግሎት እንዲያመነጩ ይረዳቸዋል።” (“Radiation of the Individual,” *Instructor*, Oct. 1964, p. 374.)

## ሙከራ

ማፍቀር የሚተችሎትን አንድ ሰው ምረጡ እና ጥሩ የሆነ ግንኙነት ለመገንባት ሞክሩ። ይህን ሰው እና ሌሎችን እንዴት በደንብ ማገልገል እንደምትችሉ ሞክሩ።

---

**የመምህር ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፡

1. የወንጌል መሰረቶች ምዕራፍ 30 “ደግነት” እና ምዕራፍ 28 አገልግሎት የሚሉትን ያጥኑ።
2. የክፍሉ ተማሪዎች ከ 3ኛ ኔፊ 17 የኢየሱስ ፍቅር የሚያሳዩትን ሁለት ወይም ሶስት ጥቀሶች እንዲመርጡ ይመድቧቸው።
3. ለዚህ ትምህርት የሚሆን ታሪክ እና ቅዱስ ፅሑፍ እንዲያቀርቡ የክፍሉ ተማሪዎችን ይመድቡ።

# ንፅህና እና ትህትና

ትምህርት 9

የዚህ ትምህርት ዓላማ የንፅህናን ህግ እንድናከብር እና ልጆቻችን እንዲሁ እንዲያደርጉ ማስተማር እንድንችል ለመርዳት ነው።

## መግቢያ

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል በሜክሲኮ እና በመካከለኛው አሜሪካ ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን እንዲህ ሲሉ ንግግር አድርገው ነበር፥ "እናንተ የእግዚአብሔር ሴቶች ልጆች ናችሁ። . . . በሰማይ እናታችን መልክ ተሰርታችኋል። . . . አካላችሁ ለእናንተ የተቀደሰ እና የተከበረ ነው።" (In *Official Report of the First Mexico and Central America Area General Conference of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints,* Aug. 1972, p. 108.) አካላችን ነፍሳችን የሚቀመጥበት ቤተመቅደስ ነው። አካላችን ንፁህ እና ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ብቁ ሆኖ እንዲቀይ ማድረግ አለብን። "ንፁህ ያልሆነ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ሊቀመጥ አይችልም።" (1ኛ ኔፊ 10፥21፤ በተጨማሪም 1ኛ ቆሮንቶስ 3፥16–17 ይመልከቱ።)

## የንጽህና ህግ

በሰውነታችን ውስጥ፤ እግዚአብሔር የተቀደሰ ኃይል አስቀምጧል። ይህ ኃይል መሬት ላይ ሕይወት ተቀጥል ዘንድ ሌላ አካል መፍጠር የሚያስችል ነው። የዚህን ኃይል ንፅህና መጠበቅ እንችል ዘንድ እና በጥበብ መጠቀም እንድንችል፤ እግዚአብሔር የንጽህና ህግ ሰጥቶናል።

*የወንጌል መሰረቶች ምዕራፍ 39 "የንፅህና ህግ" ከሚለው ንዑስ ምዕራፍ "የንፅህና ህግ ምንድነው?" የሚለውን አህቶች እንዲያነቡ ይመድቡ።*

*የንጽህና ህግ ምንድነው?*

ንፁህ መሆን ማለት ስህተት እንድንሰራ የሚያስገድዱን ንፁህ ያልሆኑ ሐሳቦችን እና ድርጊቶችን ማስወገድ ማለት ነው። (ማቴዎስ 5፥27–28 ተመልከቱ።) የዚህ ስነ ምግባር የጎደለው ዓለም መመዘኛዎች እኛን እንዲጫኑን መፍቀድ የለብንም።

## የንጽህና ህግ ጥቅም

የንጽህናን ህግ ማክበር በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሆነ ነው። ቅዱስ ፅሑፎች የንፅህና ህግ "በጣም የተወደደ እና ከሁሉም የላቀ ነገር" (ሞሮናይ 9፥9) እንዲሆነ ይነግሩናል። ጌታ እንዲህ ብሏል፥ "እኔ ጌታ እግዚአብሔር፤ በሴቶች ንፅህና እደሰታለሁ። እናም ሴሰኝነት በእኔ ፊት የተጠላ ነው።" (ያዕቆብ 2፥28)

የንፅህናን ህግ ማክበር ከጌታ ታላቅ በረከት ያቀርብልናል። እራሳችንን እንድናከብር እና ከህሊና ወቀሳ ነፃ እንድንሆን ይረዳናል። በተጨማሪም፤ ከአባለዘር በሽታ እና ከተዛማጅ በሽታዎች እንድንወገድ ይረዳናል። በተጨማሪም፤ የንፅህናን ህግ ማክበር በሌሎች ተአማኒነትን ለማግኘት እና ከመንፈስ ቅዱስ መመሪያ ለማግኘት ብቁ ለመሆን ይረዳናል።

በጣም ጠቃሚው ደግሞ፣ ቤተመቀደስ እንድንገነባ እና ለጊዜው እና ለዘለዓለም ማግባት እንድንችል ንፁህ መሆን አለብን። ንፅህና በዚህ ምድር በደስተኛ ቤተሰብ እንድንደሰት ይረዳናል። የቤተሰባችን ሕይወት ለዘለዓለም እንዲቀጥል ብቁ እንድንሆን ይረዳናል።

ልጅዋን ወደ ትምህርት ክፍሉ ያመጣቸውን እህት እሷ እና ባለቤትዋ የሚሰማቸውን ደስታ እንድትገልፅ ይጠይቋት።

የንጽህናን ህግ መጣስ ከባድ ኃጢያት ነው። ሐዘን እንዲከተለን ማድረግ ይችላል። ለራሳችን ያለንን ክብር ሊያወድመው ይችላል። የጥፋተኝነት ሸክም ሊሆንብን ይችላል። ንፁህ ያለመሆን የቤተሰብ አባላት አለመተማመን እና በመጨረሻ የቤተሰብ መበጣበጥ ሊፈጥር ይችላል። ንፁህ አለመሆን አንድ ግለሰብ ለመንፈስ ቅዱስ መመሪያ ብቁ እንዳይሆን ያደርገዋል። ከቤተሰብ ውጪ የሆኑ ልጆች ወደዚህ ዓለም እንዲመጡ ሊያደርግ ይችላል። የንፅህናን ህግ የሚጥሱ የቤተክርስቲያኑ አባላት ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቅዱስ ቃልኪዳን ይጥሳሉ። የመፍጠርን ኃይል ቀደም ብሎ ወይም ያለ አግባብ መጠቀም የዘለዓለማዊ ዕድገት እንድናጣ ሊያደርገን ይችላል።

ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ፣ በዚህ የሚሳተፉትን ሰዎች ሕይወት የሚያሳድፍ ከባድ ኃጢያት ነው። እንደዚህ ያለ እድፍ በተሟላ ንስኃ ብቻ ነው ሊወገድ የሚችለው። (ትምህርት 2 “ንስኃ” የሚለውን ተመልከቱ) አንዳንድ ጊዜ ስለ ንፁህ መሆን ጌታ ምን እንደሚሰማው ሳናውቅ ስህተት ልንሰራ እንችል ይሆናል። ይህ በሆነበት ጊዜ የቅርንጫፋችንን ፕሬዚዳንት፣ ጳጳስ፣ ወይም የሚሽን ፕሬዚዳንትን ማናገር በጣም ጠቃሚ ነው። ሊመክረን እና እንዴት ንስኃ መግባት እንደምንችል ሊረዳን ይችላል። ጌታ ኃጢያታችንን ንስኃ በምንገባበት ጊዜ ይቀር ለማለት ይጓጓል። እንዲህ ሲል ይነግረናል፥ “አስታውሱ፣ ንስኃ የሚገባ፣ኃጢያቱ ይቀር ይባልለታል፣ እና እኔ ጌታ ከእንግዲህ አላስታውሳቸውም።” (ት እና ቃ 58፥42)

## ለልጆች ንጽህናን ማስተማር

በሰሌዳው ላይ ለልጆቻችን የንፅህና ህግ ማክበር ማስተማር የሚቻልባቸውን አምስቱን ኃሳቦች ይጻፉ፣ ወይም ፖስተር ላይ ያሳዩአቸው።

1. የሰውነታቸውን አሰራር ተፈጥሮ እና ቅዱስነት እንዲያውቁት መርዳት።
2. ፍቅርን ስጡዋቸው።
3. ከጓደኛ ጋር የመውጣት ትክክለኛውን መንገድ ማበረታታት።
4. ትህትና የተሞላበትን አለባበስ እንዲኖራቸው አበረታቷቸው።
5. ትክክለኛ የሆነ የወላጅ ምሳሌ አሳዩዋቸው።

### የሰውነታቸውን አሰራር ቅዱስነት እንዲያውቁ መርዳት

ልጆች በተፈጥሮ ስለ ሰውነታቸው ለማወቅ ጉጉ ናቸው። ወላጆች በትክክለኛው ጊዜ ሰውነታቸውን የሚንከባከቡበት ትክክለኛ መንገድ ሊገልፁላቸው ይችላሉ። በተጨማሪ ሰውነታቸው የግል ሚስጥራቸው እንደሆነ እና እነርሱም ሆነ ሌላ ሰው ያለ አግባብ መንካት የሌለበት የተቀደሰ እንደሆነ ሊያብራሩላቸው ይችላሉ።

አንድን ልጅ ሰውነቱን እንዲያከብር ለማስተማር ተገቢ በሆነ ጊዜ ምሳሌ ስጡ።

ልጆች በጣም ልጅ ሳሉ፣ የራሳቸው የሆነ አስተሳሰብ ማዳበር ይጀምራሉ። የወላጆቻቸውን ባሕሪ ማንፀባረቅ ይጀምራሉ። ወላጆች ትክክለኛ ባልሆነ ነገር ላይ የሚስቁ ከሆነ፣ አጠያያቂ ፊልሞች የሚመለከቱ ከሆነ፣ ትክክለኛ ያልሆኑ ነገሮችን የሚገፋፉ መጽሐፍት እና መፅሔት

እቤት ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ከሆነ፣ ልጆች የተሳሳተን ባሕሪ ይማራሉ። ወላጆች ስለ ሰውነታቸው አክብሮት በተሞላበት ግን በግልፅ እና ያለምንም ሀፍረት መናገር አለባቸው። እርስ በርሳቸው እውነተኛ ፍቅር በማሳየት፣ ወላጆች መራባት የተቀደሰ እንደሆነ ሊያስተምሩ ይችላሉ። በተጨማሪ የፆታ ሚና ስልጠና በጣም አስፈላጊ ነው። ልጆች ሴት ወይም ወንድ መሆናቸው ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ይረዳል። ወላጆች እንደ ወንድ እና ሴት ያላቸው ሚና ጥሩ ስሜት የሚሰማቸው ከሆነ፣ ይህን ስሜት ወደ ልጆቻቸው ሊያሳልፉ ይችላሉ።

እንደ ወላጅነታችሁ ባሕሪያችሁ ብቻ ከቃላት በበለጠ እንዴት ሊያስተምሩ ይችላሉ?

ልጆች ህፃን ልጅ እንዴት እንደሚረገዝ እና እንደሚወለድ በግልፅ ሊገባቸው ይገባል። በተጨማሪም ልጆች ጌታ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በባል እና ሚስት የተወሰነ ነገር እንዲሆን እንዳዘዘ እንዲያውቁ መደረግ አለበት። ወንዶች እና ሴቶች ይህን የተቀደሰ ትዕዛዝ መጣስ የለባቸውም፣ እራሳቸውን እስከ ጋብቻ ድረስ ማቀብ መማር አለባቸው።

ስዕል 9-ሀ፣ የአንዲት እናት ፍቅር ለቤተሰብዋ በረከት ነው የሚለውን ያሳያል።

## ፍቅር ስጡዋቸው

ልጆች ህፃናት ሳሉ፣ እቤት ውስጥ ፍቅርን የመግለጫ ትክክለኛ መንገድ ልናሳያቸው እንችላለን። ለልጆች የፍቅር ፍላጎት ማሟላት ተገቢ ነው፣ ምክንያቱም ከጊዜ በኋላ ከውጪ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እንዳይፈልጉት ስለሚያደርጋቸው ነው። ወላጆች ግልፅ እና አፍቃሪ ከሆኑ፣ ልጆቻቸው በራሳቸው እንዲተማመኑ ያደርጓቸዋል። ከዚያም በሕይወታቸው ውስጥ ጥያቄ ወይም፣ ችግር ካላቸው፣ ወላጆቻቸውን ለማማከር ነፃ ሆነው ይቀርባሉ።

## ከጓደኛ ጋር የመውጣትን ትክክለኛ መንገድ ማበረታታት

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እንዲህ ብለው ነበር፣ "ማንኛውም ከተቃራኒ ፆታ ጋር የመውጣት ድርጊት ከ16 እና ከዚያ በላይ እድሜያቸው እስኪደርስ መራዘም አለበት።" ("The Marriage Decision," *Ensign,* Feb. 1975, p. 4.) ወጣቶች ወንጌላዊነታቸውን ከጨረሱ በኋላ አንዳንዴ ብቻ ጓደኝነት እንዲመሰርቱ ሊበረታቱ ሊደረግ ይገባል።

ፕሬዚዳንት ኪምቦል በክልል ጉባኤ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ለሴቶች እንዲህ ሲሉ አሳስበዋቸው ነበር፣ "አንዳንድ ወንዶች የጋብቻ ቀርበትን ህጋዊ እና ትክክል እስኪያደርጉ ድረስ መጠበቅ አይፈልጉም። . . . ሰውነታችሁን መጠቀም የሚፈልግ፣ በእጁ የሚዳብሳችሁ፣ ወይም ሌላ ነገር የሚያደርግ ወንድ ጓደኛ ካላችሁ፣ አይሆንም! በሏቸው ግልፅ በሆነ መንገድ። እናም ችክ ካለ፣ እራሳችሁን መከላከል አለባችሁ። . . .

"ውድ እህቶቼ፣ ታስታውሳላችሁን? ጓደኞቻችሁን ፀባይ እንዲገዙ ያደረጋችሁበትን ጊዜ አታስታውሱም? ፃድቅ ያልሆነ ድርጊት እንዲያደርጉባችሁ አትፍቀዱ" (In *Official Report of the First Mexico and Central America Area General Conference of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints,* Aug. 1972, pp. 108–9.)

ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ከጓደኛ ጋር የመውጣት ትክክለኛ መንገዶች ምንድን ናቸው?

9-ሀ የእናት ፍቅር ለቤተሰብዋ በረከት ነው።



9-U

ትህትና የተሞላበት አለባበስ እንዲኖራቸው አበረታቷቸው

ከአዳም እና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ፣ ጌታ ልጆቹን ገላቸውን እንዲሸፍኑ ጠይቋቸዋል። ሔዋን በገነት ውስጥ በሰይጣን እስክትታለል ድረስ፣ እሷ እና አዳም ራቁታቸውን መሆናቸውን አያውቁም ነበር። የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላ፣ እርቃናቸውን እንደሆኑ ተገነዘቡ። የተቀደሰ ሰውነታቸውን በበለስ ቅጠል ለመሸፈን ጣሩ። ቢሆንም፣ ጌታ ትህትና በተሞላበት አለባበስ ትልቅ አመለካከት ስላለው፣ . . .ምንም እንኳን በዚያን ጊዜ በዚህ ዓለም ውስጥ ብቻቸውን ቢሆኑም እራሳቸውን እንዲሸፍኑ የቆዳ ኮት ሰጣቸው። (ሞሮናይ 4፥13፣ 27 ይመልከቱ)

የጌታ የአለባበስ ህግ ከዓለም ጋር አንድ አይደለም። ከነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ ጀምሮ እስከ አሁን ያሉት ነቢያቶቻችን የራሳችን የሆነ ስታይል እና ፋሽን እንድንፈጥር ጠይቀውናል (see Spencer W. Kimball, "A Style of Our Own," BYU Devotional Assembly, 13 Feb. 1951)። ፕሬዚዳንት ብሪግሃም ያንግ ለእኛ ሞዴል የሚሆን ፋሽን ገልፀ ነበር። እንዲህ ሲል "እንበል እና አንዲት ሴት መልአክ ወደ ቤታችሁ መጥታ የማየት ዕድል ቢኖራችሁ እንዴት የምትለብስ ይመስላችኋል? . . . ንፁህና ቀንጆ ትሆናለች፣ ፊትዋ በክብር የተሞላ ይሆናል፣ የሚያንፀባርቅ፣ የሚያበራ፣ እና ፍፁም ቀንጆ ትሆናለች፣ እና ማንኛውም እንቅስቃሴዋ አቋሟ የማንኛውንም ሰው ልብ ያስደስታል። ስለ እርሷ ምንም እንከን የለም። እህቶቼ ማናችሁም ብትሆኑ ይህ አርባናቢስ እና ጅላጅል ፋሽን በሰማይ ይከተላሉ ብላችሁ እንደማታምኑ እገምታለሁኝ። እናም ደህና፣ እናንተ ጥሩ እና ሰማያዊ ምሳሌን ተከተሉ፣ እናም የልብሳችሁ ውበት የእጃችሁ የስራ ውጤት ይሁን።" (*Journal of Discourses,* 16:21.)

አለባበሳችን ትህትና የተሞላበት እንዲሆን ለማወቅ እራሳችንን እንዲህ ብለን በመጠየቅ መለካት እንችላለን፣ "ነብዩ ቤቴ የሚገባ ቢሆን ስለ አለባቤሴ ምን ይሰማኛል? አለባበሴ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ልጃገረድ ወይም ሴት ልትለብሰው የሚገባ ጥሩ ምሳሌ ነውን?" እቤታችን ውስጥም ቢሆን ትህትና የመላበት አለባበስ ሊኖረን ይገባል። የቤተሰባችን አባላት በሌሎች ተቃራኒ ፆታ ባላቸው የቤተሰብ አባላት ፊት ልብሳቸውን እንዳያወልቁ መጠንቀቅ አለባቸው። ሕፃናት ልጆችም ቢሆኑ ትህትና የሞላበት አለባበስ እቤት ውስጥ መማር አለባቸው።

አለባበሳችን በሌሎች ላይ ለሚኖረው ተፅዕኖ ኃላፊነት አለብን። ማንኛውም መጥፎ ኃሳብ ወይም መጥፎ ምሳሌ በሌሎች የሚፈጥር አለባበስ ትህትና ያለው አይደለም። በተለይ ወጣት ልጃገረዶች በወጣት ወንዶች ላይ መጥፎ አስተሳሰብ የሚያነሳሳ አለባበስ መልበስ የለባቸውም።

ዛሬ ልናስወግዳቸው የሚገባ የተለመዱ ሞዶች (ስልቶች) አሉ?

መልካም አለባበስ ንፅህናችንን እንድንጠብቅ ይረዳናል። ለአይናችን እና ለጌታ አስደሳች የሆነ አለባበስ መምረጥ ያስፈልገናል።

ትክክለኛ የሆነ የወላጅ ምሳሌ አሳዩዋቸው

የንጽህና ህግን ስንጠብቅ እና ትህትና የተሞላበትን አለባበስ ስንለብስ ትክክለኛ የሆነ የወላጅ ምሳሌ ማሳየት አለብን።

ወላጆች ልጆቻቸውን የንፅህና ህግ እንዲያከብሩ እና መልካም አለባበስ እንዲለብሱ ለማስተማር ምን ማድረግ ይችላሉ።

አምስቱን ንጹህ የመሆን ኃሳቦች በሰሌዳው ላይ ወይም ፖስተር ላይ ከልሷቸው።

እራሳችንን እና ልጆቻችንን በሌላ ምን መንገድ የንፅህናን ህግ ከመጣስ መከላከል እንችላለን?

## ሙከራ

ልብሳችሁ ትህትናን የሚያሳዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሳጥናችሁን ፈትሹ። በቤት ውስጥ መስታወት ፊትለፊት ወንበር ላይ አስቀምጡ። ከዚያም እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ወንበሩ ላይ ተቀምጦ አለባበሳችሁን እና የሰውነት አቋማችሁን የተሻለ ትህትና ገላጭ የሚሆንበትን መንገድ ወስኑ። የሚቻል ከሆነ፣ ከባለቤታችሁ ጋር ለልጆቻችሁ ስለ ንፅህና ህግ እና ትህትናን ስለማስተማር ጠቃሚነት ላይ ተወያዩ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

1. 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13 (እግዚአብሔር ለፈተና መውጫ መንገድ አዘጋጅቷል)
ያዕቆብ 2፥22–35፤ 3፥1–3 (ንፅህና ለጌታ ደስታ ነው)
አልማ 39፥1-9 (ኮርያንተን ኃጢያት ለተሞላው ስራው ተወቀሰ)

---

**የመምህር ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፣

1. *የወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ፣ 39 “የንፅህና ህግ” የሚለውን ያጥኑ
2. *የወንጌል መሰረቶች* የሚለውን መጽሐፍ ይዘው ይምጡ።
3. አንድዋን እህት ልጅዋን ወደ ክፍል ይዛ እንድትመጣ ይጠይቁ።
4. ከወንጌል መሰረቶች ምዕራፍ 39 ንዑስ ክፍል “የንፅህና ህግ ምንድነው?” የሚለውን እንድታነብ አንድ እህት ይመድቡ።
5. ጥቁር ሰሌዳ እና ጠመኔ ያዘጋጁ።
6. በጥቁር ሰሌዳው ላይ ልጆችን የንፅህና ህግ ለማስተማር የቀረቡትን አምስቱን ሃሳቦች ይፃፉ፣ ወይም ፖስተር ያዘጋጁ።

# ዘለዓለማዊ ጋብቻ

ትምህርት 10

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ የዘለዓለማዊ ጋብቻ ቃል ኪዳን ለመቀበል እንድናቅድ እና እንድንዘጋጅ ለመርዳት ነው።

---

## በቤተመቅደስ ማግባት ያለብን ለምንድን ነው

ስዕል 10-ሀ፣ የባል እና ሚስት ፍቅር በዘለዓለማዊ ቤተሰብ ውስጥ ዘለዓለማዊ ነው የሚለውን ስዕል አሳያቸው።

ሕይወት ሞት ላይ አያበቃም፣ እንዲሁም ጋብቻ ሞት ላይ እንዲያበቃ አልታሰበም። ግን ሰዎች በማዘጋጃ ቤት ወይም በቤተክርስቲያን ከቤተመቅደስ ውጭ የሚያደርጉት ጋብቻ፣ ለዚህ ሕይወት ብቻ ነው። ሴሌስቲሊያዊ ጋብቻ ከሞት በኋላ የሚቀጥል ብቸኛው ጋብቻ ነው። ከፍ ከፍ ማለት የሚመጣው የሴሌስቲሊያዊን ጋብቻ ቃል ኪዳን ለሚያደርጉት ነው።

ት እና ቃ 131፡1–4 ያንብቡ።

ከሞት ከተነሳን በኋላ፣ ከሶስቱ የክብር መንግስቶች ወደ አንዱ እንሄዳለን። እዚያ ለዘለዓለም እንቀመጣለን። ከአንዱ ወደ ሌላው መንግስት መሻሻል አንችልም። (See Spencer W. Kimball, *The Miracle of Forgiveness,* pp. 243–44.) በዚህ ምክንያት፣ በሕወይወታችን ውስጥ ቀደም ብለን የጽድቅ ውሳኔ ማድረግ አለብን። አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸውን ከእግዚአብሔር ህግ ጋር አያስማሙም፣ እንዲሁም ለዘለዓለም አይጣመሩም። ተነጣጥለው እና ብቻቸውን ሆነው ለዘለዓለም ይቀራሉ።

ት እና ቃ 132፡15–17 ያንብቡ።

ዮሴፍ ስሚዝ እንዲህ ሲል አስተምሯል፥ "አንድ ወንድ እና ሚስቱ በዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ውስጥ ካልገቡ እና ለዘለዓለም ካልተጋቡ በስተቀር . . .ከትንሳኤ በኋላ ምንም ልጆች አይኖሯቸውም።" (*History of the Church,* 5:391.)

"ዘለዓለማዊ ሕይወት፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጻድቅ አባላት ብቻ ነው፣ ወንጌልን ለተቀበሉ ብቻ፣ መንፈሳዊ ስጦታቸውን ከእግዚአብሔር የተቀደሰ ቤተመቅደስ ያገኙ እና ለዘለዓለም የተጣመሩ እና *በሕይወታቸው ሙሉ የጽድቅ ሕይወት መኖር የሚቀጥሉ* ብቻ ነው።" (Spencer W. Kimball, *The Miracle of Forgiveness,* p. 246; italics added.)

ቤተሰቦቻችን በቤተመቅደስ እንዲጣመሩ ለምን መፈለግ ተገባን? በቤተመቅደስ ከተጣመርን *በኋላ* ለዘለዓለም እንደተጋባን እንድንቆይ ምን ማድረግ አለብን?

## የዘለዓለማዊ ጋብቻ በረከት

የሚከተለውን ጥቅስ ያንብቡ። ይህን በረከት የምታገኙ ብትሆኑ ኖሮ ምን ይሰማችሁ ነበር?

10-ሀ፣ የጥንዶች ፍቅር በዘለዓለማዊ ቤተሰብ ውስጥ ዘለዓለማዊ ነው።



ፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖው እንዲህ ሲሉ አስተምረው ነበር፥ “ሁለት የኋለኛው ቀን ቅዱሳን በጋብቻ አንድ ላይ ሲጣመሩ፣ ዘሮቻቸው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም እንደሚሆኑ ቃል ተገብቶላቸዋል። ለዘሮቻቸው፣ ለዘለዓለም ደህንነትን እና ከፍ ከፍ ማለትን እንዲሁም ክብርን የማገልገል የመቆጣጠርና የመግዛት መብትና ሥልጣን ሊኖራቸው እንደሚገባ ቃል ተገብቶላቸዋል። እዚህ ምድር ዘር ካላገኙ፣ ያለምንም ጥርጥር ከዚህ በኋላ ባለው ሕይወት የማግኘት ዕድል አላቸው። የሰው ልጅ ምን ሌላ ነገር ሊመኝ ይችላል? ከዚህ ሕይወት በኋላ፣ ወንድ እና ሴት፣ ሰማያዊ አካል ኖሯቸው፣ ከህመም እና በሽታ ነፃ ሆነው፣ በቃላት መግለፅ እስኪያቅት ከብረው ተውበው፣ በልጆቻቸው መካከል ቆመው፣ ሲገዟቸው እና ሲቆጣጠሯቸው፣ ሕይወት ዘለዓለማዊነትን እና ክብርን ለዘለዓለም ይሰጣል።” (*Deseret News,* 13 Mar. 1897; quoted in Spencer W. Kimball, *The Miracle of Forgiveness,* p. 246.)

ስዕል 10-ለ፣ በሶልት ሌክ ቤተመቅደስ ለዘለዓለም የተጋቡ ጥንዶች፣ የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው።

እንዴት ያለ የተከበሩ ተስፋዎች ናቸው! ለዘለዓለም ከተጣመርን እና ብቁ ሆነን መኖር ከቀጠልን፣ ለዘለዓለም ቤተሰብ ሆነን እንቀጥላለን። የምድር ላይ ቤተሰቦቻችን በቋሚነት የእኛ ሆነው ይቀራሉ። በተጨማሪም የመንፈስ ልጆችን በዘራችን ላይ እየጨመርን፣ ያለማቋረጥ መብዛት እንችላለን።

ስዕል 10-ሐ፣ የማጣመሪያ ክፍል በዋሽንግተን ቤተመቅደስ የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው።

ወንድም ቢ ጄ ዋንርላንድ፣ ከስዊድን እሱ እና ሚስቱ በስዊዝ ቤተመቅደስ ከተጣመሩ በኋላ እነዚህን ስሜቶች እንዲህ ሲል ገልፆታል፥

“ከዚያ የቤተ መቅደስ የመጀመሪያ ጉብኝት በኋላ ነፍሴን የሞላው ፍስሃ እና ደስታ እንዲሁም ወንጌልን ለማክበር የገባሁት ቁርጥ ኃሳብ በፍፁም አይረሳኝም። ስለ ዘለዓለማዊ መድረሻዬ በተመለከተ ከዚህ በፊት አልሜው የማላውቀውን እውቀት እና የጠለቀ መረዳት አገኘሁ። በጣም የሚያስደንቀው ቤተሰባችን ለአሁን እና ለዘለዓለም አንድ ላይ በተጣመሩ ጊዜ ነበር።

“ባለቤቴን ከመሰዊያው አሻግሬ አይንዋን ተመለከተኩኝ እናም በጉንጮቿ የደስታ እንባ ሲፈስ አየሁ። ከዚህ በፊትም ቢሆን እወዳት ነበር፣ ግን ከዚያች ቀፀበተ ጊዜ በኋላ እንዳለው ሊሆን አይችልም። እሷ፣ የእግዚአብሔር ሴት ልጅ፣ የልጆቼ እናት ነበረች! ይህን እስከአሁን ድረስ በፍፁም እንዳልተረዳሁት ዓይነት ነገር መሰለ። ከዚያ በኋላ፣ ፀሎቶችን የበለጠ ትርጉም ያላቸው ሆኑ፣ ከሌላው ጊዜ በተለየ ጌታን ወደድነው፣ እንዲሁም እሱን ማገልገልን ወደድን።

“ወደ ቤተመቅደሱ መመላለሱን ቀጠልን ምክንያቱም እዚያ ያለውን ሥራ እና መንፈስ እንወደዋለን። ሁሌ በተመላለስን ቁጥር የገባነውን ቃል ኪዳን ያስታውሰናል፣ እናም ይህ ለእኛ የወንጌላዊ ሕይወት እንድንኖር ጠንካራ አነሳሽ ምክንያት ሆኖናል።” (“I Had Loved Her Before,” *Ensign,* Aug. 1974, p. 62.)

ንስኃ መግባት እና እነዚህን በረከቶች ለማግኘት ብቁ ሆኖ መኖር ይጠቅማል! እነኚህን በረከቶች ለማግኘት ታላቅ መስዋዕትነት ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን አለብን።

10-ለ፣ በሶልት ሌክ ቤተመቅደስ ለዘለዓለም የተጋቡ ጥንዶች።



10-ለ



ወደ ቤተመቅደስ የሄዱ እህቶች ስለ ዘለዓለማዊ ጋብቻ እና ዘለዓለማዊ ቤተሰብ የተሰማቸውን እንዲገልፁ ጋብዟአቸው።

## ለዘለዓለማዊ ጋብቻ እንዴት እንዘጋጃለን

ስለ ቤተመቅደስ መግቢያ ፈቃድ ቃለ መጠይቅ ያብራሩ። በዚህ ቃለመጠይቅ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች የሚያሳይ ፖስተር አሳይአቸው። (Listed in *Gospel Principles,* chapter 38.) ወይም ሰሌዳ ላይ ፃፌ።

ቤተመቅደስ ለመግባት መመዘኛውን እያሟላን ካልሆነ፣ ይህን ለማረም ምን ማድረግ አለብን? የቤተመቅደስ ጋብቻ ለማግኘት ምን ዓይነት መስዋዕትነት መፈፀም አለብን?

ሁልጊዜ ስለ ቤተመቅደስ ጋብቻ ያለንን ግብ በፊታችን ማኖር ይገባናል። ለእኛ እና ለልጆቻችን ብቁ ሆኖ ስለ መኖር ለማስታወስ በአቀራቢያችን ያለ አንድ ቤተመቅደስ ፎቶግራፍ መለጠፍ አንዱ መንገድ ነው።

ስዕል 10-መ፣ ሳኦ ፖሎ ቤተመቅደስ የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው፣

እንደ እናትነታችን፣ ሴት ልጆቻችንን የቤተመቅደስ ጋብቻ ጠቃሚነት እንዲረዱ ማድረግ እንችላለን። በእግዚአብሔር እምነት እንዲኖራቸው ልናስተምራቸው እንችላለን። በክህነት ኃይል ወደ ፅድቅ ሕይወት የሚመራቸው ጥሩ ባል ለማግኘት መሻት አለባቸው። የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ወንድ ለሚስቱ ታላቅ መፅናናት ነው፣ በተለይም በህይወት በችግር እና በስደት ጊዜ በተጨማሪም ወንድ ልጆቻችን ጥሩ፣ በቤተክርስቲያን የሚደግፏቸው እና ለልጆቻቸው እውነተኛ ህግ የሚያስተምሩላቸው ብቁ ሚስቶች እንዲፈልጉ ማስተማር ጠቃሚ ነው።

በማዕከላዊ አሜሪካ የምትኖር አንዲት ወጣት ሴት የቤተክርስቲያኑ አባል ካልሆነ ሰው ጋር በፍቅር እንደወደቀች ይሰማት ነበር። ወንጌልን ልታስታውቀው ሞከረች፣ ግን ፍላጎት አላደረበትም። ከቅርብ ጓደኞችዋ የሩቀ ርቀት ጥሪ ባደረጉላት ጊዜ፣ ይህን ሰው ለማግባት ወስና ነበር። በፊተና ጊዜ የሚደግፋት እና ከእሱ ጋር ከቀብር በኋላ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚወስዳት ሰው የማግባቱን ጠቀሜታ አበክረው ገለፁላት። ስለ ውሳኔዋ የመጨረሻ ውጤት በጥንቃቄ በማሰብ፣ ሰማቻቸው። ማበረታቻቸው ይህን ሰው ከማግባት እርሷን ለማቀብ በቂ ነበር። ዛሬ እሷ በጣም አመስጋኝ ነች ምክንያቱም ወደ ቤተመቅደስ የሚወስዳት ብቁ ባል አግኝታለችና።

ልጆቻችን የጋብቻ ጓደኛ በሚመርጡበት ጊዜ ምን ልናስተምራቸው ይገባል?

ልጆቻችን በትክክል ፃድቅ ባል ወይም ሚስት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እራሳቸው ፃድቅ እና ብቁ መሆን እንዳለባቸው፣ ልናስተምራቸው ይገባል።

ለቤተመቅደስ ጋብቻ እራሳችንን ከአሁኑ ማዘጋጀት መጀመር ያለብን ለምንድነው?

በመዘጋጃ ቤት የተጋባን ካለን በቤተመቅደስ ከባሎቻችን ጋር ለመጣመር መዘጋጀት እንችላለን፣ ልጆች ካሉን፣ እነሱ ከእኛ ጋር እንዲጣመሩ ማድረግ እንችላለን። ነገር ግን ይህን ጠቃሚ ቀን ለነገ ማሳደር የለብንም። አንዴ ስለ ወንጌል ሰምተን ከተቀበልን፣ ሥርዓቶቹን በምድር ሳለን ለማግኘት ያለንን ኃይል ሁሉ መጠቀም አለብን። (See Spencer W. Kimball, *The Miracle of Forgiveness,* p. 246.)

“ምንም እንኳን ብዙ ወጣቶች በአካባቢያቸው በአሁን ጊዜ ቤተመቅደስ ባይኖርም፣ በአጠቃላይ በጣም ሳይርቅ ቤተመቅደሶች አሉላቸው . . .።

10-ሐ የማጣመሪያ ክፍል በዋሽንግተን ቤተመቅደስ።


10-00

“ልጆቻችሁ ለቋሚነት የእናንተ እንዲሆኑ እናም እናንተ ለቋሚነት የእነርሱ ወላጆች እንድትሆኑ በአቀራቢያችሁ ባለ ቤተመቅደስ ሄዳችሁ ለዘለዓለም ለመታተም የጫጉላ ሽርሽራችሁን ለዚህ ዓላማ እንደምታቀዱት ጠንካራ ምኞታችን ነው።” (Spencer W. Kimball, “The Marriage Decision,” *Ensign,* Feb. 1975, p. 4.)

አንዳንድ ሰዎች ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ምክንያት፣ ከመሞታቸው አስቀድመው ቤተመቀደስ መግባት አይችሉም ይሆናል። የዘለዓለም ጋብቻ ሥነ ሥርዓት በቤተመቀደስ ውስጥ በውክልና በሌሎች ሰዎች አማካኝነት ማግኘት እንደሚችሉ ማወቀ የሚያፅናና ነው።

*ከወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 40፣ ሁለቱን ንዑስ ምዕራፎች አጭር ክለሳ እንድትሰጥ፣ የተመደበችዋን ተማሪ ይጠይቁ።

## መስዋዕት ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን ይገባናል

ጌታ አንድን ነገር ምን ያህል እንደተመኘን ያንን ነገር ለማግኘት መስዋዕትነት ለመክፈል ምን ያህል ፈቃደኛ መሆናችንን ያውቃል። በእውነት ዘለዓለማዊ ጋብቻ የምንፈልግ ከሆነ፣ መስዋዕት ለመክፈል ፈቃደኛ እንሆናለን።

ወንድም እና እህት ቫሂሊ ቶንጋ ከቶንጋን ደሴቶች፣ ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ መስዋዕትነት ከፍለው ነበር። “ለእንደዚህ ዓይነት ጉዞ ገንዘብ መቆጠብ ለአንድ ቶንጋ ቀዱስ ቀላል አልነበረም። ለወራት መዘጋጀት እና መቆጠብ ያስፈልግ ነበር፣ ግን በመጨረሻ ገንዘቡ ተሰበሰበ እናም እቀዶች ወጡ።”

ይሁንና፣ የሚሽን ፕሬዚዳንቱ ወደ ወንድም ቶንጋ መጥቶ ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ የቆጠበውን ገንዘብ በቀርንጫፉ ስር ለአንድ ፀሎት ቤት ግንባታ መዋጮ እንዲያዋጣ ጠየቀው። ይህን ባያደርግ ኖሮ፣ ፀሎት ቤቱ እዚያ ለመገንባት ሌላ ተጨማሪ ሁለት ዓመት ይወስድ ነበር። ወንድም ቶንጋ ስለዚህ ሁኔታ ከሚስቱ ጋር ተወያየ።

“አዲሱን ቤተመቀደስ የማየት ህልማቸውን መተው በጣም አስቸጋሪ ነበር፣” ግን በሚቀጥለው ቀን ገንዘቡን ለሚሽን ፕሬዚዳንቱ ሰጡ። “ያን ዕለት ምሽት (ወንድም ቶንጋ ለሚስቱ) እንዲህ አላት፣. . . ‘ጌታ በመሪዎቻችን አማካኝነት ትዕዛዛቱን ከጠበቅን ወደ (አዲሱ የኒውዝላንድ ቤተመቀደስ) ምርቃት መሄድ የምንችልበት መንገድ ሊያዘጋጅልን ቃል ገብቶልናል። ላሞች፣ አሳማዎች፣ እና ጥቂት ፈረሶች፣ በተጨማሪም የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች እና ምንጣፍ አለን። ሁሉንም እንሸጥ እና የምርቃቱን በረከት እንቀበል።’ ”

ወንድም ቶንጋ እና ሚስቱ ከብቶቻቸውን ሐሙስ እና አርብ ለመሸጥ ሞከሩ፣ ግን የሚገዛቸውን አጡ። ጊዜ እያጠረ መጣ። በሚቀጥለው ሰኞ ወደ ኒውዘላንድ የጫነው መርከብ ሊነሳ ነው።

“ ‘ቅዳሜ ላይ ጥቂት ላሞች፣ አሳማዎች፣ እና ሌሎች ነገሮችን የሚፈልጉ ሶስት ቤተሰቦች መጡ፣ እናም በ$500 እና $600 መካከል የሚሆን ገንዘብ በግማሽ ሰዓት ውስጥ አገኙ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ’ ” አሁን ገንዘቡን አግኝተዋልና መሄድ ይችላሉ።

ወንድም ቶንጋ እና ሚስቱ በኒውዝላንድ ቤተመቀደስ ለመጣመር የመጀመሪያዎቹ ነበሩ። ግን ታሪኩ እዚህ ላይ አያቀምም። ወንድም ቶንጋ እንዲህ አሉ፣

10-መ ሳኦ ፓሎ ቤተመቀደስ።

" 'ሚስቴ እና እኔ በተጣመርን ጊዜ፣ የሆነ ነገር ልቤን ነካው። ልጆቻችን ከእኛ ጋር አልነበሩም፣ እናም ከዓይኔ እንባ መጣ። ወደቤት ከተመለስን በኋላ፣ ለአራቱ ልጆቼ የሚያግዙን ከሆነ፣ ወደ ቤተመቅደስ አብረን እንደምንሄድ ቃል ገባሁላቸው። ለራሴ እንዲህ ስል አሰብኩ፣ "ከእነሱ ጋር አብረን ካልተጣመርን በቀር፣ እንዴት ጥሩ ወንድ ልጅ ወይንም ጥሩ ሴት ልጅ ሁኑ እላቸዋለሁ?" የእኔ አይደሉም የሚል ስሜት ተሰማኝ።

" 'ለሁለት ዓመት ያለንን ሁሉ ሰዋን። ከተምህርት ቤት የማገኘው ገንዘብ ለእያንዳንዳችን ከፋፈልኩት፣ እናም መቆጠብ ጀመርኩኝ። ግን አስራት እና የጾም በኩራታችንን እንከፍል ነበር። ለሁለት ዓመት 70 ሳንቲም በወር ብቻ ይተርፈን ነበር። በምናድግበት እና በምናገኘው ነገር መኖር ጀመርን . . .። ልጆቼ ከረሜላ ወይም ጫማ መግዛት አይችሉም ወይም ወደ ሲኒማ ቤት መሄድ አይችሉም ምክንያቱም ለቤተመቅደስ ገንዘብ እየቆጠቡ ነበር . . .።

"የመጓጓዣ ወጪዬን ለመቆጠብ ሰባት ማይል ወደሚርቀው የአውራጃ ስብሰባዎች በብስክሌት እሄድ ነበር . . .። አብዛኛው የአውራጃችን ስብሰባዎች ከጥዋቱ 12፡00 ላይ ነው የሚጀምሩት ስለዚህ ከቤት በጠዋት መውጣት ነበረብኝ።

" 'ገንዘባችንን የምንጠቀምበት ጊዜ ገደብ በደረሰ ጊዜ፣ . . . ሁለቱ ትልልቅ ልጆቼ $235 እንዳላቸው ነገሩኝ። ትንሹ ልጄ (ዕድሜው አምስት ዓመት ነበር) ለሁለት ዓመት $65 ቆጠበ። እኔም ለቤተሰባችን $1,300 ያህል ቆጥቤ ነበር።

" 'መስዋዕት በመክፈላችን ቤተሰባችንን ወደ ኒውዝላንድ ወስደን በቤተመቅደስ ለመጣመር ችለን ነበር። ግባችንን ለመምታት ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን መፈፀም ነበረብን፣ ግን ይህ ለእኛ ታላቅ በረከት ነበር።" (See "We Lived on 70 Cents a Month for the Temple," *Ensign,* Feb. 1976, pp. 30–31.)

### ማጠቃለያ

በቤተመቅደስ ስንጣመር እና ብቁ ሆነን ስንኖር፣ ለዘለዓለም ቤተሰብ እንሆናለን። በወዲያኛው ሕይወት የመንፈስ ልጆች በቤተሰባችን ላይ በማብዛት፣ መጨመር እንቀጥላለን። የቤተመቅደስ ጋብቻ ካላደረግን፣ እራሳችን በፅድቅ ሕይወት ለዚህ ዘለዓለማዊ በረከት ማዘጋጀት አለብን።

---

#### የመምህሩ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. *የወንጌል መሰረቶች*፣ ምዕራፍ 38፣ "ዘለዓለማዊ ጋብቻ፣" እና ምዕራፍ 40 "የቤተመቅደስ ሥራ እና የዘር ቆጠራ" የሚሉትን ርዕሶች ያጥኑ።
2. ከምዕራፍ 40 ሁለቱ ንዑስ ምዕራፎች ማለትም። "የቤተመቅደስ ሥነ ሥርዓት ቤተሰብን ለዘለዓለም አንድ ላይ ያስተሳስራል፣" እና "የቤተመቅደስ ሥነ ሥርዓት ለሞቱት ሊፈፀም ይችላል፣" የሚሉትን የክፍሉ ተማሪዎች አጭር ክላስ እንዲሰጡ ይመድቡ።
3. ት እና ቃ 132፡14–20 ያንብቡ።
4. በዚህ ትምህርት የተጠቀሰውን ፓስተር ያዘጋጁ።

# የክህነት አስፈላጊነት

ትምህርት 11

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ ክህነት ምን እንደሆነ እና ቤተሰቦቻችን ዘለዓለማዊ ህይወትን እንዲያገኙ እንዴት እንደሚረዳን እንድንገነዘብ ለመርዳት ነው።

---

**ክህነት—ለእግዚአብሔር ለመሥራት የተሰጠ ኃይል**

እግዚአብሔር እና ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል እዚህ ምድር ላይ ስለማይኖሩ፣ ለሰው ልጆች ሥራቸውን እንዲሰሩ ስልጣን እና ኃይል ሰጥተዋል። የእግዚአብሔር ሥራ "ለሰው ልጅ ህያውነት እና ዘለዓለማዊ ሕይወት ማምጣት ነው።" (ሙሴ 1፥39።) "(ክህነት) የሰው ልጅ በምድር ላይ ለሰው ልጅ ቤተሰብ መስራት እንዲችል፣ በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ደህንነትን ማምጣት እና በሕጋዊነት እንዲሰራ የተሰጠው ስልጣን ከእግዚአብሔር ኃይል አይበልጥምም፣ አያንስምም።" (Joseph F. Smith, *Gospel Doctrine,* pp. 139–40).

መጥምቁ ዮሐንስ በግንቦት 15፣ 1829 ለዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ ታያቸው፣ እናም የአሮናዊ ክህነት ሰጣቸው። ከዚያም ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የመልከጼዴቅ ክህነት ሰጡዋቸው። በሚያዝያ 6/1830 ዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ በክህነት ስልጣኑ ውስጥ እርስ በእርሳቸው ሽማግሌ ሆነው ተሿሾሙ።

ማንኛውም ክህነት የያዘ ሰው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወስደውን የስልጣን መስመር ማመልከት መቻል አለበት። ይህ ማለት እሱን ማን እንደሾመው እና እሱን የሾመውን ሰው ማን እንደሾመው፣ እንደዚህ እያለ ወደኋላ እስከ ዮሴፍ ስሚዝ ድረስ እሱም፣ በጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የተሾመው፣ እነርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ የተሾሙት ድረስ ማወቅ ይገባዋል። ይህ "የክህነት የሥልጣን መስመር" ተብሎ ይጠራል።

ስዕል 11-ሀ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የመልከጼዴቅ ክህነት ለዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ ሲሰጡ፣ የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው። የተመደበችው እህት የባልዋን የስልጣን መስመር ካርድ እንድታሳይ ያድርጉ።

*ክህነት* እራሱ ለቤተክርስቲያኑ አባል ለሆኑ ብቁ ወንዶች ይሰጣል። ከዚያም ልክ እንደ ዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ፣ በክህነት ውስጥ ለአንድ *ኃላፊነት* ሊሾሙ ይችላሉ። የአሮናዊ ክህነት ከተሰጣቸው በኋላ፣ በዲያቆን፣ መምህር፣ ወይም ቄስ ኃላፊነቶች ሊሾሙ ይችላሉ። የመልከጼዴቅ ክህነት ከተሰጣቸው በኋላ፣ በሽማግሌ፣ በሰባዎቹ፣ ወይም ሊቀ ካህን ይሾማሉ፣ ሊቀ ካህን በልዩ ጥሪ በጳጳስ፣ በፓትሪያርክ፣ ወይም በሐዋሪያ ኃላፊነቶች ይሾማል። እነዚህ ኃላፊነቶች የተለያዩ ኃላፊነት ያላቸው፣ የክህነት ጥሪዎች ናቸው።

አንድ ግለሰብ በቤተክርስቲያኑ ሲጠመቅ፣ እሱ ወይም እሷ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የተወሰነ ሥራ እንዲሰሩ ሊጠሩ ይችላሉ። በተመሳሳይ፣ አንድ ወንድ አባል ክህነት ከተቀበለ በኋላ፣ የተወሰኑ ሥራዎችን ለመስራት በክህነት ኃላፊነቶች ውስጥ ለአንድ ኃላፊነት ይሾማል። ወንዶች



11-U

ክህነት ሲይዙ፣ የወንጌልን ቅዱስ ሥነ ሥርዓቶች ማለትም እንደ ጥምቀት፣ አባልነት ማረጋገጫ፣ ቅዱስ ቁርባን ማስተናገድ፣ እና ሌሎችን ማከናወን ይችላሉ። (በዚህ መምሪያ መፅሐፍ ውስጥ በትምህርት 12 ላይ ስለእነዚህ የክህነት ሥነ ሥርዓቶች ተብራርተዋል።)

## የክህነት ኃይል በፅድቅ አኗኗር ይመጣል

ዮሴፍ ስሚዝ ስለ ክህነት መሰረታዊ ሕግ እንዲህ ሲል አስተምሯል፡ "የክህነት መብት ከመንግስተ ሰማያት ኃይል ጋር የሚነጣጠል አይደለም፤ እናም የመንግስተ ሰማያት ኃይልን ደግሞ ከፅድቅ ኃይል በቀር መቆጣጠርም መያዝም አይቻልም።" (ት እና ቃ 121፥36።)

ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር በሚከተለው ታሪክ ስለ ጽድቅ ሕይወት ጥቅም እና የክህነት ኃይል ገልጾልናል፡

"ጳጳስ በነበርኩበት ጊዜ፣ በዋርዴ ቄስ ሆነው መሾም የሚችሉ ስድስት ልጆች ነበሩ። ለአምስቱ ብቻ ነበር እንዲሾሙ መፍቀድ የምችለው፣ ምክንያቱም አንደኛው ዝግጁ አልነበረም። ከእሱ ጋር ብዙ ጊዜ ተነጋግረንበታል፣ እናም እሱ እንዲህ ብሎኝ ነበር፣ "እኔ ብቁ አይደለሁም።" ስለዚሁ ነገር በጣም መጥፎ ስሜት ይሰማው ነበር፣ ግን ለመታጨት አይጠብቀም ነበር . . .። አጎቱ ወደ እኔ መጡና እንዲህ አሉኝ፡ 'አንተ ይህን ልጅ ከአምስቱ ጓደኞቹ ነጥለህ መቼም እንደማትተው እርግጥ ነው።' እንድፈቅድለት ለመኑኝ። 'ይህን ካላደረክ ልጁን ከቤተክርስቲያኑ እንዲወጣ እየገፋፋኸው ነው' አሉኝ።

"ለዚህ ሰው እንዲህ ስል አብራራሁለት፡ 'ክህነት ለዚህ ልጅ ልንሰጠው የምንችለው በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። እኛ ክህነት ለማንም ዝም ብለን የምናድለው ነገር አይደለም . . .። ይህ ልጅ እና እኔ ተግባብተናል፣ እናም በቀስና ሹመት ለመሾም ዝግጁ አይደለም፤' እናም አልታጨም።

"ከጥቂት ዓመታት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤ ተሳትፌ ነበር . . . እናም አንድ ወጣት ወደ እኔ መጣና እንዲህ አለኝ፣ 'ፕሬዚዳንት ታነር፣ አታስታውሰኝም። ሽማግሌ እንድሆን ሳታጨኝ የቀረኸው ልጅ ነኝ።' እጁን ሊጨብጠኝ ሲቀርብ እንዲህ አለኝ፡ 'ላመሰግንህ እፈልጋለሁ። ዛሬ በካሊፎርኒያ ጳጳስ ሆኛለሁኝ። ብቁ ባልሆንኩበት ጊዜ አጭተኸኝ ቢሆን ኖሮ ክህነት ምን እንደሆነ እንዳላደንቅ እና ከአንድ ግለሰብ ምን እንደሚጠበቅ በትክክል ለማወቅ ይቸግረኝ ነበር፣ እናም በእርግጥ ዛሬ እንደሆንኩት ጳጳስ በፍፁም አልሆንም ነበር።' " (In Conference Report, Apr. 1973, p. 122; or *Ensign,* July 1973, p. 94.)

ወጣቱ ብቁ ሳይሆን መሾሙ ለምን ያልተገባ ሆነ?

ጌታ በጽድቅ ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ብቻ የክህነት በረከት እንደሚያገኙ ነግሮናል። ሰዎች የክህነት ሥራቸውን በመስራት የክህነት ጥሪያቸውን ማጉላት አለባቸው። በተጨማሪም ቤተሰባቸውን በፍቅር፣ በርህራሔ፣ እና በትዕግስት መምራት አለባቸው። (ት እና ቃ 121፥34፣ 41–42)

እህት ዩ ኩም ኦክ ከኮሪያ በቤት ውስጥ ክህነቱን ስለሚያከብረው ባልዋ የሚከተለውን ታሪክ ተነገረናለች፡

11-ሀ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የመልከጼዴቅ ክህነት ለዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ ሲሰጡ።

“አንድ ወንድ እና ሁለት ሴት ልጆች ያሉኝ የቤት እመቤት ነኝ። ዕድሜዬ ሰላሳ አራት ነው። በ1964 ነው ያገባሁት። ምስክርነቴን መግለፅ እፈልጋለሁ።

“በመስከረም 14/1974 ተጠመቀኩ፣ እናም በኮሪያ እውነተኛ የኋለኛው ቀን ቅዱስ በሆነው ባለቤቴ በጣም እኮራለሁ። ምንም እንኳን ከተጠመቀ አራት ዓመቱ ቢሆንም፣ ታላቅ ሰው እንደሆነ ይሰማኛል፣ እንደ ኢየሱስ ያለ ሰው ለመሆን ቀርጧል። ስለ ሕይወት ትርጉም ምንም አላውቅም ነበር። በአዕምሮዬ እንደሚከተሉት ያሉ ጥያቄዎች ነበሩኝ፣ ከየት ነው የመጣነው? እዚህ ለምን መጣን? የት ነው መሄድ የሚገባን? እግዚአብሔር እንደሌለ እና ኢየሱስ ተራ ሰው እንደሆነ አስብ ነበር። በአዕምሮዬ የነበረው ባለቤቴን መርዳት እና ልጆቼ ጠንካራ ሆነው እንዲያድጉልኝ መጣር ነው። ስለ ደህንነት ማለትም ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ግድ አልነበረኝም።

“ግን ዛሬ በጣም የተለየ ሰው ሆኛለሁ። ሕይወት ያላትን እውነተኛ ትርጉም አውቄያለሁኝ። በባለቤቴ ሥራ እና ቃላት፣ ሞርሞኒዝም በእውነት ምን እንደሆነ እየተረዳሁ መጥቻለሁ። ባለቤቴ አይጠጣም፣ አያጨስም፣ ቡና አይወስድም፣ ሻይ አይወስድም፣ እንዲሁም ስራውን እንደጨረሰ በቀጥታ ወደ ቤቱ ይመጣል። በፍፁም የሚጎዳ ነገር አያደርግም አይቆጣም፣ እንዲሁም ከልጆች ጋር መጫወት ይወዳል፣ ሳሕኖችን ያጥባል፣ ቤቱን ያፀዳል፣ ውሸት በፍፁም አይናገርም፣ ሁል ጊዜ ለስላሳ ቃላት ለመናገር ይሞክራል፣ እንዲሁም በተቻለው መጠን የቤት ውስጥ ስራዎች እንደ አቀሙ በፈቃደኝነት ይሰራል። እነዚህን ሁሉ ነገሮች በዓይኔ አይቻቸዋለሁ። ከዚህ የተለየ ተአምር ይኖራል ብዬ አላስብም። ባለቤቴ ወደ ተሻለ ሰው ተቀይሯል።

“ባለቤቴን ወደ ቤተክርስቲያኗ ከተለወጠ በኋላ፣ የተለየ ሰው እንዲሆን ያደረገው ነገር ይገርመኛል። በመጨረሻ ግን ገባኝ። ሁልጊዜ የሚያነበው፣ መፅሐፈ ሞርሞን ነበር። ስለ መፅሐፈ ሞርሞን ለመማር በቅዱስ ፅሑፍ መማሪያ ተቋም ለመግባት ወሰንኩ፣ እናም ባለቤቴ ካስተዋወቀኝ አሜሪካዊ ወንጌላዊያን ጋር ማጥናት ጀመርኩ። በመጨረሻ በውድ ባለቤቴ ተጠመቀኩኝ። ባለቤቴን ወደተለየ ሰው የቀየረው ተመሳሳይ ኃይለኛ መንፈስ እኔንም እየባረከኝ እንደሆነ እገምታለሁ።

“ዛሬ ለጊዜው እና ለዘለዓለም ከባለቤቴ እና ልጆቼ ጋር በሰማይ የክብር ቤት አብሬ መኖር እፈልጋለሁ። እራሷን አሳልፋ የሰጠች የሴቶች መረዳጃ ማኅበር አባል፣ ጥሩ እናት፣ እና ለባለቤቴ የክህነት ስራዎቹን የምደግፍ ጥሩ ሚስት መሆን እፈልጋለሁ።” (“A Real Latter-day Saint,” Leon Hartshorn, comp., *Inspirational Missionary Stories,* pp. 30–31.)

ይህ ሰው ራሱን በመቀየሩ፣ ሚስቱን ጥሩ ሚስት፣ እናት፣ እና የእግዚአብሔር ልጅ እንድትሆን አነሳስቷል።

ይህች እህት ጻድቅ ሆና ለመኖር በመወሰንዋ በባልዋ እና በልጆችዋ ምን ተጽዕኖ ፈጠረ? የጽድቅ ሕይወታችን በባሎቻችን እና ልጆቻችን ላይ ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል? ይህ በዘለዓለማዊ ሕይወታችን ላይ ምን ተፅዕኖ አለው?

## ክህነት ለቤተሰብ ዘለዓለማዊ ሕይወት አስፈላጊ ነው

ዘለዓለማዊ ሕይወታችንን ለማግኘት እና ከሰማይ አባታችን ጋር አብረን ለመኖር የተወሰኑ ነገሮችን መፈፀም ይገባናል። በክህነት እርዳታ፣ ሁሉንም ነገር ማድረግ እንችላለን።

ፕሬዚዳንት ብሪግሀም ያንግ እንዲህ ብለው ነበር፥ “ስለ ኋለኛው ቀን ቅዱሳን ኃይል ብዙ ተብሏል። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩት ሰዎች ናቸው ይህን ኃይል የያዙት፣ ወይስ ክህነቱ? ክህነቱ ነው፣ እናም ክህነቱን ካከበሩ፣ ሥራቸውን ከዚህ መጀመር ይችላሉ . . . እናም ክብርን፣ ሕያውነትን፣ እና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት መዘጋጀት ይችላሉ።” (*Discourses of Brigham Young,* pp. 131–32.)

ጌታ ትዕዛዛትን እና የወንጌል ትምህርቶችን ሰጥቶናል። ለእነሱ መታዘዝ ለቤተሰብ ዘለዓለማዊ ሕይወት አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳን ያለ ክህነት አንዳንዶቹን ትዕዛዛት መታዘዝ ብንችልም፣ የዘለዓለማዊ ሥርዓት በክህነት ኃይል ላይ የተመረኮዘ ነው። ጥምቀት፣ አባልነትን ማረጋገጫ፣ የቤተመቅደስ ጋብቻ . . .ሁሉም በክህነት ኃይል ላይ የተመረኮዙ ናቸው። ያለነዚህ ሥርዓቶች፣ ለዘለዓለም አንችልም።

አንዳንዶቻችን ባሎቻችን እና አባቶቻችን የቤተክርስቲያኑ አባል ባለመሆናቸው ወይም ክህነታቸውን ባለማክበራቸው እንዳልታደልን ሊሰማን ይችላል። ከእነርሱ ጋር ትዕግስተኞች እና አፍቃሪዎች መሆን አለብን፣ አንድ ቀን በጌታ መንፈስ እንዲነኩ መጸለያችንን መቀጠል አለብን። በዚህ መካከል እንዳለ በሌሎች ፃድቃን ባለክህነቶች ሥርዓቶችን ማግኘት እንችላለን።

“የሰማዩ አባታችን የሰለስቲያል መንግስት አባል መሆን የሚቻለው መለኮታዊ ስልጣን ባላቸው እጅ ስር ብቻ እንደሆነ ለሰው ልጆች ግልፅ አድርጓል።” (George Albert Smith, in Conference Report, Apr. 1934, p. 28.)

ት እና ቃ 132፡19 ያንብቡ። በዚህ ቅዱስ ፅሑፍ ውስጥ የተጠቀሰ ምን ዓይነት የክህነት ሥርዓት ነው? ከፍ ከፍ ማለት ምንድነው? አንድ ቤተሰብ እንዴት ከፍ ከፍ ማለት ይችላል?

“ዘለዓለማዊ ሕይወት በሴሌስቲያዊ መንግስት ከሰማይ አባታችን ጋር በከፍተኛ ክብር መኖር ማለት ነው። ብቁ ሆነው የሚኖሩ ጥንዶች በቤተመቅደስ ሊጣመሩ ይችላሉ። ከእነርሱ የሚወለዱ ልጆች፣ የዚህ ቤተሰብ ክፍል ይሆናሉ። ወይም ከጊዜ በኋላ ቤተክርስቲያኑን የተገናኙ ቤተሰቦች እና ብቁነታቸውን ያስመሰከሩ የመጣመር ሥርዓት በቤተመቅደስ ውስጥ ሊፈፀምላቸው ይችላል። በሁለቱም ሁኔታዎች፣ እስከመጨረሻው ብቁ ሆኖ መቀጠል ለዘለዓለማዊ ሕይወት አስፈላጊ ነው።” (*Learn of Me and Listen to My Words, Laurel Course A, 1977,* p. 118.)

## ማጠቃለያ

ክህነት እንደገና በመመለሱ ምክንያት የሰማይ አባታችን ዘለዓለማዊ ሕይወትን የምናገኝበትን ኃይል ሰጥቶናል። የመጣመር ሥርዓት ማግኘት እና በፅድቅ መኖር ይገባናል። ለጊዜው ብቻ ሳይሆን፣ ለዘለዓለም መኖር ይገባናል። ብቁ ለመሆን እና ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያመጣውን የክህነት ሥርዓት ለማግኘት መጣር ይገባናል።

## ሙከራ

ስለ ክህነት በተጨማሪ ለማወቅ *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች፣* ምዕራፍ 13 እና 14
ያንብቡ። ስለ ክህነት ጥቅም ከባለቤታችሁ እና ከልጆቻችሁ ጋር ተወያዩ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

ት እና ቃ 13 (ዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ የአሮናዊ ክህነት ሹመት)
ት እና ቃ 131፥1-3 (አዲስ እና ዘለዓለማዊ ቃልኪዳን)
ት እና ቃ 132፥18-20 (ዘለዓለማዊ ጋብቻ)

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረባችሁ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች* ምዕራፍ 13 "ክህነት" እና ምዕራፍ 14፣ የክህነት ድርጅት የሚሉትን ያንብቡ።
2. አንድ እህት የአንድ ክህነት ያለው ሰው የክህነት ሥልጣን መስመር ካርዱን አምጥታ እንድታሳይ ይመድቡ።
3. በዚህ ትምህርት ውስጥ ታሪኮች እና ቀዱስ ፅሑፎችን እንዲያቀርቡ የክፍል አባላትን ይመድቡ።

# የክህነት ሥነ ሥርዓቶች

ትምህርት 12

የዚህ ትምህርት ዓላማ ለቤተሰባችን በረከትን ለማምጣት የክህነት ሥነ ሥርዓቶችን እንድንጠቀም ለማበረታታት ነው።

## የክህነት ሥነ ሥርዓቶች

የክህነት ሥነ ሥርዓቶች ካህናት የጌታን ልጆች ለመባረክ የሚያከናውኑት የተለዩ ሥራዎች ናቸው። ብቁ አባቶች በሚታዘዙበት ጊዜ ይህን ለቤተሰቦቻቸው አባላት መፈፀም ይችላሉ። የቤተክርስቲያኑ አባል ስንሆን፣ ሁለት ሥነ ሥርዓቶችን ተቀብለናል . . . እነርሱም ጥምቀት እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ናቸው።

አንዳንድ የክህነት ሥነ ሥርዓቶች ለደህንነታችን እና ለዘለዓለማዊ ሕይወት አስፈላጊ ናቸው። ይህም ጥምቀት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፣ እና የቤተመቀደስ ጋብቻ እንዲሁም መታተምን ይጨምራል። ሌሎች ሥነ ሥርዓቶች ህሙማንን ለመፈወስ መባረክ ወይም ብቸኞችን የማፅናናት እና የመምራት የተለያዩ በረከቶች፣ በሕይወት ዘመን ለመርዳት በክህነት ስልጣን የሚመጡ ናቸው።

የሚከተሉትን የክህነት ሥነ ሥርዓቶችን የሚዘረዝር ፖስተር ያሳዩ፣

1. ጥምቀት
2. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፣ እንዲሁም ማጽናት ተብሎ ይጠራል።
3. ክህነትን መስጠት (ለወንድ አባላት)
4. የቤተመቀደስ ስጦታ
5. የቤተመቀደስ ጋብቻ እና ለጊዜው እና ለዘለዓለም መታተም
6. ቅዱስ ቁርባን
7. ልጆችን መባረክ እና መሰየም
8. ህሙማንን መባረክ
9. ልዩ በረከቶች
10. የፓትሪያርክ በረከት

ስዕል 12-ሀ፣ የመልከፄዴቀ ክህነት ያለው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ሲያከናውን፣ 12-ለ፣ አዲስ አባል በሁለት ቄሶች በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሲፀና፣ 12-ሐ፣ አንድ ብቁ አባት ልጁን ስም ሲሰጠው እና በረከት ሲሰጠው፣ እና 12-መ፣ ህሙማንን መባረክ። የሚሉትን ስዕሎች ያሳዩአቸው። ስለ እያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ተወያዩ። (See *Family Guidebook.*)

እናንተ እና ቤተሰቦቻችሁ ያልተቀበላችሁት ሥነ ሥርዓቶች አሉን?

## የክህነት ሥነ ሥርዓቶች በረከቶች

የክህነት ሥነ ሥርዓቶችን መቀበል በህይወታችን በጣም አስደናቂ በረከቶችን ሊያመጣ ይችላል። ጳጳስ ኤች በርክ ፒተርሰን ለካህናት በተናገሩበት ጊዜ ለካህናቶች እንዲህ ሲሉ

12-ሀ፣ የመልከጼዴቀ ክህነት ያለው የጥምቀት ሥነ-ሥርዓት ሲያከናውን።
12-ለ አዲስ አባል በሁለት ቄሶች በኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሲጸና።
12-ሐ አንድ ብቁ አባት ልጁን ስም ሲሰጠው እና በረከት ሲሰጠው።
12-መ ህሙማንን መባረክ።









12-00

እነዚህን ነገሮች ጠቀሰዋል፡ “ካከበርነው፣ ለተረበሸ ቤተሰብ ሰላም የሚያወርድ ከሰማይ አባታችን የተሰጠ ኃይል ሊሆን ይችላል። ህፃናትን የሚባርክ እና የሚያፅናና፣ በጥዋቱ በእንባ ለራሰው ዓይን እንቅልፍ የሚያመጣ ኃይል የእኛው ሊሆን ይችላል። የእኛ ሴት ልጃችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከወንድ ጋር ስትሄድ ወይም የቤተመቀደስ ጋብቻ ከማድረጓ በፊት ለመባረክ፣ ወይም ወንድ ልጃችን ወደ አገልግሎት ሥራ ወይም ኮሌጅ ከመሄዱ በፊት የመባረክ ኃይል የእኛ ሊሆን ይችላል። . . . እኛ የታመሙትን ለመፈወስ እና ብቸኞችን ለማጽናናት ኃይል ሊኖረን ይችላል።” (“Priesthood—Authority and Power,” *Ensign,* May 1976, p. 33.)

እንደ ሚስትነታችን፣ እናትነታችን፣ ልጅነታችን፣ እና እህትነታችን፣ እንዲህ ያለውን በረከት ከባሎቻችን፣ ከአባቶቻችን፣ ከወንድሞቻችን፣ ወይም የቤት ለቤት አስተማሪዎቻችንን መጠየቅ እንችላለን።

እንደዚህ ያለ በረከት ከፈለጋችሁ፣ ከባላችሁ ወይም አባታችሁ ማግኘት ብትችሉ ምን ይሰማችኋል?

የኮሪያ እህት ኪዮለን ሊ ይ የክህነት በረከት ማፅናኛ ቤቷ ውስጥ አግኝታለች። የሚከተለውን ታሪክ ትናገራለች፡ “ይህ የሆነው ከሰባት ዓመት በፊት፣ የኮሪያ የአውራጃ የበላይ ባለሥልጣናት አባል የሆነው ባለቤቴ ከሴት ልጃችን ፓ ሂይ ጋር ብቻዬን ትቶኝ በየሳምንቱ የቤተክርስቲያኑን ሥራ ለመስራት ርቆ ይሄድ በነበረበት ጊዜ . . . ነበር። በእነዚህ የሳምንቱ መጨረሻ ቀናት፣ ቀዳሚ ወደ 270 ማይል (የሰባት ሰዓት ጉዞ) ይጓዝ እና ከዚያም እሁድ ወደ ሲኦል ምስራቅ ቀርንጫፍ ይመለስ ነበር። በጣም አድካሚ ስለነበር በጣም አዘንኩለት።

“ፓ ሂይ ቀዳሚ እና እሁድ ጤነኛ ነበረች፣ ምንም እንኳን በቀዱስ ቁርባን ስብሰባ ጊዜ ብትረብሸኝም ወደ ቤት ከተመለስን በኋላ ጡጦዋን ጠብታ ተኛች። 9፡30 ላይ ማልቀስ ጀመረች። ከሌላው ጊዜ በተለየ በጣም እየጮኸች ታለቅስ ነበር፣ ሳቀፋት ከፍተኛ ትኩሳት እንዳላት ተረዳሁኝ። ምን እንደማደርግ ጠፋኝ። ቤታችን አካባቢ ያለው ብቸኛ ሆስፒታል በዚያ ቀን መዘጋቱን ተረዳሁኝ። ልቅሶዋ ለተወሰነ ጊዜ ቀጠለ፣ በመጨረሻም ባለቤቴ በሩ ላይ ሲገባ፣ እኔም ማልቀስ ጀመርኩኝ።

“ባለቤቴ ልጃችን እና እኔን አቀፈኝ እና ምን እንደሆንን ጠየቀን። ፓ ሂይ በጣም የተሰቃየች ትመስላለች። ምን እንደሆነች ስነግረው ኮቱን እና ሻንጣውን አስቀመጠና ቀብአ ቀዱሱን አወጣ። ከዚያም ልጃችንን ባረከበት። ሁሉንም ቃላት ማስታወስ አልችልም፣ ግን የተለመደውን የበረከት ጸሎት ካለ በኋላ እንዲህ ሲል ቀጠለ፡ የሰማይ አባት ሆይ፣ ስለ ሕይወቴ፣ ስለ ሚስቴ እና ልጄ አመስጋኝ ነኝ። ስለ ተመለሰው ወንጌል እና ለማገልገል ስላገኘሁት ዕድል አመስጋኝ ነኝ። ወደ ፓወሳን እና ወደ ሲኦል ምስራቅ ቀርንጫፍ የቤተክርስቲያኑን ስራ እንድንሰራ ላከኝ። የተሰጠኝን ኃላፊነት ትናንት እና ዛሬ ተወጥቻለሁኝ፣ እና ዛሬ ልጄ ታማ አገኘኋት። በሁሉም ጊዜያት ረድተሀኛል። እባክህን ዛሬም ምሽት እርዳኝ።

“ፀሎቱን ከመጨረሱ በፊት፣ ልጃችን ተኛች፣ እናም ቀና ስል፣ ባለቤቴ አይን ላይ እንባ አየሁኝ።

“ዛሬ ትንሽዋ ልጃችን ሁለተኛ ክፍል ነች፣ እናም ጤነኛ እና ደስተኛ ነች፣ ግን ባለቤቴ ለጌታ እንዲህ ሲል በጸሎቱ “የሰጠኸኝ ኃላፊነት ትናንት እና ዛሬ ተወጥቻለሁኝ።” ብሎ የተናገረውን እስከአሁን በትክክል አስታውሳለሁኝ። ለጌታ ታዛዥ እንደሆነ ሁልጊዜ መናገር እንዲችል እንደምደግፈው ተስፋ አደርጋለሁ። ክህነቱን የሚያከብር ባል ማግኘት እንዴት ያለ

መባረክ ነው!” (“Our Baby, My Husband, and the Priesthood,” *Ensign,* Aug. 1975, p. 65.)

ልዩ የክህነት በረከቶች ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ይገኛሉ። ችግር ያለበት ህፃን ልጅ ልዩ በረከት መጠየቅ ይችላል። ያገባች ወይም ያላገባች መፅናኛ ወይም መመሪያ ከፈለገች ይህን በረከት መጠየቅ ትችላለች። ነገር ግን ተሞኩሯችን ከዚህ ሂደት ሊመጣ እንደሚችል ማስታወስ አለብን። በተቻለን መጠን ልንጥር ይገባናል። ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገን ከሆነ ክህነት ወዳላቸው . . . ባሎቻችን፣ የቤት ለቤት አስተማሪዎቻችን፣ ወይም የክህነት መሪዎች ጋር ሄደን ልዩ የሆነ በረከት እንዲሰጡን መጠየቅ እንችላለን።

እህቶች በክህነት ሥነ ሥርዓቶች ያገኙትን በረከት እንዲናገሩ ይጠይቁአቸው።

## የጌታን ፈቃድ መቀበል

የክህነት ሥነ ሥርዓቶችን ካገኘን በኋላ፣ ወዲያውኑ የፈለግነውን በረከት ልናገኝ አንችል ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ በረከቶችን ላናገኝ እንችላለን፣ ምክንያቱም በጌታ በቂ የሆነ እምነት ላይኖረን ይችላል። ምናልባት ሁሉንም ትዕዛዛት አንጠብቀም ይሆናል። ምናልባት ሊሚላ የማይገባውን በረከት ጠይቀን ሊሆን ይችላል።

በህይወታችን ውስጥ የሚመጡብን ፈተናዎችን በሙሉ ማስወገድ እንችላለን ብለን መገመት አንችልም። አንዳንድ ችግሮቻችን ትሁት፣ ታጋሽ ወይም የሰው ችግር የሚገባን እንድንሆን ያስተምሩናል። ሌሎች ደግሞ ስቃይን እንድንችል ያደርጉናል። ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል አንዳንድ ጊዜ ችግሮች ለምን እንደገጠሙን ሳንረዳ ለማስወገድ እንፈልጋለን፣ ብሎ ነበር። ሁሉም ራስ ወዳድ እና ጥበባዊ ያልሆኑ ፀሎቶች መልስ ካገኙ ትንሽ ወይም ምንም ጉዳት፣ ስቃይ፣ ሐዘን፣ ወይም ሞት ባልነበረ ነበር። ግን ያለ እነሱ ደስታ፣ ስኬታማነት፣ ትንሳኤ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ መልካምነት አይኖርም ነበር። ፕሬዚዳንት ኪምቦል እንዲህ ብሎ ነበር። “ሞትን እንደሁሉም ነገር መጨረሻ የምንቆጥር ከሆነ፣ ስቃይ፣ ሐዘን፣ ውድቀት፣ እና የዕድሚ ማጠር መቀሰፍት ይሆኑብናል። ግን ሕይወትን እንደዘለዓለማዊ ነገር ከህይወት በፊት እና ከሞት በኋላ እንደተዘረጋ የምንቆጥር ከሆነ፣ ሁሉም ነገሮች በተስተካከሉ ቦታቸው ይቀመጡልናል።” (See *Faith Precedes the Miracle,* pp. 97–99.)

እህት ኤድኑ ዖ ኤፍ ሾው ይህን ትምህርት በሚከተለው ልምድ ተምራዋለች፣

“ተወዳጇ ትልቅ ሴት ልጃችን ካሮል ጂን በአበጠ የሊንፍ እጢ ታመመች። ወደ ዶክተር ወሰድናት፣ እሱም ለምርመራ ወደ ሶልት ሌክ ሲቲ ላከን። የጨጓራ ቲዩመር እንደያዛት ተረዳን። ምግብ በአፏ መውረድ አይችልም ነበር። ወደቤት ወስደናት ነበር፣ ግን በጣም ስለታመመችብን ወደ ሆስፒታል ልንመልሳት ተገደድን። ያኔ ነበር ሳርኮማ ማለትም የሉኪምያ አይነት በሽታ እንደያዛት የተነገረን።

“እንደዚያ ጊዜ በህይወቴ በጣም ፀልዬ አላውቅም። እንዲህ አይነት ነገር እኛ ላይ መድረሱን ማመን ይከብደኛል። ሆስፒታል ሳለች ቁሶች ብዙ ጊዜ ባርከዋታል። ግን ምንም ብንጥርም ሞተች።

“እራሴን ወቀስኩኝ፣ በህይወት ትኖራለች የሚል በቂ እምነት አልነበረኝም የሚል ሐሳብ ይመጣብኛል። ከዚያም ወደ ቅዱስ ጽሁፎች ተመለስኩኝ። ሳነብ በትምህርት እና ቃልኪዳን

የረዱኝ ብቁ ጥቅሶች አገኘሁ።” (“If Appointed unto Death,” *Ensign,* Dec. 1972, p. 32.)

ት እና ቃ 42፥44፤ 46፤ 48 ያንብቡ።

ለምንድነው የታመሙት ሁሉ የማይድኑት?

ሁሉም የክህነት በረከቶች ስንፈልጋቸው አይሟሉም። አንዲት ሴት ወደ ጳጳስ ቫን ጀ ፌዘርስቶን የኤጲስ ቆጶስ የበላይ አመራር በነበረበት ጊዜ መጣች። አብዛኛው የክህነት በረከቶችዋ እንዳልተሟሉላት በወቀሳ ገለፀች። እስከአሁን ጊዜ ድረስ ጤንነቷ ደካማ ነው እንዲሁም ልጅ መውለድ አትችልም። ጳጳስ ፌዘርስቶን በጌታ ሥራ ላይ የጊዜ ገደብ ማስቀመጧን ነገራት። እነዚህ በረከቶች በአምስት ዓመት ጋብቻ ጊዜያት ውስጥ ባለመገኘታቸው፤ አዘነች። እንዲህ ሲል ነገራት፣ “ቃል እገባልሻለሁ፤ ልክ በሰማይ እንዳለው እግዚአብሔር እርግጠኛ ሆኜ በጻድቃን ባለክህነቶች የተገባልሽ ቃል በህይወትሽ ይፈፀማል።” በረከቶቹ የሚፈፀሙበት ትክክለኛ ጊዜ እስከ አሁን አልደረሰም። ኢዮብ እንዳደረገው በጌታ መተማመን አለብን። (See “Acres of Diamonds,” *BYU Speeches of the Year,* 1974, pp. 346–49.)

በክህነት ሥነ ሥርዓቶች አማካኝነት ድህነት እና ዘለዓለማዊ ሕይወት ማግኘት እንችላለን። መመሪያ እና መጽናናኛን ማግኘት እንችላለን፤ ከአደጋ ልንጠበቅ እንችላለን፤ እናም ከህመም ልንፈወስ እንችላለን። እነዚህን ሥነ ሥርዓቶች ለማግኘት መዘጋጀት ያስፈልገናል።

**ሙከራ**

ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ልታገኙት በምትችሉት የክህነት ሥነ ሥርዓቶች ላይ ተወያዩ። እነዚህን ሥነ ሥርዓቶችን ለመቀበል ተዘጋጁ።

**ተጨማሪ ጥቅሶች**

3ኛ ኔፊ 17 (ለዳኞችን ህሙማንን ሲፈወስ እና ህፃናት ልጆችን ሲባርክ)

---

**የመምህር ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. *የወንጌል መሰረቶች፤* ምዕራፍ 14 “የክህነት ድርጅት፤” እና *የክህነት መሪዎች መመሪያ መጽሐፍ* ያጥኑ።
2. *የቤተሰብ መመሪያ መጽሐፍ* ያንብቡ።
3. ጥቁር ሰሌዳ እና ጠመኔ ያዘጋጁ ወይም የክህነት ሥነ-ሥርዓቶችን የሚያሳይ ፖስተር ያዘጋጁ።
4. በዚህ ትምህርት ውስጥ ታሪኮችን እና ቅዱስ ጽሑፎችን እንዲያቀርቡ የክፍሉ ተማሪዎችን ይመድቡ።

# ሴቶች እና የክህነት ሥልጣን

ትምህርት 13

የዚህ ትምህርት ዓላማ ከክህነት ስልጣን ጋር ያለንን ግንኙነት እንድንገነዘብ ለመርዳት ነው።

## የክህነት ሥልጣን ለሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላት ይጠቀማል

"(የክህነት ስልጣን . . .) የሰው ልጅ ቤተሰብ በምድር ላይ ለደህንነቱ የሚሰራበት ለሰው የተሰጠ የእግዚአብሔር ኃይል ነው።" (Joseph F. Smith, *Gospel Doctrine,* p. 139.) ጌታ የቤተክርስቲያኑ ሥራዎችን እና ቤተሰብን የማዘዝ እና የመቆጣጠሩን ዋና ኃላፊነቶች ወንዶችን መድቦአል። ይህን የተቀደሰ ኃይል በተራቸው ለቤተክርስቲያኑ አባላት ወንዶች፣ ሴቶች እና ልጆችን ለመባረክና ለመጥቀም ይጠቀሙበታል። ፕሬዚዳንት ብሪግሀም ያንግ እንዲህ ብሎ ነበር፥

"ክህነት ለሁሉም የሰው ልጅ ቤተሰብ ጥቀም፣ ለወንዶች፣ ለሴቶች እና ልጆች በተመሳሳይ ሁኔታ ለመገንባት መጠቀም አለብን። እውነተኛው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተለየ መብት ያላቸው መደብ ወይም ፆታ የለም . . . ወንዶች ሥራቸውን መሥራት እና ኃይላቸውን ለሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላት ጥቀም ማዋል አለባቸው . . .

"ሴቶችም እንዲሁ ማድረግ አለባቸው። የእሷ ልዩ ስጦታዎች ለሰው ዘር ጥቀም እና ዕድገት መገልገል አለባት።" (John A. Widtsoe, *Priesthood and Chuch Government,* pp. 92–93.)

ወንዶች እና ሴቶች በቤት እና በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ግን እኩል የሆነ ኃላፊነት አላቸው። የክህነት ኃይል እያንዳንዳቸው ለሁሉም ጥቀም ኃላፊነት እንዲጠቀሙ ሊረዳቸው ይችላል።

ዛሬ የክህነት ኃይል ምድር ላይ በመኖሩ ምክንያት፣ ለሁሉም ብቁ የቤተክርስቲያኑ አባላት ሽማግሌ ሆኑ ወጣት፣ ወንድ ወይም ሴት፣ ያላገቡም ሆነ ያገቡ ታላቅ በረከት አምጥቶላቸዋል።

አንዲት ያላገባች ሴት ክህነትን ለማክበር ምን ማድረግ ትችላለች?

አብዛኛዎቹ ልዩ መብት እና በረከቶች በዚህ መመሪያ መፅሐፍ ትምህርት 12 ላይ ተገልጸዋል።

ቄስ ጆን ኤ ዊድስ ሌሎች የክህነት ጥቀሞችን ይገልጽልናል፥

ወንዶች ከክህነት የሚመጡ በረከቶች እና የተያያዙ ጥቀሞች ላይ ከሴቶች የበለጠ መብት የላቸውም።

" . . . ወንድ ክህነትን ይይዛል፣ የቤተክርስቲያኑ የክህነት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ግን ሚስቱ ከክህነት ባለቤትነት የሚመጡ ሌሎች ልዩ መብቶች ከባልዋ ጋር ተጠቃሚ ነች። ለምሳሌ ያህል በቤተክርስቲያኑ የቤተመቀደስ አገልግሎት ግልፅ ሊሆን ይችላል። የቤተመቀደስ ሥነ

ሥርዓቶች በተለይ የክህነት ፀባይ አላቸው፣ ግን ሴቶች ሁሉንም የመጠቀም መብት አላቸው፣ እናም የቤተመቅደስ ከፍተኛው በረከት ለወንድ ከሚስቱ ጋር ብቻ የሚሰጥ ነው።” (*Priesthood and Church Government*, p. 83.)

ስለ ክህነት የአጋርነት ሚና እና ሴቶች በቁስ ብሩስ አር መኮንኪ ተገልጸዋል፥

“በእውነተኛ ፓትሪያርካል ትዕዛዝ ወንድ ክህነት ይይዛል እንዲሁም የቤተሰቡ ራስ ይሆናል፣... ግን ብቻውን እዚህ ወይም በዘለዓለማዊ ሽልማት ሙሉ ደስታ ሊያገኝ አይችልም። ሴትዋ የሁሉም ነገር ተካፋይ ሆና በጎኑ ትቆማለች። ዘለዓለማዊ ህይወት እና ዘለዓለማዊ ዕድገት የእሷም የእሱም ድርሻ ነው። (ት እና ቃ 131፥1–4) መለኮታዊነት ለወንዶች ብቻ አይደለም፣ ለወንዶች እና ለሴቶች በአንድነት ነው። (ት እና ቃ 132፥19–20።)” (Bruce R. McConkie, *Mormon Doctrine*, p. 844.)

በክህነት አማካኝነት ምን ዓይነት በረከቶች አግኝታችኋል?

## እያንዳንዱ አባል ክህነትን ማክበር እና መደገፍ አለበት

ልክ እያንዳንዱ በቤተክርስቲያኑ ከክህነት እንደሚጠቀም ሁሉ፣ ክህነትን የማክበር እና የመደገፍ ኃላፊነት አለበት። ባለክህነቶች በተደጋጋሚ የሚከተለውን ማስታወስ አለባቸው፥ “የክህነት መብት ከመንግስተ ሰማያት ኃይል ጋር የሚነጣጠል አይደለም፣ እናም የመንግስተ ሰማያት ኃይል ደግሞ በፅድቅ ኃይል በቀር መቆጣጠርም፣ መያዝም አይቻልም” (ት እና ቃ 121፥36) በተመሳሳይ ሴቶች፣ ክህነቱን እንዲያከብሩ፣ ለኃይሉ አመስጋኝ እንዲሆኑ፣ ክህነቱን ለያዙት አክብሮት እንዲያሳዩ ተመክረዋል። በተጨማሪ፣ ክህነትን የመደገፍ ኃላፊነት አለብን፣ መደገፍ ማለት “ፍላጎትን ወይም ምክንያቱን ማበረታታት፣ ጠቃሚነቱን ወይም ትክክለኛነቱን መደገፍ ወይም መንከባከብ ማለት ነው” (*Webster’s New Collegiate Dictionary*, 1973, ed.)።

ክህነትን የምናከብርበት እና የምንደግፍበት አንዳንድ መንገዶች በሚከተለው ጥቀሶች ተገልጿል፥።

የሚከተሉት የቅዱስ ጽሑፎችን ማጣቀሻዎች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉ። እያንዳንዱ ጥቅስ ሲነበብ፣ እህቶች ክህነትን ለማክበር እንዲችሉ የተሰጡትን ሐሳቦች እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው። በእያንዳንዱ ማጣቀሻ በተጨማሪ፣ የተሰጡትን ሐሳቦች ይፃፉ፥

1. ት እና ቃ 19፥23 ተማሩ፣ አዳምጡ፣ ለመማር ዝግጁ ሁኑ
2. ት እና ቃ 33 አስተዋይ ሁኑ፣ ዘወትር ፀልዩ
3. ት እና ቃ 58፥26–27 በጥሩ ምግባር ላይ ለመሳተፍ ይጓጉ
4. ት እና ቃ 64፥33–34 መልካም ነገር ላለማድረግ አትድከሙ

## ሴት በቤት ውስጥ ከክህነት መሪ ጋር ያላት ዝምድና

በቤት ውስጥ የመቆጣጠር እና የመምራት ኃላፊነት የባል ነው። የቀርብ ጊዜ የመልከጼዴቀ ትምህርት ቡድን በጥናት ኮርስ እንዲህ ሲል ይገልፃል።

“በወንጌል አንፃር መሪነት፣ ማለት ረግጦ የመግዛት፣ የመምራት፣ እና የማዘዝ መብት ማለት አይደለም። በተቃራኒው፣ መምራት፣ መከታ መሆን መንገድን መጠቀም፣ ጥሩ ምሳሌ መሆን፣ ማረጋጋት፣ ማነቃቃት፣ እና ለመደገፍ እና ለመከተል ፍላጎት እንዲያድር ማድረግ ማለት ነው። ማጠቃለያ፣ መንገዱን የሚመራው ባልየው ነው ...

“ጥበበኛ መሪ ... ሁልጊዜ ጥሩ ምክር ከሚሰጡ ሰዎች መልካም ምክር ይጠይቃል። ልክ ቤተሰቡ በባል እና ሚስት እንደሚዋቀር ሁሉ፣ ባልየው ሚስቱን እንደ ጓደኛ ምክር

ሊጠይቃት ይገባል። አንድ ቤተሰብ የሚገነባ ከሆነ፣ እነሱ ከጌታ መንፈስ ጋር ሆነው የሚገነቡት በአንድነት ነው። ምንም እንኳን ክህነቱን የያዘው ባልየው ቢሆንም ይህንን ብቻውን አያደርገውም” (*The Savior, the Priesthood and You,* 1973–74 Course of Study, p. 172)።

ባል እና ሚስት በመንፈስ መገለጥ ከተማከሩ በኋላ፣ የክህነት ኃይሉ ከሰማይ ቤቱን ለመባረክ ጥበብን እና መረዳትን እንደሚያመጣ ማረጋገጥ የባልየው ነው። ሚስት እና ልጆች ውሳኔዎችን በሙሉ ልብ ዓላማውን መደገፍ አለባቸው። በዚህ መንገድ የባልየው የቤት ራስነት ይጠናከራል፣ እንዲሁም ታላቅ የቤተሰብ ውህደት ይፈጠራል።

በተጨማሪም ባሎቻችንን እንደ ክህነት ያዥነታቸው በጨዋነት፣ በርህራሄ፣ እና ፍቅር እንደሚይዙን እነሱንም እደዚሁ በመያዝ ክህነትን ማክበር እንችላለን። ነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ የሴቶች መረዳጃ ማኅበርን እንዲህ ሲል መክረዋል፥ “ሴቶች ለባሎቻቸው ምን ዓይነት ፀባይ ማሳየት እንዳለባቸው፣ በርህራሔ እና በፍቅር እንዲይዟቸው አስተምሯቸዋል። ወንድ ችግር ሸክም ሲሆንበት፣ በሐሳብ እና በችግር በተደናገረበት ጊዜ፣ ከጭቅጭቅ እና ማጉረምረም ይልቅ ፈገግታ ከገጠመው፣ ርህራሔ ከገጠመው፣ ነፍሱን ያረጋጋዋል፣ ስሜቱን ያበርደዋል፣ አዕምሮ ተስፋ ሲቆርጥ፣ የፍቅር እና ርህራሔ ማፅናኛ ይፈልጋል።” (*History of the Church,* 4:606–7.)

በቤት ውስጥ እምነት እና አንድነት ሊኖር የሚችለው ሁለቱም ባል እና ሚስት አንዱ የሌላውን ፍላጎት እና ደስታ በቁምነገር ሲፈልጉ ነው፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ሁለቱም በህብረታቸው ደስታ ይኖራቸዋል፣ እንዲሁም እያንዳንዳቸው ያሰቡት የመሳካት እድል ይገጥማቸዋል፡፡

ለነብዩ ዮሴፍ ሚስት ኤማ ስሚዝ በተሰጠ ራዕይ ላይ፣ ሚስት በክህነት ላይ ያላት ሚና እና ዝምድና ተገልጿል፡፡ ጌታ እንዲህ አላት፥

“አንቺ የተመረጥሽ ነሽ፣ ጠርቼሻለሁኝ—

“የጥሪሽ ሐላፊነት አገልጋይ፣ ዮሴፍ ስሚዝ ትንሹ፣ ባልሽን በመከራው ጊዜ በአጽናኝ ቃላት አጽናኝ እንድትሆኚ ነው . . .

“በታዛዥነት መንፈስ ቀጥይ፣ እናም ከኩራት ተጠንቀቂ፡፡ ነፍስሽ በባልሽ እና ከእርሱ በሚመጣው ክብር ደስ ትሰኝ፡፡

“ኤማ ለባልዋ ምን እንድታደርግ ነበር የታዘዘቸው?

ዛሬ የዚህ ተመሳሳይ ምክር በመከተል የሚመጡ በረከቶች ምንድናቸው?

## ለካህናት በቤት ውስጥ የሚደረግ ድጋፍ

በቤተክርስቲያኑ እንደ ሴትነታችን፣ በቤታችን ውስጥ ክህነት ባላቸው ላይ ታላቅ ተጽእኖ ሊኖረን ይችላል። የባላችንን ወይም የአባታችንን ውሳኔ ስንደግፍ፣ ክህነትን ለያዙት እና ለቤተሰባችን ጥንካሬን እናሳያለን፡፡ ከባላችን ወይም አባታችን በረከትን ከጠየቅን እና በረከቱን ካከበርን፣ ለክህነት ያለንን ድጋፍ እናሳያለን። በተጨማሪም በቤት ውስጥ ክህነትን በፀሎታችን በማካተት ማጠንከር እንችላለን። ዮሴፍ ስሚዝ የቤተክርስቲያኑ ሴቶች “እምነታቸው እና ፀሎታቸው በባሎቻቸው እንዲያተኩር፣ እና በባሎቻቸው እምነት እንዲያሳድሩ . . . በፀሎታቸው እንዲያስታጥቋቸው እና እንዲደግፉዋቸው” መክረዋል (*History of the Church,* 4:604–5)።

በቀጣይነት ፀባያችንን ፍፁም ለማድረግ እና ኃላፊነታችንን ለመወጣት መስራት አለብን። በተጨማሪም ባሎቻችን እና ወንዶች ልጆቻችንን የክህነት ጥሪያቸውን እንዲያከብሩ እና እንዲያጎሉ ማበረታታት እና ማስታወስ ይገባናል። ወጣት ሴቶች እንዲሁም እናቶች፣ ወጣት ወንዶችን ስብሰባ እንዲሳተፉ እና በወንጌላዊነት ለማገልገል እንዲዘጋጁ በማበረታታት ብዙ መስራት ይችላሉ። ቄስ ዴቪድ ቢ ሐት የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ሸንጎ እንዲህ ብሎ ነበር፣ “እናንተ ወጣት ሴቶች ጥልቀ የሆነ ተፅዕኖ በወጣት፣ ወንዶች ላይ አላችሁ . . . በወጣት ወንዶች ያላችሁ ተፅዕኖ ጠቃሚ ነው። የቤተክርስቲያኑ ሥነ ሥርዓት እና አለባበስ እንዲሁም ጸባይ ታበረታታላችሁ።” (“Young Women—Real Guardians,” *Ensign,* Nov. 1977, pp. 56–57.)

አንዲት ሴት ባልዋ በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለው ኃላፊነት በጎ አስተሳሰብ ካላት፣ እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት ቀላል ያደርግላታል። አስተሳሰብዋ በቤት ውስጥ ክህነት ላላቸው ልጆቻቸው ታላቀ በረከት ያስተላልፋል።

አንዲት ሴት ባልዋን በክህነት ሥራው ለመደገፍ ተችል ዘንድ የዕለት ተዕለት ሥራዋን እንዴት ማደራጀት ትችላለች?

## ሴት በቤተክርስቲያን ውስጥ ከካህናት ጋር ያላት ዝምድና

ልክ አንዲት ሴት በቤተዋ ውስጥ ክህነት ያላቸው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማድረግ እንደምትችል ሁሉ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የቀርንጫፉን፣ ወይም የዋርድ እና የአውራጃ ወይም የስቴክ መሪዎችን በመደገፍ ቤተክርስቲያኑን ማጠንከር ትችላለች። የክህነት ጥሪ የእግዚአብሄር ጥሪ መሆኑን በመገንዘብ የቤተክርስቲያን ጥሪን በፈቃደኝነት ስንቀበል እና በታማኝነት ስንፈፅም መሪዎቻችንን የክህነት መሪዎቻችንን እንደግፋለን ባሎቻችንን፣ የቤት ለቤት አስተማሪዎችን፣ የጳጳሶች ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቶችን፣ የስቴክ ወይም የአውራጃ መሪዎችን፣ እና የበላይ ባለስልጣኖችን ምክር ማክበር እንችላለን። የክህነት መሪዎችን ከመውቀስ መቆጠብ አለብን፣ እንዲሁም ልጆቻችን እንዲሁ እንዲያደርጉ ማስተማር አለብን። ካህናትን መደገፍ እና ማገዝ ከአፍ ሥራ እና እጁን ከማውጣት የላቀ ነው። ለበጎ ነገር መማርን፣ መፀለይን፣ መታዘዝን፣ እና ማገልገልን ይመለከታል።

ጌታ የምንከተለውን መንገድ እንድናውቀ የክህነት መሪዎችን አዘጋጅቶልናል። ኃላፊነታችንም፣ ምክሮቹ ከጌታ ልክ እንደመጡ ማዳመጥ እና መታዘዝ ነው።

“በማንኛውም ጊዜ እነርሱ (የክህነት መሪዎች) በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው በተናገሩ ጊዜ . . .ቅዱስ መጽሐፍ፣ የጌታ ፈቃድ የጌታ ቃል . . . እና የእግዚአብሔር ኃይል ለደህንነት ይሆናሉ” (ት እና ቃ 68፥4)።

ፕሬዚዳንት ሐሮልድ ቢ ሊ የአስራሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ የክህነት መሪዎችን በተለይም ነብዩን ስለመደገፍ በተመለከተ የሚከተለውን ምክር ሰጥተው ነበር፣

“ጌታ በነቢያቱ አማካኝነት ለሚሰጣችሁ ቃላት እና ትዕዛዛት ቦታ መስጠትን መማር አለባችሁ፣ ስትቀበሏቸው በፊቴ በቀድስና ተራመዳላችሁ ልክ እንደ እኔ አፍ በታላቅ ትዕግስት እና እምነት (ት እና ቃ 21፥4-5) ትዕግስትን እና እምነትን የሚጠይቁ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ከቤተክርስቲያኑ ባለስልጣን የሚመጡ ነገሮችን አትወዱት ይሆናል። ከፖለቲካዊ አስተሳሰባችሁ ጋር ይጋጭ ይሆናል። ከማህበራዊ ጉዳያችሁ ጋር ይቃረን ይሆናል። ግን በትዕግስት እና በእምነት ከጌታ አፍ እንደመጡ ከሰማናቸው ቃል የተገባልን “የሲኦል በር

በእናንተ ኃይል እንደሌለው ቃል ነው፣ አዎ፣ እናም ጌታ የጨለማን ኃይል ከእናንተ ፊት ይበትነዋል፣ እናም ሰማይ ለእናንተ መልካም እና ለስሙ ክብር እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል።" (ት እና ቃ 21፥6)" (In Conference Report, Oct. 1970, p. 152; or *Improvement Era,* Dec. 1970, p. 126.)

## ማጠቃለያ

ክህነት ከእግዚአብሔር ለልጆቹ የተሰጠ ታላቀ በረከት ነው። በወንጌል ዕቅድ መሰረት ወንዶች እና ሴቶች እያንዳንዳቸው በእዚህ እና ከዚህ በኋላ በዘለዓለማዊ ሕይወት ለደስታ አስፈላጊ የሆነ መሰረታዊ ኃላፊነት ተሰጥቶዋቸዋል። ሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላት ክህነትን ማክበር እና የክርስቶስን የመሰለ ዝምድና በቤት ውስጥ እና በቤተክርስቲያን ማዳበር አለባቸው። እነዚህን ፀባዮችን ለማዳበር የሚጥሩ ሴቶች ለባለክህነቶች ጥንካሬ እና ለቤተሰባቸው እና ለቤተክርስቲያኑ በረከት ሊሆኑ ይችላሉ። የሴቶች ደስታ እና ተፅዕኖ የክህነት መሪዎቻቸውን መታዘዝን እና መከተልን በተማሩ ቁጥር እየተሻሻለ እና እያደገ ይመጣል።

## ሙከራ

ይህን ትምህርት በቤተሰባችሁ ውስጥ ያላችሁን የክህነት ሚና ግንዛቤያችሁን ለማሳደግ ተጠቀሙ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

1 ቆሮንቶስ 11፥3፤ 8–12 (የወንድ እና ሴት ግንኙነት)
ቆላስያስ 3፥18–24 (እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ)
1ኛ ጴጥሮስ 3፥5–7 (እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ)

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. የክፍሉ ተማሪዎች ቅዱሳን መጽሐፍታቸውን እንዲያመጡ ያስታውሱአቸው።
2. ጥቁር ሰሌዳ እና ጠመኔ ያዘጋጁ።
3. በዚህ ትምህርት ውስጥ የክፍሉ ተማሪዎች ታሪኮችን እና ቅዱስ ፅሑፎችን እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

# የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሴት

ትምህርት 14

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ እንደ ኋለኛው ቀን ቅዱሳን ያለንን ኃላፊነቶች እና በረከቶች እንድንገነዘብ ለመርዳት ነው።

---

**መግቢያ**

ፕሬዚዳንት ብሪግሀም ያንግ የሴቶችን ሚና እንደሚከተለው ገልፆታል፥

"አንድ ነገር በጣም እውነት ነው እንዲሁም እናምንበታለን፣ ይኸውም ሴት የወንድ ክብር መሆንዋ ነው . . .

"ስለ እናቶቻችን እና እህቶቻችን የተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት፣ እንዲሁም ስለአላቸው ተፅዕኖ ሳስብ፣ የእኛ እዚህ የመሆን ምክንያት እና መሰረት እንደሆኑ ይሰማኛል። ወንድ የመጀመሪያ እንደሆነ እውነት ነው . . . እናታችን ሔዋን ስትመጣ ግን በአባታችን አዳም ላይ አስደናቂ የሆነ ተፅዕኖ ነበራት . . .

"(እህቶች፣) መንግስቱን በመገንባት የእናንተን ተፅዕኖ እና ኃይል እንፈልጋለን።" (*Discourses of Brigham Young,* p. 199.)

**የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሚስት ኃላፊነት እና በረከት**

እንደ የቤተክርስቲያን አባልነታችን፣ የባል እና ሚስት ግንኙነት ተስማሚነት እንገነዘባለን። "አዳዲስ እህቶች አባል ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ያዩት ታላቅ ለውጥ ምን እንደሆነ ቢጠይቁአቸው፣ ስለቤታቸው፣ ስለ ባላቸው፣ እና ስለልጆቻቸው ያላቸው አዲስ አመለካከት እንደሆነ ይመልሱላችኋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች አስተሳሰባቸውን የመቀየር ችግር ነበረባቸው፣ ግን ሁሉም እርስ በርሳቸው መከባበርን እና ወንዱን እንደ ቤታቸው ፓትሪያርክ መደገፍን የመማሩን ጠቃሚነት ዋጋ ይሰጡታል።" (Anna Lindback, quoted by Carol Larsen in "The Gospel Counterculture," *Ensign,* Mar. 1977, p. 26.)

አንዲት የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሚስት፣ ባልዋ አባል ሆነ አልሆነ፣ ተሳትፎ የሚያደርግ ወይም የማያደርግ፣ ቢሆንም ተጓዳኝ እና አጋር መሆን ትችላለች።

ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር፣ የዘመናችን ነብይ አማካሪ፣ እንዲህ ብሎ ነበር፥ "ሴቶች፣ እናንተ በህይወት ላሉት ወንዶች ታላቅ ጥንካሬ እና ድጋፍ ናችሁ፣ እናም አንዳንድ ጊዜ ያን ያህል የሚገባቸውም ባይሆኑም የእናንተ ዕርዳታን ይፈልጋሉ። አንድ ወንድ ሚስቱ በእርሱ ላይ እምነት እንዳላት እና እንደምትወደው እንደማወቀ የመሰለ ታላቅ ማበረታቻ፣ ታላቅ ተስፋ፣ ታላቅ ጥንካሬ ሊኖረው አይችልም።" ("No Greater Honor: The Woman's Role," *Ensign,* Jan. 1974, p. 8.)

---

ባሎቻችን እንደምንወዳቸው እና በእነርሱ እንደምንተማመን እንዴት ልንገልፅላቸው እንችላለን? ለምንድነው ምንም እንኳን ያን ያህል የሚገባቸው እንዳልሆኑ ብናስብም ለባሎቻችን መግለፅ ያለብን?

ከእያንዳንዱ መልካም ወንድ በስተጀርባ አንዲት መልካም ሴት አለች ይባላል። በቤተክርስቲያኑ፣ አንድ ወንድ ለአንድ ኃላፊነት ሲታሰብ የሚስቱ ብቁነት ለውይይት ይቀርባል። ሙሉ ድጋፏን ልትሰጠው መቻል ይገባታል። ልቧ በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ ሳይሆን፣ በዘለዓለማዊ ሕይወት ላይ ማተኮር አለበት። እናም በባሏ ጎን መቆም እና መደገፍ ትችላለች። (ካህናትን የመደገፊያ መንገድ ለማወቀ፣ ትምህርት 13 በዚህ መምሪያ መጽሐፍ ተመልከቱ።)

አንዳንዶቻችን አባል ያልሆኑ ወይም ተሳትፎ የሚያደርጉ አባላት አግብተን ይሆናል። ባሎቻችን ተሳትፎ ባለማድረጋቸው ተስፋ እንቆርጥ ይሆናል። ተአምር ሊመስለን ይችላል፣ ትዕግስት እና እምነት የምታሳይ ሚስት አንድ ቀን ይህን ተአምር ታያለች። አንዳንድ ወንዶች ብዙ ዓመት ሊወስድባቸው ይችላል፣ ግን አሁንም መፀለይ እና የወንጌል ትምህርቶችን በቤታችን በክብር መቀጠል ይገባናል።

“ማርሊዝ ዴ ዶልደር ከላፕላታ ሁለተኛ ዋርድ የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለች የቤተክርስቲያኑ አባል ሆና ነበር። ሁልጊዜ በቤተክርስቲያን የምትሳተፍ እና የተለያዩ የቤተክርስቲያን ኃላፊነቶችን የያዘች ነበረች። የቤተክርስቲያኑ አባል ያልሆነ በጣም ጥሩ ወጣት ወንድ አገባች፣ ግን በቤትዋ ውስጥ የወንጌልን ምክር እና ትምህርት ሁሉንም ተግባር ላይ ለማዋል ጥበብን ትሻ ነበር። ይህንን ተሞኩሮ “ሚዛናዊነትን መፈለግ” ብላዋለች። እራሷን በፍላጎት እና በፍቅር ለቤቷ፣ ለባሏ፣ እና ለልጆቿ ሰውታለች። ከቤተክርስቲያን ስብሰባዎች በኋላ ከጓደኞቿ ጋር በመነጋገር ለመዝናናት አትቆይም፣ ግን በፍጥነት ወደቤቷ ግዴታዋን ለመወጣት ትሄዳለች።

“ዛሬ ባለቤቷ በቤተክርስቲያን ለሁለት ዓመት አባል ሆኗል፣ እንዲሁም በላፕላታ ሁለተኛ ዋርድ ጳጳስ ሆኖ ማገልገል ጀምሯዋል።” (Carol Larsen, “The Gospel Counterculture,” *Ensign,* Mar. 1977, p. 27.)

እህት ዴ ደልደር ለባልዋ ያላትን ኃላፊነት ለመወጣት እና በቤተክርስቲያኑ ተሳትፎ ለማድረግ ምን አደረገች?

“ጨዋ፣ ትሁት ሰው የሆነ አንድ አባት፣ ለቤተሰቦቹ ፍቅሩን መግለፅ አዳጋች ሆኖ አገኘው። በሚስቱ አነሳሽነት የቤተሰብ ፀሎት ጀመሩ፣ እናም በልቡ ያለውን የመግለፅ አጋጣሚ አገኘ። በተሳሳተ ግምት አባቷን ግንዛቤ የለሽ አድርጋ የገመተችው ሴት ልጃቸው፣ ይህ ተሞኩሮ ራዕይ ነበር የሆነበት። ፀሎቱ ቀላል እና የተዘበራረቀ ቃላት ነበር የሚወጣው፣ ግን “ውድ ሴት ልጄን መልካም ነገር እንድታደርግ ባርክልኝ” ሲል መስማቱ ብቻ ያስደስታት ጀመር።” (Ann H. Banks, “The Extra Blessings of Family Prayer,” *Ensign,* Jan. 1976, p. 37.)

ባሎቻችን በቤታችን መንፈሳዊ መሪዎች እንደሆኑ ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን?

ባሎቻችንን መርዳት የምንጀምርበት አንዱ መንገድ በቤተሰብ ምሽት ላይ የቤተሰብ ዝግጅት ማዘጋጀት ነው። ልጆቻችን የወንጌል ታሪክ ለቤተሰቡ እንዲያቀርቡ መርዳት፣ ባሎቻችን እንዲሳተፉ መጋበዝ እንችላለን። ቀስ በቀስ፣ የቤተሰብ ምሽት እንዲመሩ እና ከዚያም ትምህርቶችን እንዲያስተምሩ ማበረታታት እንችላለን። ብዙ ወንዶች ከቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ይልቅ የቤተሰብ ምሽት ላይ የተሻለ ምቾት ይሰማቸዋል። አንዴ በቤት ውስጥ መሰብሰብ ከለመዱ፣ ቤተክርስቲያን ውስጥም መሳተፍ ቀላል ይሆንላቸዋል።

እንደ ኋ. ቀ. ቀ. ሚስትነታችን፣ ታጋሽነታችን እና ደስተኛነታችንን በመጨመር በቤት ውስጥ መንፈሳዊ ስሜትን መፍጠር አለብን። ጥሩ የሆነ የቤተሰብ ግንኙነትን ለማዳበር መሥራት ይገባናል። ሁሌም እምነታችንን ተግባር ላይ ማዋል እና ወንጌልን ማክበር ይገባናል።

ሮሜ 15፥1–5 ያንብቡ። ታጋሽነት የሚስትነታችን ሚና የሆነው ለምንድነው?

## የኋ. ቀ. ቀ. እናት ኃላፊነት እና በረከት

የተጋቡ ብቃት ያላቸው ወንድ እና ሴት የእግዚአብሔርን የመንፈስ ልጆች ወደ ምድራዊ ሕይወት የማምጣት ኃላፊነት አለባቸው። ይህን በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን እንፈጥራለን። ለመንፈሳዊ ልጆቹ፣ ለመንፈሳዊ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን አካል እናዘጋጃለን። ስለዚህ፣ ልጆች መውለድን እምቢ ማለት እና ወደኋላ ማለት የግድፈት ኃጢያትን መፈፀም ነው። (See Spencer W. Kimball, *The Miracle of Forgiveness,* p. 97.)

ስዕል 14-ሀ፣ አንዲት እናት ከቤተሰቦቿ ጋር ስብሰባ ስትሳተፍ፣ የሚለውን አሳዩአቸው።

እህቶች ለልጆቻቸው ያላቸውን ኃላፊነት ለማስተማር፣ የሚከተሉትን ጥቀሶች በሰሌዳ ላይ ይጻፉአቸው፥ ት እና ቃ 20፥70፣ ት እና ቃ 68፥25–28፣ ሞዛያ 4፥14–15። እነዚህን ቅዱስ ጽሑፎችን ጮክ ብለው እንዲያነቡ ይጠይቁአቸው። የተጠቀሱትን አንዳንድ ኃላፊነቶችን በሰሌዳው ላይ ይጻፉ። (ስለ ወላጅነታችን ኃላፊነት መወጣት ተጨማሪ መረጃ በዚህ መመሪያ መፅሐፍ በሌሎች ትምህርቶች ውስጥ ተሰጥተዋል።)

ሴቶች የመንፈስ ልጆችን ወደ ምድር የማምጣት መለኮታዊ ዕቀድ ከመርዳት "በጌታ ፊት በታማኝነት እንዲመላለሱ" ከማስተማር የበለጠ ታላቀ ክብር ሊኖራቸው አይችልም። አንዲት ሴት ጥበበኛ እና ብቁ እናት በመሆን እና ጥሩ ልጆች በማሳደግ እርካታ እና ደስታን ታገኛለች። ይህ ለሰው ልጅ ከማንኛውም ሌላ ሙያ ይልቀ ታላቀ አስተዋፅኦ ነው። (See N. Eldon Tanner, "No Greater Honor: The Woman's Role," *Ensign,* Jan. 1974, p. 10.)

አባቶች በዕለት ተዕለት ሥራ ምክንያት ከቤት ስለሚለዩ፣ እናቶች እንደሚያደርጉት ያህል በልጆቻቸው ላይ ተፅዕኖ የማድረግ እድሉ የላቸውም። እናቶች ከአባቶች የላቀ የእያንዳንዱን ልጅ ሕይወት የመቀረፅ ኃይል የያዙ ይመስላል። (See *Gospel Standards,* p. 152.) ለዚህ ነው ለእናቶች ቤት ሆነው ልጆቻቸውን እራሳቸው መንከባከባቸው ጠቃሚ የሆነው። በሌሎች እንክብካቤ ሥር ሊተዋቸው አይገባም። መሪዎቻችን እናቶች በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከቤት ወጪ እንዳይሰሩ ጠይቀዋል።

"ምንም እንኳን እናቶች የባላቸው ደመወዝ በቂ ባለመሆን ምክንያት፣ ወይም ባላቸው በመሞቱ ምክንያት ሥራ መስራት ቢገባቸውም በቤት ውስጥ ማድረግ ያለባቸውን እንክብካቤ እና ኃላፊነት፣ በተለይ ልጆችን በማስተማሩ ቸል ማለት የለባቸውም።" (Harold B. Lee, "Maintain Your Place as a Woman," *Ensign,* Feb. 1972, p. 52.)

ሴቶች ቤተሰባቸውን ለመንከባከብ ብቻቸውን የተተው፣ ወይም ባሎቻቸው ተተዋቸው ቤተሰባቸውን ብቻቸውን ያሳደጉ፣ ከክህነት መሪዎች ልዩ እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው። ፕሬዚዳንት ሐሮልድ ቢ ሊይ ከስምንት ልጆችዋ ጋር ብቻዋን ለ ተተወች አንዲት ሴት እንዲህ ብለዋት ነበር፥ "'ባልሽ ከአንቺ ጋር ባለመሆኑ ብቸኝነት አይሰማሽ። የቤት ለቤት አስተማሪሽን እና ጳጳስሽን ተጠጊያቸው።' እሱዋም በፈገግታ እንዲህ አለችን፥ ወንድም ሊይ

14-ሀ፣ አንዲት እናት ከቤተሰቦቿ ጋር ስብሰባ ስትሳተፍ።



ማንም ሊያገኘው የማይችል ምርጥ የቤት ለቤት አስተማሪ አለኝ። እንዲሁም ማንም የእኛን ያህል ምርጥ ጳጳስ የለውም። እየተንከባከቡን ነው። በሕይወታችን ውስጥ ክህነት ያለው፣ የሚጠብቀን አባታዊ አባት አለን!።” (“Maintain Your Place as a Woman,” *Ensign,* Feb. 1972, pp. 53–54.)

አንዳንድ ሴቶች ሁሉንም ልጆቻቸውን ነፍስ እስኪያውቁ ድረስ ማሳደግ አልቻሉም። ነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ አብዛኛዎቹ ልጆች በዚህ በሙስና በተሞላ አለም ለመኖር በጣም ንፁሆች እና ተፈቃሪዎች እንዲሆኑ አስተምረዋል። ከማዘን ይልቅ፣ ከክፋት በመዳናቸው መደሰት ይገባናል። (See *Teachings of the Prophet Joseph Smith,* pp. 196–97.) በተጨማሪም እድሚያቸው ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው የሞቱ በሰማይ መንግስት እንደሚድኑ አስተምረዋል (ት እና ቃ 137፥10 ተመልከቱ)። የነዚህ ልጆች እናት በእምነት ከኖሩ፣ በአንድ ሺው ዘመን ለአቀመ አዳም እስኪደርሱ ድረስ ያሳድጓቸዋል። (See Joseph F. Smith, *Gospel Doctrine,* pp. 455–56.)

በቤተክርስቲያኑ አንዳንድ ሴቶች ልጆች መውለድ ባለመቻላቸው ተጎድተዋል። ልጅ የሌላቸው እናቶች ብዙ ጊዜ ጉዲፈቻ በመያዝ እና ቤት የሌላቸውን ልጆች በመንከባከብ ፍላጎታቸውን ያሟላሉ። መሀን እና ያላገቡ ሴቶች እንደ መምህር፣ ነርስ ልጅ አሳዳጊ፣ ወይም ሌሎች ሆነው ከሰሩ እና እራሳቸውን ለሌሎች አገልግሎት ካዋሉ ሙሉነትን ያገኛሉ። እንደዚህ የሚያደርጉ ሴቶች በልጆች ሕይወት ላይ በተለይም የእናት ፍቅር በተነፈጉት ላይ ደስታ እና የተሟላ ተፅዕኖ ሊያመጡ ይችላሉ።

ፕሬዚዳንት ብሪግሃም ያንግ የቤተመቀደስ ቃል ኪዳናቸውን በእምነት የጠበቁትን ልጅ የሌላቸውን እናቶች በእነዚህ ቃላት አፅናንተዋቸዋል፥

“ብዙ እህቶች በዘር ስላልተባረኩ አዝነዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች የሚኖራችሁን ጊዜ ታያላችሁ። ለቃልኪዳናችሁ ታማኝ ከሆናችሁ የዓለም እናት ትሆናላችሁ። . . . ታማኝ ሁኑ፣ እናም በዚህ ጊዜ በልጆች ካልተባረካችሁ፣ ከዚህ በኋላ ትባረካላችሁ።” (*Journal of Discourses,* 8:208.)

እነዚህ ልዩ የቤተክርስቲያኑ ትምህርቶች ልጅ የሌላቸውን እና መሐን ሴቶችን እንዴት ያፅናኑኗቸዋል? ለምንድነው ይህ የተገለፀው እውነት በፅድቅ እንድንኖር የሚያበረታታን?

## ያላገባች ሴት ሚና

ስዕል 14-ለ፣ አንዲት ወጣት ሴት ለወደፊት ጥሪዋ ዝግጅት ስታጠና የሚለውን ስዕል ያሳዩዋቸው።

ሁሉም ሴቶች፣ ያላገቡም ወይም ያገቡም፣ በዚህ ጊዜያዊ ሕይወት ጠቃሚ የሆነ ተግባር እና ኃላፊነት አላቸው። ወጣት ያላገባች ልጃገረድ በወጣት ላይ ጠቃሚ ሚና አላት። እራሷን ለወደፊቱ የሚስት እና የእናትነት ጥሪ መዘጋጀት አለባት። ስለ ቤት ባልትና ከእናቷ፣ ከትምህርት ቤት፣ እና በቤተክርስቲያኑ የባልትና ክፍል መማር ትችላለች። ትምህርት ቤት በመሄድ እራስዋን ማስተማር ይገባታል። በቤቷ ውስጥ አስተማሪ ለመሆን እራስዋን ማዘጋጀት አለባት። እራሷን ንፁህ በማድረግ አባል በሆኑ እና ባልሆኑ ጓደኞችዋ ፊት ጥሩ ምሳሌ መሆን አለባት።

ወጣት እና ያላገባችሁ ከሆናችሁ፣ የወደፊት ጥሪያችሁን ለማሳካት እንዴት መዘጋጀት ትችላላችሁ? በተለይ ወጣት ወንዶች በወንጌላዊነት በሚያገለግሉበት ጊዜ፣ በመንፈሳዊነት ማደግ ለምንድነው ጠቃሚ የሆነው?

14-ለ፣ አንዲት ወጣት ሴት ለወደፊቱ ጥሪዋ ለመዘጋጀት ስታጠና።




14-ሐ

ስዕል 14-ሐ፣ አንዲት ሴት በክፍል ውስጥ ልጆችን ስታስተምር የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው።

አንዳንድ ሴቶች ዘግይተውም ባል ሊያገኙ አይችሉም። አንዳንዶቹ ብቁ የሆነ ጓደኛ ማግኘት ባለመቻላቸው በዚህ ምድር ሕይወታቸው ሳያገቡ ይቀራሉ። እንደዚህ ዓይነት ሴቶች ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት ብቁ የሆኑ ባል እና ልጆች እንደሚያገኙ ቃል ተገብቶላቸዋል። ማንኛውንም በመሬት ላይ ያለውን በረከት አይከለከሉም። ፕሬዚዳንት ሐሮልድ ቢ ሊይ እንዲህ ብሎ ነበር፡

"የጋብቻ ጥያቄ ሳይቀርብላችሁ ዓመታት እየቆጠራችሁ ያላችሁ እናንተ ወጣት ሴቶች፣ ራሳችሁን ወደ ጌታ ቤት (ቤተመቅደስ) ብቁ እና ዝግጁ ካደረጋችሁ እና ምንም እንኳን በዚህ ሕይወት የጋብቻ ልዩ መብት ባይመጣላችሁም በዚህ በዘለዓለማዊ የሰማይ ጋብቻ የተቀደሰ ህግ እምነት ካላችሁ፣ ጌታ በስተመጨረሻ ጊዜ ይሸልማችኋል። እንዲሁም ምንም ዓይነት በረከት አትከለከሉም። በረከቱን እንዳታጡ ብቻ በመፍራት ብቁ ያልሆነ ሰውን ጥያቄ የመቀበል ግዴታ የለባችሁም።" (*Ye Are the Light of the World,* p. 308.)

ይህ ቃል ላላገቡ ሴቶች መፅናናት እና ማረጋገጫ እንዴት ሊያመጣ ይችላል?

አንዲት ያላገባች ሴት ስሜትዋን በዚህ መንገድ ገለፀች፡ "ብዙ የተለዩ በረከቶች እና ልዩ ዕድሎች ላላገቡ አባላት ተዘጋጅተዋል . . .

"ለማግባት ካለን ጉጉት የተነሳ፣ ለጋብቻ ብቻ ሳይሆን ለዘለዓለማዊ ሕይወት ራሳችንን የማዘጋጀት አያሌ ዕድሎችን በቀላሉ ችላ ልንል እንችላለን። . . .

"በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ አላገባች ሴትነቴ፣ ብዙ ጊዜ በፓትሪያርክ በረከቴ የተገባልኝ የቤተመቅደስ ጋብቻ ፍፃሜ ለማየት እጣደፍ ነበር። ግን . . .ታማኝ ለሆነች ያላገባች አባል ሊመጣ የሚችለው በረከት እየተገነዘብኩ እና አመስጋኝ እየሆንኩኝ መጣሁ። . . .

"እንደፈለግን ልንጠቀም የምንችለው ጊዜ እና ልዩ መብት አለን። ግን ይህን በዋጋ የማይተመን የጊዜ ስጦታ የአጠቃቀም ኃላፊነት አለብን። በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ አላገቡ አባልነታችን . . . ልንማረር እንችላለን . . . ወይም ይህን የብቸኝነት ጊዜያችንን በንቃት ለመጠበቅ ልንጠቀምበት እንችላለን። ይህን ጊዜ አጠቃቀማችን—ለደስታችን እንዲሁም ለዘለዓለማዊ ዕድገታችን በጣም ጠቃሚ እንደሆነ በፅኑ አምንበታለሁኝ።

"መነሻ ሐሳቡ የሙያ ወይም የሥራ ጥያቄ ነው . . . አንዳንድ ሴቶች ተፈታታኝ የሆነ ሙያ በመጋፈጥ ታላቅ እርካታን ያገኛሉ። በፀሎት እና በክህነት በረከት፣ ሙያዬን በመከተሉ አፅናኝ የሆነ የግል እርካታ ተቀብያለሁ አሁን የሚያደርገው ነገር በጌታ ፊት አስደሳች ነው። . . .

"በህይወት ታላቁ እና የማያልቀው ደስታ ከርህራሄ አገልግሎት እንደሚመጣ መግለፅ እፈልጋለሁ። . . . በዙሪያችን ላሉ እንባዎች እና ልብ የሚነኩ ችግሮች በራሳችን ሓሳብ እና ችግር በመጠመድ በመንፈስ ደንቆሮ መሆን ቀላል ነው። . . .

"ጊዜያችን እንደአሁኑ ነፃ አይሆንም። ለመማር . . . ጥሩ መፅሐፍ ለማንበብ . . .የተለያዩ ችሎታዎች እና ፍላጎት ለማሳደግ፣ . . . የዘር ግንዳችንን መመዝገብ ለመጀመር ጊዜ ይኖረናል። ይህ ቤተሰቡ ሁሉ የቤተሰብ መዝገብ በመፈለጉ እንዲሳተፉ ያነቃቃል።

14-ሐ፣ አንዲት ሴት በክፍል ውስጥ ልጆች ስታስተምር።

"የዘወትር እና ትጉ የቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚያመጣው ታላቅ እርካታ በጣም ሊጋነን አይችልም። እንደ ሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ ሆኜ በማገልገሌ ታላቅ ደስታን አግኝቻለሁኝ። . . .

"የሰውነታችንን አቋም የማሻሻል ጊዜ አለን። . . . ሁልጊዜ ሰውነታችን እና መንፈሳችን እንዲሁም ስሜታችንን ማነቃቃት እና ሰውነታችንን ማሳመር እንችላለን።

"ለሕፃናት ልጆች ጓደኛ በመሆን በዋርዳችን እና ቀርንጫፋችን ውስጥ ከቤተሰቦች ጋር የምንሳተፍበት ጊዜ ይኖረናል። ለህፃናት ለመስራት ተጋብዤ ነበር . . . በእኛ ምሳሌነት ለአቅመ አዳም በሚደርሱበት ጊዜ የወንጌልን ህጎች እንዲያከብሩ ልናበረታታቸው እንችላለን።

"በሰማይ ከአባታችን ጋር የምናሳልፈው ብዙ ጊዜ አለን። የፆም እና የዘወትር ፀሎት በህይወቴ ያለውን ተፅዕኖ ማጋነን አልችልም. . . .። ጌታ ለእኔ ያለውን ፍቅር እና ሐሳብ የማይናወጥ ምስክርነት አግኝቻለሁ።

" . . .በችግራችን ጊዜ፣ የሚያነቃቃን፣ የሚያጠናክረን፣ እና የሚያግዘን የፍቅር እጆች አጠገባችን አሉ እወቁ። እዚያ እንዳሉ ቃል እገባላችኋለሁ።

"ተስፋ መቁረጥ በከባዱ ሲጫነኝ፣ . . . ለሐዘን እውነተኛ መድሃኒት እዚያ የሆነ ሰው *እንደሚፈልገኝ መገንዘቡ መሆኑን ተረድቻለሁኝ*። ሌሎችን በመባረክ፣ ችግሮቼ የሌሎችን ሕይወት በማብራት በሚወጣው ሞቅ ያለ ጮራ ሲጠፉ ይሰማኛል እንድሁም ያደረኩት ነገር በጌታ ፊት አስደሳች እንደሆነ አረዳለሁኝ።

"እናም በዚህ ውድ ሐብት እና ጊዜ እንደሰት እናም ጌታን ለልዩ ስጦታው እናመስግነው።" (Anne G. Osborn, "The Ecstasy of the Agony: How to Be Single and Sane at the Same Time," *Ensign,* Mar. 1977, pp. 47–49.)

በእድሚዋ የገፋች ያላገባች ሴት ሕይወተዋን በማህበረሰባችን ጠቃሚ እንዴት ማድረግ ትችላለች?

## ማጠቃለያ

በዚህ ቤተክርስቲያን እያንዳንዷ ሴት ለራሷ ሕይወቷን ጠቃሚ ማድረግ ትችላለች። በእምነት የምንኖር ከሆነ፣ አንድ ቀን አጋር በመሆን፣ ረዳት በመሆን፣ እና እናት በመሆን በልዩ መብት እንባረካለን። ይህ ዕድል በጊዜም መጣ ዘግይቶ መጣ ወይም ከዚህ ሕይወት በኋላ መጣ፣ ህይወታችንን መሙላት እንችላለን። ሌሎችን ማገልገል እና የኋ. ቀ. ቀ. ሴትነታችንን ሚና ማሟላት እንችላለን።

## ሙከራ

የራሳችሁን ሚና የተሻለ የምታደርጉበትን መንገድ ፈልጉ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

ኤፌሶን 6፥4 (ልጆችን አታስቆጧቸው)
1ኛ ጢሞቴዎስ 5፥3–14 (ስለ ጥበብ)

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. በዚህ ትምህርት የተጠቀሰውን ፖስተር ያዘጋጁ።
2. *የወንጌል መሰረቶች፣* ምዕራፍ 36፣ “ቤተሰብ ዘለዓለማዊ ሊሆን ይችላል” የሚለውን ያጥኑ።
3. *የወንጌል መሰረቶች፣* ምዕራፍ 37፣ “የቤተሰብ ኃላፊነት” የሚለውን ያጥኑ።
4. በዚህ ትምህርት ውስጥ የክፍሉ ተማሪዎች ታሪኮችን እና ቅዱስ ፅሑፎችን እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

# ከቤተሰቦቻችን ጋር መማከር

ትምህርት 15

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ ከባሎቻችን እና ከልጆቻችን ጋር በመማከር ቤተሰባችንን ለማጠንከር እንድንችል መርዳት ነው።

---

## አባት በቤት ውስጥ ይመራል

"በሁሉም ዙሪያ ውበት አለ" የሚለውን መዝሙር ዘምሩ። (*የወንጌል መሰረቶችን* ተመልከቱ)

ምድራዊ ቤታችን የመንግስተ ሰማያት ቤት ጅምር ነው። ወላጅነት የመለኮታዊነት ልምምድ ነው።

"እያንዳንዱ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ቤት፣ አባት የቤቱ ራስ የሚሆንበት፣ ግን በፍቀር የሚመራበት፣ እና ከእናትየው የፅድቅ ፍላጎት ተስማምቶ የሚኖርበት የምሳሌ ቤት መሆን አለበት። በአንድነት ለቤተሰቡ አንድ ዕቀድ መሻት አለባቸው፣ እናም ልጆቹ ያለውን ፍቀር እና ስምምነት አብረው ሊደሰቱበት ይገባል።" (N. Eldon Tanner, "Fatherhood," *Ensign,* June 1977, p. 2.)

አባት የቤተሰቡ ፓትሪያርክ እና የበላይ ባለስልጣን ነው። የቤተሰቡን ጉዳይ የመምራት ኃላፊነት የእርሱ ነው። ወላጆች ጻድቅ የሆነ ቤተሰብ የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው፣ በእርግጥ ማናቸውም ይህን ብቻቸውን መፈፀም አይችሉም፡ እያንዳንዳቸው አስፈላጊዎች ናቸው። እኛ እና ባሎቻችን ወዳጆች ነን። ሁለታችንም ጠንካራ ጋብቻ መመስረት እና ቤተሰባችንን ወደ ጌታ ማቀረብ እንችላለን። የጌታን መንፈስ በቤታችን መጠቀም እንችል ዘንድ ከባሎቻችን ጋር መማከር ይገባናል።

## ለባሎቻችን ፍቀር እና አሳቢነትን ማሳየት

እንደ ሚስትነታችን፣ እያንዳንዳችን የሥነ ሥርዓት እና የፍቀር ቤት መመስረት ይገባናል። ከልብ የሆነ ፍቀር እና አሳቢነት ምሳሌ በቤት ውስጥ በጋብቻችን የመጀመሪያ ጊዜያት ውስጥ መጀመር አለበት። በቅርቡ ወንጌልን የተማርን ከሆንን፣ ይህን ምሳሌ አሁን መመስረት አለብን። ሁልጊዜ አብረን መፀለይ፣ እርስ በርስ ፍቀርንና ከበሬታን ማሳየት፣ ቅዱሳን መጽሐፎችን በአንድነት ማንበብ እና ማጥናት አለብን። የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እና በጋብቻ ጊዜ የገባነውን ቃልኪዳናችንን መጠበቅ አለብን።

ስለ ፍፁም ቤት፣ ፕሬዚዳንት ጄ. ሩቤን ክለርክ ጄ. አር፣ ሲገልጹ እንዲህ ብለው ነበር። "እውነተኛ ፍቀር በባል እና ሚስት ሐሳብ እና ድርጊት በረከትን እና ቅድስናን ያመጣል።" "በዚህ ቤት አክብሮት መኖር አለበት፣ ትዕግስት በብዛት . . . በሐሳብ፣ በቃል እና በሥራ ታማኝነት መኖር አለበት። . . .

"እምነት ቤትን እንደተወዳጅ መብራት መሸፈን አለበት።

“ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት መታዘዝ ሊመራቸው እና ሊያስደስታቸው ይገባል።” (Excerpted from “The Building of Home Life,” *Immortality and Eternal Life,* Vol. 2, Melchizedek Priesthood Course of Study, 1969–70, pp. 14–15.)

ለባሎቻችን ፍቅርን እና አሳቢነትን ለማሳየት ምን ማድረግ እንችላለን? ፍቅርን ማሳየት በቤታችን ስርዓትን ለመመስረት እንዴት ይረዳናል?

## በአንድ ላይ መመካከር

ስዕል 15-ሀ፣ ባል እና ሚስት አብረው ሲሰሩ። የሚለውን ስዕል አሳዩአቸው።

በባል እና ሚስት መካከል ጥሩ ግንኙነት መኖሩ ጠቃሚ ነው። ከዚያም በጋብቻ ውስጥ የተነሱትን ችግሮች አብረን ለመፍታት እንሰራለን። አብዛኛው ችግር እኛ እና ባሎቻችን በጌታ ከተመራን መፍታት እና መቋቋም ይቻላል።

አልማ 37፥37 ያንብቡ። ከጌታ ጋር መማከር እንዴት ሊረዳን ይችላል?

በተደጋጋሚ መወያየት ይገባናል። ከባሎቻችን ጋር ስለ ችግሮች እና ግቦች በፀሎት መወያየት አለብን። ባሎቻችንን የምናፈቅር ከሆነ፣ የቤተሰብን ችግር ለመፍታት ሁሌም የእነርሱን አመራር እና ድጋፍ እንሻለን። ሁሉም የቤተሰብ ታላላቀ ውይይቶች በአንድነት መደረግ አለባቸው። ይህን ለማድረግ፣ ችግሮችን ለመወያየት እና ለመፍታት ጊዜ መመደብ አለብን፥ ገንዘብ፣ ልጆች፣ ኃይማኖት፣ የቤተሰብ ምሽት፣ እና ሌሎች የግል እና የቤተሰብ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ። ውሳኔዎች ሲደረጉ፣ ወላጆች በአፈጻጸሙ ላይ አንድ ላይ መስራት አለባቸው።

የሚከተለው ልምድ አንድ የተጋቡ ጥንዶች እንዴት በአንድ ላይ እንደተማከሩ ያሳያል፥

አባቴ የተማረ እና ጥበበኛ ሰው ነበር። ሁሉን የቤተሰብ ውሳኔ ብቻውን ማድረግ ይችላል። ነገር ግን ከእናቴ ጋር ተቀምጦ ስለ ችግሮች እና መፍትሔያቸው ይወያያል። ቢያንስ በሳምንት አንዴ፣ በተለይ እሁድ ምሽት፣ ማዕድቤት ተቀምጠው ስለ ችግሮች ይነጋገራሉ። አንዳንድ ጊዜ እኛ ልጆች በውይይቱ እንድንሳተፍ እንደረጋለን። አባቴ እና እናቴ አብረው በመወያየት ሁልጊዜ እንዴት ማደግ እንዳለብን ስምምነት ላይ ይደርሳሉ። ምንም እንኳን ትንሽ ገቢ ቢኖረንም፣ በቂ ገንዘብ ሁልጊዜ ይኖረን ነበር። ወላጆቻችን የተጨቃጨቁበት ወይም የተጣሉበትን ጊዜ አላስታውስም። ጥበበኛው አባቴ እናቴን በጣም በማፍቀሩ እና ጠቃሚ ምክርዋን ለመጠቀም ጥበበኛ በመሆኑ አመሰግነዋለሁ። ዛሬ በራሳችን ቤት ልንከተለው የምንሞክረው የመንግስተ ሰማያት ቤት ምሳሌ አሳይተውናል።

በቤታችን ውስጥ ጭቅጭቅን እና ችግርን አብረን በመወያየት እንዴት ማስወገድ እንችላለን? መመካከር በጋብቻችን ፍቅርን እንዴት ይጨምራል?

## ከቤተሰብ ጋር መመካከር

ስዕል 15-ለ፣ አንድን ቤተሰብ በቤተሰብ ምሽት ላይ የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩአቸው።

አባት እና እናት ከተማከሩ በኋላ፣ በቤተሰብ ምክክር ላይ ልጆች ስለ ቤተሰብ ግብ እና ዕቅድ እንዲወያዩ ሊጠሩዋቸው ይገባል።

15-ሀ፣ ባል እና ሚስት አብረው ሲሰሩ። የሚለውን ስዕል አሳዩአቸው።

15-ለ፣ አንድን ቤተሰብ በቤተሰብ ምሽት ላይ የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩአቸው።





ከመላው ቤተሰብ ጋር መማከር ዋጋ ያለው ነገር ነው። የቤተሰብን ሕይወት ሊያሻሽል ይችላል፣ ፍቅርን ይጨምራል፣ እንዲሁም ደስታን ያሰፋል። ልጆች ስለ ቤተሰብ ዕቅዶች ቀደም ብለው ያውቃሉ። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አንዱ ምን እንደሚያደርግ ከተረዳ፣ ስርዓት እና ስምምነት ይፈጠራል። ልጆች በተቻለ መጠን በውሳኔ አሰጣጥ እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፣ እናም በውሳኔ አፈፃፀሙ ላይ መርዳት አለባቸው። ከቤተሰባችን ጋር ስንመካከር፣ የእያንዳንዱን ግለሰብ ሐሳብ፣ ችግር እና የጊዜ ሁኔታ ማክበር አለብን።

የቤተሰብ ውይይት ለማድረግ የሚያመቸው የትኛው ጊዜ ነው? (እሁድን ለሐሳብ አቀርቡ) በዚህ ምክክር የምንወያይባቸው አንዳንድ ጉዳዮች ምንድናቸው?

ስዕል 15-ሐ፣ እናት ሴት ልጇን ባልታወቀ መንገድ ስትመክር የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩአቸው።

ከልጆቻችን ጋር መመካከር ሁልጊዜ በመደበኛ ሁኔታ መሆን የለበትም። እንደ እናትነታችን፣ ስለችግራቸው ለመስማት ማንኛውንም አጋጣሚ መጠቀም አለብን። አስተሳሰባቸውን እንደራሳችን ማየት አለብን። በሐሳባቸው መሳቀ ወይም አሳንሰን ማየት የለብንም። ይልቁንም፣ በፍቅር ልንረዳቸው እና ልንመክራቸው ይገባናል። በተጨማሪም አባት ከእያንዳንዱ ልጆች ጋር ለየብቻ መወያየቱ ጠቃሚ ነው።

"አባት እና እናት ከወንድ ልጃቸው ወይም ከሴት ልጃቸው ጋር ስለ ግል ችግራቸው ሲወያዩ በጣም አስደናቂ ነው። (እናም እኛ ጥበበኛ ከሆንን ልንቀንሰው የማንችለው ችግሮች አሏቸው)። ወንድ ልጆቻችን እና ሴት ልጆቻችን ጥንካሬ የሚያስፈልጋቸው ጫና እና ፈተና አለባቸው . . .

"በእንደዚህ የልብ ለልብ ንግግሮች፣ ወላጆች ለልጆቻቸው ዓላማ ሊያስቀምጡላቸው ይችላሉ።" (ElRay L. Christiansen, "Successful Parenthood—A Noteworthy Accomplishment," *Ensign,* July 1972, p. 55.)

እንደ ወጣት ሴትነታችሁ፥ ከወላጆቻችሁ ጋር ምን መወያየት ትፈልጋላችሁ?

እንደ እናትነታችሁ፥ ከልጆቻችሁ ጋር ምን መወያየት ትፈልጋላችሁ?

ጠንቃቃ የክፍል ተማሪ የሌሎችን ሐሳብ መቀበል ጥበብ ይሆንላታል። ችግሮቻችን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አይደሉም።

ቄስ ሪቻርድ ኤል ኤቫንስ ከልጆቻችን ጋር ስለመማከር ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፥

"እናንተ እና እነሱ በአንድ ላይ ተቀምጣችሁ ሐሳባችሁን የምትካፈሉበት እና ውሳኔያችሁን የምትመረምሩበት፣ ሁላችሁም የምትደማመጡበት እና የምትከበሩበት ልዩ መብት፣ ኃላፊነት፣ አላችሁ . . . እናም ለደስታችሁ ሙላት ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የምትሰሩበት የምትፀልዩበት እና የምታቀዱበት መብት አላችሁ።" ("As Parents and Children Come to Common Ground," *Improvement Era,* May 1956, p. 342.)

## ማጠቃለያ

በሰለስቲያል መንግስት በሰላም እና በስምምነት ስለምንኖር፣ ዛሬ አንድነት እና ፍቅርን ለማግኘት መጀመር አለብን። እንዲሁ በተፈጥሮ ሊሆን *አይችልም*። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬ እንዲህ ብለው ነበር፥

"በቤት ውስጥ አንድነት እና ስምምነት ካለመኖር የበለጠ የማያስደስት ነገር ይኖራል ብዩ ማሰብ ያዳግተኛል፣ በሌላው አንፃር አንድነት፣ እርስ በርስ መረዳዳት፣ እና ፍቅር የሰፈነበት

15-ሐ፣ እናት ሴት ልጇን ባልታወቀ መንገድ ስትመክር የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩአቸው።


THE COMPLETE HUMOROUS SKETCHES AND TALES OF
MARK TWAIN

ቤት በምድር ላይ የመንግስተ ሰማያት ክፍል እንደሆነ አውቃለሁ።" (In Conference Report, Oct. 1967, p. 7.) ከባሎቻችን እና ልጆቻችን ጋር በተማከርን ጊዜ፣ ቤተሰባችንን ማጠንከር እንችላለን። እያንዳንዳችን ታላቀ ፍቅር እና ቀርበት ይሰማናል።

## ሙከራ

ከባሎቻችሁ እና ከልጆቻችሁ ጋር የመማከሩን ጥቅም ተረዱ። ለዚህ ዕድል በፀሎት እንዲዘጋጁ አበረታቷቸው። ባሎቻችሁ እያንዳንዱን ልጆቻችሁን እንዲያወያዩ አበረታቷቸው።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

1 ቆሮንቶስ 13 (የፍጹም ፍቅር ጥሩነት)
ወደ ገላትያ ሰዎች 5፥22–23 (የመንፈስ ፍሬዎች)
ያዕቆብ 2፥35 (ኔፋይቶች በልጆቻቸው ላይ እምነት አጡ)
ያዕቆብ 3፥7 (ሌመናይቶች ልጆቻቸውን ያፈቅራሉ)
ት እና ቃ 121፥36–41 (ከቁጣ በኋላ፣ የፍቅርን መጨመር አሳዩ)

---

#### የመምህሩ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረቶች*፣ ምዕራፍ 37፣ "የቤተሰብ ኃላፊነት" ያንብቡ።
2. የክፍሉ አባላት ቅዱሳን መፅሐፍቶቻቸውን ወደ ክፍል እንዲያመጡ ያስታውሱዋቸው።
3. የክፍሉን አባላት በዚህ ትምህርት ጥቅሶችን እና ታሪኮችን እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

# የቤተሰብ
# የቤት ምሽት

ትምህርት 16

የዚህ ትምህርት ዋና አላማ የተሳካ የቤተሰብ የቤት ምሽት እንዲኖረን ለማበረታታት እና ለመርዳት ነው።

## የቤተሰብ የቤት ምሽት ለሁሉም ሰው ነው

እያንዳንዱ ቤተሰብ ሁልጊዜ በየሳምንቱ የቤተሰብ የቤት ምሽት ሊኖረው ይገባል። ቤተክርስቲያኑ ሰኞ ምሽትን ለዚህ ዓላማ ሲባል ከየትኛውም ሌሎች ዝግጅቶች ነጻ አደርጓል።

ስዕል 16-ሀ ፣ወላጆች ከወጣት ልጆቻቸው ጋር በቤተሰብ ምሽት ውስጥ ሲሳተፉ፣ እና ስዕል 16-ለ ፣ በእድሜ የገፉ ጥንዶች ብቻቸውን የቤተሰብ ምሽት ሲያካሂዱ የሚያሳዩ ስዕሎችን ያሳዩ።

ሁሉም ቤተሰብ አንድ አይደለም። አንዳንድ ቤተሰብ ቤት ውስጥ ወላጆች እና ልጆች ይኖሩታል፣ ሌሎች አንድ ወላጅ ከልጆች ጋር ይኖራቸዋል። አሁንም ሌሎች ቤተሰቦች፣ ወላጆች ልጆች ቤት ውስጥ አይኖራቸውም። ብዙ ያላገቡ ጎልማሶች ብቻቸውን ወይንም ከደባል ጋራ ይኖራሉ። በማንኛውም ሁኔታ፣ የቤተሰብ የቤት ምሽት ለሁሉም ሰው ነው። አንድ ግለሰብ ብቻውን የሚኖር ከሆነ፣ የቤተሰብ የቤት ምሽት ለመሳተፍ ከሌላ ግለሰብ ጋር መደባለቅ ይችላል። ብቸኞች ለሆኑ፣ ይህ ልዩ በረከት ሊሆናቸው ይችላል።

“ከቤት የተሻለ ወንጌልን የማስተማሪያ ቦታ የለም። ልጆች በሰማዩ አባታችን የታዘዘውን የቤተሰብ ሕይወት ሁኔታን በቤት ውስጥ ብቻ ነው መማር የሚችሉት። ሰኞ ምሽት ቤተሰቦች አንድ ላይ ሲሆኑ ለሁሉም የቤተሰብ ተሞክሮ መንፈስን ይፈጥራል። ይህ መንፈስ ያላቸው የታላቀ ደስታቸው ምንጭ በመሃከላቸው ይሆንላቸዋል” (ደብዳቤ ከቀዳሚ አመራር፣ *Family Home Evening,* 1971)።

ሁልጊዜ የቤተሰብ የቤት ምሽት ማዘጋጀት ለልጆቻችን የወንጌል መሠረተ ሀሳቦችን የማስተማሪያ አንዱ መንገድ ነው። የቤተሰብ አባላት በፍቀር እና በአንድነት እንዲቀራረቡ ያደርጋል።

የእንጨት እስር ወይንም የክብሪት እንጨት በእጅ ያዙ። ለክፍሉ ተማሪዎች ይህ የቤተሰብ አባላትን እንደሚወክል ንገሯቸው። አሁን ከአስሩ እንጨት አንዱን አውጣ እና ለሁለት በግማሽ ስበሩ። ለክፍሉ ተማሪዎች ብቻችንን ስንሆን ከቤተሰባችን ጋር ስንሆን ያለን ጥንካሬ እንደማይኖረን ንገሯቸው። ከዚያም ክር ወይም ላስቲክ አምጣ እና በተሮቹን አንድ ላይ አሰሯቸው። ለክፍሉ ተማሪዎች ክሩ የወንጌል ትምህርት ያለው የመተሳሰር ተጽእኖ እንደሚወክል ይንገሯቸው። ከዚያም እነዚህን እስር በተሮች መስበር ምን ያህል አስቸጋሪ እንድሆነ ይንገሯቸው። እንደ ቤተሰብ አንድ ስንሆን እና በወንጌል እውነቶች ስንተሳሰር ምን ያህል ጠንካሮች እንደምንሆን ይግለጹላቸው።

## የቤተሰብ የቤት ምሽት እንዴት ይዘጋጃል

አባት፣ እንደ የቤት ፓትሪያሪክነቱ፣ የቤተሰብ የቤት ምሽትን መምራት አለበት። አባት በማይኖርበት ጊዜ ወይም አባት በቤት ውስጥ የሌለ እንደሆነ፣ እናት መሪነቱን መውሰድ

16-ሀ ወላጆች ከወጣት ልጆቻቸው ጋር በቤተሰብ የቤት ምሽት ውስጥ
16-ለ በዕድሚያቸው የገፉ ጥንዶች ብቻቸውን የቤተሰብ ምሽት ሲያካሄድ።



16-U



16-ለ

አለባት። የሚቻል ከሆነ፣አባት እና እናት እያንዳንዱን የቤተሰብ የቤት ምሽትን ከጊዜው ቀደም ብለው አንድ ላይ ማቀድ አለባቸው። ከዚያ በኋላ ለቤተሰብ አባላት የቤት ሥራ መስጠት ይችላሉ።

በእያንዳንዱ የቤት ምሽት መጀመሪያ ላይ፣ አጭር የምክር ወይም የእቅድ ስብሰባ ለሚመጣው ሳምንት የቤተሰቡ አባላት ዝግጅት እና እቅድ ምን እንደሆነ ለማወቀ ይረዳል። ይህ በተለይ ታዳጊ ወጣቶች ባሉበት ቤተሰብ ጠቃሚ ነው።

"አባት እራሱ ያስተምራል ወይም ትምህርቱን ሌላ ሰው . . . ለሚስቱ ወይም ለትልልቀ ልጆቹ. . . . ትንንሽ ልጆች ሙዚቃ በመምራት፣ ከቀዱሳን መጽሐፍት በመጥቀስ፣ ጥያቄዎችን በመመለስ፣ ስዕሎችን በመያዝ፣ የሚበሉ ነገሮችን በማደል፣ እና በመጸለይ ሊረዱ ይችላሉ።

"የሚከተሉት አስተያየቶች የቤት ምሽት ፕሮግራም ናሙና ናቸው።"

የመክፈቻ መዝሙር (በቤተሰቡ)
የመክፈቻ ጸሎት (በሕጻን ልጅ)
የግጥም ወይም የቀዱሳን መጽሐፍት ንባብ (በአንድ የቤተሰብ አባል)
ትምህርት (በአባት፣ በእናት፣ ወይም በትልቀ ልጅ)
ዝግጅት (በአንድ የቤተሰቡ አባል የሚመራ ጨዋታ እናም ሁሉም የቤተሰብ አባል የሚጫወትበት)
የመዝጊያ መዝሙር (በቤተሰቡ)
የመዝጊያ ጸሎት (በቤተሰቡ አባል)

የሚበሉ ነገሮች

"አንድ ቤተሰብ የቤተሰብ ምሽትን በተለያዩ መንገዶች ማዘጋጀት ይችላል። ማንኛውም ዝግጅት ቤተሰብን የሚያቀራርብ እና አንዱ ለአንዱ ያለውን ፍቀር የሚያጠነክር፣ እንዲሁም የጽድቀ ኑሮን የሚያሳድጉ፣ ኑሮን የሚያበረታታ፣ የቤተሰብ የቤት ምሽቱን ዓላማ ያሟላል። እነዚህ ዝግጅቶች ቀዱስ መጽሐፍቶችን ማንበብ፣ ስለ ወንጌል መወያየት፣ ምስክርነትን መስጠት፣ የአገልግሎት ፕሮጀክት ማከናወን፣ አብሮ መዘመር፣ ሽርሽር መሄድ፣ የቤተሰብ ጨዋታ መጫወት፣ የእግር ጎዞ፣ እናም ሌሎችንም ሊያካትት ይችላል። ሁሉም የቤት ምሽት ጸሎትን ማካተት አለበት።" (*Family Guidebook,* pp. 2–3.)

እያንዳንዳችን፣ እንደ ቤተሰብ አባልነታችን፣ የቤተሰብ ምሽት እንዲሳካ መርዳት እንችላለን። በመጀመሪያ፣ የግል ሥራችን በቤተሰብ የቤት ምሽት ነጻ እንድንሆን ቀደም ብለን ማቀድ እንችላለን። በተጨማሪም የተሰጠንን ሥራ መሥራት፣ ወይም በዝግጅት መርዳት እንችላለን። እናቶች ወይም ትልልቀ ልጆች ህፃናት ልጆችን በሳምንቱ የተሰጣቸውን ሥራ እንዲዘጋጁበት መርዳት ይችላሉ። ወጣት ልጆች የጨዋታ ታሪኮችን ማቅረብ እና በተለያዩ መንገዶች መጫወት ይወዳሉ። እያንዳንዱ ልጅ እናት እና አባት ሲፈቅዱላቸው እና ለጥረታቸው ሲታገሱዋቸው መሳተፍ ይችላሉ። እያንዳንዳችን ለተሰጠን ሥራ ስንዘጋጅ ወደ ሰማይ አባታችን በመጸለይ የቤተሰብ የቤት ምሽታችንን ለማሻሻል እንችላለን።

የሚከተለው የተሳካ የቤት ምሽት ምሳሌ ነው፡-

የቶምፕሰን ቤተሰብ አንዱን የቤተሰብ ምሽታቸውን "የቶሚ ሽልማት" ምሽት ብለው ሰየሙት። እድሚያቸው ከአሥራ ሰባት እስከ አምስት የሚሆናቸው ሰባቱ ልጆች ለእራት የሚወዱትን ምግብ ይመርጣሉ። የአሽናፊ እራት ቀረበ፣ ከዚያም "የቶሚ ሽልማት" ተነገረ።

አባት ምርጥ ልብሱን፣ የትልቅ ቢራቢሮ ቀርጽ ክራቫት በአንገቱ ላይ አድርጎ፣ ዝግጅቱን ያስታውቃል። እናትም ረጅም እና ቀንጆ ቀሚሷን ለብሳ "የአሸናፊዎችን" ስም የያዘ ፖስታዎችን ይዛ ከአባት አጠገብ ቆማለች። ሴት እና ወንድ አያት ልጆች ሽልማታቸውን ሲቀበሉ እንደ አድናቂ እና ደጋፊ ተመልካች ተጋብዘዋል። የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በአባት ከተደረገ በኋላ፣ የስጦታ ሥነ-ሥርዓት በዚህ ዓይነት ቀጥሏል።

አባት "በሒሳብ መስክ ለላቀ ሽልማት የታጩ አልበርት አልስተን እና ጳውሎስ ቶምፕሰን የሚከተሉ ናቸው፡- እባክዎን ፖስታውን አሉ " እናት ለአባት የከፈቱትን ፖስታ አቀበሉ። ከዚያም፣ በአድናቆት "አሸናፊው . . . ጳውሎስ ቶምፕሰን! " እንደሆነ አስታወቁ።

ቤተሰቡ ፓውል "የቶሚ ሽልማት" የተሰኘውን ሲቀበል ደስታውን ገለጸ። (በዚህ ጊዜ ሽልማቱ የልጁ ስም እና ያከናወነው ሥራ በፊት ለፊቱ የተፃፈበት የፕላስቲክ ስዕል ነበር)

በዚህ አይነት መንገድ ልጆቹ በብሔራዊ ወይም አለማቀፋዊ ሻምፕዮን ወይም ዝናዎች አሸናፊ እንደሆኑ እስኪገለጽ ድረስ ሥነ-ሥርአቱ ቀጥሏል። ሼሪ በውኃ ዋና የላቀ ውጤቷ ሽልማትዋን ተቀበለች፣ ብሪያን በስካውቲንግ፣ ሚቸል በሙዚቃ ክንዋኔዋ፣ ሚካኤል በትንሿ በቤዝ ቦል ማኅበር ክንዋኔው፣ ዴኒስ በንባብ ከፍተኛ ችሎታዋ፣ እና ሲንትያ የቤተሰብን ቀናት በማድመቅ እንዲሳካ ማድረግዋ ነበር። ሽልማትዋ "ሰንሻይን አዋርድ" የተባለ ልዩ ሽልማት ነበረ።

ከዚህ በመቀጠል፣ እያንዳንዱ ልጅ በሳምንቱ ያጠናውን መዝሙር አቀረቡ፣ እናም ደስታ እና ምስጋና ቀረበላቸው። ከዚያም ዴንስ እና ሲንትያ በአንድነት "በብርሐን መኋዝን አስተምረኝ" (See *Gospel Principles.*) የመዝጊያ ፀሎት በሚካኤል ከተደረገ በኋላ የሚበላ ነገር ቀረበ።

የቤት ምሽት የቤተሰቡን ፍላጎት እና ምኞት እንዲያሟላ ተደርጎ ማቀዱ ጠቃሚ ነው። ልጆቻችሁን የሚማርኩ ነገሮችን አድርጉ። የቤት ምሽቶች ቤተሰቦችን ለመርዳት ነው። ብዙ ጊዜ በጣም የተሳኩ የቤት ምሽቶች ቤተሰቡ በራሱ መንገድ የሚያዘጋጀው ዋነኛ ናቸው።

በየሳምንቱ ለቤተሰብ የቤት ምሽት ዝግጅት ምን ያህል ጊዜ ታጠፋላችሁ? የቤት ምሽታችሁን በተሻለ እቅድ እንዴት ማሻሻል ትችላላችሁ?

"ማህበራዊ ጉዳዮችን እና ሙያዎን እንደሚከታተሉት ሁሉ ለቤተሰብዎ እና ለቤትዎ ተገቢውን ጊዜ ይሰጡታልን? ያለዎትን የፈጠራ ኃይል ለማህበረሰቡ—ለቤተሰብ ይሰዋሉን፣ ወይስ ከቤተሰብዎ ጋር ያለዎትን ግንኙነት እንደተራ፣ ዋጋ የሌለው የሕይወት ክፍል አድርገው ይወስዱታል?

"ወላጆች እና ልጆች የቤተሰብ ለዘለአለም መዳንን ለማምጣት በመጀመሪያ ለቤተሰብ ሐላፊነት ፈቃደኞች መሆን ይገባቸዋል።" (ደብዳቤ ከቀዳሚ አመራር፣ *Family Home Evening,* 1973.)

ፀሎትን የቤተሰብ የቤት ምሽታችንን ለማሻሻል እንዴት መጠቀም እንችላለን?

## ሁልጊዜ የቤተሰብ የቤት ምሽት በማድረግ የሚገኝ በረከት

ቤተሰባችን የቤተሰብ የቤት ምሽትን በመደበኛነት በማዘጋጀት ብዙ በረከቶችን ሊያገኝ ይችላል። ተሳትፎ ማድረግ በራሱ ብቃት የመተማመን ስሜት በእያንዳንዱ አባል ላይ ይፈጥራል። የስነ-ስርዓት ጉድለቶችን ይቀንሳሉ፣ ታማኝነት እና ስምምነትን ይጨምራል።

እህት ሬምዴ ማሎይ የጀርመን ምዕራብ ሚሲዮን አባል እና የአምስት ልጆች እናት እንዲህ ብላ ነበር፤ “ምንም እንኳን ትልቁ ልጃችን እድሜው ስድስት ዓመት ቢሆንም፤ በየሰኞ ምሽት የቤተሰብ የቤት ምሽት ስለምናዘጋጅ ልጆቻችን የተለየየ ባህሪይ እንዳላቸው ተገንዝበናል . . . የምንሰጣቸውን ትምህርት እንደሚቀበሉ ማወቁ አስደናቂ ነው። “(በቤተክርስቲያን ውስጥ ሴት መሆን፤” *Ensign,* Aug. 1973, p. 38.) እህት ማሎይ እንደመሰከረችው፤ ልጆች ከቤተሰብ የቤት ምሽት የሚማሩትን ትምህርት ያስታውሳሉ።

በሚድላንድ፤ ቴክሳስ የአምስት ዓመቱ አለን ጥቂት ህፃናት በወዲያኛው ግቢ መጣላት በጀመሩበት ጊዜ እርሱ ከወንድ አያቱ ጋር በግቢያቸው ውስጥ ይጫወት ነበር። ጭቅጭቁም ከፍ እያለ መጣ፤ ትንሹ ድምጽ በቁጣ እየጨመረ መጣ መጋፋት እና መተነኳኮስ ተጀመረ። ከዚያም አንድ ልጅ አንድዋን መታት እናም በተቃውሞ ጮኸች። አለን ይህን የሁከት ትዕይንት ተመለከተ፤ እናም በሐሳብ ተመስጦ “አያቴ፤ እነዚህ ልጆች የሚያስፈልጋቸው የቤተሰብ የቤት ምሽት ነው!” አለ።

ውጤታማ የሆነ፤ የዘወትር የቤተሰብ ምሽት በሰማይ አባታችን ያለንን ፍቅር እና እምነት ይገነባል። የቤተሰብ የወንጌል እውቀትን ይጨምሩልናል። የቤተሰብ ዝምድናን ያጠናክራሉ እንዲሁም እያንዳንዱ ችሎታውን እንዲያዳብር ያግዛሉ።

የቤተክርስትያኑ ቀዳሚ አመራር ይህን መግለጫ ሰጥቶ ነበር

“ባለፉት በርካታ አመታት ህዝባችንን በተለይም ወጣቶችን የሚፈታተን አዲስ . . .የክፉት ኃይልን በተግባር ላይ አይተናል . . . የቤተሰብ የቤት ምሽት፤ ፕሮግራም ከበጎ ሐይሉ ጋር፤ ለወላጆች ታላቅ ረዳት ሆነዋል . . . በቤተሰብ በቤት ምሽታችን እና ሌሎች በጎ የሆኑ የቤተሰብ ተሞክሮዎች ክፋት በልባችን፤ እና በአእምሮዋችን ምንም ቦታ ባለመተው ነፍሳችንን የእግዚአብሔር ነገሮች ሊሞሉት ይችላሉ።” (*Family Home Evening,* 1972, p. 4.)

የቤት ምሽት ለአንተ እና ለቤተሰቦችህ ምን በረከት አመጣላችሁ?

“እንደገና ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቀር በትዕግስት እና በመረዳዳት በዙሪያቸው አድርገው በእውነት እና በፅድቅ እንድትመርዋቸው በቁም ነገር እናደፋፍራችኋለን . . .

“ቤት ልጆች የሐይወት ትምህርት የሚማሩበት የመጀመሪያው እና ውጤታማ ቦታ ነው።” (የቀዳሚ አመራር፤ *Family Home Evening,* 1975, p. 3.)

**ሙከራ**

መደበኛ የቤተሰብ የቤት ምሽቶችን ማዘጋጀትን አበረታቱ። *የማቀድ፤ የትዕግስት፤ እና የፀሎት ቀመር በአምሮአችሁ ያዙ።*

በሚቀጥለው ሳምንት በቤተሰብ ምሽት እናንተ እና ቤተስባችሁ መማር የምትፈልጉትን የወንጌልመሠረተ ሀሳብ ፃፉ።

---

**የመምህር ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፡-

1. በቤተሰብ አንድነት ለማሳየት ትንንሽ የእንጨት ስብስብ ወይም የክብሪት እንጨቶች ያዘጋጁ።
2. በዚህ ትምህርት ላይ የክፍሉ አባላት ታሪኮችን እና የቀዱስ መጸሐፍት ጥቀሶችን እንዲያቀረቡ መድቧቸው።

# የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች

ትምህርት 17

የዚህ ትምህርት አላማ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን እንድንረዳ እና ሁልጊዜም እንድንሳተፍ ለማበረታታት ነው።

## የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ዓላማ

ኢየሱስ፣ "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።" (ማቴዎስ 5፡48) ብሏል። ፍጹም መሆን አስቸጋሪ በመሆኑ፣ አባታችን ረድቶናል። ቤተክርስቲያኑን አቋቁሟል፣ መሪዎችን ጠርቷል፣ እንዲሁም ትዕዛዛትን፣ ሕጎች፣ እና ሥነ-ሥርዓቶችን ሰጥቶናል። በቤተክርስቲያናችን ስብሰባዎች እነዚህን ነገሮች በተመለከተ መመሪያ እንቀበላለን። ፍጹም ለመሆን የእግዚአብሔርን ሕጎች መታዘዝ እና ማክበር አለብን። ጌታ እንዲህ ብሎ ነበር፡- "በአንድነት ስትሰባሰቡ፣ እርሱ የሰጠንን ሕግና ትዕዛዛት እንዴት እንደምንተገብር እናውቅ ዘንድ . . . መመሪያ እና መተራረሚያ ሰጥቷችኋል" (ት እና ቃ 43:8)።

የምንሳተፍባቸው የተዘጋጁ ብዙ የተለያዩ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች አሉ።

ስዕል 17-ሀ፣ የመጨረሻው እራት የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው።

የቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎች

ሐዋሪያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላሉ ቅዱሳን ሲነግር "ጌታ ኢየሱስ አልፎ በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ፡-

"አመሰገነ፥ ቆርሶም፥ እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፣

"ከእራት በኋላ ፅዋውን ደግሞ አንስቶ፥ ይህ ፅዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፣ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ፣ ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

"ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ እናም ይህንም ፅዋ በጠጣችሁት ጊዜ፣ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" (1 ቆሮንቶስ 11፡23–26)።

የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ አላማ ቅዱስ ቁርባንን እንድንካፈል ነው። ይህ ጌታ ለኛ ሲል የከፈለውን መስዋዕት ያስታውሰናል። በጥምቀት የገባነውን ቃል ኪዳን እናድሳለን። በጥምቀታችን ወቀት፣ የቤተክርስቲያኑ አባል ሆነን እናም ስሙን . . . የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ተላበስን ማለት ነው።

ስዕል 17-ለ፣ ቅዱስ ቁርባን የክርስቶስ ስጋ እና ደም መታሰቢያ ነው፣ የሚለውን ስዕል ያሳዩአቸው።

17-ሀ *የመጨረሻው እራት* በካርል ብሎች ኦሪጂናሉ በንጉሱ ጸሎት ወንበር በፌሬድሪክ ስበርግ ግምብ ላይ ዴንማርክ አገር።
በፍሬድሪክ ስበርግ ብሔራዊ የታሪክ ቤተ-መዘክር ፈቃድ የተወሰደ።
17-ለ ቅዱስ ቁርባን የክርስቶስ ስጋ እና ደም መታሰቢያ ነው።
(በመነሻው የሚታየው *የክርስቶስ* ግልባጭ ነው፣ ቅዱስ መጽሐፉ በበርተል ቶርቫልድሰን)



17-U



በት እና ቃ የምናነበው "ለጌታ ኢየሱስ መታሰቢያነት ቤተክርስቲያኑ ዘወትር ዳቦውን እና ወይኑን ለመካፈል መሰባሰቡ ጠቃሚ ነው" (ት እና ቃ 20፡75 ) ለኛ የሚቀርቡልን ዳቦ እና ውሃ "የክርስቶስ ስጋ እና ደም ምሳሌዎች ናቸው" (ት እና ቃ 20፡40)። እነዚህን ምሳሌዎች መከተል በጣም የተቀደሰ መብት ነው። ማንም ብቁ ያልሆነ ሰው ቅዱስ ቁርባን መካፈል የለበትም (3ኛ ኔፊ 18፡28–29 ይመልከቱ)።

"ቅዱስ ቁርባንን ስንካፈል ያለን ባሕሪ" በሚለው በንዑስ ክፍል ላይ የተመደበችው እህት መግለጫ እንድታቀርብ ያድርጉ፣ *Gospel Principles*, chapter 23, "The Sacrament."

የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ልጆችን ጨምሮ፣ ለሁሉም ቤተሰብ ነው። ብዙን ጊዜ ሕፃናት ልጆች በስብሰባው ላይ አርፈው ስለማይቀመጡ፣ ከስብሰባው ይጠቀማሉ ወይስ አይጠቀሙም የሚል ጥያቄ ያድርብናል። ሆኖም ግን፣ እያንዳንዱ ልጅ መማር የሚችል መንፈስ አለው። የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን መካፈል መማር የሚገባን መንፈስ እንዲማር ያደርጋል።

የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ እንድንሳተፍበት የታዘዝንበት ብቸኛ ስብሰባ ነው። ኢየሱስ ለሀዋሪያቶች የቅዱስ ቁርባን ዓላማን እና እንዴት መካፈል እንዳለባቸው ሲያስተምር እንዲህ ብሎ ነበር፣ "እናም እነዚህን ነገሮች [ዳቦውን እና ውሃውን ውሰዱ] እንድታደርጉ ትእዛዝ ሰጥቻችኋለሁ። (3ኛ ኔፊ 18:12)

"ቤተክርስቲያኑ በስሩ ባደራጃቸው ክፍሎች በየሳምንቱ *የቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎች* እንዲዘጋጁ ያዛል። እነዚህ የቤተክርስቲያኑ የተከበሩ እና የተቀደሱ ስብሰባዎች ናቸው። ዓላማቸው ምዕመናን የገቡትን ቃል ኪዳን ቀዱስ ቁርባንን በመውሰድ እንዲያድሱ፣ ከመንግስተ ሰማያት ትምህርቶች መመሪያ ለመቀበል፣ ኃያል አምላክን በመዝሙር ለማምለክ፣ ለመጸለይ እና፣ ለመስበክ እንዲችሉ ነው።" (Bruce R. McConkie, *Mormon Doctrine*, p. 661.)

### የጾም እና የምስክርነት ስብሰባ

የጾም እና የምስክርነት ስብሰባ በወር አንዴ ብዙን ጊዜ የመጀመሪያው እሁድ በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ላይ ይደረጋል። ይህ ስብሰባ የግላችን ምስክርነት በፈቃደኝነት የምንሰጥበት ነው። ምስክርነታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ተልእኮ ያለንን እምነት እና እውቀት፣ ስለ የቤተክርስቲያኑ መሪዎች ጥሪ እና ስልጣን፣ እና ስለ ጌታ ለእኛ ያለው ይቀር ባይነት ያለን የልብ ምስጋናን በአጭሩ የምንገልጽበት መሆን አለበት። እነዚህ ስብሰባዎች መንፈሳችንን ያነሳሳሉ። በእግዚአብሔር ያለን እምነት እና ታዛዥነት ይጨምራል። በጾም እና ምስክርነት ስብሰባ እንደ ልጅን መሰየም እና መባረክ እና አዲስ አባል በቤተክርስቲያኑ ማጽደቀ የመሳሰሉትን ሥነ-ሥርዓቶች ማከናወን ተገቢ ነው።

### የክህነት ስልጣን ስብሰባ

ይህ ስብሰባ የአሮን እና የመልከ ጸዲቀ ክህነቶች ላላቸው ሰዎች በየሳምንቱ የሚዘጋጅ ነው። የክህነት ሥልጣን የሌላቸው እድሚያቸው ከአሥራ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው የቤተክርስቲያኑ ወንድ አባላት ሊጋበዙ ይችላሉ።

### የሰንበት ስብሰባ ለሴቶች፣ ለልጃገረዶች፣ እና ሕፃናት ልጆች

ስብሰባው በየሳምንቱ ለሴቶች፣ ለልጃገረዶች፣ እና ለህፃናት ልጆች ወንጌልን እንዲያጠኑ ይዘጋጃል። በቂ ሴቶች፣ ልጃገረዶች፣ እና ሕፃናት ከተካፈሉ፣ ይህን ቡድን በዕድሜ ወደ

ሶስት ክፍል ለመከፋፈል ይቻላል። ሴቶች በሴቶች የመረዳጃ ማኅበር ክፍል ሲሳተፉ፣ ልጃገረዶች (ዕድሜያቸው ከአስራ ሁለት እስከ አስራ ሰባት የሚሆናቸው) በወጣት ሴቶች ስብሰባ ይሳተፋሉ፣ ህፃናት ልጆች ደግሞ (ዕድሜያቸው ከሶስት እስከ አስራ አንድ የሚሆናቸው) በልጆች ክፍል ይሳተፋሉ።

የሰንበት ትምህርት ቤት

የሰንበት ትምህርት እድሚያቸው ከአስራ ሁለት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ወጣቶች እና አዋቂዎች፣ በየሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ወንጌልን ለሁሉም ወጣቶች የማስተማር ሐላፊነት አለው።

**የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን ስኬታማ ማድረግ**

ስብሰባው ምንም ይሁን ምን፣ የተሻለ እንዲሆን መርዳት እንችላለን።

እህት ሎሮ ሲ ላንግደን ሰለራሷ ይህን ታሪክ ተናግራ ነበር፥

“በጣም ወጣት በነበርኩበት ጊዜ (ያኔ በጣም የማውቀ ይመስለኝ ነበር) ለተወዳጁ የሰንበት ትምህርት አስተማሪያችን ከአሁን በኋላ ወደ ቅዱስ ቁርባን ስብሰባ እንደማልሄድ ምክንያቱም አሰልቺ እና ደረቅ እንደሆነ መንገሬ ትዝ ይለኛል. . . . [መምህሩ] አየት አደረጉኝ እና እንዲህ አሉኝ፣ “እንዲህ ስትይ ከአሁን በኋላ እንዳልሰማሽ! እግዚአብሔር ወደዚያ ሰብሰባ በመምጣት የኢየሱስ ክርስቶስን ስቃይ እና ለእኛ የሰጠንን ስጦታ ምሳሌ እንድትካፈይ ጋብዞሻል። በመጋበዝሽ ልዩ መብት አግኝተሻል። ወደ ስብሰባው ትክክለኛ መንፈስ ይዘሽ ከሄድሽ፣ አንድ ጥሩ ነገር ከአንቺ ጋር ይዘሽ ተመለሻለሽ።’ ” (Leon R. Hartshorn, comp., *Remarkable Stories from the Lives of Latter-day Saint Women,* 1:97–98.)

እህት ላንግደን ምን እንድታደርግ መምህሯ ሐሳብ ሰጡ? ትክክለኛ መንፈስ ይዘን ከመሄድ በተጨማሪ፣ ስብሰባን ጠቃሚ እንዲሆን ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን? በጥቁር ሰሌዳው ላይ የቀረቡትን ሐሳቦች ይፃፉ።

ስብሰባውን የተሳካ ለማድረግ፣ ከልብ በሆነ ፀሎት መሄድ አለብን። ይህ እዚያ በምንሆንበት ጊዜ መንፈስን እንድንቀበል ይረዳናል። በቋሚነት በሰዓቱ መገኘት እና ያለማቋረጥ መሳተፍ እንችላለን። ለሁሉም ወዳጅ መሆን እንችላለን። በመዝሙር መሳተፍ እና በስብሰባው ለሚሳተፉት መጸም እና መፀለይ እንችላለን። ሐሳባችንን በሚባለው እና በሚደረገው በመጠበቅ፣ በአክብሮት የተሞላን መሆን እንችላለን። በምንጠየቀበት ጊዜ በፈቃደኝነት መሳተፍ እንችላለን። በፍጥነት የመንፈስ ማበረታቻ እንቀበላለን እንዲሁም ምስክርነት መስጠት እንችላለን።

እያንዳንዷ እናት ልጆቸዋን በደስታ እና በተሳካ ስብሰባን ለመሳተፍ እንዲዘጋጁ የማድረግ ልዩ ሐላፊነት አለባት። ልጆችን በጊዜው መመገብ እና ማልባበስ በመጨረሻ ሰዓት የሚኖረውን ጥድፊያ ለማስወገድ ይረዳል። በስብሰባው ስለሚደረገው ነገር በፀጥታ ለልጆች መግለፅ እንዲረዱ እና እንዲጠቀሙበት ሊረዳቸው ይችላል። መዝሙሮችን እቤት ውስጥ ማስተማር በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች በመዘመር እንዲሳተፉ ይረዳቸዋል።

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል “ወደ ሰንበት ስብሰባዎች ለመስተናገድ አንሄድም . . .ጌታን ለማምለክ ነው የምንሄደው. . . .አግልግሎቱ ያልተሳካላችሁ ከሆነ፣

እናንተ ደክማችኋል። ማንም ስለእናንተ አያመልክላችሁም።” ሲሉ አሳስበውናል። (“The Sabbath—A Delight,” *Ensign,* Jan.1978, pp. 4–5.)

በአንድ ወቀት ጆሮዋ ሙሉ በሙሉ ደንቆሮ የሆነች እህት በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ሁሌ በየሳምንቱ ትመጣ ነበር። በሚነገሩት ነገር ላይ እውነተኛ ፍላጎትዋን ታሳይ ነበር። እንዲህም ብላ ነበር፦ “በማፈቅራቸው እና ወንጌልን በሚያፈቅሩ መሐል . . . መሆንን እመኛለሁኝ። አንድም ቃላት ባልሰማም ከመንፈሳቸው ብቻ እካፈላለሁኝ እናም ንቁ ከሆንኩኝ ጌታ ሹክ ይለኛል። (Robert K. Thomas, “Listening with the Spirit,” *Ensign,* Jan. 1978, p. 40.)

የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን ስንሳተፍ፣ ጥንካሬ እና ድጋፍ ልንሰጥ እንደምንችል ሁሉ እንዲሁም ከሌሎች እንቀበላለን።

## የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን በመሳተፍ የሚገኙ በረከቶች

ለምንካፈልባቸው ስብሰባዎች አስተዋጽኦ ስለምናደርገው ነገር ተነጋግረናል። ከመሳተፍ የምናገኘውን ነገር እስኪ እንመልከት።

እህቶች የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን በመካፈል ያገኙትን ጥሩ ነገር እንዲወያዩ አድርጉ።

የቤተክርስቲያን ስብሰባችንን መሳተፍ ለጌታ ትእዛዛት በጣም ታዛዥ እንድንሆን ሊረዳን ይችላል። የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ችሎታችን እንዲሰፋ፣ ስለ ወንጌል ትምህርት እና መሠረተ ሀሳብ ያለንን እውቀት እንዲጨምር ታላቅ እምነት እና ምስክርነት እንድንገነባ ይረዳናል። በጽድቅ እንድንኖር የሚረዱንን ከጓደኞቻችን እና ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለንን ትስስር ሊያጠነክሩልን ይችላሉ። ወደ ሰማዩ አባታችን እና ወደ አዳኛችን ኢየሱስ እንድንቀርብ ያደርጉናል። የጌታ መንፈስ እንዲኖረን ይረዱናል። አዳኛችን እንዲህ ሲል ቃል ገብቶልናል “ሁለት ወይም ሶስት ሆናችሁ በስሜ በምትሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና” (የማቴዎስ ወንጌል 18፥20)። የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን መሳተፍ ለዚህ ሕይወታችን ወደ ሰላም እና ዘለዓለማዊ ሕይወት እንድንመራ ሊረዱን ይችላሉ። ስብሰባዎች ከጌታ የተሰጡን በረከቶቻችን ናቸው።

## ሙከራ

ስዕል 17-ሐ ያሳዩ፣ ለቅዱስ ቁርባን ጊዜ ሐሳቦች።

በስዕል 17-ሐ የታተሙትን ቃልኪዳኖች አንብቡ። ቢያንስ አንዱን ቃል ኪዳን ይምረጡ። የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ በረከትን እንድታገኙ ጠንክራችሁ ሥሩ። ከቤተሰባችሁ ጋር ከቤተክርስቲያን ስብሰባዎች እንዴት ብዙ መጠቀም እንደምትችሉ ተወያዩ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4፥11–13 (ቅዱሳንን ማንጻት)
ት እና ቃ 20፥45፥55 (ቄሶች ስብሰባዎችን ይመራሉ፣ ዘወትር በአንድነት ይሰበሰባሉ)
ት እና ቃ 59፥9–12 (የጌታ ቀን ማክበር)

17-ሐ በቅዱስ ቁርባን የጥሞና ግዜ።

ለቅዱስ ቁርባን መዝሙሮች የበለጠ ትኩረት እሰጣለሁኝ።

የቅዱስ ቁርባን ጸሎቶችን በጥንቃቄ አዳምጣለሁኝ።

ለራሴ እና ለኢየሱስ ትዕዛዛቱን እንደምጠብቅ ቃል እገባለሁኝ።

አእምሮዬን ከዓለማዊ ሐሳብ አስወግጄ ስለ ኢየሱስ ብቻ አስባለሁኝ።

እነዚህን ነገሮች በመፈፀም፤ መንፈሱ ከእኔ ጋር እንዲሆን አደርጋለሁኝ።

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፦

1. *የወንጌል መሰረቶች* ምዕራፍ 23፣ "ቅዱስ ቁርባን" የሚለውን ያጥኑ።
2. "ቅዱስ ቁርባን ስንወስድ ያለን ባህሪ፤" በሚለው ንኡስ ምዕራፍ ላይ አንዲት እህት መግላጫ እንድታቀርብ ይመድቡ፤ *ከወንጌል መሰረቶች፣ ምዕራፍ 23።*
3. በዚህ ትምህርት እህቶች ታሪኮች እና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# የሚሲዮናዊነት ሥራ እና ጓደኝነት

ትምህርት 18

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ የቤተክርስቲያኑ አባል ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁ አባላት በማግኘት እና በማስተማር ንቁ እንድንሆን፣ እንዲሁም አዲስ አባላት ጋር ወዳጅ መሆን እንድንችል ለመርዳት ነው።

---

**የሚሲዮናዊ ሥራ አስፈላጊነት**

የችንቴሬይዋ፣ ሚክሲካዊት እህት ፔትራ ጂ. ዴ ሔርናንዴዝ ታሪኳን እንዲህ ስትል ትናገራለች፡-

ከአስራ ዘጠኝ ዓመት በፊት ባለቤቴ በመኪና አደጋ ሞተ። ያኔ ነበር እግዚአብሔርን ከቤተሰቤ ጋር እንዲረዳኝ ማግኘትን የተመኘሁት። ትንሽዋ ሴት ልጄ የአስራ አንድ ወር ልጅ ነበረች።

"አንድ ቀን ምሽት፣ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሳለሁኝ፣ . . . ከአንድ ሰው ጋር እንደምነጋገር ያህል ለጌታ ፀለይኩኝ። በሕይወት የሚወስደውን መንገድ እንዲያሳየኝ ለመንኩት። እሱ እንዳለ እንደማውቅ፣ ግን የት እንዳለ እንደማላውቅ ነገርኩት። እሱን እንዴት ወይም የት እንደማገኘው እንዲያሳየኝ ለመንኩት። ያንን ፀሎት እስከማልረሳው ድረስ እውነቱን ለማግኘት በእምነት እና በጉጉት ነበር ያደረኩት።

"የጸሎቴ መልስ በፍጥነት ነበር የመጣው። አንድ ቀን ጠዋት ሁለት ወጣት ወንጌላውያን በሬን አንኳኩተው ከሞርሞን ቤተክርስቲያን እንደመጡ እና ጠቃሚ መልእክት ይዘው እንደመጡ ነገሩኝ። ስለ ሞርሞኖች ሰምቻለሁኝ፣ በእነሱም ምንም ያህል አልተደሰትኩም ነበር። እንዲገቡም ፈቀድኩላቸው እና የመጀመሪያውን ትምህርት ጀመሩልኝ። የመጀመሪያውን ትምህርት እንደተቀበልኩኝ፣ የሚናገሩት ነገር እውነት እንደሆነ ተሰማኝ . . . ከቤተሰቤ ጋር መጠመቅ እንደምፈልግ ነገርኳቸው . . .

"ወንጌልን ከተቀበልንበት ቀን ጀምሮ ሕይወታችን ሙሉ ለሙሉ ተለወጠ። ዛሬ እግዚአብሔር ፀሎታችንን እንደሚሰማ እርግጠኛ ሆኛለሁ . . .

"በወንጌል እና ከአስራ አምስት አመት በፊት በሬን በአንኳኩት ወንጌላውያን ምክንያት አንድነት ያለን ቤተሰብ መሆን እንደቻልን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁኝ።

"በሩን ያንኳኩትን ሁለቱን ሰዎች ሁልጊዜ አመሰግናለሁ፣ እንዲሁም ልጆቼ በራቸውን አንኳኩተው ወንጌል የሚያመጡላቸውን እንደሚያመሰግኑ አውቃለሁኝ።" (Leon R. Hartshorn, *Inspirational Missionary Stories,* pp. 123–25.)

እህቶች ላስተማሯቸው ወንጌላውያን ያላቸውን ምስጋና እንዲያካፍሉ ጠይቋቸው። እህቶች ወንጌል እንዴት እንደለወጣቸው በአጭሩ እንዲናገሩ አድርጉ።

የሰማይ አባታችን ወንጌላውያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ጋር ወደኛ በመላክ ታላቅ ፍቅሩን አሳይቶናል። እሱ ስለ ሁሉም ልጆቹ ያስባል። ጌታ እንዲህ አለ፣ "ወንጌልን ላልደረሳቸው

*ለእያንድንዱ ፍጥረት ስበኩ” (ት እና ቃ* 112:28)፣ ቤተክርስቲያኑ በ1830፣ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ፣ በሺህ የሚቆጠሩ፣ ወንዶችና ሴቶች ወንጌላውያን ወንጌልን እንዲሰብኩ ተጠርተዋል።

ፕሬዚደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እንዲህ አሉ፡-

“ጌታ በነብያቶቻችን አማካይነት ለዓለም ህዝብ ወንጌልን እንድናደርስ ግልፅ አድርጎልናል። . . .እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ቢሆንም፣ ለሁሉም በቋንቋቸው መዳረስ አለበት። ከኛ በቀር ለዓለም ህዝብ የሚያስተምር የለም። ያሉት ወጣቶች ወንዶች ቁጥራቸው የተወሰነ በመሆኑ፣ ሁሉም አባል እንደ ጌታ ትዕዛዝ ወንጌላዊ መሆን ይገባዋል ብለዋል፣

“ ‘እነሆ፣ ለሰዎች እንድትመሰክሩ እና እንድታስጠነቅቁ ልኬያችኋለሁኝ፣ እናም ማስጠንቀቂያውን የሰማ ሁሉ ጎረቤቱን እንዲያስጠነቅቀ ይሁን።’ ” (ት እና ቃ 88:81)” (“Advice to a Young Man: Now is the Time to Prepare,” *New Era,* June 1973, pp. 8–9.)

ወንድና ሴት ልጆቻችንን ወደ አገልግሎት እንዲሄዱ ማበረታታት ያለብን ለምንድነው?

በተጨማሪም ሁሉም አባል ወንጌላዊ መሆን ያለበት ለምንድነው?

## ወንጌልን ማካፈል ደስታን ያስገኛል

ዛሬ የቤተክርስቲያኑ አባሎች ነን፣ በተፈጥሮ የወንጌልን ደስታ ከሌሎች ጋር መካፈልን እንሻለን።

ት እና ቃ 18:15–16 ያንብቡ።

ፕሬዚዳንት ኪምቦል ስለዚህ ደስታ እንዲህ ሲሉ ያስታውሱናል፡- “የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሆነው፣ የደስታ ወንጌል አለን። ማንኛውንም ግለሰብ መልካም እና የተሟላ የሚያደርግ፣ ማንኛውንም ጋብቻ ደስተኛ እና ጣፋጭ የሚያደርግ፣ የትኛውንም ቤት የሰማይ ቤት የሚያደርግ እውነት አለን። ቤታችን እና ሕይወታችን እንዲሁም የሌሎችን ህይወት የምንባርክበት የእግዚአብሔር የክህነት ኃይል አለን። . . .እናም እንደተቀበልነው ደግሞ አባል ላልሆኑት ጎረቤቶቻችን እና ጓደኞቻችን እንድንሰጥ ታዘናል። ጌታ በዚህ ዓይነት እንድንፈጽመው አዞናል። ጥረታችንን ማስፋት እና አሁኑኑ መፈፀም አለብን።” (“Always a Convert Church,” *Ensign,* Sept. 1975, p. 3.)

ወንጌልን ያካፈለች እህት ምን እንዲሰማት እንዳደረጋት እንድትናገር ይጠይቁት።

## ወንጌላዊ እንዴት መሆን ይቻላል

ዛሬ ወንጌላዊ ለመሆን ምን ማድረግ እንችላለን?

የሚከተሉትን ወንጌላዊያን የመሆን መንገዶችን የሚዘረዝሩ ፖስተር ያሳዩ፣

1. እንደ ምስክር ለመቆም ድፍረት ይኑራችሁ።
2. በስሚታችሁ ስትገፋፉ ምስክርነታችሁን ስጡ።
3. የቤተክርስቲያኑን ጽሑፎች አባል ላልሆኑ ይስጡ።
4. የመንፈስ ግፍፊነት ይከተሉ።
5. አባል ላልሆኑ ቤተሰቦቻችን እና ጓደኞቻችን ጥሩ ምሳሌ እና ትዕግስት እናሳይ።
6. ጓደኞች እና የምናውቃቸው ሰዎች ወደቤታችን ወይም በቤተክርስቲያን እንዲሳተፉ ይጋብዙ።

## እንደ ምስክር ለመቆም ድፍረት ይኑርዎት

ቄስ ጄን አር ኩክ የሰባዎቹ ቀዳሚ ኮረም እንዲህ ብለው ነበር፡- “አንዳንድ ጊዜ ለባሎቻችን እውነትን መናገር ይፈራሉ። . . .ለጌታችን እና ለእሱ ነቢይ የዘመናችንን ጠቃሚ ርእስ መናገር መፍራት የለብንም።” (In Conference Report, Apr. 1976, pp. 152–53; or *Ensign,* May 1976, p. 103.) ይህ እንደ ቤተክርስቲያኑ ተጠማቂነታችን ኃላፊነታችን ነው። (ሞዛያ 18:9 ይመልከቱ)

ቄስ ኩክ አንዲት እህት እውነትን እንዴት ደፍራ እንደተናገረች ይናገራሉ፡-

“ከበርካታ የቤተክርስትያኑ አባላት ጋር በምሳ ላይ ነበረች፣ አንዳንዶቹ ቋሚ ተሳታፊ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እስከዚህም የማይሳተፉ ነበሩ፣ እንዲሁም አባል ያልሆኑ ጥቂቶች ተገኝተው ነበር። የመነጋገሪያ ጉዳያቸው ጽንስን ማስወረድ እና ወሊድን ስለመቆጣጠር በተመለከተ ሲሆን፣ እናም አባል ካልሆኑት አንዷ ይህን ርዕስ በተመለከተ ሞቀ ባለ ስሜት ለአምስት ደቂቃ ያህል ተናገረች። ጽንስ ማስወረድ ምንም ስህተት እንደሌለው እና የወሊድ መቆጣጠሪያን በተመለከተ በማንም ወንድ ወይም ሴት ላይ ምንም አይነት ገደብ መደረግ የለበትም ስትል የተሳሳተ እምነትዋን ገለጸች። ይህች ጎበዝ የቤተክርስቲያኑ እህት ስለአየሩ ታውራ፣ ወይስ ስለሌላ የሚያከራክር ርእስ ታውራ፣ ወይስ በእውነት ደፍራ እውነቱን ትናገር አስቸጋሪ በሆነ ምርጫ ውስጥ ገባች። በዚህ ምርጫ የገባችው ሴት የመጨረሻውን ለማድረግ መረጠች። ስለዚህ ጉዳይ ጌታ ምን እንዳለ ከገለፀች በኋላ፣ ስለሚሰማት ነገር ምስክርነትዋን ሰጠች እንደምትጠብቁት ሰው ባለመስማማት ተቀረጠ። ቢሆንም፣ ከዚያ በኋላ ተሳትፎ ከማያደርጉት አንድዋ እህት ወደዚህች ጎበዝ እህት ቀረበች እና ከዚህ በፊት በነዚህ ጉዳዮች ላይ የጌታ አስተያየት ምን እንደሆነ እንደማታውቀ ገለፀችለት፣ እንዲሁም በዚያን ቀን እውነት እንደሆነ እንደሚሰማት ገለፀችላት።” (In Conference Report, Apr. 1976, p. 153; *Ensign,* May 1976, p. 103.)

የማህበራዊ ጉዳይ እውነታዎችን እንዴት ልንቋቋም እንችላለን?

## ምስክርነትን በስሜት ስትገፋፉ ስጡ

ወንጌልን ለማስፋፋት ለራሳችን አጋጣሚዎችን መፍጠር እንችላለን። ከእንግዳ ሰው ጋር ውይይት ብንጀምር፣ የንግግሩን አቀጣጫ ወደ ወንጌል ማምራት እንችላለን። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት፣ ምስክርነት የምንሰጥበት መንገድ ማግኘት አስቸጋሪ አይሆንብንም።

ስሟ አሊስ ከሊተን ስሚዝ የተባለች አይነስውር እህት ከአውሮፓ ከተማ፣ ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት የወንጌላዊ አባል እንድተሆን ጥያቄ ቀረበላት። ኋደኞችዋ በሙሉ የቤተክርስቲያን አባል ስላልነበሩ፣ “እንዴት አድርጌ አንድ ሰው ወደ ቤተክርስቲያኑ ማምጣት እችላለሁኝ?” ስትል ጠየቀችው!” ታሪክዋ ይቀጥላል።

“የቀርንጫፉ ፕሬዚዳንት እንዲህ አላት፣ እህት፣ የሱን ፈቃድ ለመፈፀም እምነቱ እና ፍላጎቱ ካለሽ፣ እግዚአብሔር መንገዱን ያሳይሻል።

“ከጥቂት ሳምንት በኋላ፣ ይህቺ እህት በባቡር ትጓዝ ነበር። በጉዞዋ ላይ፣ መንገደኞች ሻንጣዋን በመያዝ በመርዳት እና በደረሰባት ጉዳት በሐዘኔታ በመርዳት ፍላጎትዋን ተንከባከቡላት። እህት “ እንዴት አድረጌ ውለታቸውን ልመልስ?” ስትል አሰበች። ከጥቂት

ደቂቃዎች በኋላ ወደ ፊት ዞር ብላ 'ለደግነታችሁ አንድ ነገር ልሰጣችሁ እፈልጋለሁኝ አለች። የምትቀበሉኝ ከሆነ፣ ለእናንተ የሚሆን ታላቅ ስጦታ አለኝ።' አለቻቸው።

"አዲሶቹ ጓደኞቿ ፈገግ አሉ። እንዴት ይህች በግልፅ ጤነኛ ያልሆነች ሴት፣ ታላቅ ስጦታ ልትሰጣችሁ ትችላለች? በማለት በጨዋ ደንብ አመስግነዋት አስፈላጊ እንዳልሆነ ነገሯት። በመጨረሻ አንድዋ ሴት 'ለመቀበል ፈቃደኛ ነኝ' አለቻት።

"አባል የሆነችው እህት እንዲህ ስትል መለሰች፡- 'ይህ ስጦታ የገንዘብ ወይም የጌጣጌጥ ስጦታ አይደለም፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር እንዳለ አውቃለሁኝ። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ አውቃለሁኝ። የእግዚአብሐርን ቃል የሚያሳውቀን የእግዚአብሔር ነብይ የሆነ ዛሬ በምድር ላይ በሕይወት እንዳለ አውቃለሁኝ። ይህን ታላቅ የእውቀት ስጦታ ልሰጣችሁ እችላለሁ።'

"ሴትየዋ ምንም እንኳን ሁኔታው እንግዳ ቢሆንባትም " እንዴት?" ስትል ጠየቀች።

" 'አድራሻሽን ስጭኝ እና የሚያብራሩልሽ ሁለት ወጣት ወንዶችን ወደ አንቺ እልክልሻለሁኝ " ይህን አለቻት' እንዳለችው አደረገች።

"[ሴትየዋ ቤተክርስትያኑን ተቀላቀለች እንዲሁም ሰባት ዘመዶችዋን እንዲቀላቀሉ አደረገች]" (Leon Hartshorn, comp., *Inspirational Missionary Stories,* pp. 168–69.)

የቤተክርስትያኑን ጽሑፍ ስጡ

የመጽሐፈ ሞርሞን ግልባጭ፣ የቤተክርስትያኑ በራሪ ጽሑፎች፣ ወይም የቤተክርስቲያኑ መጽሐፍ ሰዎች ወንጌላውያንን ለመቀበል እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል። ፓትሪሺያ ሌት፣ የምትባል የትምህርት ቤት አስተማሪ፣ የሚከተለውን ታሪክ ትነግረናለች፥

"ባለፈው ፀደይ አንድ ቀን ካሮል [ከተማሪዎቼ አንድዋ] ወንበሬ ላይ አንድ መጸሐፍ አስቀመጠች እና ማንበብ እፈልግ እንደሆን ጠየቀችኝ።

"ደህና፣ ካሮል፣ በደስታ አነባለሁኝ፣ " አልኳት።

"ትምህርት ቤት በቀርቡ የሚዘጋ በመሆኑ እና ማከናወን ያለብኝ ብዙ ሥራ በመኖሩ፣ መጽሐፉን ሙሉ ለሙሉ ረሳሁት። ነገር ግን ካርል አልረሳችም። ብዙም ሳይቆይ ትንሺ ድምፅ "ወይዘሮ ሌት መጽሐፌን አነበብሽው? . . ." ሲለኝ ሰማሁኝ።

"አንብቤዋለሁ . . .

"በሚቀጥለው ቀን የመጽሐፈ ሞርሞን ግልባጭ አመጣችልኝ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ትንሿ ድምጽ እንደገና፣ "ወይዘሮ ሌት፣ ከቤተ ክርስቲያናችን አንዳንድ ሰዎች ጋር መገናኘት ትፈልጊያለሽ?" አለችኝ . . .

"በሚቀጥለው አርብ ቄስ ግራስሌ እና ሎት ትምህርት ከማለቁ አስር ደቂቃ ቀደም ብለው ክፍሉ በር ላይ ነበሩ።" (Leon Hartshorn, comp., *Inspirational Missionary Stories,* pp.70–71.)

ሕጻናት ልጆችም ቢሆኑ ጥሩ የወንጌላውያን አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

የመንፈስ ግፊቶችን ተከተሉ

መንፈስ ቅዱስ እንደመራን ለመፈጸም ጊዜ መውሰዱ ጠቃሚ ነው። በዚያን ጊዜ ግፊቱ ያን ያህል ሊሆን ይችላል፣ እናም ማዳመጥ እና መታዘዝን መማር ይገባናል። ካትሪን ኤ. ማርቲን በመንፈስ ቅዱስ መመራትን በተመለከተ የራሷን ተሞክሮ ተነግረናለች፡-

“ትንሿን ሱቀ ያየሁበት የመጀመሪያውን ቀን አስታውሳለሁ። በዚያ ሳልፍ፣ . . .በዚያች ሱቀ አንድ ሰው የቤተክርስቲያኑ አባል መሆን አለበት የሚል እንግዳ የሆነ ስሜት ተሰማኝ። ቸኩየ ስለነበረ እንዲሁ አለፍኩኝ። . . . ትንሽዋን ሱቀ ብዙ ጊዜ አለፍኳት፣ እናም አያንዳንዱ ጊዜ ወደ ውስጥ እንድገባ የሚነግረኝ ጠንካራ ስሜት ይሰማኝ ነበር። አንድ ቀን ሱቀዋን በእግሬ ሳልፋት . . . በዚህ በሚወር ስሜት ወደ ውስጥ ተሳብኩኝ በውስጡ የሆነ መንፈሳዊ የሆነ ነገር እንደሚኖር እየነገረኝ።

“በሩን እንደከፈትኩኝ፣ . . . የፎቶግራፍ መያዣዎች በሁሉም ቀርፅ እና መጠን አየሁኝ። . . .

“ቤቱን በአይኔ ሳማትር፣ . . . ግርግዳው ላይ ያለ የስእል ቀብ አይኔን ሳበው። ስእሉ የተለያየ ዩኒፎርም የለበሱ በሰልፍ ያሉ ወታደሮች የሚያሳይ ነበር። የሆነ ነገር ይህን ስእል ከሰራው አርቲስት ጋር ስለ ወንጌል መነጋገር እንዳለብኝ ነገረኝ።

“የሱቁን ጠባቂ የአርቲስቱን አድራሻ ሊሰጠኝ ይችል እንደሆነ ጠየቀኩት። ፈራ ተባ በማለት አርቲስቱ ከስሙ በስተቀር ሌላ መረጃ እንዳይሰጥ እንዳዘዘው ተናገረ፣ ግን ከዚያም እንዲህ አለ፣ “ታውቀያለሽ፣ በዚህ ጊዜ እንደማይቃወም እገምታለሁኝ። አደውልለት እና ስምሽን እና ስልክ ቁጥርሽን እሰጠዋለሁኝ።’

“አርቲስቱ. . . . ደወለልኝ እናም ስለ አርት እና ታሪክ ለመወያየት እንድንገናኝ ወሰንን። . . .

“ሕይወቱን ወደ ጥሩ ነገር ሊለውጥ የሚችል አንድ ነገር . . . ማወቀ እንዳለበት ስነግረው ትዝ ይለኛል። ያ ምን ይሆን ብሎ ፍላጎት አደረበት ስለዚህ በድፍረት የክርስቶስ ቤተክርስተያን በምድር ላይ ማደጉን እና መቋቋሙን መናገሩን ቀጠልኩኝ። ስለ እውነት ለመፈለግ ያደረኩትን ጥረት እና ጌታ እኔን ምን እንድሆንለት እንደሚፈልግ ለማወቀ የነበረኝን ፍላጎት ነገርኩት። ከዚያም ወንጌልን ለማግኘት ያበቃኝን እንግዳ እና አስገራሚ ገጠመኝ እንዲሁም በዚያው ጊዜ በሕይወቴ የገባውን ውብ ነገር ነገርኩት. . . .

“ስለሚነገረው ነገር ተቀባይ ነበር፣ ነገር ግን ምንም መልስ ከመስጠቱ በፊት እውነቱን ማጥናት እና መመርመር ስላለበት ከመናገር ተቆጠበ። (እርሱም) እውነትን ለማወቀ ግልጽ፣ ታማኝ፣ እና ትጉህ ነበር፣ እናም ከውጪ ተቃዋሚዎች ፊት ተጠመቀ . . . በሐምሌ 18, 1969 . . .

“[እህት ማርቲን እንዲህ አለች] ጌታ በእውነት እያንዳንዳችንን ያውቀናል ይወደናል። ቃሉን ለመስማት ዝግጁ የሆኑትን ያውቃል እናም ፀሎተኛ ከሆንን እና ሐላፊነታችንን የምንወጣ ከሆነ ወደ እነዚህ ፃድቀ ሰዎች ይመራናል። የሌሎችን ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደራሳችን የምናፈቅር እና ግምት የምንሰጥ ከሆነ ብቻ የሚሰጥ ውብ የሆነ በመንፈስ ሹክሹክታ የሚሰጥ ስጦታ አለኝ።” (Margie Calhoun Jensen, comp., *Stories of Insight and Inspiration,* pp. 124–25.)

እህት ማርቲንን በተለያዩ ጊዜ ይህን ሰው እንድታገኝ መንፈስ እንዴት ገፋፋት? አንዳንድ ጊዜ የመንፈስን ገፋፊነት ለመከተል ተደንቃችሁ ግን ጊዜ የለኝም ብላችሁ ወስናችሁ ነበር?

አባል ላልሆኑ ቤተሰቦቻችን እና ጓደኞቻችን ጥሩ ምሳሌ እና ትእግስት ማሳየት

ቄስ ኤድኒይ ዋይ ከማትሱ፣ የሰባዎቹ የመጀመሪያ ኮረም እንዲህ ብሎ ነበር።

"እዚህ አብዛኞቻችሁ ቤተክርስቲያኑን ስትቀበሉ የቤተሰባችሁ ፈር ቀዳጆች ናችሁ። በእርግጥም እናንተ የቤተሰባችሁ እውነተኛ ፈር ቀዳጆች ናችሁ . . .

"ከወላጆቻችሁ፣ ጓደኞቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስለ ወንጌል ህጎች ስትወያዩ ልታስተምሯቸው የምትሞክረውን መሠረተ ሀሳቦች ባያዳምጡ ወይም ባይገባቸው ተስፋ አትቁረጡ። ትእግስተኞች እና ወላጆቻችን፣ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን፣ እና ጓደኞቻችን በሕይወታችን በጣም ጠቃሚ ሰዎች እንደሆኑ ማስታወስ አለብን። እናፈቅራቸዋለን፣ እንዲሁም ምርጥ የሆነው ነገር እንመኝላቸዋለን፣ ይህም የኢየስሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነው። በዚህ አለም እና በሚመጣው አለም የግል ደስታችን የቤተሰብ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያካትታል።

"ባለማግባታችሁ፣ አሁንም ከወላጆቻችሁ እና ከወንድሞቻችሁ ጋር የምትኖሩ እና አዲሱን ሕይወታችሁን ያልተቀበሉ እንደሆነ፣ አክብሯቸው፣ አፍቅሯቸው እንዲሁም በምሳሌያችሁ ውብ የሆነውን የወንጌል እውነት አሳዩዋቸው።" (In *Official Report of the Korea Area Conference,* Aug. 1975, p. 4.)

የሚስዮናዊነት ሥራ የሚፈፀመው ለራሳችን ክብርን ለማምጣት አይደለም። ልንረዳቸው የመረጥናቸውን ሰዎች ማፍቀር ይገባናል። ምንም እንኳን ወንጌልን ባይቀበሉ ወይም ብዙ አመታት ቢወስድባቸውም ልባዊ የሆነ የማያልቅ ወዳጅነታችንን መስጠት ይገባናል።

ጓደኞችን እና የምናውቃቸውን ሰዎች ወደ ቤታችን ወይም ቤተክርስትያን እንዲሳተፉ መጋበዝ

ቤተክርስቲያኑን ሌሎች ከእኛ ጋር እንዲሳተፉ በመጋበዝ ማስተዋወቅ እንችላለን። ከሌላ ቤተሰብ ጋር ልዩ የቤተሰብ ምሽት ማዘጋጀት እና ወንጌላውያን እንዲገኙ ማድረግ እንችላለን። አባል ያልሆኑ ጓደኞቻችን እና ወላጆቻችን ሁሉ ከእኛ ጋር ቤተክርስቲያን እንዲሳተፉ መጋበዝ አለብን። ምን አይነት ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳለን ለራሳቸው እዚያ መፍረድ ይችላሉ። ከዚያም የበለጠ ማወቅ ካለባቸው መወሰን ይችላሉ።

እህት ቪላፍራንካ ከሳን ፈርናንዶ፣ ሜክሲኮ፣ ወንጌላውያን ልዩ የሰንበት ትምህርት ባዘጋጁበት ባለ አንድ ክፍል ቤት ሃምሳ ሰዎችን ጋበዘች። በኋላም ሰዎቹ ለመጀመሪያው ውይይት እንዲቀሩ ተጋበዙ። ከነዚያ አብዛኛዎቹ ተጠመቁ እናም በስድስት አመት ውስጥ በሳን ፈርናንዶ ሁለት መቶ አባላት ያሉበት አንድ ቅርንጫፍ ተቋቋመ። (See Glenn V. Bird, "Miracle at San Fernando," *New Era,* Jan. 1977, pp. 28–29.)

አንድ ወይም ሁለት እህቶች ለቤተክርስቲያኑ እንዴት ፍላጎት እንዳደረባቸው በአጭሩ እንዲናገሩ ያድርጉ።

**እርስ በርሳችን መወዳጀት**

በመሐላችን አዲስ አባላት እንዲኖሩ፣ ወዳጆቻቸው እና ረዳታቸው እንድንሆን ያለንን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለብን። እንግዳነት ሊሰማቸው ይችላል። እንዲረጋጉ ማድረግ አለብን። በቤተክርስቲያን ይህን "ወዳጅነት" እንለዋለን።

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እርስ በእርሳችን መፈቃቀር እና ወዳጆች መሆን ስላለብን ሐላፊነት ያስገነዝቡናል። ኢየሱስ እና ሐዋሪያቶቹ ሰለአስተማሯቸው የመጀመሪያወቹ የቤተክርስቲያን አባላት ተናገሩ፣ ከዚያም እንዲህ በማለት ሲቀጥሉ፦

“በነዚያ በጥንቶቹ ብዙዎች የቤተክርስቲያን ቀርንጫፎች ያበቡትን ወዳጅነት እና ወንድምነት ማየት አስደሳች ነበር። ለእያንዳንዱ ዘለዓለማዊ ደህንነት አሳቢነት፣ ለእያንዳንዱ አካላዊ ደህንነት አሳቢነት ነበር፣ በመሐላቸው ፍቅር ነበር፣ ምናልባትም በዘመናችን ለወንድማችን እና እህታችን እንዳለን ውብ ፍቅር ሊሆን ይችላል።

“ብዙ ጊዜ እነዚህ የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን አባላት በእውነት እርስ በእርሳቸው እንደተማሩት እንደ ወንድም እና እህት ተቀብለው ይሆን? እያልኩኝ እገረማለሁኝ . . .

“ሁሉም በፍቅር እና በወንድምነት ያለምንም ምቀኝነት፣ ቀናት ወይም ያለምንም የማዕረግ፣ ወይም ትምህርት ወይም ዜግነት ክፍፍል አብረው ሰርተዋልን? ጌታ በጌተሰማኒ በመጨረሻ ሰዓቱ ‘እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት’ ሲል እንዳስተማረ በእርግጠኛ ለእኛም ግልጽ ነው። (ዮሐንስ 15፡12)

“ዛሬ መልእክቱ ለእኛም ተመሳሳይ ነው። . . . በመሐላችን አዲስ አማኞች እንደሚኖሩ፣ በክርስቶስ እቀፍ ስር ወንድሞች እና እህቶች “በጓደኞቻቸው እና ጎረቤቶቻቸው ጥረት እንዲመጡ የጌታ እቀድ ነው። በእውነተኛ የወንጌል መንፈስ እርስ በእርሳችን ወዳጅ መሆን እና መፋቀር አለብን።” (“Always a Convert Church,” *Ensign,* Sept. 1975, pp. 3–4.)

ኤፌሶን 2፡19–20 ያንብቡ። አዲስ አባላትን እንደምናፈቅራቸው እና እንደተቀበልናቸው እንዴት ማሳየት እንችላለን?

አዲስ አባላት ቤተክርስቲያኑን እንዲሳተፉ በመጋበዝ ልንረዳቸው እንችላለን። በቤተክርስቲያኑ እና በአካባቢያችን ጓደኛ ልንሆናቸው እንችላለን። ወደ ስብሰባችን የሚመጡ እንግዶችን ሁልጊዜ መልካም አቀባበል ልናደርግላቸው ይገባናል። ወንጌልን ለአለም መስበክ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሐላፊነት መሆኑን መገንዘብ አለብን። ይህን ለማድረግ፣ ሁላችንም ወንጌላዊ መሆን አለብን። ጓደኞቻችን እና ጎረቤቶቻችን የወንጌልን ትምህርት እንዲቀበሉ ማዘጋጀት አለብን። ለዚህ ሁሉም ወደ አለም ዙሪያ መሄድ አስፈላጊ አይደለም፣ ግን ለጓደኞቻችን እና ጎረቤቶቻችን ስለ ወንጌል መንገር ይገባናል። በተጨማሪም፣ ለጌታ ትእዛዛት ታማኝ በመሆን በአካቢያችን ላሉት የዘለአለማዊ ሕይወትን መንገድ እናሳያቸዋለን።

### መልመጃ

የሚስዮናዊ ሥራ ለመስራት አንዱን መንገድ በፀሎት ይምረጡ። አንድ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ ለማስተማር ይምረጡ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብ በፊት፣

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳብ፣* ምዕራፍ 33 “የወንጌላዊ ሥራን” ያንብቡ
2. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔን ያዘጋጁ።
3. የሚለጠፍ ማስታወቂያ ያዘጋጁ (ገጽ 132 ይመልከቱ)።
4. ታሪኮችንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቀሶችን በዚህ ትምህርት ላይ እንዲያቀርቡ የክፍል አባላትን ይመድቡ።

# ሚሲዮናውያንን ማዘጋጀትና ማበረታታት

ትምህርት 19

የዚህ ትምህርት ዓላማ ወጣቶቻችንን ለማዘጋጀትና የሚስዮን ጥሪያቸውን እንዲያሟሉ እንዴት እንደሚረዳን ሊያስተምረን ነው።

## ወጣቶቻችንን ለሚስዮናዊነት ማዘጋጀት

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ወንጌልን ለዓለም እንዲያዳርሱ ተጨማሪ ሚሲዮናውያንን ጠየቁ፣ ሆኖም እነርሱም ከቀድሞው በተሻለ መዘጋጀት እንዳለባቸው አጥብቀው አሳስበዋል። "እያንዳንዱ ወንድና ብዙ ልጃገረዶች እናም ባልና ሚስቶች በሚስዮናዊነት ማገልገል አለባቸው። እያንዳንዱ ዕጩ ሚሲዮናዊ ሕይወቱን በሙሉ በታማኝነት፣ በቀልጥፍና፣ እናም በታላቁ የወንጌላዊ ሥራ ፕሮግራም በአግባቡ ለማገልገል *በህሊናዊ፣ በመንፈሳዊ፣ በአዕምሮአዊ* እናም *በገንዘብ* መዘጋጀት አለበት" ብለዋል። ("Advice to a Young Man: Now Is the Time to Prepare," *New Era,* June 1973, p. 9. italics added.)

ፕሬዚዳንት ኪምቦል ሚሲዮናውያንን የማሰልጠኑ ሃላፊነት በይበልጥ የሚወድቀው በወላጆች ላይ ነው ሲሉ አጥብቀው አሳስበዋል። ሚሲዮናውያኖቻችንን እያንዳንዱ ተልዕኮውን በታላቀ ደስታ ይጠብቁ ዘንድ "በተሻለ፣ ቀደም ብሎ፣ ለረዥም ጊዜ፣ እንድናሰለጥናቸው ጠይቀውናል" ("When the World Will Be Converted," *Ensign,* Oct. 1974, p. 7)።

ወጣቶችን በጣም በልጅነት ዕድሚያቸው ለወንጌላዊነት አገልግሎት እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን?

ስዕል 19- ሀ፣ ወጣቱ ልጅ በሚሲዮን መዋጮ ሳጥኑ ውስጥ ገንዘብ ሲቀጥር ያሳያል።

ቄስ ኤስ ዲልወርዝ ያንግ የቀዳሚ የሰባዎቹ ቡድን ወጣት ልጆችን ለወንጌላዊ አገልግሎቶች ለማዘጋጀት አጋዥ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። እርሳቸውም ተልዕኮው እንዲሳካ ለማድረግ በየጊዜው ከልጆቻችን ጋር ሆነን የሰማዩ አባታችንን በፀሎት መጠየቅ አለብን ብለዋል። ለቤተሰቦቻችንም የራሳችንን የሚስዮናዊነት ተሞክሮዎችና ታሪኮችን መንገር አለብን ብለዋል። እርሳቸው ደግሞ በተጨማሪም ወጣቶችን ከቅዱሳን መጻሕፍት ጋር እንዲላመዱ፣ ታዛዥነትን በማስተማር እናም ሌሎችን እንዲያገለግሉ ዕድል በመስጠት እንረዳለን ብለዋል። ቄስ ያንግ በሰጡት አስተያየታቸው እነዚህን ታላላቅ እውነቶች በቤተሰብ የቤት ምሽት ትምህርት ወቀት፣ በምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ፣ ከመኝታ ሰዓት በፊት ባለው ጊዜ፣ እናም በቤተሰብ የመዝናኛ ጊዜ መስጠት ይቻላል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። (See "Missionary Training Begins Early," *Ensign,* July 1972, pp. 76–77.)

ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ዲ. ሪቻርድስ የቀዳሚ ሰባዎቹ ቡድን ሲናገሩ፣ "እኔ ወጣት ልጅ በነበርኩ ጊዜ፣ ማድረግ ከምመኛቸው ነገሮች አንዱ ለሚስዮናዊነት መሔድን ነበር . . . በእኔ

19-ሀ ወጣቱ ወንድ ልጅ በሚስዮኑ የመዋጮ ሳጥኑ ውስጥ ገንዘብ ሲቀጥር።



ውሳኔ ቤተሰቦቼ አስፈላጊ ሚና የሚጫወቱ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ። ሴት አያቴ፣ ጀኒ ስኒደር ሪቻርድስ፣ ስለወንድ አያቴ የነገሩኝንና ያደመጥኩትን ታሪኮች አስታውሳለሁ . . . በጣም ነው ያደነቀሁት። ታላቅ ሚስዮናዊ ነበር፣ በሕይወት ዘመኑ በተለያዩ ሚስዮኖች አገልግሏል። ይህ ሁኔታ ተፅዕኖ እንዳሳደረብኝ እርግጠኛ ነኝ።" ("Have a Dream," *New Era,* Jan. 1978, p. 4.)

ስዕል 19-ለ፣ በሥዕላዊ መግለጫው እናት ልጇን ለሚስዮናዊነት ሕይወት ስታዘጋጅ አግባብ ያለውን የምግብ ዝግጅት በማስተማር እንደሆነ ያሳያል።

ወጣት ልጆቻችን በሚስዮናዊነት አገልግሎታቸው ወቀት እንዳይዳከሙ አካላዊ ጥንካሬ እንዲኖራቸው መርዳት አለብን። ቀለል ያሉ እና ገንቢነት ያላቸውን ምግቦችን በማዘጋጀት እና በብልሃት መሸመትን መማር አለባቸው። ጥሩ የአመጋገብ ልምድ በሚገባ የሚጠብቁ ከሆነ፣ እናም ለሥራቸው ጉልበት የሚሰጡ ከሆኑ አስፈላጊ ናቸው። ልብሳቸውን አጥበውና በመተኮስ የተቀደደውንም በመጣፍ ልናስተምራቸው ይገባል። የሚኖሩበትን አካባቢያቸውን በጽዳት መጠበቅ እንዳለባቸው ደግሞ ማስተማር እንችላለን። አግባብ ያለውን ልብስ በመልበስና በአለባበስ ሥርዓታቸው ኩራት እንዲሰማቸው መማር ይችላሉ። የገንዘብ ቁጠባን፣ አሳሳቢ ጋብቻን ማዘግየትን፣ ምስክርነት ማግኘትና መስጠት፣ እናም የንስኀን ቀደም ተከተል መከተልን መማር ይችላሉ። ይህን ሁሉ ወደ ሚስዮን መስክ ከመሔዳቸው በፊት ማድረግ ይችላሉ።

ወጣቶችን ለሚስዮናዊ አገልግሎት ገንዘብ እንዲያገኙ እና እንዲቀጥቡ እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

ቄስ ኤም ሩሴል ባላርድ የሚስዮን ፕሬዚዳንት ሆነው ባገለገሉበት ወቀት፣ የራሳቸውን ወንጌላዊያን ይህን ጥያቄ እንዲመልሱላቸው ጠየቁ፣ "እኔን በተሻለ ሁኔታ ለማዘጋጀት እናቴ ምን ማድረግ ትችል ነበር?"

"እነርሱም 'እማማ ስለ ቤት አጠባበቅ . . . ምግብ ማብሰል፣ በጽዳት በመጠበቅ፣ ልብስ በማጠብ፣ ተክራክሮ ከሱቅ መሸመትን፣ በግል ንጽህና፣ በጥገና፣ በፈጣን የምግብ አሰራር መምሪያን ልታስተምረኝ በምትሞክርበት ጊዜ እንደምንም የበለጠ ትኩረት እንድሰጥ ግፊት ልታደርግ ይገባት ነበር።' አሉ።"

ቄስ ባላርድ ይህን ምክር ሰጡ፣ "እናቶች፣ ልጆቻችሁ የሌሎች ፍላጎት እንዲገባቸውና እንዲያውቁ አስተምሯቸው። ጥሩ የሰብአዊ ግንኙነቶችን ከመሰረታዊ ግብረገብ ጋር እንዲያውቁና እንዲላመዱ አስተምሯቸው . . .ልጆቻችሁን እቀፉአቸውና፣ በዓይናቸው ውስጥ በትኩረት በማየት፣ እናም እነዚህን ሙያዎች እንዲማሩ ንገሯቸው፣ ምክንያቱም በሚስዮን ሥራቸው ወቀት እንዲደሰቱና እንዲሳካላቸው ትፈልጋላችሁና።" ("The Making of a Missionary," *Ensign,* Nov. 1976, p. 88.)

ልጆቻችን የሌሎችን ፍላጎቶች እንዲያውቁ እንዴት መርዳት እንችላለን? በምግብ ወቀት? በጓደኞች ቤቶች? በሕዝባዊ ሥፍራዎች?

ጌታ እንደጠየቀው ጥሪያቸውን እንዲያሟሉ፣ ሚሲዮናዊያኖች የስራን ደንብ መማር አለባቸው። በመጽሐፈ ሞርሞን፣ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብኩ "በሙሉ ትጋት" እና "በሙሉ ኃይላቸው" እንዲያስተምሩ ይመከራሉ። (ያዕቆብ 1፥19)። የራሱን ታታሪነት የሚያሳይና በጥንካሬ የሚሰራ ሚሲዮናዊ ደስተኛና ውጤታማ ነው።

19-ለ አግባብ ያለውን ምግብ ማዘጋጀትን በማስተማር እናት ልጇን ለወንጌላዊ ሕይወት ስታዘጋጅ።



ሌላው የሚሲዮን ፕሬዚዳንት (ቂስ ቫን ጂ ፌዘርስቶን) ይህን ታሪክ ተናገሩ፣

“በሚሲዮናችን አንድ ቄስ በጣም ከባድ የጤና ችግሮች ነበረበት . . . እኔ በሚስዮኑ ስደርስ፣ ድክመትንና ጉንፋንን ለማስወገድ ዘግይቶ ይተኛ ነበር። ከዚያም ለምሳ በገባም ጊዜ ራሱን ከብርድና ከጉንፋን ለመጠበቅ ለብዙ ሰዓቶች ይተኛል። ጓደኛው ይህን ሁኔታ ፈርቶ እኔን ጠራኝ።

“እኔም የቄሶችን ሐኪም ጠራሁ። እርሱም መጥቶ አይቶት፣ ‘ደህና፣ የእርሱ ሁኔታ አስጊ ነው፣ ነገር ግን ከዚህ ቀደም ከነበረበት አሁን ወደ ሚስዮን መስክ ከመጣ በኋላ የተሻለ ነው አለ። የፈለገውን ያህል ሰዓቶች ቢሰራም ብዙ ለውጥ አይኖርም።’ ቄሱን ወደ ቢሮ ጠራሁትና ሁሌ ለዚህ ከመጨነቀ ይልቅ በጉንፋን ህመም እርሱን ማየት የሚሻል እንደሆነ አስተያየቴን ሰጠሁት። ዝም ብሎ ወደ ስራው በመሔድ እና ጌታ እንዲያደርግ የጠራውን እንዲሰራ በሚሉ መመሪያዎች ተነጋገርን . . . ከእርሱም ጋር በመሰረተ ሃሳቡ ላይ ተወያየንበት . . .

“እርሱም ምክሩን ተቀብሎ ተግባራዊ አደረገ። በሚስዮኑም ውስጥ በጣም ጎበዝ ከሆኑት ወንጌላውያን አንዱ መሆን ቻለ። እንዴት እንደሚሰራም . . .ተገነዘበ።” (“Self-Denial,” *New Era,* Nov. 1977, p. 7.)

ወጣቶች ሴቶች ወጣት ወንዶችን ለሚስዮን ስራቸው ዝግጅት እንዴት ማግባባት ይችላሉ?

ወጣት ሴቶች በከፍተኛ ሁኔታ በወጣት ወንዶች ጸባይ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ይችላሉ። ወጣት ሴቶች ከፍ ያለ የስነ ምግባር የአለባበስ፣ የአነጋገር፣ እና የምግባሮች መለኪያዎችን ማሳየት አለባቸው። እርሷ ሁልጊዜ የሴትነት የፍቀር ባህሪይ ምሳሌ መሆን አለባት። ለቤተክርስቲያኑ ወጣት ሴቶች ቄስ ዴቪድ ቢ. ሔይት ሲናገሩ፣

“እናንት ወጣት ሴቶች ለወጣት ወንዶቻችን በዚህ ዝግጅት እና ቅድመ ስልጠና በጣም አስፈላጊ ሚና አላችሁ . . .

“እናንተ፣ የጽዮን ሴት ልጆች፣ ትክክለኛ አርአያ ስትሆኑ የሚያበራ ብርሃን መሆን ትችላላችሁ። ያለ ጊዜ ጋብቻን ከማድረግ ወይም ለዕድገታችሁ ከማይመች አካሄድ ተቆጠቡ. . . . አዕምሮአችሁንና ሁለንተናችሁን አዳብሩ . . . ሁለታችሁም ልትካፈሉትና ልታሳድጉት የምትችሉት የተፈጥሮ ስጦታዎች አሏችሁ።

“ታላላቅ መጽሐፍቶችን አንብቡ። መልካም ሙዚቃዎችንም አዳምጡ። በጥበብ ቃል ውስጥ የተጠቃለሉትን በረከቶች አጥኑ እናም ተወያዩበት . . .

“ቅዱሳን መጽሐፍትን አንብቡ. . . .

“ወጣት ወንድን በአስጊ ህይወቱ ወቀት ማበረታታት፣ ማግባባት፣ እና ማዳን ትችላላችሁ . . . በዚህ ዓይነት ወጣት ወንድን ብቁ እንዲሆንና ጌታን ለመርዳት እንዲዘጋጅ ስትረዱ ለጌታ ፍቀራችሁን ገልጻችኋል ማለት ነው።” (“Young Women—Real Guardians,” *Ensign,* Nov. 1977, pp. 57–58.)

ወጣት ሴቶች ወጣት ወንዶችን ማክበርና ሚሲዮናዊያንን የማገልገል ፍላጎታቸው እንዲኖር ማድረግ ጠቃሚ ነው። ማንኛውም የጋብቻ ሃሳብ ወጣቱ ሚሽኑን ፈጽሞ እስከሚመለስ ድረስ መቆየት አለበት።

## ሚስዮናውያን ጥሪያቸውን እንዲፈጽሙ መርዳት

አብዛኛውን ጊዜ ስለምናውቃቸው ሚስዮናውያን፣ በተለይም ቀደም ሲል ወንጌልን ያስተማሩንን እናስባለን። መስዋዕትነታቸውንና አርአያነታቸውን እናደንቃለን። ሌሎች ሚስዮናውያን ጥሪያቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲያከናውኑ እነርሱን በመርዳት ለሰማዩ አባታችን ምስጋናችንን እንገልጻለን። ወጣት ሴቶቻችንና ወንዶቻችን በሚስዮናዊነት በሚያገለግሉበት ጊዜ፣ የማያቋርጥ እርዳታና ድጋፋችንን ይሻሉ። ለእነርሱ ልንፀልይላቸው እንችላለን እናም እነርሱም የፀሎትን አስፈላጊነት መረዳታቸውን እርግጠኛ እንሆናለን።

ቄስ ሐፍ ቢ. ብራውን በእንግሊዝ በሚስዮናዊ አገልግሎት ላይ በነበሩበት ወቀት እናታቸው በጌታ ላይ መተማመን እንዴት እንዳለባቸው እንደረዷቸው ተናግረዋል። እርሳቸው እንደሔዱ እናታቸው እንዲህ አሏቸው፣ "ልጄ፣ ሐፍ፣ ሕፃን ልጅ በነበርክበት ጊዜ ብዙውን ጊዜ መጥፎ ሕልሞችን ታልም ነበር፣ እኔ በሚቀጥለው ክፍል ስተኛ "እናቴ፣ አለሽ እንዴ?" እያልክ ስትጣራ እንደነበር ታስታውሳለህ?" እኔም ሁልጊዜ "አዎን፣ ልጄ፣ እዚህ ነኝ። ሁሉም ነገር ደህና ነው፣ ስልህ ቀና ብለህ ተመልክተህ የምትተኛውን፣ ታስታውሳለህ?" 'እሺም ልጄ፣ አሁን አምስት ሺህ ማይልስ፣ አህጉራትና ውቅያኖስ ይለየናል አለችኝ። ከእንግዲህ በሌሊት ብቻ፣ መጥፎ ሕልም አይኖርህም፣ ነገር ግን በቀንም ወቀት፣ ብዙ ጊዜ፣ የምትሄድበት ጠፍቶህ ግራ በተጋባህ ጊዜ "አባት ሆይ እዚህ አለህን?" ብለህ ተጣራ፣' ብላኝ፣ 'ልጄ ቃል እገባልሃለሁ እርሱ ሁልጊዜ ይመልስልሃል እናም መፍራት የለብህም አለችኝ።' " (*The Abundant Life*, pp. 202–3.)

ወንጌላዊያን ጥሪያቸውን እንዲያከናውኑ ሌላ በምን መንገድ መርዳት እንችላለን?

ከቤት ደብዳቤ መኖር አለበት። ቄስ ጎርደን ቢ. ሂንክሊ ለወንጌላውያን መጻፍን በተመለከተ የሚከተለውን ምክር ስጥተዋል፣ "ቋሚ ደብዳቤ ከቤተሰብ ስለማያገኝ ሚስዮናዊ ልቤን ሃዘን ይሰማዋል። በአጠቃላይ በሳምንት አንድ ጊዜ ድብዳቤ ማግኘት መልካም ደንብ ነው። ሆኖም ግን በሌላ መንገድ፣ በጣም ብዙ ደብዳቤዎች የሚስዮናውያንን ግብረገብ ያበላሻሉ። ሚስዮናዊው ብቁ ለመሆን ከቤተሰብ መራቅ አለበት፣ ስለዚህ የሚቀበላቸው የደብዳቤ ዓይነቶች ከሚያደርገውና ከሚሰማው ሰፊ ልዩነት ያደርጋል። የሚላኩት ደብዳቤዎች የቤተሰብን ችግሮች የሚያሳዩ፣ በመከራዎች ላይ የተመረኮዙ ከሆኑ፣ የሚስዮናዊውን አዕምሮ ይጎዳሉ። ብልህ ደብዳቤ ፀሐፊዎች ቀና ስሜቶቻቸውን ብቻ ለመግለጽ እርግጠኛ ሆነው ይጽፋሉ. . . . በመስበክ አገልግሎት ላይ ስላላቸው ሚስዮናውያን ምንኛ ኩራት እንደሚሰማቸው፣ ለስራው በማገልገላቸው ጌታ እንዴት እንደሚባርካቸው ይገልጻሉ። እንደዚያ ያሉ ደብዳቤዎች የወንጌላዊውን ሕይወት ይባርካሉ፣" (Quoted by Brian Kelly in "A Visit With Gordon B. Hinckley about Missionary Work," *New Era,* June 1973, p. 32.)

ወጣት ሴቶች ለሚስዮናውያን ምን ዓይነት ደብዳቤ መጻፍ አለባቸው?

ወጣት ሴቶች ቅዱስ መጻህፍትን ማንበብና ከሚስዮናውያን ጋር መንፈሳዊ ልምዶችን ማካፈል፣ የወዳጆችንና የቤትን አስደሳች ዜናዎች ጭምር መንገር አለባቸው።

በክልላችን ሚስዮናውያንን መርዳት የምንችልበት አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው?

አባል ያልሆኑትን ቤተሰቦችና ወዳጆቻችንን ለሚስዮናውያን ማስተዋወቅ እንችላለን። ድግሞም የሚስዮናውያንን ጊዜ ላለመጣስ መጠንቀቅ አለብን። ለምግብ ወደ ቤቶቻችን

ስንጋብዛቸው፣ በቀልጥፍና ልናስተናግዳቸው እንችላለን። ከዚያም ሄደው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማበረታታት እንችላለን። በማድቤት ሥራዎች እንዲረዱ መጠበቅ ወይንም መፍቀድ የለብንም። ከእኛ ጋር ቴሌቪዥን እንዲከታተሉ መጋበዝ የለብንም። የሚስዮን ሕጎችን በመማር እናም ሚስዮናውያን እንዲያከብሩት መርዳት እንችላለን።

ወጣት ሴቶች በተለይም እርባናቢስ በሆነ ተግባር የሚስዮናውያንን ጊዜ ከመውሰድ መቆጠብ አለባቸው። ወጣት ሴቶች ከሚስዮናዊ ጋር ለብቻ በፍጹም መሆን ወይንም ከእርሱ ጋር በቀርበት ግንኙነት ለመፍጠር ማደፋፈር የለባቸውም። ወጣት ሴቶች ከሚስዮናውያን ጋር በክልላቸው በመጻጻፍ ወይንም በስልክ መገናኘት የለባቸውም።

ለሚስዮናውያን እና ለጥሪያቸው ሁላችንም አክብሮት ስናሳይ፣ ለሌሎች ወንጌልን እንዲያስተምሩ እንረዳቸዋለን።

**ማጠቃለያ**

ቄስ ጎርደን ቢ ሂንክሊ "የወንጌላዊ ሥራ ቀላል ሆኖ አያውቅም፣ እናም አስደሳች ዋጋው ከማንኛውም ሌላ ተሞክሮ ጋር ሊወዳደር አይችልም። ማንኛውንም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ከፍ ያለ ዋጋ ያለው በጣም ውድ የሆነን ነገር ለማስተማር ዘዴን በመፈለግ እናም ጊዜን በመሰዋት ማስተማር ነው" ብለዋል። (Quoted by Brain Kelly in "A Visit with Gordon B. Hinckley about Missionary Work," *New Era,* June 1973, p. 30.)

በሴትነታችን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ፣ ወጣቶቻችን እንዲዘጋጁና የሚስዮን ጥሪያቸውን እንዲያከናውኑ ለመርዳት የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን። ጥረታችን እነርሱ ለሚስዮናዊነት ቢሄዱም ባይሄዱም ልዩነትን ያደርጋል። ማበረታታችን በሚስዮን መስክ ክንዋኔአቸው ወቅት ታላቅ ልዩነትን ያደርጋል። ሚስዮናውያኖቻችን ለወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደህንነትን የማምጣት ደስታን ለመለማመድ እንዲዘጋጁ መርዳት እንችላለን። (ት እና ቃ 18፥15-16 ይመልከቱ።) በየጊዜው ጥረቶቻችንን መገምገም አለብን፣ ለሃሳቦቹ የቤተክርስቲያኑን መሪዎችና ሌሎች አባላትን ማነጋገር፣ እናም ሚስዮናውያኖቻችንን ወንጌልን ለዓለም እንዲያዳርሱ ስንረዳ የሰማዩ አባታችንን በመንፈስ እንዲያነሳሳን እንጠይቃለን።

**ሙከራ**

ይህን ትምህርት በቤት ያንብቡ። ወንዶችና ሴቶች ልጆችዎን ለሚስዮናዊነት እንዲዘጋጁ ለመርዳት አንዳንድ መንገዶችን ይምረጡ። ያላገቡ ከሆነ ጠባይዎን ከዕጩ ሚስዮናውያንና በክልልዎ በአገልግሎት ላይ ከሆኑት ሚስዮናውያን ጋር ራስዎን በማዛመድ ይገምግሙ። በመስክ ላይ ለሆነ ሚስዮናዊ በቋሚነት ለመጻፍ የቤተሰብ ፕሮጀክት ይኑርዎት።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1ኛ. *ከወንጌል መሰረተ ሃሳቦች*፣ "የሚስዮናዊ ሥራ" ምዕራፍ 33 ያጥኑ።

2ኛ. በዚህ ትምህርት ላይ ታሪኮችንና የመጽሃፍ ቀዱስ ጥቅሶችን የክፍሉ አባላት እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# ቤቶቻችንን በሚገባ ማስተዳደር

ትምህርት 20

የዚህ ትምህርት ዓላማ ቤቶቻችንን እንድናደራጅና ጊዜያችንን በጥሩ ሁኔታ እንድንገለገልበት ለማድረግ እንዲረዳን ነው።

"ሥርዓትንና ንጽህናን በተለያዩ ሥራዎቻችሁ አጥኑ . . . ቤታችሁን አስደሳች አድርጉ፤ እናም ልባችሁን በእግዚአብሔር ፀጋ የተሞላ እንዲሆን አድርጉ።" (*Discourses of Brigham Young,* p. 200.)

## ጥሩ ሥርዓት ያላቸው ቤቶች ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን እንድናደርግ ያስችሉናል

እንደ ቤት አዘጋጆች፣ ከሥራችን ክፍል አንዱ የሰለጠኑ የቤት ጠባቂዎች ለመሆን ነው። ቤቶቻችንን በንጽህና ስንጠብቅ፣ ነገሮችን ለመፈለግ ጊዜን ማጥፋት አንችልም። ጥሩ ሥርዓት መያዝ የኩራት ስሜት እንዲያድርብን ያደርገናል። ስለሆነም በቤታችን ውስጥ ባለው ሰላማዊ ሁኔታ እንደሰታለን። የፈለግነውን ማንኛውንም ነገር በፈለግንበት ወቀት ማግኘት እንችላለን። በሚገባ የተደራጀውን ቤት ንጽህና በቀላሉ መጠበቅ በሚገባ ያልተደራጀን ቤት ከመጠበቅ በጣም አመቺና ቀላሉ መንገድ ነው።

ቤቶቻችንን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ጊዜያችንንም ደግሞ ማስተካከል አለብን። አንዳንድ ቤት አዘጋጆች ቤታቸውን በጽዳት ለመጠበቀና ለማደራጀት *በጣም ብዙ ጊዜን* ያጠፉሉ። በቤት ሥራ እንዴት አነስተኛ ጊዜን ማጥፋት እንደሚቻል መማር አለባቸው። ከዚያም የበለጠውን ጊዜ ከቤተሰቦቻቸውና ሌሎችን በመርዳት ሊያጠፉ ይችላሉ። የቤት ሥራ አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን የበለጠ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች የሚያርቀን መሆን የለበትም። ይሁንና፣ ንጹህ መኖሪያ አለን ማለት ለፍጻሜ የሚረዳ መፍትሄ ነው፣ በራሱ ፍጻሜ አይሆንም። የእኛ የበለጠ አስፈላጊ ዓላማችን ደስተኛ መሆንና ደስተኛ ቤተሰብን ለመመሥረት ነው። ችሎታችንን ለማዳበርና የወንጌልን መሰረተ ሃሳቦች በማክበር ለመማር ጊዜን እንሻለን። በቤተክርስቲያን ሹመቶች ለማገልገል፣ ጎረቤቶቻችንና በችግር ውስጥ ያሉትን ለመርዳት፣ እናም ጥሩ ሚስዮናውያን ለመሆን ጊዜ ሊኖረን ይገባል። ብዙ ጊዜን በቤት ሥራ ላይ ሳናጠፋ ቤቶቻችንን በንጽህና ብንጠብቅ፣ የበለጠውን ጊዜ በቤተሰብ ተሳትፎዎችና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን በማድረግ ለማጥፋት ነፃ እንሆናለን።

ትዕይንት 20-ሀ፣ ቤተሰብ በአንድነት ሆነው በሙዚቃ ምሽት እንደሚደሰቱ ያሳያል።

የሕይወቴ ዓላማ ምንድነው? የበለጠውን ጊዜዬን እንዴት ማጥፋት ይገባኛል? በተሳትፎዎቼ፣ በቤተሰቤና፣ በቤተ ጥበቃ መካከል ሚዛናዊነትን መጠበቅ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

## ለሁሉም ነገር ሥፍራ

የተመቻቸ እንዲሆን ቤታችን አገልግሎት ሰጪ መሆን አለበት። ይህም ማለት እያንዳንዱ ክፍል፣ እያንዳንዱ መሳቢያ፣ እያንዳንዱ ቁምሳጥን የተለዩ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል። የወጥ ቤት ቁሳቁሶችን በመኝታ ክፍል ወይንም በመኖሪያ ቤት ማግኘት ግራ ይሚያጋባ ይሆናል።



ቤታችንን ለማደራጀት የመጀመሪያ እርምጃችን የእያንዳንዱን ክፍል ተግባር መወሰን ነው። ከዚያ በኋላ በዚያ ክፍል በሚገባ በተደራጁ መሳቢያዎችና ቁምሳጥኖች ውስጥ የምንፈልገውን ነገር ማስቀመጥ እንችላለን።

አማራጭ መግለጫዎች፦ የተለያዩ ዕቃዎችን የያዘውን ሳጥን በጠረጴዛ ላይ ያኑሩ። ጎረቤት ቤቷን እንድታደራጅ የምትረዳ በማስመሰል አንዲትን እህት ያድርጉ። እርሷም በሳጥኑ ውስጥ ዕቃዎቹን በመለያየት፣ የተለያዩ ንጹህ የሆኑትን በመከመር እንድታስቀምጥ ይጠይቋት። እያንዳንዱ ክምር ዕቃ በሚገባ በተደራጀ መሳቢያ ወይንም ቁምሳጥን ውስጥ እንዲሆን ተመሳሳይ የሆኑትን የያዙ መሆን አለባቸው።

አንዳንድ ጊዜ በቂ ማከማቻዎች፣ ቁምሳጥኖች፣ ወይንም መሳቢያዎች አይኖሩንም ይሆናል። ይህ ከሆነ፣ ባሎቻችንን እንዲገዙልን ወይንም እንዲሰሩልን ማበረታታት እንችላለን። ቀላል የሆኑትን ዓይነቶችን እኛም ለመሥራት መሞከር እንችላለን።

ብዙ ቁምሳጥኖች ሲኖሩን እንኳ፣ አሁንም፣ ለሁሉም ነገር ሥፍራ ሊኖረን የማይችልበት ሁኔታ እንደሚኖር እናውቃለን። በዚህ ምክንያት፣ በሌላ ሰው ምን መጠቀም እንደሚቻል፣ ምን መጣል እንዳለበት፣ እናም በሌላ ስፍራ ምን መከማቸት አለበት በማለት መለያየት ጥሩ ሃሳብ ነው። አንዳንድ ዕቃዎችን ለማከማቸት ብንወስን፣ በደንብ መለያ ባላቸው መያዣዎች ውስጥ መግባት አለባቸው። መለያዎች የተስተካከሉት ዕቃዎችን በአስቸኳይና በቀላሉ እንድናገኝ ይረዱናል። አስፈላጊ ወረቀቶች . . . እንደ ኑዛዜ፣ ሙያ፣ የዋስትና ወረቀቶች፣ እና የቤተሰብ ፎቶዎችን . . . መሰናዳት፣ መለየት እናም ደግሞ በማህደር መያዝ አለባቸው።

የቤተሰብ አባላት ከተባበሩ ቤቶቻችንን የተቀናበሩ ማድረግ ቀላል ነው። ቤትን በንጽህና የመጠበቅና የማቀናበር ኃላፊነት የሁሉም ድርሻ መሆን አለበት። ፕሬዚዳንት ብሪግሃም ያንግ ሲመክሩ፣

“ትንንሽ ልጆችን የስርዓትን ዓላማ አስተምሯቸው፣ ትንሿ ልጃገረድ የቤት መጥረጊያን በትክክለኛ ቦታው እንድታስቀምጥ . . .እናም ሁሉም ነገር በቦታ ቦታው መሆኑን እወቁ። ልብሶቻቸውን በንጽህና እንዲያኖሩ፣ እና ማግኘት የሚቻልበት ቦታ እንዲያኖሩ አስተምሯቸው . . . ትንንሽ ወንድ ልጆችን የአትክልት ዶማን፣ አካፋን፣ ወዘተ፣ በዝገት የማይበላሹበት ቦታ . . .እና ከሰሩበት በኋላ መሳሪያዎቹን እንዲሰበስቡ ማሳየትና፣ አግባብ በሆኑ ቦታዎች እንዲያስቀምጡ አስተምሯቸው።” (*Discourses of Brigham Young,* p. 211.)

የሥዕላዊ መግለጫ 20-ለ፣ አንዲት እህት በሚገባ የተደራጀ ወጥቤቷን ስታሳይ ያሳያል።

እህቶች የቤተሰብ አባላትን ቁሳቁሶችን ዞር አድርገው የማስቀመጥን ልምድ እንዲያበጁ እንዴት እንዳስተማሩ እንዲናገሩ ያድርጉ።

## የቤት ሥራችንን ማቃለል

በቀድሚያ የሥራችንን ሁኔታ ከአደራጀን ሥራውን ለመሥራት አነስተኛ ጊዜ ይጠይቀናል። ሥራውን ከመጀመራችን በፊት ማሰብ አለብን። መሣሪያዎችን ማቀናጀት ሥራችን በአንድ አቀጣጫ ይጓዝ ዘንድ ይረዳናል። ከዚያም ደረጃዎችን እንደገና መከለስ አያስፈልገንም። የምንፈልጋቸውን ዕቃዎች በቀላሉ በምንደርስበት ቦታ በማስቀመጥ ጉልበትን ደግሞ መቆጠብ እንችላለን።

20-ሀ በሙዚቃ ምሽት በአንድነት የሚደሰት ቤተሰብ


Gerber
BARLEY
WESTERN
FAMILY

ሌላው ሥራችንን የምናቃልልበት መንገድ ቆሻሻንና ፍሳሽን ወዲያውኑ እንደተገኙ በማስወገድ ነው። ምስቅልቅሎች በፍጥነት ይባዛሉ። ምስቅልቅል በጠረጴዛ ላይ ሲቀር ብዙ ነገሮች እንደአጋጣሚ ይወድቃሉ። ማሰሮዎች፣ መጥበሻዎች፣ እና ድስቶች ከተሰራባቸው ምግቦች ጋር ከቆዩ ለማጽዳት ይከብዳሉ። ምግብ የተሰራባቸው ቁሳቁሶች ከተጠቀምንባቸው በኋላ ከቆሻሻ ጋር ከማቆየት ወዲያውኑ ማጽዳት ይመረጣል።

ሶስተኛው መንገድ የቤት ስራን የምናቃልልበት የተለያዩ ነገሮችን በአንድ ወቀት በማከናወን ነው። አንዳንድ የቤት አዘጋጆች ኪስ ያላቸውን ሸርጥ ይለብሳሉ። እየተራመዱ ባሉበትም ጊዜ ቤትን ማስተካከል ይችላሉ። በቂ ችሎታ ያላቸው ቤት አዘጋጆች የተለያዩ ሥራዎችን ያጣምራሉ። ለምሳሌ ያህል በእጃቸው እየሰሩ ይናገራሉ ወይንም ቀጣዩን የሥራ ዕቅድ ያወጣሉ። ልጆችን የግል ችግሮቻቸውን እንዴት ማቃለል እንደሚገባቸው እያስተማሩ ወይንም በስልክ በሚያናግሩበት ወቀት ልብሶችን ያጥፋሉ። ጊዜያችንን በቀልጥፍና ለመጠበቅም ዘዴዎችን ማግኘት አዝናኝ ነው።

የክፍሉ አባላት የቤት ሥራ ጊዜን እንዴት ማሳጠር የሚችሉበትን ዘዴ እንዲያካፍሉ ይጠይቁ።

ብዙዎቻችን እንዴት እንደምንጠቀምባቸው አስቀድመን ባለማቀዳችን በቀን ውስጥ በከንቱ የምናጠፋቸው ጊዜያት አሉ።

ትርፍ ጊዜዎን የበለጠ ውጤታማ በማድረግ እንዴት መጠቀም ይችላሉ?

በትጋት በመስራታችን ያገኘነውን በቂ ጊዜ ራሳችንን፣ እናም ቤተሰባችንን በማዝናናትና በማስደሰት፣ ሌሎችን በችግሮቻቸው በመርዳት ወይንም በረዥም ጊዜ ፕሮጀክት ሥራ ማለት እንደ የዘር ግንድ በመሳሰሉት ላይ በመሥራት መጠቀም እንችላለን።

ጊዜ ቢኖርዎ ምን ልትሰሩበት ይፈልጋሉ?

## ማቀድ ነገሮችን ለማከናወን ይረዳል

አንዳንድ ሰዎች ምንጊዜም በሥራ የተጠመዱ ናቸው፣ ነገር ግን ብዙን ነገር የሚያከናውኑ አይመስሉም። ጥሩ መከተል ያለብን ደንብ ይህ ነው፣ በጣም ተፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በጣም ተፈላጊ ላልሆኑ ነገሮች መስዋዕት ማድረግ አይገባም። የበለጠ አስፈላጊ የሆኑትን በመውሰድና ቅድሚያ በመስጠት መሥራት ያስፈልገናል።

አንድ እህት ነገ ማድረግ የሚገባትን ስድስት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንድትጠራ ያድርጉ። ይህንኑ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ። ከዚያም እንደ አስፈላጊነታቸው በቀደም ተከተል እንድትቀጥራቸው ይጠይቁአት። ሁሉም እህቶች የዕለት ሥራቸውን የሚያቀዱት ይህን ሥርዓት በመጠቀም፣ ሌላን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የጀመሩትን ሥራ በመፈጸማቸው መሆኑን አስተያየትዎን ይስጡ።

አንዳንድ ጊዜ ለዕለቱ ያቀድናቸውን ሁሉንም ነገር ሰርተን አንጨርስም። የበለጠ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች አስቀድመን ብንሰራ፣ ጊዜያችንን በሚገባ ተጠቀመናል። ሥራችንን እንዳቀድን ተገቢ ለውጥ ማድረጋችንን እናውቃለን። እቅዳችን ሁሌ እንደጠበቅነው ይፈጸማል። በዕለቱ ውስጥ ትንሽና ትልቅ አስቸኳይ ነገሮች ያደናቅፉናል፣ ነገር ግን የት እንደምንሔድ ብናውቅ ሥራችንን ከግቡ እናደርሳለን። በዕለቱም ፍጻሜ ላይ ደስታ ይሰማናል። ከቤተሰቦቻችን ጋር የምናሳልፈው በቂ ጊዜ ይኖረናል። መደራጀት ለቤታችን ተጨማሪ ሰላምና ስምምነትን ያመጣልናል። ችሎታችንን ለማዳበርና ሌሎችን ለመርዳት በቂ ጊዜ ሊኖረን ይችላል።

20-ለ አንዲት እህት በሚገባ የተደራጀ የማዕድ ቤቷን ስታሳይ።

## ሙከራ

በዚህ ሳምንት መደራጀት ይጀምሩ። የጊዜ ጠቀሜታዎን ያሻሽሉ።

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. ከቤት ድብልቅ ዕቃዎች፣ የተለያዩ መጠን ካላቸው ልብሶች፣ የወንድና ልጃገረዶች አሻንጉሊት፣ መሳሪያዎች፣ የወጥ ቤት ቁሳቁሶች የመሳሰሉትን ወዘተ . . . የተሞላባቸውን ሰፌ ሳጥን ያምጡ (በአማራጭ)።
2. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ያዘጋጁ።

# የቤተሰብን ገንዘብ አያያዝን ማስተዳደር

ትምህርት 21

የዚህ ትምህርት ዓላማ ገቢያችንን እንዴት እንደምናስተዳድር ለመማር እንዲረዳን ነው።

## መግቢያ

"ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፣ አለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።" (መዝ 24፡1)።

ፕሬዚዳንት ብሪግሃም ያንግ ሲናገሩ ጌታ "ለዚህ ሕዝብ አብዛኛውን ክፍል አሳልፎ ሰጥቷል . . . ሆኖም ግን የእኛ አይደለም፣ እናም ማድረግ ያለብን ጌታ ባለን ሃብታችን እንድናደርግ የሚፈለግብንን ሁሉ ለማወቅ በመሞከር፣ እናም ከዚያ በኋላ ማድረግን ነው።" እንዲሁም ብርግሃም ያንግ ይህን ማድረግ የምንችለው "በእምነታችን፣ በትዕግስትና በእንዱስትሪ አማካይነት ነው" ብለዋል። (See *Discourses of Brigham Young,* p. 305.)

ለቤተሰቦቻችን በማቀረብ እንድንረዳ ጌታ የሰጠን ምንን ነው? የቤተሰብዎ ገቢ እንዴት ጌታ ይህችን ምድር ሲፈጥር ባቀረበልን ላይ የተወሰነ እንደሆነ ያስቡ።

ጌታ የምድር በረከትን ሰጥቶናል። ሰዎች ገንዘብን ፈጥረው እነዚህን ነገሮች እርስ በርስ ይሸማመታሉ። "ገንዘብ ሰዎች ለሚሸጧቸው ነገሮች ወይም ለሚሰሯቸው ሥራዎች በመለዋወጥ የሚቀበሉበት ማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል።" (*World Book Enyclopedia,* 1977 vol. 13 p. 588.) ገንዘብ የዋጋ መለኪያ ነው። ሁሉም ባህሎች አንድ የገንዘብ ዓይነት አላቸው። ገንዘብን እንዴት ጌታ በሚፈልግብን መንገድ እንድንጠቀምበት መማር አለብን።

## ገቢን እንዴት እንድምንጠቀምበት ማቀድ

በታማኝነት የተገኘ ገንዘብ እናም በጥበብ ከሰሩበት መልካምን ለመስራት መሳሪያ መሆን ይችላል። ጌታ መልካምን እንድናደርግ ይፈልጋል። ለቤተሰቦቻችን እንድናስብና በምድር ላይ ሥራውን እንድናከናውን ይፈልጋል። "ገንዘባችንን በጥብብ ስንጠቀም፣ እርሱ እንዳቀደው ስንጠቀምበት፣ የራሳችንን ፍላጎቶች እንድናሟላም ይባርከናል። ገንዘብን እንዴት እንደምንገለገልበት መማር አለብን። ገንዘብን በጥበብ ለመያዝ ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። የገንዘብ አጠቃቀማችን ለሌሎች፣ ለጌታና ለስራው፣ እናም ለራሳችንም ያለንን አመለካከት ያሳያል። ደጎች ወይንም ራስ ወዳድ፣ ቀጣቢ ወይንም አባካኝ እንደሆንም ያሳያል።

ማንኛውንም የራሳችን የሆነ ገንዘባችንን ከመጠቀማችን በፊት ምን ማድረግ ይገባናል? ሉቃስ 14፡28–30 ያንብቡ።

በቤተሰብ፣ ገንዘባችንን እንዴት እንደምናባክን በጋራ ማቀድ አለብን። ይህም ዕቅድ በጀት ይባላል። እርሱም ቁጥጥርን ይሰጠናል። ጠቃሚ ባልሆኑ ነገሮች ገንዘባችንን እንዳንጠቀም ይከላከለናል። ማንኛውም የተሳካለት ስራ በበጀት ይከናወናል። ቤተክርስቲያናችንም ቢሆን በጀትን ይገለገልበታል።

እያንዳንዱ ቤተሰብ የተለያዩ በጀት ይኖረዋል። ለአንዱ ቤተሰብ አስፈላጊ የሆነ ለሌላው አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ለቤተሰባችን የትኛው የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ መወሰን ያስፈልገናል። ለራሳችን የገንዘብ ዕቅድ ማውጣት ያስፈልገናል። ይህን በቤተሰብ ሸንጎ ማድረግ እንችላለን።

ከተሰጡን ትዕዛዛት አንዱና ታላቁ የአስራት ህግ ነው። እንደኋለኛው ቀን ቅዱሳን፣ ይህን በበጀታችን ውስጥ እንደ ቀዳሚ ጉዳይ መውሰድ አለብን። ይህን ትዕዛዝ ከጠበቅን ጌታ ይባርከናል። ከገቢያችን ለአስራት አንድ አስረኛውን በቋሚነት ስንከፍል፣ ጌታ በራሱ መንገድ እንደሚባርከን ዋስትና አለን። (ይህንኑ በሚልክያስ 3፥10 እናም በማቴዎስ ወንጌል 6፥33 ይመልከቱ።) ጌታ ለጊዜያዊ ደህንነታችን ማሰቡን ማወቅ ያጽናናል። የገንዘብ ችግሮች ሲኖሩን፣ በታማኝነት ብንሰራና የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስቀደም ፈቃደኞች መሆናችንን ብናሳይ እርሱ ይባርከናል።

በጀትን ስለመወሰን

በጀትን በመመሥረት ቀዳሚው እርምጃ የገቢ ምንጮችን ሁሉ መደመር ነው። በየወሩ የሚኖረንን ጠቅላላ ገቢያችንን ማወቅ አለብን።

በጥቁር ሰሌዳው ላይ፣ ጠቅላላ ገቢን ይጻፉ።

ከዚያ በኋላ ከጠቅላላ ገቢ 10 ከመቶውን ለአሥራታችን እንወስዳለን።

በጥቁር ሰሌዳው ላይ፣ አሥራት . . . 10 ከመቶ ብለው ይጻፉ።

ቀጣዩ እርምጃ የሚሲዮናውያንን መዋጮዎች እና የጾም መስዋዕቶች በማጠቃለል ለቤተክርስቲያኑ መዋጮዎች ገንዘብን፣ ማስቀመጥ ነው።

በጥቁር ሰሌዳው ላይ፣ የቤተክርስቲያኑ መዋጮ ብለው ይጻፉ።

አስራታችንን ከከፈልንና ሌሎች የቤተክርስቲያን ግዴታዎችን ከተወጣን በኋላ፣ ለቁጠባ ገንዘብ ማስቀመጥ አለብን። በየወሩ አስራት ስንከፍል የምንችለውን ያህል ገንዘብ ለመቆጠብ እንድንሞክር የቤተክርስቲያን መሪዎች ሐሳብ ያቀርባሉ . . . በሌላ አነጋገር፣ ከመቶ አስሩን እጅ ማለት ነው። (*Relief Society Courses Of Study,* 1977–78, pp. 56–57 ይመልከቱ።) የገንዘብ ችግር የሚኖረን ከሆነ፣ ከምንቀጥበው መቀነስ እንችላለን፣ ሆኖም ግን በየወሩ በመጠኑ መቆጠብ አለብን። ቁጠባችን ላልተጠበቀ አጣዳፊ ሁኔታዎች ይውላል፣ ከሥራ መውጣትን ወይንም መታመምን ወይንም የአደጋ አጋጣሚን ለመሳሰሉት ነው። እናም ደግሞ ለሚስዮን አገልግሎታችን፣ ለትምህርት፣ ለቤተመቅደስ ጉዞ፣ ወይንም ለሌላ ረጅም ርቀት ግቦች መቆጠብ አለብን።

በጥቁር ሰሌዳ ላይ፣ ቁጠባ ብለው ይጻፉ።

ብዙ ገንዘብ መቆጠብ ካልቻልን፣ በየቤታችን ቆጣቢ መሆንን መለማመድ እንችላለን። በራሳችን ተሰጥኦ እና በችሎታችን መተማመን እንችላለን። ይህ ታላቅ የሆነ ገንዘብን ለመቆጠብ ይረዳናል። አትክልትን በመትከልና አንዳንድ የራሳችን የሆኑ ምግቦችን ማምረት እንችላለን። አሮጌ ልብሶቻችንን በመቀደድና በአንድነት በመጣፍ በአዲስ መልክ መጠቀም እንችላለን። ከአሮጌ የቤት ቁሳቁሶች አዲሱን ማበጀት፣ አዲስ አሻንጉሊቶችን በምናገኛቸው ዕቃዎች ማበጀት እንችላለን። በድጋሚ ልብሶችንና የቤት ቁሳቁስን በማደስ በመጠቀም ብዙ ነገሮችን ለራሳችን ማቅረብ እንችላለን።

ስዕል 21-ሀ፣ በቤት የተዘጋጁ የቤት ቁሳቁሶች በመጠነኛ ወጪ መገንባት እንደሚችሉ ያሳያል።

እህቶች ያመጡትን ዕቃዎች እንዲያሳዩ ያድርጉ። እነዚህን በማምረት ወይንም በመሥራት ምን ያህል እንደቀጠቡ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።

በበጀታችን ውስጥ ቀጣዩ ጉዳይ መሰረታዊ የሕይወት ፍላጎቶች መሆን አለባቸው፣ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው። በአቀጣጠባችን ላይ እና በቤተሰባችን ብዛት፣ በመመርኮዝ የምናባክነው የገንዘብ መጠን ይለያያል። በንግድ ደረጃ ተዘጋጅተው እናም የታሸጉ ምግቦችን የሚሸምቱ ቤተሰቦች መሰረታዊ ውህደት ያላቸውን ምግባቸውን ከሚያዘጋጁት ወይንም ከራሳቸው አትክልት ቦታ አምርተው ከሚመገቡት የበለጠ ወጪ አለባቸው። በጥንቃቄ መሸመት ሲባል ዕቃዎች በቅናሽ ሲሸጡ፣ የቅንጦትን በማስወገድ እናም የሚፈልጉትን ዕቃዎች መግዛት ማለት ነው። አሮጌን ልብስ የሚያድሱ ወይንም በቅናሽ የሚሸጡ ልብሶችን ልብስ ለማድረግ የሚገዙ ለንግድ የተዘጋጁትን ከሚገዙት ያነሰ ወጪ ያወጣሉ። አንዳንድ ቤተሰቦች በርካሽ ቤቶች ውስጥ በመኖር ገንዘብን ይቆጥባሉ።

"ምግብን፣ ልብስን፣ ቤትን" እንደቀጣይ ሶስቱ ጉዳዮች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ።

ቤተሰብ ገንዘብን በሌሎች ብዙ ክልሎች ለሚገኙ ዕቃዎች ለማጥፋት ይወስናሉ። ከነዚህ አንዱ የሕክምና ወጪ ነው። አንዳንዶቹ ከተለመዱት ውስጥ መጓጓዣ፣ ሙቀት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል እና ውሃ ናቸው። እነዚህ የኋለኛዎቹ ዕቃዎች የራሳችን "ፍጆታዎች" ናቸው።

"የመድኃኒት ወጪዎችን፣ መጓጓዣን፣ ፍጆታዎችን" በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ።

በሚተርፈን ገንዘብ ለቅንጦት ዕቃዎች በጀት መያዝ እንችላለን፣ እነዚያ እንዲኖሩን የምንፈልጋቸው ነገሮች ቢሆኑም በእርግጥ አያስፈልጉንም። የቤተሰብ የዕረፍት ጊዜያት፣ ጌጣጌጦች፣ ፊልሞች ወዘተ . . . ሊሆኑ ይችላሉ።

በጥቁር ሰሌዳ ላይ፣ ሌላ ብለው ይጻፉ።

የተረፈ ገንዘብ ከሌለ፣ ወይንም ለሁሉም ፍላጎቶች የማይበቃ ከሆነ፣ ለተለያዩ ቦታዎች ያቀድነውን የገንዘብ መጠንን መለወጥ አለብን። አንዴ ገንዘባችንን እንዴት እንደምናወጣ ከወሰንን፣ በጀታችንን መከተል አለብን። በአንድ ቦታ ገንዘብን ካወጣን በኋላ፣ ቀጣዩን ገቢያችንን እስከናገኝ ድረስ ተጨማሪ ገንዘብን ማጥፋት የለብንም። አጣዳፊ ሁኔታ ከገጠመን፣ ከበጀታችን አነስተኛ ከሆነው ጠቃሚ ክፍል መበደር አለብን።

በመጀመሪያው ወር ከያዝነው ይልቅ በተለየ በቀጣዩ ወር በጀትን ለመያዝ መወሰን እንችላለን። የቤተሰባችንን ፍላጎት የሚያሟላ በጀት ሊኖረን ይገባል። በበጀት ላይ ስንሰራ፣ ገንዘባችንን በጥበብ እንድንጠቀምበት የሚረዳንን ጥቅም እንማራለን።


የበጀት ዕቅዳችንን በመከተል ምን ዓይነት በረከቶች ሊመጡ ይችላሉ? ልጆቻችን ገቢያቸውን እንዲያስተካክሉ ማስተማር ለምን አስፈለገ? ይህንንስ እንዴት ልናደርግ እንችላለን?


### ዕዳን ስለማስወገድ


ትምህርት እና ቃልኪዳን 104፡78 ያንብቡ።


ደግሞም በፕሬዚዳንት ጄ.ሩበን ክላርክ ጁንየር ተመክረናል።


21-ሀ በቤት የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች በአነስተኛ ወጪ ሊሰሩ ይችላሉ።
21-ለ የበጀት ናሙና ቅጽ
21-ሐ ቤተሰብ በራሱ በጀት ላይ ሲወያይ።











# በጀት

**ጠቅላላ ገቢ** ______________________

አስራት አስር ከመቶ ______________________

የቤተክርስቲያን መዋጮ ______________________

ቁጠባዎች ______________________

ምግብ ______________________

አልባሳት ______________________

መጠለያ ______________________

የመድሃኒት ወጪዎች ______________________

መጓጓዣ ______________________

ጠቃሚ መገልገያዎች ______________________

ሌሎች ______________________

ሌሎች ______________________

ሌሎች ______________________

**ጠቅላላ ወጪዎች** ______________________

21-ለ


予算
300000円
十分の一
30.000円
10.000円
20.000円
30.000円
20.000円
10.000円
30.000円
25.000円
20.000円
25.000円
270.000

“መቀሰፍትን እንደምናስወግድ ሁሉ ዕዳንም እናስወግድ፣ በአሁኑ ወቀት በዕዳ ውስጥ ካለን ከዕዳው እንውጣ፣ ዛሬ ባይሆንም ነገ።”

“በቀጥታና በጥብቀ ከገቢያችን በላይ አናጥፋ፣ እና በመጠኑ እንቆጥብ።” (In Conference Report, Apr. 1937, p. 62.)

የበጀታችን ክፍል በማድረግ ዕዳችንን መቀነስ እንችላለን። በሌላ ክፍሎች ለነስተኛ ገንዘብ ማስቀመጥ እንችላለን፣ ነገር ግን ነቢያችን ዕዳን እንድናስወግድ ነግረውናል። ቤትን ወይንም ሌላ በጣም አስፈላጊ ቁሳቁስ ከመግዛት በስተቀር፣ በብድር መግዛትን ማስወገድ አለብን። ገንዘብን ብንበደር፣ በገባነው ቃል መሰረት መልሰን መክፈል አለብን፣ ከሌሎች ጋር በምናደርገው ማንኛውም ግንኙነት ታማኞች መሆን አለብን።

ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር ስለዕዳ አደገኛነት እንዲህ በማለት አስጠንቀቀውናል፣

“ሰዎች በጣም ባለዕዳ ሲሆኑ በሕይወታቸው ሙሉ አይደሰቱም፣ እንዴት እንደሚዘልቁም አያውቁትም። ይህ ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ ጠብን ይፈጥራል፣ ሰዎች ልክ በአቀማቸው መጠን ስለማይኖሩ ጭንቀትንና ጥርጣሬን፣ እናም አንዳንድ ጊዜ ፍችዎችን ያስከትላል።” (Address at Welfare Agriculture Meeting, 9 Apr. 1966; quoted in *Relief Society Courses of Study*, 1977–78, p. 81.)

ከዕዳ ውጭ በመሆን ምን ዓይነት በረከት ያመጣልናል?

## ማጠቃለያ

ጌታ ይህችን ምድር የሰጠን እኛው ለራሳችን አስፈላጊውን ለማድረግ እንድንችል ነው። እኛ እንድንበለጽግ እርሱ አቀዶልናል። ገንዘባችንን በጥበብ ከተጠቀምን እና በሕይወታችን የእግዚአብሔርን መንግሥት ካስቀደምን ጌታ በዛብተም ሆነ በመንፈሱ ይባርከናል።

## ሙከራ

ስዕል 21-ለ የበጀት ቀጽ ናሙና፣ እናም 21-ሐ ቤተሰብ በበጀት ላይ ሲወያይ ያሳያል።

የቤተሰብ ሸንጎን ስለማካሔድ ባለቤትዎን ያነጋግሩ። በዚህ የቤተሰብ መማክርት (ወይም ላጤ ከሆኑ፣ በራስዎ) ለቀጣይ ወር የገንዘብ በጀትን ይያዙ። ዕዳ ካለብዎ፣ እንዴት እንደሚቀንሱ ለመወሰን ቤተሰብዎን ያጠቃሉ። አባካኝነትን በማስወገድ በቤት ገንዘብን ለመቆጠብ ይሞክሩ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፣

1. እያንዳንዷ እህት ከአካባቢ ምርት አንዱን ዓይነት እንዲያመጡ ይጠይቁ፣ ማለትም ከአካባቢ የተመረቱ ፍራፍሬ ወይንም አትክልት፣ በእጅ የተሰራ ልብስ፣ መጫወቻ፣ አሻንጉሊት፣ ወይንም የቤት ማስጌጫ ዕቃ።
2. የጥቁር ስሌዳና ጠመኔን ያዘጋጁ።
3. በዚህ ትምህርት ላይ ታሪክንና የቅዱሳን መጻህፍትን ጥቀሶችን የክፍሉ አባላት እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# አልሚ ምግብ ለቤተሰብ

ትምህርት 22

የዚህ ትምህርት ዓላማ በጤና ለመኖር መመገብ ያለብንን የምግብ ዓይነት እንድንማር ለመርዳት ነው።

## መግቢያ

የሰማዩ አባታችን በጣም ይወደናል። በምድር ላይ በመልካም ጤንነት እንድንደሰት ስለሚፈልግ፣ ለሰውነታችን ውስጥ ስለምንወስዳቸው ምግቦችና ሌሎች ነገሮች መመሪያ ሰጥቶናል። እነዚህ መመሪያዎች በትምህርትና ቃል ኪዳን፣ ክፍል 89 ይገኛሉ። ይህም "የጥበብ ቃል" ይባላል። በጥበብ ቃል ውስጥ፣ ለመልካም ጤንነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን የምግብ ዓይነትን እንድንመገብ ተነግሮናል። እናም ደግሞ አንዳንድ ንጥረ ነገሮችን እንድናስወግድ ተነግሮናል . . . ለእኛ ጎጂ የሆኑትን እንደ ሻይ፣ ቡና፣ የአልኮሆል መጠጦችን . . . እናም ትምባሆ . . . የመሳሰሉትን ነው።

## የተለያዩ ምግቦች በተሻሉ መንገዶች ጤናማ ያደርጉናል

ስዕላዊ መግለጫ 22-ሀ፣ የምግቦች ናሙና ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች መሆኑን ያሳያል።

ትምህርትና ቃልኪዳን 89፡10–11 ያንብቡ።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ምን ዓይነት ምግቦች ተጠቅሰዋል? በአካባቢያችን ምን ዓይነት ፍራፍሬና አትክልት እናገኛለን?

ፍራፍሬና አትክልቶች ከተለያዩ በሽታዎች በመጠበቅ ስለሚረዱን አስፈላጊ ናቸው። እነዚህን ምግቦች መብላት ከአንዳንድ የዓይን መታወርና ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል ሊረዱን ይችላሉ። እናም ቁስሎች በአግባቡ እንዲድኑልን ይረዱናል። እነዚህ ምግቦች ደግሞ ከብዙ ሌሎች የጤና ችግሮች ይከላከሉልናል።

ስዕላዊ መግለጫ 22-ለ፣ ከመሰረታዊ የምግብ ክፍል የተዘጋጀውን ምግብ ያሳያል።

ትምህርትና ቃልኪዳን 89፡12–13 ያንብቡ።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ምን ዓይነት ምግቦች ተጠቅሰዋል?

ይህ ጥቅስ "ሥጋን" በመጠኑ እንድንበላ ይነግረናል። ከእንስሳት ሥጋ በተጨማሪ፣ ዓሳ፣ እና በሰማይ ከሚበሩት፣ ሌላ የእንስሳት ተዋጽኦ ደግሞ ጤንነትን ይሰጡናል። እነዚህ እንቁላልን፣ አይብን፣ እና ወተትን ያጠቃልላሉ። ሁለቱም ሥጋና የእንስሳት ተዋጽኦ ሰውነታችን በጥንካሬ እንዲያድግ የሚረዳንን "ፕሮቲን" የተባለ ንጥረ ነገር ይዘዋል። ፕሮቲን የጡንቻችንን የሥጋ ልባስ ይገነባል እናም ከሕመም እንድንፈወስ ይረዳናል። በተለይ ነፍሰጡር ሴቶች እና ትንንሽ ልጆች በአግባቡ ለመጠንከር ፕሮቲን ይፈልጋሉ።

ትምህርትና ቃልኪዳን 89፡14–17 ያንብቡ።

22-ሀ ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች የምግቦች ናሙና።





22-٨

ምን ዓይነት ምግቦች ተጠቀሰዋል? የምትበሉአቸው ተመሳሳይ የሆኑ ምግቦች ምንድን ናቸው? ለእናንተ ምን ዓይነት ኃይል ሰጪ ስራስሮች ይገኛሉ?

ከእህል በተጨማሪ፣ ቁጥር 16 በጓሮ የሚመረቱ ምግቦች፣ እንደ ከርቡሽ፣ ጫማቂ ቲማቲም፣ አተርና ባቄላን ይገልጻል። ኃይል ሰጪ ሥራሥሮች ከነዚህ ምግቦች ጋር የሚጠቃለሉ ናቸው ድንች፣ ታሮ፣ እናም ሌሎችም። እነዚህ ምግቦች ሁሉ እንደ እህል አካልን በመርዳት ተመሳሳይነት አላቸው። መጠነኛ አካል ገንቢን፣ ቪታሚንን እና የምንፈልገውን ማዕድን ይሰጡናል። ኃይል ሰጪ ምግቦችንም ይሰጡናል (ኃይል ሰጪዎችን እና ስኳሮችንም) ይሰጡናል። ለዕለት ሥራችን ኃይል ለማመንጨት ሰውነታችን ኃይል ሰጪ ምግቦችን ይጠቀማል።

## ሶስቱ የምግብ ክፍሎች አስፈላጊዎች ናቸው

በዚህ ዘመን ራዕይ በልዩ ሁኔታ የተሰየሙትን ስለ ሶስቱ ዓይነት ምግቦች ተምረናል።

በጥቁር ሰሌዳው ላይ የሶስቱን የምግብ ዓይነቶች ስም ይጻፉ፥ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ስጋና የእንስሳት ውጤቶች፣ እህልና ኃይል ሰጪ ስራስሮች ናቸው። እነዚህን ሶስቱ የምግብ ዓይነቶች "ክፍሎች" እንላቸዋለን።

አንዱም ዓይነት ምግብ የሌላውን ቦታ መያዝ አይችልም። እያንዳንዱ ዓይነት የራሱ ልዩ ጥቅም አለው። በየዕለቱ ከምንመገበው ውስጥ የአንዱ ዓይነት ምግብ ቢጎድል፣ ሌሎች የጎደለውን መተካት አይችሉም።

ምግብን ከነዚህ ከሶስቱ ክፍሎች እንፈልጋለን። ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን ከአንዳንድ በሽታዎች እንዲጠብቁን እንፈልጋቸዋለን። ሥጋንና የእንስሳት ውጤቶችን ለዕድገታችን እንፈልጋለን። እናም እህሎችንና ቀባታማ ሥራሥሮችን ሃይልን ለማግኘት እንፈልጋለን።

አንዳንድ ሰዎች የፈለጉትን ቢበሉ ሆድ ከሞላ ምንም አያስፈልግም ብለው ያስባሉ። ይህ ትክክል አይደለም። ቢያንስ በየዕለቱ ከሶስቱ የምግብ ዓይነቶች አንዱን መመገብ አለብን። ከተቻለ፣ ከእያንዳንዱ ክፍል በእያንዳንዱ የምግብ ወቀት አንድ ምግብ ሊኖረን ይገባል።

ሴቶቹ ትናንት እና ዛሬ ከክፍል ጊዜ በፊት የበሉትን ምግቦች እንዲያስታውሱ ጠይቁአቸው። የራስዎን ምግብ እንደምሳሌ ይጠቀሙ። በጥቁር ሰሌዳ ላይ የበሉትን ነገሮች ይጻፉ።

ከእያንዳንዱ ክፍል አንድ ነገር ነበረበትን? ከእያንዳንዱ የምግብ ክፍሎች በየምግብ ወቀት አንድ ነገር ነበረበትን? ከአንዱ ክፍል ምግቡ ከጎደለ፣ ምን ዓይነት ምግቦች መጨመር አለባቸው?

በምትበሉት ምግብ ላይ ለመጨመር አስቸጋሪ የሚሆን አንድ የምግብ ክፍል አለን? በምግብዎ ላይ የተሟላ ለማድረግ ምን ዓይነት የአካባቢ ምግቦች መጨመር ይችሉ ነበር?

ምግቦችን በምናዘጋጅበት ጊዜ፣ በትክክል ሁሉም የምግቦች፣ ማብሰያ ቁሳቁሶች፣ የመሳሰሉት፣ በንጽህና መጠበቃቸውን እና በሽታን ከሚያመጡ ጀርሞች ነጻ መሆናቸውን ማየት አለብን።

## ሶስቱን የምግብ ክፍሎች በምግቦቻችን ውስጥ ማጠቃለል

በእያንዳንዱ ምግብ ውስጥ የእያንዳንዱን ክፍል ምግቦችን ለማጠቃለል የተለያዩ ነገሮች ማድረግ እንችላለን።

1. ማለዳ በዕለቱ ለምግብ ምን ማዘጋጀት እንዳለብን ማሰብን መጀመር እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ፣ ምግቡን የምናዘጋጅበት ወቀት እስኪደርስ ስንቀይ፣ በቤት ውስጥ ጥሩ አማራጭ ምግብ እንደሌለን እንረዳለን።

22-ለ ከመሰረታዊ የምግብ ክፍሎች የተዘጋጀ ምግብ።

2. ለምግብ ስናቅድ፤ የተለመዱ ምግቦችን ለማስብ ቀላል ነው። በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች ሩዝ፤ ስንዴ፤ እና በቆሎ የተለመዱ ምግቦች ናቸው። በተለመዱት ምግብ በመነሳት፤ ከሌሎች ክፍሎች ምግቦችን መጨመር እንችላለን።
3. ከገበያ ምግብን ስንገዛ፤ ሶስቱን የምግብ ክፍሎች ሁሉ ለማስታውስ እንዲረዳን ዝርዝር ማዘጋጀት አለብን።
4. በአትክልት ሥፍራ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ በመትከል ማምረት እንችላለን። የአትክልት ሥፍራ ከሌለን፤ የምግብ ተክሎችን በባልዲ ወይንም በእንጨት ሳጥን ውስጥ መትከል እንችላለን። ምናልባት ከወዳጆችና ከዘመዶቻችን ጥቂት መሬት መካፈልም እንችል ይሆናል።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት ሶስቱ ዋና የምግብ ክፍሎች በተጨማሪ፤ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች ሌሎች ምግቦች እንዲጨመሩ ሳይንቲስቶች ይደግፋሉ። እነዚህ ተጨማሪ ምግቦች ሰዎችን በአስፈላጊ ፍላጎቶች ይረዳሉ።

ሁላችንም ጤነኞች መሆንን እንፈልጋለን። ስለሆነም የምንበላውን በጥንቃቄ በማቀድ፤ እያንዳንዱን የምግብ ክፍሎች በማጠቃለል ይረዱናል።

## ሙከራ

ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች ጋር የሚበሉትን እያንዳንዱን ምግብ ያነጻጽሩ። የሚፈልጉትን የምግብ ዓይነት ሁሉ ማግኘትዎን ይመልከቱ። አስቀድሞ በምግብ ዝግጅት ላይ ቢያቀዱ፤ ይህ ሶስቱን የምግብ ክፍሎች ለማጠቃለል እንደሚረዳዎት ያስታውሱ።

አብዛኛውን ጊዜ ከምግብዎ የቀሩትን ምግቦች አዲስ የአዘገጃጀት ዘዴን ይማሩ። ትምህርትና ቃልኪዳን 89 ቢያነቡ በበለጠ ስለጌታ የጤና ደንቦች መማር ይችላሉ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. በአካባቢዎ የትኛው ምግብ ጥሩ ምግቦችን መስጠት እንድሚችል ለመማር ከመንግሥት ወይንም ከዩኒቨርሲቲ ያመጋገብ ዘዴ ሰራተኞች ወይንም ከሌላ ባለሙያ ጋር ይነጋገሩ።
2. የየዕለቱን ምግቦችዎን ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ። ምግብዎን የበለጠ ጤናማ ለማድረግ የትኛውን ምግብ መብላት እንዳለብዎ ይወቁ።
3. *የወንጌል መሰረተ ሃሳብ፤* ምዕራፍ 29፤ “የጌታ የጤና ደንቦችን” ያጥኑ።
4. ትምህርትና ቃልኪዳን 89 ያንብቡ። በተለይ በዚህ ትምህርት የተወያዩበትን ቁጥሮች ያስታውሷቸው።
5. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ያዘጋጁ።
6. (በአማራጭነት) የባህል ምግብ ሆነው ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች ጋር የሚመጣጠኑትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ያዘጋጁ።

# ለእናትና ለሕፃኑ አልሚ ምግብ

ትምህርት 23

የዚህ ትምህርት ዓላማ ነፍሰጡርና ጡት አጥቢ ሴቶች መብላት ያለባቸውንና ሕጻናቶቻቸው መመገብ ያለባቸውን እንድናውቅ ይረዳናል።

## መግቢያ

ሁሉም ወጣት ልጃገረዶችና ሴቶች ለነፍሰጡር ሴቶችና አዲስ ለተወለዱ ሕጻናት ጥሩ ምግብ የትኛው እንደሆነ ማወቅ አለባቸው።

## አልሚ ምግብ ለነፍሰጡር ሴቶች

ነፍሰጡር ሴት እርሷና አዲሱ ሕጻን ልጅ ጤናማ እንዲሆን የሚረዳን ምግብ ለመብላት መጠንቀቅ ያስፈልጋታል። በእያንዳንዱ ምግብ ከሶስቱም የምግብ ክፍሎች ምግቡ መኖሩን እርግጠኛ መሆን አለባት። እነዚህ ሶስቱ ክፍሎች 1) አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ 2) ሥጋ፣ የእንስሳት ተዋጽኦ (ወተት፣ አይብ እና እንቁላልን በማጠቃለል)፣ እናም ጥራጥሬዎች፣ እና 3) እህሎችና ኃይል ሰጪ ሥራሥሮች ናቸው። በጥንቃቄ ምግባቸውን የሚመርጡ ሴቶች የማይገባውን ከሚበሉት እናቶች ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ ጤናማና ጠንካራ ሕጻናት ይኖራቸዋል።

ሴቶች ከእያንዳንዱ ክፍሎች ጥቂቱን ምግቦች እንዲጠሩ ያድርጉ፣ ከዚያም በኋላ ለነፍሰ ጡር ሴት ምግብ እንዲያቀዱ ይጠይቁ። ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች ቢያንስ አንዱን እንደሚያጠቃልሉ እርግጠኛ ይሁኑ።

ለነፍሰጡር ሴት አግባብ ያለው አልሚ ምግብ ለምን አስፈለገ?

“እናት በሚገባ የማትመገብ ከሆነና በተገቢ መጠን ሕጻኑ የሚፈልገውን አልሚ ምግብ ወደ ሰውነቷ የማትወስድ ከሆነ፣ ሕጻኑ አያድግም፣ እናም በተገቢው ሁኔታ አይፋፋም።

“የህጻናት ሞት መጠን፣ በመጀመሪያው ዓመት ዕድሚያቸው የሚሞቱ ሕጻናትን ብዛት የሚመዘግበው፣ በዓለም ውስጥ በማደግ ላይ ባሉ በብዙ አገሮች ከፍተኛ ነው። ይህም ከፍተኛ የሞት መጠን የተከሰተው ከጤናና ከቁስል መመርቀዝ መተላለፍ፣ *የተመጣጠነ ምግብ ካለመመገብ ችግር የተነሳ ነው*። ሆኖም፣ ባደጉት አገሮች እንኳን . . . በነፍሰጡር እናቶች መካከል በቂ ያልሆነ ያመጋገብ ዘዴ ከመጠን በላይ የሆነ ለህጻናት ሞት መጠን አስተዋጽኦ አድርጓል። እናት በእርግዝናዋ ወቀት ደካማ በሆነ ሁኔታ የምትመገብ ከሆነ፣ በተለይም በጣም ወጣት ከሆነች፣ ህጻኑ ትንሽና በወሊድ ጊዜ አነስተኛ ክብደት ያለው የመሆን ዕጣው ሰፊ ነው። ይህ በወሊድ ጊዜ አነስተኛ ክብደት ያለው ህጻን ከተወለደ ከአጭር ቀን በኋላ የሞቱ ዕጣ ከፍተኛ ነው። የእናት የአመጋገብ ዘዴ መኖር በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ለሕጻኑ ጤንነት አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ ነው። የልጁን ሰውነት ለመገንባትና ለመጠበቅ አልሚነት ያለውን ምግቦች መብላት አለባት።” (“Expectant Mothers Need Nutritious Food,” *Relief Society Courses of Study*, 1973–74, p 105; italics added.)

## የእናቶች ወተት ለሕጻናት ከሁሉ የተሻለ ነው

የሰማዩ አባታችን የእናቶችን አካል የፈጠረው ወተት መስጠት እንዲችል በማድረግ ነው። ይህ ወተት በተለይ የተሰራው ሕጻናት ልጆች እንዲጠጡት ነው። ከእንስሳት ወተት ይልቅ ለሕጻናት የተሻለ ነው። አዲስ ሕጻን ከተወለደ በኋላ ከእናቶች ጡት የሚወጣው የመጀመሪያው ፈሳሽም አስፈላጊ ነው። ለመጀመሪያው ጥቂት ወራት ሕጻኑን ከበሽታዎች ለመጠበቅ የሚረዱ ንጥረ ነገሮችን ይይዛል።

አንዳንድ ጊዜ፣ በጤና ምክንያት፣ እናት ከጡቷ ልጇን መመገብ አትችልም። ስለሆነም የላም፣ የፍየል ወተት፣ የጎሽ ውሃ፣ ወይንም የተቀመመ ፎርሙላ ወተት ደግሞ መጠቀም ይቻላል፣ ነገር ግን እናት ለወተቱ ንጽህና ታላቅ ጥንቃቄ መውሰድ አለባት። ከተቻላትም እናት ልጇን የጡት ወተት መመገብ አለባት። የእናት ምግብ ሕጻኑ ምን ያህል የእናት ጡት ማግኘቱን ይወስነዋል። መልካም ምግብን በሚገባ የምትመግብ እናት አብዛኛውን ጊዜ በቂ ወተትን ለሁሉም ልጇቿ ታስገኛለች።

አንዳንድ እናቶች ለምን ሕጻናቶቻቸውን ጡት አያጠቡም?

ከወተት በፊት የሚወጣው ፈሳሽ ለሕጻናት ለምን ጥሩ ሆነ?

ልጆቻችንን ጡት የማጥባት አርኪነቱ ምንድን ነው? (ለሕጻናት የተሻለ አመጋገብ፣ ለበለጠ ንጽሕና፣ ለሕጻናት ጥበቃ፣ የእናት ደስታ፣ ለአነስተኛ ወጪ)

## የጡጦ አመጋገብ

እናት ልጇን ጡት ማጥባት የማትችል ከሆነ፣ ለሕጻኑ ሌላ ዓይነት ወተት መስጠት ትችላለች። ይህ አብዛኛውን ጊዜ ሕጻኑን በጡጦ (በኋላ በኩባያ) መመገብ ማለት ነው። ህጻንን በጡጦ መመገብ የሚከተሉትን ጥንቃቄ ይጠይቃል፥

1. ጡጦውን በንጽህና መጠበቅ። መሬት ላይ ቢወድቅ፣ ወይንም ዝንቦች በጡጦው ጫፍ ላይ አርፈው ረቂቅ ሕዋሳቶችን ትተው ቢሄዱ፣ ምናልባት ሕጻኑ ሊታመም ይችላል። ጡጦውንና ጫፉን በሞቀ የሳሙና ውኃ፣ በሚገባ ይጠቡት እናም በሚገባ ያለቅልቁት።
2. ንጽህና የጎደለውን ውኃ በፍጹም አይጠቀሙ። ወተቱ ንጽህና ከሌለው ውኃ ጋር ሲቀላቀል፣ በውሃው ረቂቅ ሕዋሳት የተነሳ ሕጻኑ ሊታመም ይችላል። ውኃው ንጹህ የማይሆንበት አጋጣሚ ካለ፣ ሁልጊዜ ለሃያ ደቂቃዎች ያህል ያፍሉትና ለሕጻኑ ከመስጠትዎ በፊት እንዲቀዘቅዝ ያድርጉት።
3. ወተቱ ከተበላሸ፣ አፍስሱትና ትኩሱን ወተት ይጠቀሙ።
4. በተቀመመ የቀርቀሮ ፎርሙላ ወተት ላይ ያለውን መጠን ያንብቡ እናም *ትክክለኛውን*የውሃ መጠን ይጠቀሙ። ወተታቸው በተገቢው መንገድ ካልቀጠነና ወይንም በጣም ከቀጠነ ሕጻናት ይታመማሉ። ወተቱ እንዲበረክት ለማድረግ ሲባል ከመጠን በላይ ውሃ መጨመር አይገባም።

ሕጻናትን በጣም ያልቀጠነ ወተት የመመገብን አስፈላጊነት የሚገልጽ በዶክተር ጄምስ ኦ ሚሰን የተነገረ ታሪክ፣

ወጣት አባትና እናት ዶ/ር ሚሰን ልጃቸውን እንዲያዩላቸው ቤታቸው ጋበዟቸው። እናት የስድስት ሳምንቷን ሕጻን ስትገልጣት፣ በጣም ከሲታ ስለሆነች ዶክተሩ ይህን በማየታቸው ደነገጡ። የአጥንቶቿን ቀርጽ ማየትም ይችሉ ነበር። ወላጅ እናት በእርግዝናዋ ወቅት

ሐመምተኛ ስለነበረች ሐጻኗን ማጥባት እንዳልቻለች ተናገሩ። ሐጻኗ እንደተወለደች ደረቅ የቀርቀሮ ፎርሙላ ወተት ገዝተውላት ነበር፤ ነገር ግን እሱ ካለቀ በኋላ ሌላ መግዛት አልቻሉም። ዶ/ሩ "በአሁኑ ጊዜ ምን እየመገባችኋት ነው?" ሲሉ ጠየቁ፤ የሐጿኗን ጡጦ ንፁህ ሊሆን ወደተቃረበ ፈሳሽ የተሞላውን አሳዩዋቸው። ፈሳሹ ከጥቂት የቀርቀሮ ወተት ጠብታዎች ጋር የተደባለቀ ነበር። ዶ/ር ሚሰን ለሐጻኗ ወተት በመግዛት ቤተሰቡ እንዲጠቀሙበት ገንዘብ ለቀርንጫፉ ፕሬዚዳንት ሰጡ። ደግሞ ወተቱን እንዴት እንደሚያዘጋጁ ለቤተሰቡ መመሪያ ሰጡ። የዶ/ሩ ጥረት ቢኖርም የኋላ ኋላ ሐፃኑ ሞተ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ቤተሰቡ የአከባቢው ሐዝባዊ ድርጅቶች ለሐጻናቸው ወተት መስጠት ይችሉ እንደነበረ አወቁ። (See "For the Health of the Saints," *Speeches of the Year,* 1974, pp. 153–54.)

ጡጦን መመገብ ተጨማሪ ጥንቃቄን ይጠይቃል፤ ሆኖም ግን ከጡጦ የሚመገቡ ህጻናት ጤነኞች መሆን ይችላሉ። ሐጻኑ ከጡጦ አንዳንዴ መመገብ ያለበት ቢሆንም የእናት ወተት መስጠት ይሻላል።

**ሌሎች ምግቦች ለሐጻናት**

ሐጻናት ማደግ ሲጀምሩ፤ ወተት ብቻ ካላቸው ጤናማ ሆነው ሊቀዩ አይችሉም። ሌላ ምግቦችንም ይፈልጋሉ። የእናት ወተት ለምን ያህል ጊዜ የሐጻኑን ፍላጎት እንደሚያሟላ ለማወቀ አስቸጋሪ ነው፤ ስለሆነም፤ ሐጻኑ ስድስት ወር ገደማ ሌሎች ምግቦችን መመገብ መጀመር አለበት። ሐጻናት ለሰው ዕድገት አስፈላጊ የሆኑትን ሶስቱን የምግብ ክፍሎች ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ምግቦች በጣም በንጽህና መጠበቅ ይፈልጋሉ። ምግቦቹ ሐጻኑ ጥርስ ከማብቀሉም በፊት በቀላሉ እንዲበላቸው የተፈጩ ወይንም የነጠሩ መሆን አለባቸው።

አትክልት እና ፍራፍሬዎች

በቀርፊት የተሸፈኑ ፍራፍሬዎች ከሌሎች ይልቀ ንጹሐ ናቸው። የበሰሉ ሙዞች ለሐጻናት ጥሩ ምግብ ናቸው። ሌሎች ፍራፍሬዎች በንጹህ ቢላዋ መላጥ እና በንጹህ እጅም መያዝ አለባቸው። የበሰሉ ቀጠልማ አትክልቶች ለሐጻን ምግብ በጣም ጥሩ ናቸው። ሐጻኑ በቀላሉ እንዲመገብ መከተፍ ወይንም መፈጨት ይችላሉ።

እህልና ኃይል ሰጭ ሥራሥሮች

የእህል ምግቦች ለሐጻናት ከስኳር ድንች፤ ከድንች፤ ወይንም ከሥራሥር የተሻሉ ናቸው። ሐጻናት ስኳር ድንች ወይንም ድንች ብቻ በልተው ጤናማ መሆን አይችሉም። እነዚህ ምግቦች በራሳቸው በቂ አይደሉም፤ ነገር ግን ከሌላ ምግቦች እንደ ዕንቁላል፤ ፍራፍሬዎች፤ አትክልትና ሥጋ ጋር ቢበሉ ለሐጻናት ጥሩ ናቸው።

ስጋና ጥራጥሬዎች

የባቄላ ወይንም የሥጋ መረቅ ከሞላ ጎደል ምንም ጥቅም የለውም። ዋናው ጥቅም በባቄላ፤ በዓሳ፤ በሥጋ በዶሮ ወዘተ . . . አካል ውስጥ ነው። መረቅ ጥሩ ፈሳሽ ነው ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ይበስላል እናም ረቂቅ ሐዋሳቶች አይኖሩትም፤ ነገር ግን መረቅ ብቻውን ለሐጻኑ ዕድገት አይረዳም።

ሐጻን ልጅ ከሶስቱ የምግብ ክፍሎች የትኛውን መብላት ይችላል?

እነዚህ ምግቦች እንዴት ሊዘጋጁ ይችላሉ?

ከተቻለ ሁለት ወይንም ሶስት የህጻን ልጅ ምግብን አዘገጃጀትን፣ ያሳዩ። እህቶች ልጆቻቸውን የእናት ወተትን እንዲመግቡ አበረታቷቸው። ሕጻኑ በሚገባ ካደገ፣ በየቀኑ ጥሩ የተለያዩ ምግቦችን ማግኘት አለበት።

## ማጠቃለያ

የምንበላውን ምግብ በጥንቃቄ መምረጥ አለብን። ይህ በተለይ ለነፍሰጡር ሴቶችና ጡት ለሚያጠቡ እናቶች አስፈላጊ ነው። እንዲበሉ በምንሰጣቸው የልጆቻችንን ጤንነት ደግሞ መረዳት እንችላለን። የእናቶች ወተት ሕጻናትን ለመመገብ ከሁሉም የላቀ ነው፣ ነገር ግን በጥቂት ወራት ውስጥ ብቻ፣ ሕጻናት በጥንካሬ ለማደግና ጤናማ ለመሆን ከሶስቱም የምግብ ክፍሎች መብላት አለባቸው።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. ትምህርት 22 ይከልሱ።
2. የሕጻኑን ጡጦ ወይንም ኩባያ ወደክፍሉ ያምጡ። ለእናቶች ወተት እንዴት እንደሚዘጋጅና እንዴት እንደሚጸዳ ያሳዩዋቸው (በአማራጭነት)።
3. አንዳንድ ምግቦችን በተለይም ለሕጻናት ጥሩ የሆኑትን ወደ ክፍል ያምጡ። ከተቻለም፣ ምግቡ እንዴት እንደሚዘጋጅ ለማሳየት የመሥሪያ መሳሪያን ያምጡ።
4. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔን ያግኙ።
5. በዚህ ትምህርት ላይ ጥቀሶችን እንዲያቀርቡ የክፍል አባላትን ይመድቡ።

# በሽታን መከላከል

ትምህርት 24

የዚህ ትምህርት ዓላማ ጤናማ ሆነን እንድንቆይ በሽታን የመከላከልን መሰረተ ሃሳቦችን መላመድን ለማስታወስ ነው።

**መግቢያ**

በጥንት ዘመን፣ ሰዎች የበሽታዎችን መንስኤ አያውቁም ነበር። በሽታዎች የሚመጡት ክፋትን በመሥራት፣ መስዋዕትን ባለማቅረብ፣ ወይንም በሌሎች ሰዎች አስማት ማድረግ ነው ብለው ያስቡ ነበር። ለመቶ ዓመታት ያህል ካጠኑ በኋላ፣ ሳይንቲስቶችና ሐኪሞች በአሁኑ ወቀት የብዙ በሽታዎችን መንስኤ አውቀዋል። ወንጌል ወደዚህች ምድር እንደገና በ1830 ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ዕውቀቶችን አግኝተናል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ የጌታ መንፈስ በምድር ላይ ለሚኖሩት ሰዎች ተሰጣቸው። ጤነኞች እንድንሆን እንዲረዱን ብዙ አዳዲስ ግኝቶች ተደርገዋል።

በጎልማሳነት፣ ጤናማ ሆነን መኖር ይረዳን ዘንድ ማወቅና ማድረግ ያለብንን ማድረግ አለብን። እናም ደግሞ እነዚህን ነገሮች ለልጆቻችን ማስተማር አለብን። ቤተሰቦቻችንን ስለመልካም ጤንነት ጥሩ ሃሳብ እንዲኖራቸው ማስተማር አለብን። በአንዳንድ ባህሎች፣ ልጆቻቸው መጥፎ ሲሆኑ መርፌ ይወጋሉ ይሉዋቸዋል። ይህ ቂልነት ነው። ይህም ደግሞ ልጆች የመልካም ጤንነትን ጥንቃቄ እንደቀጣት እንዲያስቡ ማስተማር ነው።

በዚህ ትምህርት፣ ጤናማ ሆነን እንድንኖር የሚረዱንን አንዳንድ ነገሮችን እንከልሳለን።

**ረቂቅ ሕዋሳትን መቆጣጠር በሽታን ለመከላከል ይረዳናል**

የበሽታ መንስኤ የሆኑ ረቂቅ ሕዋሳት በጣም ጥቃቅን ነፍሳት ናቸው። አንዳንድ ረቂቅ ሕዋሳት ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ሰው ይተላለፋሉ። ሌላ ረቂቅ ሕዋሳት ከእንስሳት ወደ ሰዎች ይተላለፋሉ። ረቂቅ ሕዋሳት ወደ አካላችን ሲገቡ ብዙ የተለያዩ በሽታዎችን ይፈጥራሉ። በሞቃት፣ በእርጥበታማ ቦታና በጨለማ ሥፍራዎች በሚገባ መኖርና ማደግ ይችላሉ። በእንስሳት ዙሪያ ወይንም በሰዎች ዓይነ ምድርና በእንስሳት ፍግ ውስጥ ያድጋሉ። ረቂቅ ሕዋሳት የሚኖሩበትን ሁኔታዎች ማስወገድ ወይንም የሚራቡበትን አካባቢ ማጽዳት አለብን።

እነዚህን ሁኔታዎች ለማስወገድ ምን ማድረግ እንችላለን? በእህቶች በተሰጡት አስተያየት ላይ የሚከተሉትን ይጨምሩበት፣

ከቤት አካባቢ ተባዮችን መከላከል

ተባዮችን ከቤት ውጭ የምንከላከልበት አንዱ መንገድ የሽቦ ወንፊትን በመስኮት፣ በበርና በሚመችበት ቦታ ላይ በማድረግ ነው። እነዚህ የሽቦ ወንፊቶች፣ በተለይም በሞቃት የአየር ወቅት፣ በጥሩ እድሳት መጠበቅ አለባቸው።

## ረቂቅ ሕዋሳት የሚኖሩበትን ቦታዎች ማጽዳት

በቤት አካባቢ የምናበስልበት፣ ገላችንን የምንታጠብበት ወይንም ልብሳችንን የምናጥብበት አካባቢዎች አብዛኛውን ጊዜ እርጥበታማ ናቸው። እነዚህን አካባቢዎች ከእርጥበት የምንጠብቅበት መንገዶች አሉ። እርጥበታማ አካባቢዎች በተለይ ሞቃት በሆነ ጊዜ አስቸጋሪዎች ናቸው። የፀሃይ ብርሃን ሞቃት ቢሆንም፣ የረቂቂ ሕዋሳትን ዕድገት ለመከላከል ይረዳል።

ረቂቂ ሕዋሳትን ለመከላከል እንዲረዳን አልፎ አልፎ በፀሃይ ብርሃን ላይ መቀመጥ ያለበት ዕቃ ምንድነው? [ልብስ በተለይም በታጠበ ጊዜ] የአልጋ ልብስ፣ መወልወያዎች፣ ምንጣፎች እና ከጨርቅ ሽፋኖች ጋር የቤት ቁሳቁስ ናቸው።)

## የእንስሳትን ፍግ እና የሰዎችን ዓይነ ምድር በአግባቡ መጣል

ረቂቅ ሕዋሳት ከእንስሳትና ከሰው በሚወጡ ዓይነምድር ውስጥ ይኖራሉ። ቆሻሻው በግልፅ ሥፍራ ሲቀመጥ፣ ዝንቦች እዚያ ያርፉና ረቂቅ ሕዋሳቶቹን በቀጫጭን ፀጉራቸውና እግራቸው ያነሳሉ። ዝንቦቹ በሆነ ቦታ ሲያርፉ፣ እነዚህ ረቂቅ ሕዋሳቶች ሊወድቁ ይችላሉ።

የእንስሳትን ፍግ እና ዓይነ-ምድርን እንዴት መጣል እንችላለን? (ዓይነምድርን ለመጣል መፀዳጃ፣ ሽንት ቤት፣ ወይንም ገላ መታጠቢያ ክፍልን ይጠቀሙ። እንስሳትን በበረት ውስጥ ያቆዩአቸው። ስጋ በል ያልሆኑትን የእንስሳት ቆሻሻን በአትክልት ሥፍራ ላይ ቀብሩ። ቆሻሻውን ዝንቦች እንዳይደርሱበት በአፈር፣ በወንፊት በሽቦ ወይንም በክዳን ነገር ይሸፍኑት።

## ምግብን ከነፍሳቶች መጠበቅ

ያልተበላን ምግብ ነፍሳት በማይደርሱበት ቁምሳጥን ውስጥ ያስቀምጡ። ቀዝቃዛ ስፍራዎች ካለዎት ምግቦችን እዚያ ያስቀምጡ። ማቀዝቀዣ፣ የበረዶ ሳጥን፣ ወይንም ቀዝቃዛ ቤት ምግብን በሚገባ በማቀዝቀዝ ያቆያል። ምክንያቱም አንዳንድ ረቂቅ ሕዋሳት በአየር ላይ ስለሚበኑ፣ እንደዚሁ ምግቦችን ከነፋስም መጠበቅ አለብን። በአንዳንድ በጣም ሞቃታማ የአየር ጠባይ፣ ምግብን በጥሩ ሁኔታ ለመጠበቅ የአየር ማስገቢያ ባለው ማራገቢያ ሳጥን ውስጥ መቀመጥ አለበት። ይህም ሰንዱቅ በውስጡ አየር ያሳልፋል። አንዳንድ ረቂቅ ሕዋሳት በምግብ ላይ በማረፍና እዚያ በመኖር የሚራቡ ቢሆንም በአጠቃላይ ይህ ጥሩ ተሞክሮ ነው።

## **ክትባት በሽታን ለመከላከል ይረዳል**

ክትባት በመውሰድ ራሳችንንና ቤተሰቦቻችንን ከአንዳንድ በሽታዎች መጠበቅ እንችላለን። ለአንዳንድ በሽታዎች አንድ ክትባት ብቻ እንፈልጋለን፣ ነገር ግን ለሌላ በሽታዎች በተወሰኑ የጊዜ ልዩነቶች ብዙ ክትባቶች ያስፈልጉን ይሆናል። የልጅነት ልምሻ በአንድ ወቀት በጣም የተለመደ በሽታ ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ የሕክምና ጠቢብ ሰዎች በዚህ በሽታ እንዳይያዙ መከላከያን አገኙ። እርሱም የልጅነት ልምሻን ክትባት ሰሩ። በአንድ ወቀት ብዙ ሰዎችን የገደለውንና ሌሎች ብዙዎችን ሽባ ያደረገውን ክትባቱን ያገኙ ሰዎች ከዚህ በሽታ ራሳቸውን መከላከል ችለዋል። በአብዛኛው የዓለም ክፍሎች፣ ሰዎች ክትባትን ከጤና ጣቢያ ወይንም ከሐኪም ማግኘት ይችላሉ።

በክልልዎ የተለመዱ የበሽታ ዓይቶች ምንድናቸው? ሐኪሞች ወይንም ሰራተኞች በጤና ጣቢያ የምን ዓይነት ክትባትን ያዛሉ? በየምን ያህል ጊዜ ሊሰጡ ይገባል? ተገቢውን ክትባት በማግኘት ቤተሰብዎን ለመጠበቅ ምን ማድረግ ይችላሉ?

አስቀድሞ ክትባቱ የሚሰጥበትን ጊዜና ቦታ ያጣሩ። እህቶች ሔደው እንዲያገኙ ቀጠሮ እንዲይዙ ሃሳብ ያቅርቡ።

በሽታን መቋቋምና መከተብ የሚለውን ስዕላዊ መግለጫ 24-ሀ ያሳዩ።

እህቶች ሰንጠረዡን እንዲያጠኑ አድርጉአቸው።

## መልካም የጤንነት ልምምዶች በሽታን ለመከላከል ይረዳሉ

ትዕይንት 24-ለ፣ ብልኳ ወጣት ሴት በቂ የእንቅልፍ መጠን ማግኘቷን፣ አልሚነት ያለውን ምግብ ማግኘቷን፣ ጥርሷን በአግባቡ በብሩሽ በቀን ሁለት ጊዜ ማጽዳቷን፣ እናም በየጊዜው መታጠቧን እርግጠኛ መሆኗን ያሳያል።

የተሻለ ጤንነት የሚያስገኙልንን ልምድ ማሳደግ እንችላለን። ከእነዚህ ልምዶች ጥቂቶቹ በሌሊት በቂ እንቅልፍ ማግኘት፣ የተለያዩ ተገቢ ምግቦችን መመገብ፣ እናም ለተወሰነ ጊዜ በየቀኑ የሰውነት ማጠንከሪያ ማግኘት ናቸው። ደግሞም ዓይነምድርን የማስወገድ መልካም ልምዶች እንዲኖሩን ይገባል። በየወቀቱ ገላን መታጠብ፣ ከእያንዳንዱ ምግብ በኋላ ጥርስን መፋቅና በጥርስ ክር ማጽዳት፣ ሽንት ቤት ከተጠቀምን በኋላ እጅን መታጠብ፣ እናም በሚያስነጥሰን ጊዜ አፋችንን መሸፈን ሌላው የጥሩ ልምድ ዓይነት ነው። ሞቃታማ የአየር ጠባይ ባለበት፣ ቁስል መመርቀዝን ለመከላከል ሁሉም ሰው ነጠላ ጫማ ወይንም ሌላ እግርን የሚሸፍን ነገር ማድረግ አለበት።

እህቶች የቤተሰብ አባላትን እንዴት ጥሩ የጤና ልምዶችን እንዳለማመዷቸው ይጠይቁአቸው።

## ሕመም በተሰማን ጊዜ

ሕመም አብዛኛውን ጊዜ በስሜታችን ወይም በሰውነታችን ቀርጽና እንቅስቃሴዎች ላይ ለውጥን ያመጣል። ቀጽበታዊ ወይንም ፍጹማዊ ለውጥ አብዛኛውን ጊዜ የተሳሳተ ምልክት ነው። አንዳንድ ለውጦች የሕመም ምልክቶች የሆኑት፣ ውጋት፣ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ የምግብ ስሜት ማጣት፣ ማቅለሽለሽ፣ መገርጣት፣ ራስን ማዞር፣ ድካም፣ ሽፍታ፣ ማሳከክ፣ የሰውነት ማበጥ፣ እና ተቀማጥ ናቸው።

ከታመምን፣ ወደ ጤና ጣቢያ መሔድ አለብን ወይንም ሕመምን በሚገባ እንዴት መቆጣጠር እንድሚቻል ለማወቅ በሐኪም መታየት አለብን። በተጨማሪም የክህነት ባርኮትን መቀበል ደግሞ ሊረዳን ይችላል። ጌታም ራሳችንን በመርዳት በረከትን እንደምናገኝ ይጠብቀብናል። ሐኪም ከበሽታችን ለመዳን እንዲነግረን ፈቃደኛ መሆን አለብን፣ ከዚያም በኋላ መልካም የጤና ልምዶችን፣ እምነት፣ ፀሎት፣ እና የክህነት ቡራኬን ማከል አለብን። እነዚህን ካደረግን፣ ብዙ በሽታዎችን ማሸነፍ እንችላለን።

ዛሬ ወይንም በዚህ ሳምንት በሽታን ለመከላከል ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላሉ?

## ማጠቃለያ

እኛ በዚህ ምድር ላይ የጌታ ሰራተኞች ነን። በሚገባ እርሱን ለማገልገል ጤነኞች መሆን አለብን። እኛ ራሳችን ጤናማዎች ስንሆን እና ጤነኛ ልጆችን ስናሳድግ ፅዮንን ለመገንባት ልንረዳ እንችላለን።

ጌታ በሽታዎችንና ሕመሞችን እንድንከላከል የተለያዩ መንገዶችን አመቻችቶልናል። ጥበብን እንድንጠቀምና የምንችለውን ሁሉ እንድናደርግ ይጠብቀብናል። ለሕመምተኞች ጥሩ ዕርዳታ እንድናደርግላቸው ይጠበቀብናል። የመሞቻችን ወቀት ካልሆነ በስተቀር በእምነት፣ በፀሎት፣ እና በክህነት ሥልጣን ኃይል መፈወስ እንደምንችል ቃል ገብቶልናል።

ሰሌዳ 24-ሀ፣ በሽታን መቋቋም እና መከላከል።

# በሽታን መከላከል እና መቋቋም

| በሽታ | በመጀመሪያ የዕድሜ መጠን | ቁሳቁስና (አንቲጅን) እና መጠኑ |
|---|---|---|
| የጉሮሮ በሽታ | በ2 ወራትና 6 ዓመታት ዕድሜ መካከል የሚገኙ ልጆች፣ 3 መጠንን ከ4 እስከ 6 ሳምንት ልዩነቶች፣ ከሶስተኛ ክትባት በኋላ በ1 ዓመት (ዲፒቲ) 4 መጠንን በግምት። | |
| የጡንቻ በሽታ | ከሁለት ወራት እስከ 6 ዓመታት ውስጥ | |
| ትክትክ (ፐርቱሲስ) | የትምህርት ቤት ልጆችና ጎልማሶች፣ 3 የቲዲ መጠኖች (ጎልማሳ) ከሁለተኛ መጠን ጋር ከ4 እስከ 6 ሳምንታት ከአንደኛው በኋላ፣ እና ሶስተኛውን መጠን ከ7 ወራት እስከ 1 ዓመት ከሁለተኛ በኋላ | |
| የልጅነት ልምሻ | ሁለት ወራት | ስቢን (ኦራል) የሚከተብ የልጅነት ልምሻ ክትባት ዓይነቱ 1፣ 3፣ እና 2 በዚያ ቀደም ተከተል፣ ወይንም ትሪቫላንት (ኦራል) የሚከተብ ክትባት 3 መጠኖች፣ ከ6 እስከ 8 ሳምንት ልዩነቶች |
| የጀርመን ኩፍኝ (ሩቤላ) | የ1 ዓመት ዕድሜ እና በለቀመ ለዳም መካከል ያሉ ሁሉም ልጆች። ላልተከተቡ ኮረዳ ልጃገረዶችና ጎልማሳ ሴቶች የሚመቹ። | ነፍስ ያለው ሩቤላ ቫይረስ ክትባት . . . መጠን አንድ |
| የጆሮ ደግፍ | ዕድሚያቸው 12 ወራት ወይንም ከዚያ በላይ | ሊቭ፣ የጆሮ ደግፍ ቫይረስ ክትባት . . . መጠን አንድ |
| ፈንጣጣ | የልማድ ክትባት ባልተጋለጡ ሕዝቦች ዘንድ ከመስከረም 1971 ጀምሮ ተቀባይነት የለውም። | |
| ኩፍኝ (ሩቤላ) | ዕድሚያቸው 12 ወራት ወይንም ከዚያ በላይ (6 ወራት ለተላላፊ በሽታ ይጋለጣሉ) | ሊቭ የሚያቀጭጭ ኩፍኝ ክትባት፣ መጠኑ ነጠላ፣ ወይንም ሊቭ የሚያቀጭጪውን ኩፍኝ ክትባት እና የኩፍኝ መድን ግሎቡሊን (MIG)፣ የእያንዳንዱ መጠን አንድ፣ |
| የተስቦ በሽታ | በተፈለገ ጊዜ ብቻ፣ የልማድ ክትባት በዩ. ኤስ. ኤ አልተጠቀሱም | 2 የተስቦ ክትባት መርፌዎችን 4 ወራት ወይንም ከዚያ በላይ ሳምንቶች በመለያየት ወይንም እንደ ሐኪሞቹ አስተያየት፣ |
| ጉንፋን | ዓመታዊ ክትባት ሥር የሰደደ አድካሚ ሁኔታዎች ላለባቸው ሰዎች | ተቀዳሚ ተራ፣ መጠኖቹ 2 በቆዳ ስር ይሰጣሉ፣ ከ6-8 ሳምንት በማራራቅ፣ እንደ አስፈላጊነቱም እስከ ጥቅምት አጋማሽ ለመጨረስ |

| መጠኖቹን መጨመር | የጎልማሳ ክትባት |
|---|---|
| ከ3 እስከ 6 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች፣ አንድ "ዲፒቲ" በጡንቻ ውስጥ ይሰጣቸዋል። ሌሎች ሰዎች ሁሉ፣ ቲዲ (ለጎልማሶች) በየ10 ዓመቱ ይሰጣቸዋል። በቅርቡ በመጠኑ እንደ ቁስሉ ሁኔታ ከተሰጠ፣ ቀጣዩ ክትባት ለሚቀጥሉት አስርተ ዓመታት አስፈላጊ አይሆንም | ቲዲ (ለጎልማሳ) በየ 10 ዓመታት፣ ወዲያው እንደ ቁስሉ ሁኔታ ከተሰጠ፣ ቀጣዩ የመርፌ ጭማሪ ለሌላ 10 ዓመታት አስፈላጊ አይሆንም። ከ6 ዓመት በኋላ አልተጠቀሰም። |
| ከ12 እስከ 15 ወራት መጠኑ አንድ የሆነ የትሪቫለንት የሚከተብ ክትባት፣ መጠኑ አንድ ደግሞ በትምህርት መግቢያ ጊዜ ይሰጣል | ባልተለመደ አስጊ ሁኔታ ላይ ላሉ ጎልማሶች፣ በውትድርና አገልግሎት ላይ ላሉ፣ ወደ ውጭ የሚጓዙ ሁለት የትሪቫለንት የሚከተቡ ክትባት ከ6 እስከ 8 ሳምንታት በማራራቅ ማግኘት አለባቸው። |
| ምናልባት አያስፈልግም | በ . . . ወቀት መወሰድ የሌለበት ወይም አደገኛ በእርግዝና በክትባት ለውጥ ደረጃዎች<br>ከፍተኛ ትኩሳት<br>በክትባት አለመስማማት ወቀት፣ ለክትባት እጅግ ቁጡነት። |
| ምናልባት አያስፈልግም | ጎረምሳ እና ጎልማሳ ተባዕት ጆሮ ደግፍ ያልነበረው፣ |
|  | ፈንጣጣ አሁንም ካለባቸው አካባቢዎች ለሚመጡ መንገደኞች ከሰራተኞች ጤና ጣቢያ ከጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ልማዳዊ የመድን ክትባት ይሰጣል። |
| ከ9-10 ወራት ዕድሜ በፊት የተከተቡ ልጆች (በተለይም ክትባቱ ከኤም አይ ጂ ጋር የተካሄደ ከሆነ)፣ በድጋሚ ከሊብ የኩፍኝ ክትባት ጋር ስጧቸው። በ10 እስከ 12 ወራት ዕድሜ ለተከተቡት ሕፃናት የልማድ ክትባት በልማዳዊነቱ አያስፈልጋቸውም | የጎልማሳ ክትባት ብዙም አስፈላጊ አይደለም። ማስጠንቀቂያ፣ ብርቱ የትኩሳት በሽታ፣<br>ለክትባት ዘሮች ፈጣን የሳንባ ነቀርሳ በብርቱ ቁጡነትን የሚያሳይ<br>አሻራ የሚያስከትል ሲሆን፣ የመድን ክትባት ለውጥ የክትባት ለውጥ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜና በእርግዝና ጊዜ አይፈቀድም ወይንም አደገኛ ነው። |
| በ4 ዓመታቸው አልፎ አልፎ ነጠላ ክትባት እስከ 2 ጭማሪዎች ይሰጣቸዋል | አስፈላጊ ሲሆን ብቻ፣ በአስጊ ሁኔታ ላይ ለሆኑ ሰዎች ወይንም ወደ ውጭ ለሚሔዱ ብቻ፣ የተስቦ በሽታ ክትባት፣ 2 መርፌዎች ከነጠላ ጭማሪዎች ጋር አልፎ አልፎ በ4 ዓመት ይሰጣል። |
| የቢቫለንት ክትባት ነጠላ የሆነ መጠን ከጥቀምት አጋማሽ በፊት በቆዳ ሥር የሚሰጥ ነው | ማስጠንቀቂያ፡- በእጅጉ የሚያስቀጣ መርፌ ለወሰዱ ወይንም የእንቁላል ፕሮቲን ለተወጉ አይሰጥም፣ ወይንም የብርድ ምልክት ለሚያሳዩ፣ ምልክቱ ጋብ እንዳለ የሚሰጥ ነው። |

(See American Medical Association Chart on immunization.)



24-٨

“ከዚያም እያንዳንዱን የጤና ደንቦችን በመጠበቅ የቻልነውን ያህል ለመኖር እንሞክር፣ የጤና ሕግን በመከተል እና ጥረትን፣ ዕረፍትን በማድረግ፣ እናም በመዝናናት ከዚያም ለተሻለ ሕይወት መዘጋጀት ነው። እነዚህን መሰረተ ሃሳቦች ለልጆቻችን እናስተምር።” (*Discourses of Brigham Young,* p. 186.)

## ሙከራ

የቤተሰብ አባላትዎን መልካም የጤና ልምዶችን እንዲለማመዱ ለማስተማር በዚህ ትምህርት የተጠቀሱትን መንገዶች ይጠቀሙ። የሰንጠረዥ 24-ሀ ስዕል ያጥኑ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፦

1. በአካባቢዎ ላለው ኅብረተሰብ የሚሰጠው ክትባት ምን እንደሆነ ለማወቅ የአቀራቢያዎን የጤና ጣቢያ ይጎብኙ። መቼ እንደሚሰጡ፣ ምን ማስረጃዎች መውሰድ እንዳለብዎትም ወዘተ ያረጋግጡ።
2. በዚህ ትምህርት ላይ የክፍሉ አባላት ታሪክና የቀዱሳን መጽሐፍትን ጥቀሶች እንዲያቀርቡ ይመድቡአቸው።

24-ለ ብልህ ወጣት ሴት በእርግጠኛነት አግባብ ያለውን የእንቅልፍ መጠን ማግኘቷን፣ የሚገነቡ ምግቦችን መመገቧን፣ በአግባቡ ጥርሷን ቢያንስ በቀን ሁለቴ መፋቀዋን፣ እናም እጇን በየጊዜው የምትታጠብ መሆኗን ያሳያል።

# የጓሮ አትክልትን መትከል

ትምህርት 25

የዚህ ትምህርት ዓላማ የጓሮ አትክልት ሥራን ለመጀመር ወይንም ነዋሪ አትክልታችንን በተሻለ ሁኔታ ለማዘጋጀት ለመርዳት ነው።

## ነቢያችን የአትክልት ቦታ እንዲኖረን መክረውናል

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል በየትኛውም ሥፍራ የሚገኙትን የኋለኛውን ቀዱሳን የራሳቸውን ምግብ እንዲያመርቱ አበክረው ያሳስባሉ። ለብዙ ዓመታትም እያንዳንዱን ቤተሰብ የራሳቸው የሆነ የአትክልት ሥፍራ እንዲኖራቸው መክረዋል። እርሳቸው ሲናገሩ፣

“ሁሉንም በራሳችሁ ንብረት መስራት የምትችሉትን ምግቦች እንድታመርቱ እናበረታታችኋለን። የዱር እንጆሪን፣ የወይን ሐርግን፣ የፍረፍሬ ዛፎችን . . .የክልልዎ የአየር ጠባይ የሚያሳድጋቸው ከሆነ ይትከሏቸው። አትክልትን ያምርቱና ከራስዎ የአትክልት ሥፍራ ይመገቡ። በአፓርታማ የሚኖሩም ቢሆኑ . . . በጥቀሉ በማሰሮዎችና በመትከያ ዉሳዉስ ውስጥ ማምረት ይችላሉ። የራስዎትን የተሻለ ምግብ የሚያገኙበትን ዘዴ ያጥኑ። የአትክልት ቦታዎን . . .ንጹህና ማራኪ እንደዚሁም ምርታማ ያድርጉት። በቤትዎ ልጆች ካሉ፣ በዚደቱ ውስጥ በምድብ ኃላፊነት ያሳትፏቸው።” (In Conference Report, Apr. 1976, pp. 170–71; “Family Preparedness,” *Ensign,* May 1976, p. 124.)

ፕሬዚዳንት ኪምቦል እያንዳንዳችንን ከአትክልት ቦታችን እንድናመርት ሲመክሩን፣ “እናም ያልኩአችሁን ሳትፈጽሙ፣ ለምን ጌታ፣ ጌታ በማለት ትጠሩኛላችሁ?” (ሉቃስ 6፥46) የሚለውን የጌታን ቃል አስታውሰውናል።

የአዳኛችንን ቃል በእውነት የምናምን ከሆነ፣ የእርሱ ነብይ ምክር ሲሰጠን ምን እናድርግ?

ይህ የነብያችን ምክር ጥሩ ምክንያቶች አሉት። አትክልትን ማምረት ብዙ ጥቀሞች አሉት። በፍጥረት ላይ ያለንን የአድናቀታችንን አድማስ ያሰፋል። ቤተሰብ በጋራ እንዲሰራ ያስተምራል። በሚገባ ምርት የሚያስገኝ የአትክልት ሥፍራ ካለን፣ ለምግባችን በፍጹም በሌሎች ላይ ጫና አንሆንም። መጋቢነት ያለውን ሰብል መምረጥ እንችላለን። የራሳችንን ምግብ ማምረት ለራሳችን በማስገኘታችን እርካታን ይሰጠናል። ምርቶቻችንን ለጎረቤቶቻችን ለመሸጥም እንችላለን የገንዘብ ቁጠባንም በማድረግ፣ ችግረኞችንም መርዳት እንችላለን።


እህቶች ከጓሮ አትክልት ያገኙትን ጥቅም እንዲያስረዱ ይጠይቁአቸው።

## በዕቅድ መጀመር

የአትክልት ቦታችንን ከመትከላችን በፊት፣ አንዳንድ ውሳኔዎችን ማድረግ አለብን።

ትዕይንት 25-ሀ፣ በአፓርታማ የሚኖሩት በማሰሮዎችና በመትከያዎች አትክልትን መትከል እንደሚችሉ ያሳያል።

25-ሀ፣ በአፓርታማ ውስጥ የሚኖሩት አትክልትን በማሰሮና በመትከያ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ።


25-U

## የት መትከል እንደሚገባ

በቀድሚያ ለተክልትን የት መትከል እንዳለብን መወሰን አለብን። አትክልት በተቻለ ምቹ አካባቢን ይፈልጋል። ጠቃሚ የሆነ አነስተኛ መሬት ሊሆን ይችላል። ቢያንስ በየቀኑ የስድስት ሰዓታት ያህል የፀሐይ ብርሃን ማግኘት የሚችል ፀሐያማ አካባቢን ይምረጡ። የአፈሩንም ሁኔታ ይመርምሩ። አንዳንድ አፈር በጣም አሸዋማ ስለሆነ ውኃን መቋጠር አይችልም፤ ወይንም በጣም ሸክላማ በመሆኑ ውሃ በአናቱ በመጠራቀም በጣም በዝግታ ወደ ውስጥ ያልፋል። ይህ ከሆነ ማዳበሪያን መጨመር ወይም እንዲያሻሽለው ተቃራኒ የሆነውን አፈር መጨመር አለብን። በቂ ዝናብ የሌለበት አካባቢ ከሆነ ውሃ መኖር አለበት። ከተቻለ የአትክልት ሥፍራው በመኖሪያ ቤቱ አቅራቢያ መሆን አለበት። የውሃውም ሥፍራ በጣም በመራቅ በሳምንት የተወሰኑ ጊዜያትን ለመሥራት አድካሚ መሆን የለበትም። በጣም ቀጥ ያላለ ስፍራ ወይም ውሃ አፈርንና ዘርን ጠርጎ የማይወስድበትን ሥፍራ ይምረጡ። ቀጥ ባለ ዳገታማ ሥፍራ ላይ መትከል ካለብዎ፤ ወደ ላይና ወደታች ከማረስ ፈንታ አግድም የሚሔድ ትልም ያብጁለት። በአፓርታማ ውስጥ የሚኖሩት በማሰሮና በመትከያ ነገሮች መትከል ይችላሉ።

ትዕይንት 25-ለ፤ በሚገባ በአካባቢዎ የአየር ጠባይና አፈር የተሻለ ምርት የሚሰጠውን አትክልት መርጠው ይትከሉ።

ሰፊ የአትክልት ሥፍራን የሚፈልጉ በመኖሪያ አካባቢ ወይም የአበባ አትክልት ቦታን ወይም መሬትን በመዋስ ወይንም በመከራየት መቀፈር ይችላሉ። ሁለት የጀርመን ቤተሰቦች የአትክልት ሥፍራን እንዴት እንደሚያገኙ ዘዴውን ደርሰውበታል፤

“ ‘እኛ በፍራንክፈርት ሚስዮን ውስጥ የምንገኝ ሁለት ቤተሰቦች ስንሆን፤ እናም ስለ አትክልት ሥፍራችን ልንነግራችሁ እየጻፍንላችሁ ነው።

“ ‘እንደ ፍራንክፈርት ባሉ ሰፊ ከተሞች ቁራጭ መሬት ማግኘት ቀላል አይደለም. . . . ቀጭን የአትክልት ሥፍራ ነች. . . . እናም በተከራየን ጊዜ ምድረበዳ የመሰለች፤ ከተሰባበረ አጥር፤ ጋር በተጣመመ ጎጆና በሜዳ ሣር የተሞላች ነበረች። ይህ ተስፋ አላስቆረጠንም።

“በቀድሚያ አዲስ አጥር አጠርን፤ ጎጆዋንም ጠገንን፤ እናም ሙሉውንም የአትክልት ሥፍራ ቆፈርን። በፀደይ ወቀት አትክልትም ተከልን እናም ጎረቤቶቻችንም እንደማያመርቱ ነገሩን። ከትንሽ ምንጭ በብስክሌት ጋሪ የውኃ ቆርቆሮዎችን ጭነን በዚህ ዓይነት ውኃ የምናመላልስበት ነበረች። የአትክልት ቦታችንን እንዲባርክልን ወደ ጌታ ፀለይን። ጌታም ለፀሎታችን ምላሹን ሰጠን። የተለያዩ አትክልቶች በቀሉልን። አትክልት ሲመረት ማየት በጣም አስደናቂ ነው’።” (Spencer W. Kimball, “A Report and a Challenge,” *Ensign,* Nov. 1976, p.5.)

## ምን መትከል እንደሚገባ

ማድረግ ያለብን ሁለተኛው ውሳኔ ምን መትከል እንደሚገባን ነው። አንዳንድ የአትክልት ቦታዎች ብዙ የመትከያ ቦታ አላቸው፤ አንዳንዶቹ ትንሽ ብቻ ይኖራቸዋል። ያለው ቦታ የተወሰነ ከሆነ፤ ወደላይ የሚያድጉትን ሰብሎች፤ እንደ የወይን እንጆሪን፤ ባቄላን ወይንም የችካል ቲማቲም የመሳሰሉትን ይምረጡ። ከበድ ያሉ ፍሬ የሚያፈሩትን፤ ከነጠላ ፍሬ እንደ ቀይ ሥር አይነቶቹ ይልቅ እንደ ዱባና ቲማቲም ያሉትን ይምረጡ።

25-ለ፤ በክልልዎ የአየር ንብረትና አፈር በሚገባ ማደግ የሚችሉትን የምግብ ተክሎችን ይምረጡ።


25-A

ቤተሰቦችዎ የሚፈልጉትተ ጠቃሚ ምግብ የሚገኝበትን ምግቦችን ለመምረጥ እርግጠኛ ይሁኑ። ነገር ግን እነርሱ የማይወዱትንና የማይበሉትን መትከልን ይተዉ። ጥራጥሬዎች . . . እንደ ምስር፣ ቦሎቄ፣ አተር እና ኦቾሎኒ. . . . የሰውነት ጡንቻዎችን መልሶ ለመገንባት ይረዳሉ። ፍራፍሬዎችና የቀጠላቀጠል አትክልቶች ከበሽታ ይጠብቁናል። ጣፋጭ የሆኑ አትክልቶች ኃይል ይሰጡናል። ለማምረት በቂ ሥፍራ ካለዎት እህሎች ደግሞ ኃይልን ይሰጣሉ። በአካባቢዎ የአየርና አፈር ጠባይ በሚገባ የሚመረተውን የምግብ አትክልትን ይምረጡ።

በአካባቢዎ የሚመረተውን ልዩ ፍራፍሬዎችን፣ አትክልቶችን ጥራጥሬዎችን፣ ሥራሥሮችን፣ እና እህሎችን የያዘውን ሰንጠረዥ ያሳዩ።

የትኞቹ እህሎች በተወሰነ መጠነኛ ቦታ ላቀ ያለ ምግብን ሊሰጡ ይችላሉ?

በየአመቱ ለአትክልት ቦታ በሚያቀዱበት ጊዜ በካርታ ላይ የአትክልት ሥፍራዎን መሳል ጥሩ ሃሳብ ነው። አንድ ዓይነት የሆነ ተክልን በተመሳሳይ ቦታ ከዓመት ወደ ዓመት መልሶ ማምረት አይገባም። እህሎች ካልተለዋወጡ፣ በየጊዜው ምርቱ እየቀነሰ እየቀነሰ ይሔዳል።

ትዕይንት 25-ሐ፣ የአትክልትን ናሙና ዓይነት ያሳያል።

## መቼ መትከል እንደሚገባ

ሌላው ውሳኔ ማድረግ ያለብን መቼ እንደምንተክል ነው። እያንዳንዱ ምግብ በበለጠ የሚመረተው በራሱ ተስማሚ ሁኔታ ላይ ሲሆን ነው። አንዳንድ እህሎች በደረቅ ወራት በጥሩ ሁኔታ ሲያድጉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ብዙ ውሃን ይፈልጋሉ። አንዳንዶቹ በቀዝቃዛ የአየር ንብረት በበለጠ ያድጋሉ፣ ጣፋጭ የአገዳ ተክሎች፣ ጥቀል ጎመን፣ ካሮት፣ ሰላጣ፣ ሽንኩርት፣ አተርና ቆስጣ ሌሎች በሞቃት የአየር ጠባይ የበለጠ ያድጋሉ፣ ባቄላ፣ ማሽላ፣ ከርቡሽ፣ ዱባ፣ እና ቲማቲም።

በአካባቢዎ ለሚመረቱ ለልዩ እህሎች የመትከያ ወቀቶችን የያዘውን ሰንጠረዥ ያሳዩ።

## **የአትክልት ክልልን ማዘጋጀት**


ከመትከያ ጊዜ ከአራት እስከ ስድስት ሳምንታት በፊት፣ የአረም ቦታን፣ ስሮችን ደንጊያዎችን፣ ቆሻሻን እና ቀምበጦችን ይመንጥሩ። አፈሩን በአካፋ ወይም በዛባ ይከስክሱት በመሆኑም ውሃ በቀላሉ በውስጡ ሊሄድ ይችላል። በመትከያ ወቀት እንዳይጠናከር አፈሩ መፈርፈር አለበት።

ትዕይንት 25-መ፣ ከመትከያ ወቀት በፊት አፈርን በሚገባ ማዘጋጀትን ያሳያል።


በዚህን ጊዜ፣ አብዛኛው አፈር የተሻለ መሆን ይችላል። የአሸዋማና የሸክላማ አፈርን መልክ የበሰበሰ የተክልና የእንስሳት ቆሻሻ በሚገባ ያሻሽለዋል። አስፈላጊ ምግቦች ስለተጨመረባቸው የተሻለ እህሎችን ደግሞ ለማምረት ይረዳሉ። ነገር ግን ማዳበሪያ በአንድ ቀን ተሰርቶ በአፈር ውስጥ ሊደረግ አይችልም። በአፈር ውስጥ ለመዋሃድ የሚችለውን ማዳበሪያ ለማምረት ከአራት እስከ ስድስት ወራት ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ይህም በመሆኑ፣ አንዳንድ ሰዎች በየዓመቱ ኩስ ይቀልሉና በአትክልቶቻቸው ውስጥ በቀጣዩ አመት ይጨምራሉ።

የማዳበሪያ ኩስንን ለማበጀት፣ መቀለሉን መጀመር፣ ጉድጓድ መቀፈርን፣ ወይም ሶስት ጎን ያለው እንጨት ወይም በላዩ ላይ በሽቦ የታጠረን መሬት መገንባት ይችላሉ። የቆሻሻው አካል

25-ሐ የአትክልት ቡድን ናሙና


25-ሐ
ባቄላዎች
ሰላጣ
ካሮት
ጥቅል ጎመን
ሽንኩርት
አረንጓዴማ አበባ ጎመን
ቲማቲም
የዱባ ተክል









ውፍረቱ ስድስት ኢንች የሆነውን ይዘርጉ። ለዚህም ቀጠሎችን፣ የተቆራረጠ የበቆሎ ጆሮ፣ ገለባ፣ አትክልት ወይም የፍራፍሬ ልጣጭ፣ ወይም ትራፊ ምግብ (ቶሎ ከማይበሰብስ ከአጥንትና ስብ በስተቀር) ይጠቀሙ። ቀርቀሮዎች ብረታብረት ነገሮች፣ ወይም ሌላ የማይበሰብሱ ቁልሎች እንዳይገቡ ይጠንቀቁ። የከብቶችን ቆሻሻ (ማዳበሪያ) እንደ የዶሮ ኩስ፣ የፍየሎችን በጠጥ፣ የላሞችን እበት፣ የፈረሶች ወይንም የዓሳማዎችን ፋንዲያ ይጨምሩ። ነገር ግን የሰው ቆሻሻን ወይንም የስጋ በል እንስሳትን ቆሻሻዎች በአፈሩ ውስጥ ጀርሞችን መጨመር ስለሚችሉ በፍጹም እንዳይጨምሩ።

የቆሻሻን ቁጥኝ በሁለት ኢንች የአፈር ውፍረት ይሸፍኑ። የቁልሉ ጫፍ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳን ማበጀት መጀመሩን ሁልጊዜ እርግጠኛ ይሁኑ። በቂ ቆሻሻ እንዳጠራቀሙ፣ ሌላ ስድስት ኢንች ውፍረት ያለውን በቁልሉ ላይ ይጨምሩና በአፈር ይክደኑት። ቆሻሻውን በሰበሰቡ ቁጥር ቋጥኙን መጨመሩን ይቀጥሉ። እያንዳንዱን ቋጥኝ መሰብሰብ እንደቀጠሉ ያርሱት። ሁልጊዜ ቁልሉም ይራስ ግን በጣም እንዳይረጥብ። አየር በመካከሉ እንዲገባ ለማድረግ ወይም በመንሽ በየሳምንቱ ያገላብጡት። መሃሉ በ160 ዲግሪ “ከፈላ” ቁልሉ በፍጥነት ይበሰብሳል። የብስባሹ ቁልል መካከሉ ካልሞቀ፣ በተፈጨ እህል መልክ ተጨማሪ ናይትሮጅንን ይጨምሩበት። ቁልሉ ሽታውን ከጨረሰ ብስባሹ ከአፈር ጋር ለመዋሃድ ዝግጁ ይሆናል።

እህቶችን ብስባሹን የሚያዘጋጁበትን የራሳቸውን ዘዴ እንዲያስረዱ ይጠይቁ።

## የአትክልት ቦታን መትከል

የምርቱ ወቀት በሚያጥርበት አካባቢዎች፣ አትክልትዎን እቤት ውስጥ በማሰሮ አፈር በመሥራት መጀመርን ይፈልጉ ይሆናል። ከቤት ውጭ ቢጀምሩ፣ አረምን ቀጥ ባለ መስመር በመዝራት ከአትክልቱ አረምን መለየት ይችላሉ። በዘሮቹ መካከል ርቀትን ያኑሩ። ለእያንዳንዱ እህል ዘሩን መቼ እንደሚዘሩና በቀናቶቹም መዝራትን ይማሩ። አንድን ዓይነት ሰብል በአንድ መስመር በተወሰኑ ሳምንታት ልዩነቶች በየሳምንቱ ይትከሉ። ከዚያም ሰብሉን ለማሳደግ ረዥም ወቀት ያገኛሉ ማለት ነው።

ዘሮቹ በመጠን ይለያያሉ፣ ሁሉም በተመሳሳይ ጥልቀት ከተተከሉ አያድጉም። እያንዳንዱን ዘር ከጎን ስፋቱ ከሶስት ጊዜ ባልበለጠ ጥልቀት ይትከሉ። ከዚያም አፈሩን በኃይል ወደ ታች ይጠቀጥቁት። በሚያድጉበት ጊዜ አፈሩን ለማላላት ያመች ዘንድ በተክሎቹ መስመር መካከል በቂ ርቀት መኖሩን እርግጠኛ ይሁኑ።

ዘሮቹ ከተተከሉ በኋላ መሬቱ እርጥበት እንዲኖረው ያድርጉት። መሬቱ ከደረቀ፣ ዘሮቹ አይበሰብሱም።

## አትክልትን መጠበቅ

በምናደርጋቸው ሁሉም ዕቅዶች፣ ዝግጅቶች፣ እናም ተከላዎች ለአትክልቶቻችን የማንጠነቀቅ ከሆነ በኋላ ላይ አነስተኛ ጥቅም ብቻ እናገኛለን። ስለሆነም የሚከተሉትን ልናደርግ ይገባናል፣

25-መ፣ ከመትከልዎ በፊት አፈርን በሚገባ ያዘጋጁ።

ውሃ

በቂ ዝናብ የማይጥል ከሆነ አትክልቱን በሳምንት አንዴ በሚገባ ውሃ ያጠጡት። ውኃ ከጠጣ በኋላ አፈሩ እስከ ሰባት ኢንች ጥልቀት መርጠብ አለበት። መሬቱ እንዳይቦካ የፀሐይ ኃይል በማይጠናክርበት ጊዜ ሁልጊዜ ውኃ ያጠጡት።

መኮትኮት

አረሞች ከአትክልቶች ውስጥ ውኃንና ምግብን ይወስዳሉ። በእጅ ወይም በዛባ ይቆፍሩና ነቀለው ያጥፉአቸው። ወፍራም ከለላ አረሞች እንዳያድጉ ሊያግድ ችላል፣ ነገር ግን አፈሩን ለማላላት በየሳምንቱ ከለላውን በመንቀልና ወደአንድ በኩል በማድረግ ይኮትኩቱ። አፈሩን ካላሉት በኋላ ከለላውን በቦታው ይመልሱ።

ከለላ

ተክሉ በተወሰኑ ሴንቲ ሜትሮች ከፍ ካለ፣ ማንኛውንም ቀሪ አረሞችን ያስወግዱ። ሰጋቱራን፣ የተበላሹ የጋዜጣ ወረቀቶች፣ ሳርን፣ ቀጠሎችን ወይም ገለባን ከአምስት እስከ ሰባት ነጥብ አምስት ሳንቲ ሜትር ሶስት ኢንች ከፍታ በተክሎቹ ዙሪያ በየመስመሮቹ መካከል ያስቀምጡ። ይህም ከለላ አፈሩን ከመድረቅና በጣም ከመሞቅ ያግዳል። ብዙዎች ከለላን የሚጠቀሙ ሰዎች ብዙ አረሞችን ለመንቀል አይቸገሩም።

የተባይ ጥፋትን መቆጣጠር

ተባዮች ተክልን ያጠፉሉ፣ እህልንም ሊያበላሹ ይችላሉ። የደረሰ እህልን ከማበላሸታቸው በፊት ማንሳትዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ካላነሱ ተባዮቹ ይመገቧቸዋል። ፍሬ ማፍራት ያቆሙትን እህሎች ደግሞ ያንሷቸው። ተባዮችን በእጅ በማንሳት ከተክሎቹ ላይ ያጥፉአቸው። ወይንም የተባይ ማጥፌያን ይጠቀሙ። የተባይ ማጥፌያን ከተጠቀሙ ምግብን ከመመገብዎ በፊት መታጠብዎን ያረጋግጡ።

ሰብልን መሰብሰብ

ፍራፍሬን እና አትክልትን ልክ ከመብሰሉ፣ ከመመገብዎ፣ ወይንም ከማቆየትዎ በፊት ካነሱ፣ የበለጠ ጣዕምና ምግብነትን ይሰጣሉ። አንዳንድ ሰብሎች እንደ ክያር የመሳሰሉት በየጊዜው ቢሰበሰቡ በጣም የተሻለ ምርትን ይሰጣሉ። ከሚገባ በላይ እንዲበስሉ እንዲጠወልጉ፣ ወይም እንዲደርቁ አታድርጉአቸው። ቀጠልማ አትክልትን በለጋነታቸውና በለስላሳ ወቅታቸው ይሰብስቧቸው።

ትዕይንት 25-ሠ፣ አትክልትዎን መሰብሰብ የደስታ ጊዜዎ መሆን ይችላል።

ለአትክልት ብናቀድ፣ ብንዘጋጅ፣ እና ብንተክል፣ ከዚያም ካልተጠነቀቅንለት ምን ይደርስበታል?

**ማጠቃለያ**

ነቢያቶቹ እንደጠየቁን በማድረግ ጌታን እንደምንወደውና እንደምናምነው ማሳየት እንችላለን። ብናቀድ እና የአትክልት ሥፍራዎቻችንን ብናዘጋጅ፣ ከዚያም በሥርዓት እንዲሆኑና በአግባቡ እንዲያመርቱ ብንጠነቀቅላቸው እያንዳንዳችን በረከቶችን እንቀበላለን። ፕሬዚዳንት ኪምቦል ሲመክሩን፣

25-ሠ፣ አትክልትዎን መሰብሰብ የደስታ ጊዜዎ ሊሆን ይችላል።



“መስክዎንና አትክልትዎን በሚገባ በመጥረግ ይጠብቁ። ሁኔታዎ ምን ይሁን ምን፣ ድርጅትዎ ሥርዓትን፣ ውበትን፣ እና ደስታን ያንፀባረቀ ይሁን። ዕቅድዎን በሥርዓቱ እናም በብልሃታዊ ሁኔታ በማካሄድ በሚገባ ያቀዱ።” (In Conference Report, Apr. 1976, p. 171; “Family Preparedness,” *Ensign,* May 1976, p. 125.)

## ሙከራ

አሁን አትክልትዎን ለመጀመር ወይንም ለማሻሻል ያቀዱ። የተዋጣለት አትክልት እንዲኖራችው ቤተሰቦች በሙሉ በጋራ መሥራት እንደሚችሉ ያስታውሱ።

ትምህርትና ቃልኪዳን 59፥16–19 ያንብቡ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፣

1. ከምንባብ ቤትዎ፣ ከክልልዎ የእርሻ አማካሪዎች፣ ወይም ልምድ ካላቸው አትክልተኞች የሚከተሉትን ይማሩ።
   ሀ. በጓሮ አትክልት የትኛው ሰብል የበለጠ ምርትን ይሰጣል።
   ለ. ለእያንዳንዱ ሰብል የተከላ ወቀቶች እንዴት እንደሆኑ
   ሐ. በጓሮ አትክልት የተሳካ የኩስ ቁልል እንዴት እንደምናበጅ
   መ. ውሃን እንዴት እንደምናጠጣ፣ እንደምናርም፣ የተባይ ጥፋትን እንደምንቀጣጠር፣ ከለላን እንደምናደርግ፣ እናም የጓሮ አትክልታችንን እንደምንኮተኩት።
2. በትምህርቱ ውስጥ መጠቀም ይቻል ዘንድ ሰንጠረዥን ያዘጋጁ።

# የቤት ምርት

ትምህርት 26

የዚህ ትምህርት ዓላማ በቤታችን የምንፈልገውን በማምረት ራሳችንን እንዴት መርዳት እንደምንችል ለመማር እንዲረዳን ነው።

**ራስን መርዳት**

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል እንዲህ አሉ፣ "ሁሉም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ቤተሰቦች ራሳቸውን እንዲችሉና ነፃ እንዲሆኑ እናበረታታቸዋለን" (In Conference Report, Apr. 1976, p.170; "Family Preparedness," *Ensign,* May 1976, p. 124)። ለዚህ ምክር ጥሩ ምክንያት አሉ፣ ፕሬዚዳንት ማሪዮ ጂ. ሮምኒ ሲያስረዱ፣

"እኛ በመጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ እየኖርን ነው . . . ልክ የጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽዓት በሚያስከትለው ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው። በሰለስቲያል መንግሥት ሥር ከሁሉም ፍጥረት ነጻ ሆነን. . . . እንድንዘጋጅና መሆን በምንችለው እንድንኖር ተነግሮናል"። (In Conference Report, Apr. 1975, p. 165.) (ት እና ቃ 78፣13–14 ይመልከቱ፡፡)

ስዕል 26-ሀ፣ ዶሮዎችና ሌላ ትንንሽ እንስሳት ለምግብነት በትንሽ ቦታ ማደግ መቻላቸውን ያሳያል።

ፕሬዚዳንት ኪምቦል ራሳችንን የምንችል እንድንሆን አስጠንቀቀውናል፡፡
ምክንያቱም የጥንቱ ትንቢቶች በመፈጸም ላይ ናቸው። እንዲህም ሲሉ ተናግረዋል፣

"ከፍተኛ ሃዘን የሚሆንበት ጊዜ፣ ከፍ ያለ ኀይለኛ ዓውሎ ነፋስና ከፍተኛ የጎርፍ መጥለቅለቀ . . . ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ እየመጣ ይመስለኛል። ወደ መጨረሻው ስንቃረብ ምናልባት እየጨመሩ የሚሄዱ ይመስለኛል፣ እናም ለዚህ መዘጋጀት አለብን።" (In Conference Report, Apr. 1974, p.184.)

ፕሬዚዳንት ኪምቦል ደግመው ሲናገሩ፣

"የከፋ ቀን ቢመጣ፣ ብዙዎች የፍራፍሬ ጠርሙሳቸው ሁሉ የሞላ ቢሆን እና በጓሯቸው አትክልት እና ጥቂት የፍራፍሬ ዛፎች እና የእንጆሪ ቁጥቋጦች እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጣ ሸቀጦች ለማዘጋጀት ይመኙ ይሆናል፡፡

"ጌታ በማንኛውም ፍጥረት ጥገኞች መሆን እንዳንችል አቀዷል፣ ነገር ግን ብዙ አርሶ አደሮች ወተታቸውን ከወተት ማደያ፣ እናም ብዙ ቤተሰቦች የአትክልታቸውን ውጤት ከመደብሮች እንደሚገዙ ጭምር አውቀናል። እናም የጭነት መኪናዎች የመደብሮችን መደርደሪያዎች መሙላት ቢያቅታቸው ብዙዎች ደግሞ ይራባሉ።" (In Conference Report, Oct. 1974, p. 6.)

እህቶችን መደብሮች መዘጋታችውንና በማንኛውም ነገር በራሳቸው መተማመን እንዳለባቸው እንዲያስቡ ንገሯቸው። በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በአካባቢያቸው ምን ማምረት እንድሚፈልጉ ይጠይቁአቸው።



## የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንዴት ማዘጋጀት እንደምንችል

ቄስ ቫን ጄ.ፊቱርስተን በቤተክርስቲያኑ የጳጳሳት አመራር በነበሩበት ጊዜ፣ ፍላጎታችንን ለማሟላት የትኛውን ሙያ ማጎልበት እንዳለብን አስተምረውናል።

“አሁን የቤት ምርትን በተመለከተ፣ ሁኔታዎችና የአካባቢ ደንቦች በሚፈቅዱት መሰረት እንስሳትን ያርቡ። የፍራፍሬ ዛፎችን፣ የወይን ሐረግን፣ እንጆሪን፣ እና አትክልቶችን ይትከሉ። በዚህ ዓይነት ለቤተሰብዎ በአብዛኛው ተስማሚና ንጹሕ ሆኖ የሚበሉትን ምግቦች ማቅረብ ይችላሉ። ሌሎች የሚመረቱት ምግቦች መቆየት የሚችሉና ከቤት ክምችት ክፍል የሚጠቃለሉ መሆን ይችላሉ። በሚቻለው ስፍራ ሁሉ፣ ምግብ አልባ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ለማምረት ይሞክሩ። የራስዎን ልብስ ይስፉ እናም ይጠግኑ። አስፈላጊ ዕቃዎችን ያብጁ ወይም ይገንቡ። እኔ ደግሞ ንብረትዎን ሁሉ ማሳመር፣ ማሳደስ፣ እና መጠገን እንዳለብዎ አስተያየቴን እሰጣለሁ።“ (“Food Storage,” *Ensign,* May 1976, p. 117.)

የጳጳስ ጄ. ፌቱርስተንን መመሪያዎች ለመከተል፣ ፍላጎታችንን እንዴት እንደምናሟላ በሚከተሉት መንገዶች መማር አለብን።

የሚከተሉትን ዝርዝር የሚያሳዩትን ስዕላዊ መግለጫዎች ያሳዩ፣

1. የከብት እርባታዎች ይኑርዎ።
2. የፍራፍሬ ዛፎችን፣ እንጆሪንና፣ የወይን ሐረግን ይትከሉ።
3. በአትክልት ስፍራዎ ተክሎችን ይትከሉ።
4. ምግብን ያቆዩ።
5. የልብስ ስፌት ጥገና ያድርጉ።
6. የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ያብጁ ወይም ይገንቡ
7. የራሳችንን ንብረት ማደስ ወይም መጠገን

### የከብት እርባታ ይኑርዎ

በቂ መሬት ካለንና በሕጋዊ መንገድ የከብት ርቢ ሊኖረን በሚችል አካባቢ ብንኖር፣ ጥቂት ከብቶችን ማርባት ይገባናል። የትኛውን ከብት ማርባት እንዳለብን ከመወሰናችን በፊት፣ ስለምግባቸው፣ መጠለያቸው፣ እናም ጤናማ እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸውን ጥንቃቄዎች መማር አለብን። አስቀድመን ልንጠነቀቀላቸው መዘጋጀት ይገባናል። ከምንጠነቀቀላቸው ቀላል እንስሳት ጥቂቶቹ ዶሮዎች፣ ጥንቸሎች፣ ዳክዬዎች፣ እና የወተት ፍየሎች ናቸው።

በክልልዎ በአብዛኛው የሚረቡትን የከብት እርባታ ዓይነቶች ይወያዩ።

እያንዳንዳቸው የሚፈልጉትን ምግቦች፣ መጠለያ፣ እና ጥንቃቄ ላይ ይወያዩ።


ስዕል 26-ለ፣ የዛፎችን እና የአትክልት ተከላን ያሳያል።

### የፍራፍሬ ዛፎችን፣ የወይን ተክሎችንና እንጆሪዎችን መትከል

የፍራፍሬ ዛፎች፣ የወይን ሐረጎች፣ እና እንጆሪዎች በየዓመቱ ወይም በወዲያኛው ዓመታቸው ፍሬ ያፈራሉ። እንደ አትክልት በየዓመቱ መተከል አይፈልጉም። ነገር ግን፣ ከተተከሉ በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት ፍሬ ላያፈሩ ይችላሉ። በጣም በምንፈልግበት ጊዜ ፍሬያቸውን እንድናገኝ በተቻለ ፍጥነት መትከል አለብን።

እያንዳንዱ ዛፍ፣ የወይን ሐረግ፣ እና እንጆሪ በትክክለኛው መጠን ውኃ ይፈልጋሉ። ተባያቸውንና በሽታቸውን መቆጣጠር ይገባናል። አንዳንድ ዛፎችና እንጆሪዎች ከሌሎች

26-ሀ ዶሮዎችና ሌሎች ትናንሽ እንስሳት በአነስተኛ ቦታ መርባት ይችላሉ።



26-۸

በጣም ሰፊ ሆነው ያድጋሉ። ከመትከላችን በፊት፣ ሙሉ በሙሉ በሚያድጉበት ጊዜ ምን ያህል የቦታ ስፋት እንደሚበቃቸው ማወቅ አለብን።

በአካባቢዎ የትኛው የፍራፍሬ ዛፍ፣ የወይን ሐረግ፣ እና የዱር እንጆሪ በሚገባ እንደሚመረት ይነጋገሩበት። አያንዳንዳቸው በሚያስፈልጋቸው ጥንቃቄዎች ላይ ይወያዩ።

ስዕል 26-ሐ፣ እነዚህ ቤተሰብ በአትክልት ቦታቸው ላይ በጋራ ሲሰሩ ያሳያል።

## በአትክልት ስፍራ ላይ አትክልትን መትከል፣

ፕሬዚዳንት ኪምቦል እያንዳንዱ ቤተሰብ የአትክልት መትከያ ቦታ እንዲኖረው ይመክራሉ። ትኩስ ምግብ፣ እናም ተጨማሪ የምናስቀምጣቸውንና የምናከማቻቸውን ምግቦች ያስገኙልናል። ትምህርት 25 በዚህ መምሪያ ስለ ጓሮ አትክልት ይጠቅሳል።

ስዕል 26-መ፣ ምግቦችን፣ በቆርቆሮ በማሸግ፣ አዲስ ምርት በሌለበት ጊዜ ለመጠቀም ድርቀሽ በማድረግ ማከማቸት እንደሚቻል ያሳያል።

## ምግቦችን ማቆየት

ለብዙ ዓመታት፣ ነብያቶቻችን በሕጋዊነት ማከናወን በምንችልበት አካባቢ፣ ምግቦቻችንን እንድናቆይና እንድናከማች ይመክሩናል። ምናልባት ሌላ ምግብ የማይገኝበት አጋጣሚ ሊመጣ ስለሚችል ምግብን ማከማቸት አለብን። በ1974 ማለቂያ ላይ፣ ሁንዱራስ በቸነፈር በተመታች ጊዜ የቤተክርስቲያኑ አባላት ምግባቸውን አድርቀው አከማችተው ስለነበር ዕድለኞች ነበሩ። ከቸነፈሩ ጥቂት ወራት ብቻ ቀደም ብሎ፣ የሚሲዮኑ ፕሬዚዳንት ወደፊት ስለሚከሰተው አደጋ አስጠንቅቀአቸው ነበር። የምግብ ማከማቸቱን ፕሮግራም እንዲጀምሩ አበክረው አሳስበዋቸዋል። ባቄላ፣ ዱቄት፣ ሩዝ፣ እናም ሌሎች የቀዩአቸው ቀለል ያሉ መሰረታዊ ምግቦች ምዕመናኑን ከረሐብ አደጋ ሊታደጉ ችለዋል። (See Bruce Chapman, “Hurricane in Honduras,” *New Era,* Jan. 1975, pp. 30–31.)

የራሳችንን ምግቦች ለማቆየትና ለማከማቸት ማድረግ፣ የምንችለው . . .

1. በምድር ስር ማከማቸት። በጣም ብዙ ዝናብ ከሌለ ወይም አነስተኛ የመስኖ አጠቃቀም ባለበት ጊዜ፣ ይህ ብልሃት ለአንዳንድ ሥራሥርና ለተለያዩ የአረንጓዴ አትክልቶችና፣ ቀጠላማ አትክልቶች ጥሩ ነው።

2. ያድርቁት። በሞቃት ወቀት፣ በፀሃያማ አየር ሁኔታ፣ ፍራፍሬዎችና አትክልቶች በፀሃይ ላይ ሊደርቁ ይችላሉ። ነገር ግን በዝናብ ጊዜ መክደን፣ ወይም ወደ ውስጥ ሊያስገቡአቸው ይገባል። የሚደርቁት ምግቦች ከዝንቦችና ሌሎች ተባዮች መጠበቅ አለባቸው።

3. በጠርሙስ ውስጥ ያድርጉአቸው። ይህ ብልሃት ቀላል ነው፣ ነገር ግን ያለአግባብ ከተደረገ አደገኛ ናቸው። በአግባቡ ከተከናወኑ፣ በጠርሙስ ውስጥ ምግብን ማድረግ ጥሩ የማከማቸትና የጣዕም መጠበቂያ ዘዴ ነው። በአግባቡ በጠርሙስ የማሸግ ስራ ቢያንስ ሰፊ ክትሊ ክዳን ያለውና ሙሉ የሸቦ ማዕዘን የሆነ ያስፈልጋል። (በዚህ የተካተቱት ቁሳቁሶች በብዙ ቤተሰብ መካከል ሊከፋፈሉ ይችላሉ።) ይህ ብልሃት ደግሞ ጠርሙሶቹን ከስብራት እንዲጠበቁ ይረዳል።

26-ለ ዛፎችንና አትክልቶችን መትከል።

26-ሐ ይህ ቤተሰብ በአትክልት ስፍራቸው ውስጥ በጋራ ይሰራሉ።
26-መ አዲስ ምርት በማይኖርበት ጊዜ ምግብን ማከማቸት፣ በቆርቆሮ ማሸግና ለአገልግሎት ማድረቅ ይቻላል።





4. በጨው መለወስ ወይም ምግቦችን በጨው ውሃ ማድረቅ። ይህ ፍራፍሬን፣ አትክልትን፣ እና ስጋን የማቆያ ውድ የሆነ ብልሃት ነው። ትንሽ ወይም ምንም መሳሪያ አያሻም።

በአካባቢዎ ባህላዊ ምግብን የማቆየት ዘዴዎችን ይወያዩበት።

እህቶች መማር በሚፈልጉት አዲስ ብልሃት ላይ ይወያዩበት።

ስዕል 26-ሠ በስፌት፣ በማብሰያ እና በቤት ዙሪያ ግንባታ ላይ የዋሉትን ቁሳቁሶች ያሳያል።

## መስፋትና መጠገን

የራሳችንን ልብሶች መስፋትና መጠገንን መማር አለብን። ለችግር ጊዜ ለመዘጋጀት፣ ደግሞ እንዴት አሮጌ ልብሶችን እንደምናድስ መማር አለብን። ምንም ነገር ባይኖርም እንኳ ልብሶቻችንን ለማዘጋጀት ጨርቆችን ማከማቸት መልካም ሐሳብ ነው። ልብስ ከመስፋት በተጨማሪ ብዙ ነገሮችን ለመስራት መማር እንችላለን፣ የመኝታ አልጋ ልብሶች፣ የመስኮት፣ እና የወለል መሸፈኛዎችን፣ ፎጣዎችን፣ የጠረጴዛ ልብሶችን፣ እና የቤት ቁሳቁሶችን ማስዋብ ወይም መሸፈኛ ዓይነትን መስራት። ሌሎች ሙያዎችን ደግሞ . . . እንደሽመና፣ የአልጋ ልብስ ሥራ፣ የሹራብ አሰራር ዘዴ፣ በኪሮሽ የሚሰሩ ስራዎችን፣ እናም ሌሎች የስፌት ሥራዎች መማር እንችላለን። እነዚህ ሁሉ ልብሶቻችንና ቤቶቻችንን ሊያስውቡልን ይችላሉ።

ለቤታችን ምን መስፋት ወይም መስራት እንችላለን?

## ተፈላጊ ዕቃዎችን ማበጀት ወይም መገንባት

ለተፈጥሮ አደጋ የምንጋለጥ ቢሆን፣ ምግብን ለማብሰል፣ ቤቶቻችንንና ምግቦቻችንን እናም ልብሶቻችንን ለማሞቅ፣ እና ልብሳችንን፣ ሰውነታችንን፣ እና አካባቢያችንን ለማጽዳት መዘጋጀት አለብን። ነዳጅንና ሳሙናን ማጠራቀም፣ ወይም ለአደጋ ጊዜ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግን መማር ጠቃሚ ነው።

በአደጋ ጊዜ፣ ቤታችንን፣ ጎተራዎችን፣ ወይም የከብት ማጎሪያ በረትን ደግሞ መልሰን የምንገነባበት አጋጣሚ ሊኖረን ይችላል። የቤተሰብ አባላት መሳሪያዎችን ለመገልገል በእንጨትና በሌሎች ቁሳቁሶች መሥራትን መማር አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ንብረትን መስራትንና መጠገንን ሊማሩ ይችላሉ።

በዚህ አካባቢ የምናውቃቸው ባለሙያ ሰዎች አሉ?

የቤተሰቦቻችን አባላት እነዚህን ሙያዎች እንዲማሩ እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

## ንብረቶቻችንን መጠገንና ማደስ


ጊዜያችንና ገንዘባችንን መቆጠብ እንፈልጋለን እናም በሌሎች ላይ ጥገኝነትን ማስወገድ እንፈልጋለን። ይህንን ለማድረግ፣ ንብረቶቻችንን መጠገንና ማደስን መማር እንችላለን።


ንብረቶቻችንን በጥሩ እድሳት መጠበቅ ለምን ያስፈልጋል?


## **የጎደሉንን ሙያዎች መማር**


ቤተክርስቲያኑ ራስን መቻል ለመማር የተለያዩ ክፍሎች እንዲኖሩ ያሳስባል። አንዳንዶቻችን ያሉንን የተማርናቸውን ሙያዎች ለሌሎች እህቶች ማስተማር እንችላለን። እኛ የሌለን ሙያዎች ካሉ፣ ከዚያም የሚያስተምሩንን ሰዎች መፈለግ እንችላለን። ምናልባት ከመጻሐፍት፣

26-ሠ በስፌት፣ በማብሰል፣ እና በቤት ዙሪያ በመገንባት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች።









ከመጽሔቶች፣ ከባልትና መማሪያ ክፍሎች፣ ከመንግሥት ሠራተኞች፣ ወይም ከትምህርት ቤት የጊዜ ሰሌዳዎች መማር እንችላለን።

ሌሎቹን ለማስተማር ሙያ ያላቸው እህቶች የትኞቹ እንደሆኑ አረጋግጥ። መማር የምንፈልገውን ሙያዎች ሊያስተምሩን የሚችሉ ሰዎች አሉን? ልጆቻችን ጠቃሚ ሙያዎችን እንዲማሩ የምናበረታታው የትኛውን ክፍል እንዲወስዱ ነው?

በብሉይ ኪዳን ጊዜ እንኳ፣ ጌታ ህዝቡን በራሳቸው የሚተማመኑ እንዲሆኑና ራሳቸውን እንዲችሉ አበረታቷቸዋል። ከመጽሐፈ ምሳሌ ለቤተሰቦቿ ለማዘጋጀት ሙያዋን ስለምትጠቀም ጥሩ ባልትና ስላላት ሴት ይገልጻል፣

"የበግ ጠጉርና፣ የተልባ እግር ትፈልጋለች፥ በእጆችዋም በደስታ ትሰራለች።

" . . .ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች . . .

"እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች፥ ጣቶችዋም እንዝርትን ይይዛሉ።

"እጅዋን ወደ ድሃ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰዳለች።

"ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተነሳ አትፈራም፥ የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና. . . .

"የቤትዋን ሰዎች አካሄድ በደህና ትመለከታለች፥ የሃሚትንም እንጀራ አትበላም።" (ምሳሌ 31፥13፣ 16፣ 19–21፣27)

ችግሮችና ፈተናዎች በምድር ላይ የተሞክሮአችን አካል እንዲሆኑ ጌታ አቀዷል። ነገር ግን እርሱ ለእኛ መኃሪያችን ነው። እነዚህን ችግሮች እንድንወጣ መንገድን አዘጋጅቶልናል። በነብያቶቹ አማካይነት የተሰጠንን ምክር የምንታዘዝ ከሆነ፣ ለራሳችን እንድናመርት ማወቅ ይገባናል። ከዚያም በኋላ ዝግጁ ስለሆንን አስቸጋሪ ጊዜያትን አንፈራም። "ብትዘጋጁ አትፈሩም" ይላል ጌታ፣ (ት እና ቃ 38፥30)።

## ሙከራ

እርስዎና ቤተሰብዎ የትኛውን ሙያ ለመማር እንደሚፈልጉ ይወስኑ። በዚህ ሳምንት ከነዚህ ሙያዎች ቢያንስ አንዱን መማርና መለማመድ ይጀምሩ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

1. ሙያተኞች ሰዎች ሊያስተምሯቸው መምጣት በሚችሉባቸው አካባቢዎች በቤተክርስቲያኑ ህዝባዊ ክፍሎች ወይም ተጨማሪ ክፍሎች የመሳሰሉትን እህቶች የቤት አመራረት ሙያዎችን እንዴት መማር እንደሚችሉ ያረጋግጡ።
2. ለ . . . ከመንግስት የክፍል ሥራ ሠራተኞች ወይም ልምድ ካላቸው ሰዎች ማረጋገጥ
   ሀ) በአካባቢዎ ምን ዓይነት የከብት ርቢ እንደሚረባ ለመረዳት። የትኛው በቀላሉ እንደሚረባ ለማወቅ።
   ለ) በአካባቢዎች የትኛው የዛፍ ፍሬ፣ የወይን ሐረግ፣ እና እንጆሪ በሚገባ እንደሚጸድቅ ለመረዳት። ምን ዓይነት ጥንቃቄ እንደሚፈልጉም ለመረዳት።
   ሐ) የስፌት ሙያዎች የሚማሩበት ክፍሎች መኖራቸውን ለመረዳት። ከሌሉ፣ ስፌትን ለክፍሉ አባላት ማን ማስተማር እንድሚችል ይረዱ።
   መ) የቤተሰብ አባላት ቤትን እንዴት እንደሚገነቡ፣ የቤት ቁሳቁስን እንዴት እንደሚሰሩ፣ እና ሌሎች ተፈላጊ ዕቃዎችን እንዴት እንደሚሰሩ ለመማር ክፍሎች እንዳሉ ለመረዳት። ከሌሉ፣ በነዚያ ሙያዎች የተካኑትን ሰዎች ለማስተማር ፈቃደኛ የሆኑትን ለማግኘት ይሞክሩ።
3. በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሰውን የሚለጠፍ ማስታወቂያ ያዘጋጁ።

# ተሰጥዎአችንን ማጎልበት

ትምህርት 27

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ በሰማዩ አባታችን በየግላችን የተሰጠንን ተሰጥዖና ችሎታዎችን እንድናውቀ፣ እንድናጎለብት እናም እንድንጠቀምበት ሊረዳን ነው።

---

**እያንዳንዱ ሰው ተሰጥአዎች እና ችሎታዎች አሉት**

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪሞቦል፣ "እግዚአብሔር በተሰጥዎና በጊዜ፣ ወሰን ከሌላቸው ችሎታዎች እና እድሎች ጋር ለመጠቀም እንዲሁም አገልግሎቱን ለማዳበር የመንፈስ ስጦታዎችን አድሎናል። ስለሆነም እርሱ ከእኛ ልዩ መብት ከሰጠን ልጆቹ ብዙ ይጠበቅብናል" ብለዋል። (*The Miracle of Forgiveness,* p. 100.)

አንድ ሰው ምን ተሰጥዎ እንዳለን ቢጠይቀን፣ እንዴት እንመልሳለን? አንዳንዶቻችን ተሰጥዎ የለንም ብለን እናስብ ይሆናል። በኪነጥበብ ዓለም ውስጥ እንደ መዝሙር፣ ዘፈን ወይንም ሥነ ጽሑፍ ዓይነት የፈጠራ ችሎታ ላይኖረን ይችል ይሆናል። ነገር ግን እንደተሰጥዎ የማንገነዘባቸው ችሎታዎች ሊኖሩን ይችላሉ። በማደራጀት፣ ወዳጅነትን በማፍራት፣ ሰላምን በማስፈን፣ ሌሎችን በማስተማር፣ ወይም ለልጆች እንክብካቤ የማድረግ ልዩ ሙያዎች ሊኖሩን ይችላሉ።

ሊላ የምትባል ከ12-18 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ስላለች ሴት ልጅ የተነገረ ታሪክ እንዲህ ይላል። ሊላ ታላቅ እህቶቿ ያላትን ተሰጥዎ ስላልነበራት ደስተኛ አልነበረችም። እነርሱ የተቀበሉትን ምሥጋናም ሆነ አድናቆት አትቀበልም ነበር። አንድ ቀን በማልቀስ ሱዛን የምትባል አክስቷ ዘንድ ሄዳ፣ "እኔን ማንም አይወደኝም። "ምንም በማድረግ ጥሩም አይደለሁም" አለቻት።

ሊላን ካረጋጋቻት እና ትንሽ ካሰበች በኋላ፣ አክስት ሱዛን፣ "እንዴት እንደተሰማሽ ገብቶኛል፣ ሊላ። በጣም ታዋቂ ተሰጥዎ ካላቸው ሁለት ፣ታላላቅ እህቶች ጋር መኖር አስቸጋሪ ይሆናል። ትንሽ የበታችነት ስሜት ሊፈጥርብሽ ይችላል።" በመቀጠልም፣ "ሊላ የሰማዩ አባታችን እያንዳንዳችንን በግል ሲፈጥረን ታላቅ ጥንቃቄን አድርጓል። ራስሽን እንደሌላ ሰው ለማድረግ አትሞክሪ። ለራስሽ ተሰጥዎና ስጦታ አመስጋኝ በመሆን እንዲሁም ልታዳብሪያቸው የተቻለሽን አድርጊ።" በማለት አክስት ሱዛን ነገረቻት።

አክስት ሱዛን ስትገልጽም፣ ሊላ ልጅን በሚገባ መያዝ ያልተለመደ ልዩ ችሎታ የተነሳ፣ በጣም ማራኪ የሆነች ህፃን ሊኖራት ችሏልች። በመቀጠልም፣ "እናትሽ ስትል ከሰማሁት. . . . ሁልጊዜ ሥራሽን በሚገባና በፈቃደኝነት እንደምታከናውኚ፣ እናም ቤትሽን በጣም የተሻለ እና ልዩ ስፍራ ለማድረግ ብዙ እንደምትጥሪ ነው" አለቻት።

"ሊላ፣ ይህንን ተገንዝበሻል? አንድ ሰው በታመመ ጊዜ፣ የበለጠ መጽናናትን እንዲያገኝ ምን እንደሚደረግለት እንደምታውቂ ታውቂያለሽን? (እኔ በታመምኩበት ጊዜ) አንቺ ነሽ እየተላላክሽኝ፣ አዲስ አበቦችን በአልጋዬ ጎን በማስቀመጥና፣ በመጎብኘት ያስደሰትሽኝ። ሊላ፣

ግሩም አእምሮ አለሽ. . .ትምህርት ትወጃለሽ እናም እዚያም በጣም ጥሩ ትሰሪያለሽ። . . . .አሁን ላለሽበት ሁኔታ ልዩ የሚያደርግሽን ብዙ ስጦታዎችና ተሰጥዎች አለሽ።” እናም ከዚያ በኋላ አክስት ሱዛን ሊላ ይህን ትገነዘብ እንደሆነ ጠየቀቻት “ሁለት አልማዞች አይመሳሰሉም፣ ወይንም፣ ተመሳስለው አያውቁም... ለዚያም ነው አልማዝ ዋነኛ የዓለምን ዛብት ታላቅ ዋጋን የያዘው፣ ሁለት የሚመሳሰሉ አልማዞች የሉም፣ ነገር ግን ሁሉም ጌጦች ናቸው። ስለዚህ አንቺ ጌጥ መሆንሽን ከቶም አትርሺ ሊላ።” አለቻት። (See Daryl V. Hoole and Donette V. Ockey, *With Sugar 'n Spice,* pp.19–21.)

ተሰጥዎአችንና ችሎታችን ከሰማዩ አባታችን የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። እያንዳንዱ ሰው ከእነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች በከፊል ተቀብሏል።

**ተሰጧችንን ማወቅ እና ማጎልበት**

ተሰጧችንን ማወቅ እና ማጎልበት አስፈላጊ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ “በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል” ብሏል። (1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡14)። ነገር ግን ተሰጧችንን ማግኘት እና ማሻሻል ጥረትን ይጠይቃል።

ተሰጧችንን እንዴት እንለያለን?

የግል ተሰጥዎአችንን ለማግኘት ስንፈልግና ስንሞክር ከሰማዩ አባታችን መመሪያን ለማግኘት መጸለይ አለብን። እንድናውቃቸው እንዲረዳን ልዩ በረከትን እንጠይቃለን። ለቤተክርስቲያኑ ጥሪ ከተመረጥን፣ ምናልባት በዚያኑ ጊዜ፣ ወይም ከጥሪው በምንሰናበትበት ወቀት ተገልጸውልን ይሆናል። “ትምህርትን እንዳቀርብ የሚረዳኝ፣ ንግግር እንዳደርግ፣ በኮሚቴ ምድብ ላይ እንድሰራ፣ ወይም ፓርቲን እንዳቀድ ለመርዳትም ምን ዓይነት ችሎታ አለኝ?” በማለት ራሳችንን እንጠይቀ ይሆናል። የምናደንቃቸውን ሰዎች ሕይወት ማየት አለብን። ከዚያም በአነስተኛ መለኪያም ቢሆን፣ የእነርሱን አንዳንድ ጥሩ ችሎታዎች እንዳሉን ራሳችንን መጠየቀ እንችላለን። ወላጆችና ሌሎች ዘመዶች፣ ወዳጆችና፣ አስተማሪዎች በየጊዜው ተሰጥዎአችንን እንድንገነዘብና እንድናሳድግ ሊረዱን ይችላሉ።

የቤተክርስቲያኑ ስቴክ በተደራጀበት አካባቢ፣ ብቃት ያላቸው አባላት ከስቴኩ ፓትሪያርክ በረከቶችን ማግኘት ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ልዩ ስጦታዎችና ተሰጥዎች በፓትሪያርካዊ በረከት ይገለጻሉ። ተሰጥዎአችንን በምንፈልግበትና በምናጎለብትበት ጊዜ እንደ መመሪያ እንጠቀምበታለን። ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል እንዳሉት “እያንዳንዱ ሰው፣ ወጣቶችን ጨምሮ፣ የፓትሪያሪካዊ በረከት እድል እንዲኖረው ታላቅ ምኞታችን ነው።” (“The Foundations of Righteousness,” *Ensign,* Nov. 1977, p. 4).

የሐመር አላስካዋ እህት ናንሲ ሲልጀስተድ ተሰጥዖዋን እንዴት እንዳገኘች ትናገራለች። ባለቤቷን ለልዩ በረከት ጠየቀችው። በረከቱን በምትቀበልበት ወቀት ተሰጦቿን ወዲያው ካላጎለበተች ከእርሷ ተወስዶ ለሌላ ሰው እንደሚሰጡ ሊነግራት በመንፈስ ተገለጸለት።

“ተንቀጠቀጥኩ ፈራሁም እናም ታዘዝኩ አለች።

“እንዳስብ አደረገኝ . . . እንደተሰጥዎ ምንም ስለራሴ ግልጽ የሆነልኝ የለም። ማስታወስ ያቃተኝን ነገር እንዴት ማሳደግ እችላለሁ? በውስጤ አንድ ቦታ ተቀብረው ያላደጉ፣ ያልታወቁ፣ ያልተነኩ፣ ያልተጠቀምኩባቸው የተሰጠ ምንጬች መኖር አለባቸው. . . .

"እንደ አማኝ፣ ሕይወታቸውን በሙሉ በቤተክርስቲያን ያሉ ተሰጦ ያላቸውን ሰዎች፣ በዓመታት ልምድ ዝማሬያቸውን፣ ጽሑፋቸውን፣ እና የመናገር ተሰጧቸውን እያዳበሩ አያለሁ። ከእነዚህ ነገሮች ምንም የለኝም።

"በድንገት ግንዛቤዬ መጣ። ባለኝ ምኞት እና ፍላጎት በመመርኮዝ እናም በዚህ መሰረት ተሰጦዬን በአነስተኛው መንገድ በመግለጽ እጠቀምበታለሁ።

"ከልብ በማሰብና በጸሎት ምኞቶቼና ፍላጎቶቼ፣ የሚከተሉት መሆናቸውን ተረዳሁ፣

"*ሰዎች*፥ ብዙ ጊዜ የሚሰማኝን፣ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ማንኛውም ሌሎችን ደስተኛ የማድረግ መልካምና ጥልቀ ዛሳቤን ለማሟላት እወስናለሁ። እንደ ጀማሪ፣ እናቱ እርቃ ለሔደችበት አንድ ትንሽ ልጅ ምግብ ጋገርኩ።

"*ሙዚቃ*፡- ኖታዎችን ማንበብ ወይም መሳሪያ መጫወት አልችልም፣ ሆኖም ግን ሙዚቃን እወዳለሁ። የሙዚቃ ችሎታ ያላትን እህት ተገናኘኋትና እናም፣ 'መዝሙር ካንቺ ጋር መዘመር እፈልጋለሁ።' አልኳት።

"*ትርዒት*፡- በቀርንጫፋችን ወደ ቤተመቀደስ ለሚሄዱ ወጣቶች ለሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ የሚውል 'የምሽት ትርዒት' ላይ በፈቃደኛነት ለመካፈል ወሰንኩ።

"*መጻፍ*፡- ብዙ ጊዜ አንድ ሰው በተናገረው ወይም ባደረገው በጣም በተነካሁ ጊዜ ጠንካራው ስሜት ይኖረኛል። እነዚያ ስሜቶቼ በሚከሰቱበት ጊዜ በወረቀት ላይ ለማስቀመጥና ስሜቴን ለነካው ሰው ለመላክ እወስናለሁ . . .

"ዕድሎች 'ዝነኛ' መሆን በፍፁም አይቻለኝም የሚሉ ናቸው . . . ምንም እንኳ የእኔ ቢሆንም፣ ለእኔ ወዳጆች ከሆኑት . . . ከቤተሰቦቼ፣ ከቀርንጫፋችን አባላት እና ከጎረቤቶቼ ጋር ልካፈላቸው እችላለሁ አነስተኛ ቢሆኑም፣ ምናልባትም፣ ስለዕድገት ማወቀ፣ የተከበረና እግዚአብሔር የሰጠኝ . . . ልዩ ችሎታዎቼ ናቸው።" ("I Dug Up My Talents," *Ensign,* Mar. 1976, p. 31.)

በመጀመሪያ ተሰጥዎአችን አነስተኛ ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በብርቱ ስራ ማደግ ይችላሉ። አንድን ተሰጥዎ በየጊዜው ማሻሻል ሌሎችን ተሰጦዎች ለማሳደግ ይረዳናል። ሕጋዊ ትምህርት ወይም ልዩ ሥልጠና ብዙ ሙያዎችን እንድንገነባ ይረዳናል። የተለዩ ችግሮችን ወይም መሰናክሎችን መቋቋም ደግሞ አዲስ ተሰጦዎችን እንድናሳድግ ይረዱናል። እንደ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት፣ ለማገልገል ጥሪዎችን ስንቀበል አዲስ ተሰጦአችንን ለማግኘትና ለማሳደግ በርካታ ዕድሎች አሉን። ብዙዎቻችን የምንጠራው ማከናወን ለምንችለው ሳይሆን፣ ነገር ግን መሆን ለምንችለው ነው።

ቄስ ፍራንክሊን ዲ.ሪቻርድ፡- "በቤተክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን እንዲያገኙ የሚጠየቁ ሰዎች አዘውትረው ራሳቸውን ደፍተው፣ 'ኦ፣ ያንን መሥራት አልችልም። በማገልገል ላይ እንዳሉ ሌሎች ሰዎች ልምድና ዕውቀት የለኝም።' ነገር ግን በእምነት፣ ጥናት፣ ሥራ፣ እና ጸሎት፣ ጌታ የማይቻል መስሎ የሚታየንን እንድናከናውን መፍትሔ ይሰጠናል።" (In *Official Report of the Sao Paulo Area Conference,* Mar. 1975, p. 23.)

እህት ማሪያ ቴረሳ ፒ. ዴ. ፓረድስ፣ የሚክሲኮው ቬራክሩዝ ሚስዮን ፕሬዚዳንት ባላቤት፣ ሲመሰክሩ፡- "ሴት በቤተክርስቲያን ጽኑ ተሳታፊ ስትሆን፣ እንዳላት የማታውቀውን አስገራሚ

ተሰጥዎን ታጎለብታለች። ወንጌልን በማጥናትና ለዕለት ሕይወቷ ትክክለኛውን መሰረተ ሃሳብ በማመልከት፣ ወደ ተሻለች ሴት ትለወጣለች፣ ከቤቷ አስተናጋጅነቷን በማሟላት ቤተሰቦቿን እናም ኅብረተሰቡንም በመርዳት በበለጠ የተዋጣለት ትሆናለች።” (Quoted by Carol Larson, “The Gospel Counterculture,” *Ensign,* Mar. 1977, p. 23.)

“(ፕሬዚዳንት) ብርግሃም ያንግ፣ “ማንኛውም ክንዋኔ፣ ማንኛውም ንጹህ ጸጋ፣ ማንኛውም ሂሳብ ግኝት፣ ጠቃሚ የሙዚቃ፣ እናም ሁሉም ሳይንሶች እና ኪነጥበብ የቅዱሳን ናቸው ብለዋል።” (quoted by Spencer W. Kimball, “The Gospel Vision of the Arts,” *Ensign,* July 1977, p. 3.)

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል ታላላቅ የኪነጥበባትና የእጅ ጥበብ ሙያተኛ መሪዎች የቤተክርስቲያኑ አባላት የሚሆኑበትን ጊዜ ይጠብቃሉ። በተሰጦአችንና ሙያችን ከሌሎች በበለጠ እንድናድግ መክረውናል። “በጥሩ” ሥራችን ብቻ ሳንረካ ግን ከዛ ለበለጠ አስደናቂን እንድንሰራ ያስጠነቀቁናል። በመንፈስ ቅዱስ ድጋፍ ተሰጦአቸውን ያሳደጉ የላቀውን ውጤት ማግኘት እንዳለባቸውም ያሳስቡናል። (See “The Gospel Vision of the Arts,” *Ensign,* July 1977, p. 3.)

ስዕል 27-ሀ፣ ሸማ የምትሰራ ሴትን፣ እና 27-ለ፣ በእጅ ጥበብ ሙያ ላይ የምትሰራን ሴት ያሳያል።

## ተሰጥኦን መጠቀም ወይም ማጣት

ተሰጦአችንን ካወቅን እና ካሳደግን በኋላ፣ ጌታ እንድንጠቀምባቸው ይጠብቀናል። የማንጠቀምባቸው ከሆነ፣ እናጣቸዋለን ተሰጦአችንን ጌታ በምድረበዳ ለእስራኤል ልጆች ከሰጠው መና ጋር ማነጻጸር እንችላለን። በየዕለቱ ብዙ መና ምድርን ይሸፍን ነበር። ሰዎቹም የፈለጉትን ያህል ሰበሰቡ፣ ነገር ግን ያልተጠቀሙበት ተበላሸ። በችሎታችንም እንደዚሁ ነው፣ ካልተጠቀምንበት፣ እናጣቸዋለን።

ጌታም እንዲህ ብሏል፣ “ነገር ግን በአንዶቻችሁ በጣም ደስተኛ አይደለሁም፣ አፋቸውን ስለማይከፍቱ፣ ነገር ግን እኔ የሰጠሁአቸውን ተሰጥዎ ሰዎችን በመፍራት ይደብቃሉ። ለእነዚያ ወዮላቸው፣ ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ይቀጣጠላልና።

“እናም እንዲህም ይሆናል፣ ለእኔ በበለጠ ታማኞች ካልሆኑ፣ ያላቸውም ቢሆን፣ ይወሰድባቸዋል።” (ት እና ቃ 60፡2–3።)

ቄስ ሪቻርድ ኤል ኤቫንስ ስለአንዲት እናት “ልጇ ከራሷ ተሰጥዎና አጋጣሚዎችም ጋር ስላደረገቻቸው እና ስላላደረገቻቸው ሲናገሩ. . . .እናት አንድ ቀን . . . .እኔ ሕይወትን ሰጠሁሽ፡ አሁን አንቺ አንድ ነገር አድርጊበት!’” ብለዋል ከዚያም ቄስ ኤቫንስ፣ “የሁላችን አባት የሆነው የሚለውን በተመሳሳይነት ማሰብ እንችላለን፦ ‘እኔ ሕይወትን ሰጠኋችሁ። አሁን አንድ ነገር አድርጉበት! አሁን የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉበት! ጊዜን፣ ማስተዋልን፣ መልካም ምድርንና የምታፈራቸውን ሁሉ ሰጠኋችሁ . . . አሁን ተጠቀሙበት።’ ” (“We Are Going to Be What We Live Like,” *Improvement Era,* Dec. 1970, p. 88.)

27-ሀ የሸማ ልብስ የምትሰራ ሴት።



27-U



27-ח

ያለን የተሰጥኦ ብዛት ምን ያህል በአግባቡ ከምንጠቀምበት ያነስ አስፈላጊነት አለው። ጌታም አለ፣ “ብዙ ለተሰጠው ብዙ ይጠበቅበታል።” (ት እና ቃ 82፥3) ተሰጦአችን ትልቅ ወይም ትንሽ ቢሆን፣ ልንጠቀምበት ይገባል።

**ተሰጦአችንን በቅድስና የመጠቀም ደስታ**

ጌታ እንዲህ አለ፥ “ከሁሉ የተሻለ ስጦታዎችን ከልብ እሹ፣ ሁልጊዜ ለምን እንደተሰጡ በማስታወስ፣

“በእውነት እላችኋለሁ፣ ሁሉም ይጠቀምበት ዘንድ . . . ተሰጥተዋልና” (ት እና ቃ 46፥8–9)።

ተሰጦዎችና ችሎታዎች ሌሎችን እንዲሁም ደግሞ ራሳችንን መርዳት አለባቸው። በምስጋና፣ ልዩ የሆኑ ተሰጦአችንን ሌሎችን ለማነጽ፣ ማንሳት ለመገንባት መጠቀም አለብን። ልጆችንና ወጣቶችን ለማስተማር መጠቀም እናም እነርሱን ለታላቅ ጥረት ማነሳሳት አለብን። ችሎታችንን በቤት ውስጥ ስንጠቀም ቤተሰቦቻችን የተባረኩ ይሆናሉ። ለመስፋት፣ ለማብሰል፣ እናም ቤትን በስርዓት ለመጠበቅ፣ በተማርን ጊዜ ሕይወታችንን እናስውባለን እናም የሌሎችን ሥራዎችን እንቀንሳለን። የደግነት እና የፍቅር ተፈጥሮ ስናሳድግ፣ ሰላምና ስምምነትን ወደ ቤታችን እናመጣለን። በምንኖርበት አካባቢ ጎረቤቶቻችንን ለመባረክ ተሰጦአችንን ማስፋፋት እንችላለን። በችግር ላይ ያሉትን ስንረዳ በዙሪያችን ለሚገኙት ወዳጆቻችን ደስታ ልናመጣላቸው እንችላለን።

እንዳጋጣሚ ሆኖ፣ አንዳንድ ሰዎች ተሰጧቸውን አውቀዋል፣ በሚገባ አሳድገውታል፣ ነገርግን ሌሎችን በማይረዱበት መንገድ ይገለገሉበታል። በእርግጥ፣ አንዳንዶቹ ተሰጦአቸውን ኃጢአትን ሊያስፋፉበት ይጠቀሙበታል። ቆንጆ የመዝሙር ድምጽ ያለው ሰው ግብረገብነት የጎደለውን መዝሙር ለመዘመር ይጠቀምበት ይሆናል። መንፈስን የሚቀሰቅስ ግጥም መጻፍ የሚችል ተሰጦኦውን በተሳሳተ መልኩ በመጠቀም እናም አስነዋሪ ጽሁፎችን ይጽፍ ይሆናል። ተሰጦዎ ያለው ተናጋሪ ወይም አስተማሪ ሌሎችን ወደ ኃጢአት ይመራ ይሆናል። “ተሰጦዎ ያለ ፀባይ ከሚወደስ ይልቀ ሊፈራ ይገባል።” (Richard L. Evans, *Thoughts . . . for One Hundred Days,* p. 208.)

ቀደም ሲል በዚህ ትምህርት የተለያዩ ብዙ አዳዲስ ተሰጦዎችን ስላገኙትና ስላወቁት ስለ እህት ሴል ጆ ስታድ ተምረናል። የእህት ሴል ጆ ስታድ ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት የቀርንጫፉ የህዝብ ግንኙነት ሥራ አስኪያጅ እንዲሆኑ ጠየቋቸው። ይህ አንዳንዶቹን አዳዲስ የተገኙትን ተሰጧቸውን እንዲጠቀሙበት ዕድልን ሰጣቸው። እርሳቸውም በሕብረተሰባቸው ሳምንታዊ ጋዜጣ የእምነት አምድን የመጻፍ ሃሳባቸውን በመያዝ የአካባቢውን ጋዜጣ አዘጋጅ ለማነጋገር ቀረቡ። ይህ ከሌሎች ቤተክርስቲያኖች መሪዎች ጋር ለመገናኘትና አብሮ ለመሥራት ዕድል ሰጣቸው። በአምዱም የተነሳ፣ “ስለቤተክርስቲያኑ ብዙ አፈታሪኮችን ለመበተን ችያለሁ፣ እናም የመጽሃፈ ሞርሞንን ቅጂዎች ማከፋፈል ችያለሁ።” አሉ። (See “Calling Inspires New Talent,” *Church News,* 4 Feb. 1978, p. 14.)

ቄስ ቦይድ ኬ ፖከር ይህን ምክር እንዲህ ሲሉ ሰጡ፡- “ለመሥራት ጀምሩ፣ ከዚያም፣ እናንተ ስጦታ ያላችሁ፣ ስጦታችሁን አዳብሩ። በማንኛውም ጥበብ እናም በማናቸውም መልካም

27-ለ በእጅ ጥበብ ሙያ የምትሰራ ሴት።

ምሳሌዎቻቸው፣ አሳድጉት። ችሎታና ፍላጎት ካላችሁ፣ ሥራን ወይም የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ተሰጦኦዎን ይቁጠሩ፣ ወይም እንደ ትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ያሳድጉት። ነገር ግን በሁሉም መንገዶች ሌሎችን ባርኩበት። የከፍተኛ ችሎታ ደረጃን ይወስኑ . . . ችሎታዎን ያለአግባብ አይጠቀሙ።” (“The Arts and the Spirit of the Lord,” *Speeches of the Year,* 1976; *Ensign,* Aug. 1976, p. 65.)

## ማጠቃለያ

እያንዳንዳችን ተሰጦአችንንና ችሎታዎቻችንን ለማጎልበት በዕድሎች ተባርከናል። የሰማዩ አባታችን ተሰጦአችንን ለሌሎች ጥቅም፣ እንዲሁም ለራሳችን እንድናውለው ይጠብቀናል። እናም እነዚያ የእኛ የሆኑትን በጽድቅ ዓላማዎች ከተጠቀምንባቸው ብዙ ደስታ ሊመጣልን ይችላል። በዚህ መንገድ ከተጠቀምንባቸው ይስፋፋሉ፣ እናም አዲስ ዕድሎችና ችሎታዎች ያድጋሉ። ተሰጦዎቻችን ከእግዚአብሔር የተሰጡ እና በምንሰራባቸው ሁሉ ኃላፊነት እንዳለብን ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

## ሙከራ

አዲስ ተሰጦዎችን የማሳደግ እና የመሻት፣ ፍላጎትዎን ይመርምሩ። ቤተሰብዎ ተሰጦዎቻቸውን እንዲያገኙና እንዲያሳድጉ ያበረታቱ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

የማቴዎስ ወንጌል 25፥14–30 (የመክሊቶች ምሳሌ)

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፦

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች*፣ ምዕራፍ 34፣ “መክሊታችንን ማሳደግ” የሚለውን ያንብቡ።
2. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ይኑርዎ
3. በዚህ ትምህርት የክፍሉ አባላት ታሪኮችንና የቅዱሳን መጻሕፍት ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# የቅጥር ሙያዎችን ማዳበር

ትምህርት 28

የዚህ ትምህርት ዓላማ የቅጥር ሙያችንን እንድናገኝና እንድናዳብር ለማነሳሳት ነው።

## አንዳንድ ጊዜ ሴቶች ሊቀጠሩ ይገባል

በአብዛኛው ቤተሰቦች፣ አባት ወይም ባል የቤተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት ይሰራል። ይሁንና፣ ሁልጊዜ ምክንያቱ ይህ መሆን የለበትም። ሌሎች ደግሞ ድጋፋቸውን ለማበርከት መዘጋጀት ይገባቸዋል። ብዙ ሴቶች ራሳቸውን ለመርዳት መሥራት ይገባቸዋል፣ እናም እንዲሁ ሌሎችም ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት መሥራት ይገባቸዋል።

ሴቶችም መሥራት የሚገባቸው አንዳንድ ምክንያቶች ምንድናቸው? መልሶቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ዘርዝሬ።

ሴት የሥራ ተቀጣሪነትን ማግኘት አለባት ምክንያቱም. . . .

1. ባለቤቷ ወይም አባቷ በሞተ ጊዜ።
2. ባለቤቷ ወይም አባቷ በህመም ወይም በአደጋ ምክንያት አካለ ስንኩል በሆነ ጊዜ።
3. የላገባች በሆነች ጊዜ ራሷን መርዳት ስላለባት።
4. ትዳሯን በፈታች ጊዜ።
5. የቤተሰቡ መሰረታዊ ፍላጎት በአንድ ወገን ገቢ ብቻ ሊሟላ ስለማይችል።
6. ያልታሰበ ሕመም ወይም ሌላ ችግር ተጨማሪ የገቢ ፍላጎትን ስለሚፈጥር።

## ሴቶች ለሥራ ቅጥር መዘጋጀት አለባቸው

ሴቶች ለሥራ ቅጥር ራሳቸውን በሁለት መንገዶች ማሰልጠን አለባቸው. . . .የቤት ውስጥ ባለሙያ ለመሆን እና በደመወዝ ለመተዳደር ናቸው።

“ያላገባች ሴት ልዩ ሙያ ኖሯት በማህበራዊ አገልግሎትና በገንዘብም ራሷን ከቻለች ሁልጊዜ ደስተኛ ትሆናለች. . . . ማንኛዋም ያገባች ሴት ካለምንም ማስጠንቀቂያ ባል አልባ መሆን ትችላለ። ባል እንደሞተ ንብረት ወዲያው ሊጠፋ ይችላል። በመሆኑም፣ ማንም ሴት ራሷን ለማስተዳደርና ጥገኛ ልጆቿን ለመደገፍ ትችል ዘንድ በገቢ አስፈላጊነት ሥር ትሆናለች። ለሥራውና ለሚመጣባት ያልተጠበቀ ሕይወት በቂ ሥልጠና ያገኘች ቢሆን፣ በጣም ደስተኛና ታላቅ የደህንነት ስሜት ይኖራታል።” (Camilla Kimball, “A Woman’s Preparation,” *Ensign,* Mar. 1977, p. 59.)

እናቶች ከቤት ውጭ እንዲሰሩ አይበረታቱም፣ በተለይም ሕጻናቶቻቸው ጨቅላ በሆኑ ጊዜ፣ ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ ለኑሮአቸው ገቢን ለማስገኘት መዘጋጀት አለባቸው። የትንሽ ልጆች እናት መሰረታዊ ፍላጎትን ለቤተሰብ ለማስገኘት ከቤት ውጭ ለመሥራት ከመወሰኗ በፊት፣ እነዚያ ፍላጎቶች ጠቃሚ ለመሆናቸው እርግጠኛ መሆን አለባት። በጥንቃቄ በሚደረገው በጀትና የቤት ምርት ችግራቸው የማይቃለል መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለባት። ከልጆቿ ጋር ቤት ለመቆየት ማንኛውንም ዓይነት ጥረት ማድረግ አለባት።

"በቤታቸው ጨቅላ ህጻናት ያላቸው እናቶች የመጀመሪያ ሃይላቸውን ለልጆቻቸው ሕብረት እና ሥልጠና እናም ለቤተሰባቸው ጥንቃቄ፣ አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው፣ የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎት የሚሟላበት መንገድ ካልጠፋ በስተቀር ከቤት ውጭ የቀጥር ሥራን መፈለግ የለባቸውም።" (Letter from the First Presidency to Neal A. Maxwell and Dallin H. Oaks; quoted by Dallin H. Oaks, "Insights," *Ensign,* Mar. 1975, p. 56.)

ስዕል 28-ሀ፣ አካለ ስንኩል ባለቤቷን የምትረዳ ሴትን ምስል አሳዩ።

ለቤተሰቧ እንዳጋጣሚ በደመወዝ ገቢ ራሷን ለማስተዳደር የምትሰራ እናት፣ የቤት ሥራን ከማዘጋጀት በተጨማሪ፣ ለትምህርት ታላቅ ፍላጎት ያስፈልጋታል። አስቀድማ ራሷን ካዘጋጀች፣ የተሻሉ ዕድሎችን በማግኘትና በበለጠ ፍጥነት መቀጠር ትችላለች።

መሥራት ከቻልን መንግስት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለፍላጎቶቻችን እንዲረዱን መጠበቅ የለብንም። የቤተክርስቲያኑ ሃላፊ የሆኑት ጳጳስ፡-"አነስተኛ ክፍፍል ወይም አንድን ነገር ያለምንም ጥረት ማግኘት፣ ሥራ ፈትነትንና ጥገኝነትን ያጠናክራል እናም የራስ ክብርን ያጠፋል።

"የጌታ መንገድ የተዘጋጀው እያንዳንዳችን ለግል ፍላጎታችን እንድንዘጋጅ ለመርዳት ነው።" (Victor L. Brown, "The Church and the Family in Welfare Services," *Ensign,* May 1976, p. 110.)

## ለቀጥር ሥራ እንዴት መዘጋጀት እንደሚቻል

ሴቶች ለቀጥር ሥራ መዘጋጀት በሚችሉበት በሚከተሉት መንገዶች ላይ ተነጋገሩበት። ከክፍሉ አባላት የሚያበረታታ ተጨማሪ ሃሳቦችንም ያጠናክሩ።

ያላገቡ ሴቶች እና ልጃገረዶች . . .

1. ለዘላቂ ሥራ እቅድ ለማቀድ እና አስፈላጊ ትምህርትና ሥልጠና ለማግኘት ይችላሉ።
2. ለቀጥር ሥራ ለመዘጋጀት መደበኛ ወይም የማታ ትምህርት መውሰድ ይችላሉ።
3. ሙያንና ልምድን ለመቀሰም የከፊል ጊዜ የሥራ ቀጥርን መፈለግ ይችላሉ።
4. እንደሚስቶችና እናቶች ለኃላፊነት ለመዘጋጀት ትምህርት መሻት ይችላሉ።
5. የፈቃደኝነት ሥራን በሆስፒታሎች፣ በኅብረተሰብ ወኪል መስሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች ወዘተ መሥራት ይችላሉ።
6. የገንዘብ ገቢ ለማግኘት በቤት መጠቀም የሚችሉትን ሙያ መማር ይችላሉ።

በአካባቢዋ የከፊል ጊዜ ሥራ ዕድል ይገኛልን? ትምህርትዎን ለመቀጠል የትምህርት ክፍለ ጊዜ ይገኛልን?

በአሁኑ ጊዜ መስራት የማያስፈልጋቸው ያገቡ ሴቶች . . .

1. ለቀጥር ሥራ የሚያዘጋጃቸውን ትምህርት መውሰድ ይችላሉ።
2. በአካባቢያቸው ካሉት ትምህርት ቤቶችና የአገልግሎት ሰጪዎች ጋር መምክርና መነጋገር ይችላሉ።
3. የሥራ ሙያን ለማሳደግ የሚረዳ የፈቃደኝነት አገልግሎትን ማበርከት ይችላሉ።

28-ሀ አካለ ስንኩል ባለቤቷን የምትረዳ ሴትን ያሳያል።



በእርግጥ፣ ከእነዚህ ተግባሮች አንዳቸውም እናት የቤተሰቦቿን ፍላጎት እንዳታሟላ ከማድረግ አያግዱም። እርሷ በቤት ልጆች እያላት ከውጭ የቀጥር ሥራን እንድትፈልግ መፈተን አይገባቸውም።

*ራስዎን ለቀጥር ሥራ ማዘጋጀት እንዲችሉ አንዳንድ ተጨማሪ መንገዶች ምንድናቸው?*

በመካከለኛ አሚሪካ የምትኖር አንዲት እህት ትንሽ ልጇ አመት ሳይሞላው ባል አልባ ሆነች። በመጀመሪያ፣ ያለደጋፊ ብቸኝነት ተሰማት። ሶስት ትንንሽ ልጆችን ለመደገፍ፣ አንዳንድ የሥራ ልምድን ማግኘት እንዳለባት ታውቀ ነበር። ንድፍና የልብስ ሥራን ለመማር በቤቷ ውስጥ ከልጆቿም ጋር በመሆን መሥራት እንድትችል በክፍል ተመዘገበች። ሙያዎቿን በጣም አሻሻለች በኋላም ለመንግስት አንዳንድ ክፍልን እንድትመራ ተጠየቀች። በጥረቷ እና በጥበባዊ የገንዘብ አጠቃቀም ውጤት ምክንያት፣ ሶስቱም ልጆቿ ጥሩ ትምህርት ቤቶች ለመግባት ቻሉ። ሁሉም አስተማሪ ለመሆን ቀጠሉ። ይህች እህት ከብዙ ሴቶች ተሰጧቸውን ለማሳደግ መንገድ ካገኙት እና ወደ ሥራ ሙያ ከለወጡት አንዷ ነች።

ለቀጥር ሥራ ሙያን ስንፈልግ፣ በትክክል ምን ማድረግ እንደምንፈልግ መወሰን አለብን። ከታቻለ፣ የሚያስደስተንን ነገር መምረጥ አለብን። ከዚያም የምንችለውን ሁሉ ስለዚያ ነገር መማር አለብን። በቤታችን አንድን ነገር ለማምረት ብንወስን፣ በገበያ ላይ በሚገባ የሚሸጠውን ዕቃና የተሻለ ትርፍ የሚያስገኘውን ዕቃ እስክናገኝ መሞከርን መቀጠል አለብን። የእጅ ጥበባችንን ውጤት ለጓደኞቻችን፣ ለጎረቤቶቻችን እናም ለዘመዶቻችን ማሳየት እንችላለን። በአካባቢ የንግድ ትዕይንትና መግለጫዎች ልናሳያቸው እንችላለን።

ውሳኔዎችን ለማድረግ ይረዳን ዘንድ ሁልጊዜ መፀለይ አለብን። መንገዳችንን ለማግኘት ራሳችንን እንድናዘጋጅ የሰማዩ አባታችንን መጠየቀ አለብን።

“ጌታ ለእኛ የሚያደርግልንን ከመመርመር ይልቀ፣ ለራሳችን ማድረግ የምንችለውን እንጠይቀ” (*Discourses of Brigham Young,* p. 293)።

## በቤት የገንዘብ ገቢን ማግኘት

ስዕል 28-ለ፣ ከብዙ የእጅ ጥበቦች አንዱ ሴቶች ከአካባቢ ቁሳቁሶች የገንዘብ ቦርሳዎችን መሥራት ነው፣ 28-ሐ፣ ወፍራም የብርድልብስ፣ የአሻንጉሊት ልብሶች፣ የሕፃን ልብሶች፣ እና ሌላ የሕፃን ዕቃዎች፣ እናም 28-መ፣ በቤት የተሰሩ የዳቦ መጋገሪያ ዕቃዎችን ሊሸጡ ይችላሉ የሚሉትን ምስሎች አሳዩ።

ብዙ ሴቶች በቤት የገንዘብ ገቢን ለማግኘት ተሰጦአቸውንና ፍላጎታቸውን ለመጠቀም መፍትሔዎችን አግኝተዋል። በተለይ ይህ እናት ከትንሽ ልጆች ጋር መሥራት በሚገባት ወቀት ይረዳል። ሴቶች በቤት ሆነው የገንዘብ ገቢን የሚያገኙበት አንዳንድ መንገዶች የሚከተሉ ናቸው።

1. በልብስ ስፌት፣ የልጆችን ልብሶች፣ የግድግዳ ጨርቆች፣ የሰርግ ረጅም ቀሚሶች፣ ማሊያዎች፣ የቤት ቁሳቁሶች፣ በጨርቀ የተከፈኑ እንስሳት፣ አሻንጉሊቶች፣ እና የአሻንጉሊት ልብሶች፣

28-ለ ከብዙ ጥበቦች አንዱ ሴቶች ሊሰሩበት የሚችሉት ከአካባቢ ቁሳቁሶች የገንዘብ ቦርሳን መሥራት ነው።
28-ሐ የብርድልብስ ሥራ፣ የአሻንጉሊት ልብሶች፣ የሕፃን ልብሶች እና ሌሎች የሕጻን ዕቃዎች።
28-መ በቤት የተሰሩ የመጋገሪያ እቃዎች ሊሸጡ ይችላሉ።



28-ለ




28-00

2. የእጅ ጥበብ፣ የጥልፍልፍ ሥራ፣ የሹራብ ሥራ፣ የብርድልብስ ሥራ፣ በኪሮሽ መሥራት፣ በመርፌና ክር ሽማን መስፋት፣ አበባን ማበጀት ወይም ማዘጋጀት፣ ጌጣጌጥን ማምረት፣ ብርን ማንጠር፣ የቤት ጌጥ በወረቀት የሚሰራ ወይም የአበባ ጉንጉን ማበጀት ነው።
3. ምግብ ማብሰል፣ ኬክን ማስዋብ፣ በትኩሱ የሚበላ ኬክ ማዘጋጀት፣ የሠርግ ኬኮች፣ ዳቦ፣ ብስኩቶች፣ ከረሜላ፣ ከፍራፍሬ የተጋገረ ምግብ፣ የትምህርት ቤት ምሳን ማዘጋጀት።
4. የልጅ አያያዝ፣ በቤት ውስጥ ልጅን መንከባከብ ወይንም በቤት ውስጥ የህፃናት ማሳደጊያን ማስተማር።
5. አትክልትን እና ምርትን መሸጥ፣ በጓሮ የተመረቱ ያልቀዩ ምርቶች ሁልጊዜ ተፈላጊ ናቸው እናም በሚገባ ይሸጣሉ። አንዳንድ ሴቶች በእርሻ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ከአካባቢው ፍራፍሬ ማርማላታ እና የረጋ ፈሳሽን ይሰራሉ። በመንገድ ዳር በመቆም ወይም በመደብሮች ይሸጣሉ።
6. ሙዚቃን፣ ዳንስን፣ ወይም ኪነጥበብን ማስተማር።
7. በዕድሜ ለሚበልጡን የየዕለት ጥንቃቄን ማድረግ።
8. ተማሪዎችን በትርፍ ጊዜያቸው ማሰልጠን።
9. ለጋዜጣ ጽሁፎችን ማዘጋጀት።
10. በታይፒስትነት ወይንም በመዝገብ አጠባበቅ።
11. በስልክ እቃዎችን መሸጥ።
12. ለአፓርታማ ባለቤቶች የኪራይ ወኪል መሆን።
13. አንድን ሰው ቤት ማከራየት።
14. ለአካለ ስንኩላን ልጆች የማደጎ እርዳታን መስጠት።
15. የእንስሳት አጠባበቅን ማድረግ።
16. ፀጉርን መቁረጥ ወይንም ማበጀት።

ገንዘብ ለማግኘት በቤት ለመሥራት ማንኛውንም ሕጋዊ የፍቃድ ጥያቄዎች መረዳት እና መታዘዝ አለብን።

ገንዘብን በቤት ለማግኘት ሌላ አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው?

ከቤት ውጭ በፍጹም የማንሰራ እንኳ ቢሆን ተሰጦአችንን ማሻሻል ብልሀታዊ ለምን ሆነ?

### ማጠቃለያ

ራሳችንን እንድናስተዳድር ተነግሮናል። ቅዱሳን መፃህፍትም ሰነፍ እንዳንሆን ይነግሩናል። (ት እና ቃ 42፡42 ይመልከቱ።) የቤተክርስቲያን መሪዎች የራሳችንን ፍላጎት እንድናሟላ ደጋግመው አስጠንቅቀውናል።

ለራሳችን ፍላጎት ማዘጋጀት ለምን አስፈላጊ ሆነ? ይህን እንዲያደርግ በሌላ ሰው ላይ ለምን አንመካም?

ሁላችን ለራሳችን እና ለቤተሰባችን ለማዘጋጀት መዘጋጀት አለብን። ተሰጦአችንን ለማሳደግ ቀደም ብለን መጀመር አለብን። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለኑሮአችን ገቢ ለማስገኘት ራሳችንን ማሰልጠን አለብን። የገንዘብ ማግኛ መንገዶችን ለማግኘት፣ ተሰጢችንን በመጠቀም እርካታንና ደህንነትን ለማምጣት መፍትሔውን መፈለግ አለብን።

መሥራት ካለብን፣ ስለቀጥር ዕድሎች ጠቃሚ መረጃዎችን መሰብሰብ አለብን፣ አስፈላጊ ሥልጠናና ልምድን ማግኘት፣ እናም ውሳኔያችንን በማድረግ ፀሎት አድራጊዎች መሆን አለብን።

ፕሬዚዳንት ማሪዮን ጂ ሮምኒይ እያንዳንዳችን በዓለማዊ እና በመንፈሳዊ ነገሮች ደኅንነታችንን መፈጸም አለብን ብለዋል። እርሳቸውም በችግር ላይ የሚገኙት "ነፃነትን እና እራስ ማስከበርን በራሳቸው ኢንዱስትሪ እና ቁጠባን ማግኘት ሲችሉ ብቻ ከፍ ከፍ ማለት ይችላሉ" ብለዋል። ("In Mine Own Way," *Ensign,* Nov. 1976, p. 125.)

## ሙከራ

ለቤተሰባችሁ ለማዘጋጀት የሚረዱ ተሰጦዎችንና ሙያዎችን ዘርዝሩ። ቢያንስ አንዱን ሙያ ምረጡ እና ለማሻሻል ሞክሩ። ወጣት እህቶች ሙያቸውን በተግባራዊ ልምምድ፣ በትምህርት ክፍሎች፣ ወይም በፈቃደኝነት አገልግሎት አሁን ለማሳደግ እንዲጀምሩ ጠይቋቸው።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብሽ በፊት፥

1. በዚህ መምሪያ ትምህርት 27 "ተሰጦአችንን ማሳደግ" የሚለውን አንብቡ።
2. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ያዘጋጁ።
3. በአካባቢዎ ሴቶች የተሰሩትን ጥቂት ቁሳቁሶች ይሰብስቡ እናም በክፍሉ ማሳያ ላይ ያዘጋጇቸው።
4. በዚህ ትምህርት ላይ የክፍል አባላት ጥቀሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# የሥራን ጥቅም እና ኃላፊነትን ለቤተሰቦች ማስተማር

ትምህርት 29

---

የዚህ ትምህርት ዓላማ የቤተሰብ አባላት ሥራን እንዲያከብሩና በቤተሰብ አኳያ ሃላፊነት እንዲሰማቸው ለማስተማርና ለመርዳት ነው።

---

## የሥራ ዕድል

“አንድ ጋዜጣ . . . ዕድሚያቸው በ165 ክልል ከሆኑ ጡረታ ከወጡ አረኛ ጋር የተደረገውን ቃለ መጠይቀ አትሟል። ስማቸው *ሺራሊ ሚስሊመፍ* ይባላል። የተወለዱትም ሙሉ ሕይወታቸውን ከኖሩበት ከካውካሰስ ተራሮች ውስጥ ነበር . . . ይህም በጥቁር ባህርና በካስፒያን ባህር መካከል ነበር. . . .

“ሚሲሊመፍ አሁንም እንጨት ፈላጭ ነው። በስራ ፈት ብዙ ጊዜ መኖር እንደማይችል ተረዳሁ፣” ሲሉ ለቃለመጠይቀ ጠያቂው ነገሩት . . .

“ ‘ጽሑፉ ሽማግሌው አሁንም በዕድሚያቸው ዘመን በየጊዜው በድጋሚ በተከሉት በአትክልታቸው ቦታ ባሉት ዛፎቻቸው ዙሪያ ይኮተኩታሉ ይላል’።

“ ‘የማያቋርጥ ሥራ፣ የተራራ ነፋሻ አየር እና መካከለኛ አመጋገብ እንደዚህ ያለውን የተራዘመ ዕድሜን እንዳገኝ ረድቶኛል፣’ አሉ። ምንም የማይጠጡትና የማያጨሱት ሚስሊመፍ።” (Wendell J. Ashton, “The Sweetness of Sweat,” *Ensign,* July 1971, p. 35.)

ፕሬዝዳንት *ዴቪድ ኦ ማኬይ* “የመሥራት ዕድል ስጦታ መሆኑን፣ የመሥራት ኋይል ደግሞ በረከት፣ ሥራን መውደድ ስኬት መሆኑን እናስታውስ ይላሉ” (Quoted by Franklin D. Richards, “The Gospel of Work,” *Improvement Era,* Dec. 1969, p. 101)።

መሰልቸትንና ማዘንን ማሸነፊያ የተሻለ መንገድ ጠንካራ ሥራ ነው። ሥራ ምንድነው? የተሟላ ዕቀድ ያለው ሥራ ለቀና ውጤት የሚያበቃ ጥረት ነው። አጥርን መቀባት፣ አትክልትን መኮትኮት፣ እና ጉድጓድ መቆፈር የአካል የሥራ ዓይነቶች ናቸው። ትምህርትን መማር ደግሞ ሥራ ነው። ሌሎችን መርዳትም ሥራ ነው።

ሌሎች የሥራ ዓይነቶች ምንድናቸው?

## ልጆችን ጠንክረው እንዲሰሩ ማስተማር

ለልጆች በወጣትነታቸው ጊዜ የጥሩ ሥራ ልምዶችንና ሃሳቦችን መማራቸው አስፈላጊ ነው። እነዚህ ልምዶች በመጨረሻ ከእነርሱ ጋር ይቆያሉ። በጠቃሚ፣ በምርታማ ሕይወት፣ በሥራ ፈትና ብኩንነት መካከል ልዩነትን ያደርጋሉ።

ልጆች ለምን ጥሩ የሥራ ልምድን እና አመለካከትን መማር አለባቸው?

ጳጳስ *ቫን ጄ ፌተርሰተን* አንዲት ሴት ልጅ እንዴት እንደሚሰራ ያስተማረቸውን ታሪክ ተናገሩ

አንዲት መሳፍንት የሆነች ሴት ዕድሚው አሥራ ሶስት ዓመት የሆነውን ልጅ በአትክልት ቦታዋና በማሳዋ ውስጥ እንዲሰራላት ቀጠረችው። ከመጀመሪያው ሳምንት በኋላ፣ "ሰዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መስክንም ለማጨድ የተለያዩ መንገዶች አሉ፣ እናም ከሳንቲም አንስቶ እስከ አምስት ብር ይገባቸው ይሆናል። ዛሬ የሰራኸው የሶስት ብር ስራ ነው እንበል. . . . የአምስት ብር መስክ—ደህና፣ ይህ የማይቻል ነው፣ ስለዚህ ስለእርሱ እንርሳው።" ስትል አስረዳችው።

ልጁ ሥራውን እንዲገምት እና ምን ያህል እንደምትከፍለው እንዲወስን ፈቀደችለት። ለመጀመሪያው ሳምንት የሥራ ጥረቱ ሁለት ብር ከፈለችው። ልጁ በቀጣዩ ሳምንት አራት ብር ለማግኘት ወሰነ፣ ነገር ግን ሶስት ብር እንኳን የሚያስገኝ ሥራን አልሰራም። በጥንቃቄ በመሥራት እና እንዴት የአትክልቱን ቦታ ማሻሻል ያለበትን መንገድ ተመለከተ፣ ሆኖም ግን በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ አሁንም ከሶስት ብር ከአምሳ ሥራ በላይ ማለፍ አልቻለም። በመጨረሻም ለአራት ብር ሥራ ብቻ ከመሞከር አምስት ብር ለማግኘት መሞከር እንዳለበት ወሰነ። የአትክልት ቦታውን የበለጠ ቀንጆ የሚያደርግበትን ሁሉንም መንገድ አሰበ። ትንሽ ጊዜን ያህል ብቻ ለዕረፍት አልፎ አልፎ ከመውሰድ በስተቀር ቀኑን ሙሉ በጣም ጠንክሮ ሰራ። አሁንም ከበፊቱ የበለጠ ጊዜ በላይ ወሰደበት፣ ነገር ግን ከፍፃሜ በደረሰ ጊዜ አምስት ብር የሚያስገኝን ሥራ በመስራቱ ተደሰተ።

ሴትዮዋ የአትክልት ቦታውን በሚገባ ከመረመረች በኋላ፣ ልጁ የማይቻለውን ሥራ እንደሰራ ወስና ለሥራው አመስግና የሚገባውን አምስቱን ብር ልትከፍለው ደስተኛ ሆነች።

ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ልጁ አድጎ ትልቅ ሰው በሆነ ጊዜ፣ ተሞክሮው እንዴት አስፈላጊ እንደነበር አስታወሰ፣

" 'ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ከተወሰኑ 25 ዓመታት በኋላ፣ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ምን ማድረግ እንዳለብኝ ባላወቅሁበት ጊዜ በድንገት፣ በዚያ "አይቻልም" የሚለውን ቃል በምሰማበት ጊዜ፣ በውስጤ አዲስ ተስፋ ወይንም ውሳኔ ተሰማኝ፣ እናም ማድረግ የነበረብኝ የማይቻለውን መሞከር ብቻ ነበር።' " (See Conference Report, Oct. 1973, p. 98; "The Gospel of Jesus Christ is the Golden Door," *Ensign,* Jan. 1974, pp. 84–86; quoted from Richard Thurman, "The Countess and the Impossible," *Reader's Digest,* June 1958.)

ልጆች አብዛኛውን ጊዜ የሚችሉትን ማድረግ እንደማይቻል ይሰማቸዋል። ነገር ግን፣ ይህ ታሪክ እንድሚያሳየው፣ ከቀድሞአቸው ትንሽ የተሻለ እንዲያደርጉ ልንመክራቸው እንችላለን። ደግሞም ጥሩ አድርገው ለሰሩት ሥራና ላደረጉት መልካም ዕድገት ልናመሰግናቸው ይገባል። ከዚያም ተስፋቸውንም አይቆርጡም ማለት ነው።

ልጆቻችንን በትምህርት ቤት በሚገባ እንዲሰሩ እንዴት ልንመክራቸውና ልናበረታታቸው እንችላለን?

አንዲትን እህት እንዴት በቀለም ትምህርት ባልሆነ መንገድ ልጆቿን ለግብ ውጤት እንዲበቁ እንዳበረታታች እንድትናገር ይጠይቁ።

## ሥራ ለቤተሰብ ስኬት አስተዋፅኦ ያደርጋል

ስዕል 29-ሀ፣ እናት ልጆቿን በማዕድቤት ውስጥ እንዲሰሩ ስታስተምር፣ እና 29-ለ፣ ወንድም እህቱን የሚጠጣ ወተት በማምጣት ሲረዳ ያሳያል።

29-ሀ እናት ልጆቿን በማዕድ ቤት እንዲሰሩ ስታስተምር ያሳያል።
29-ለ ወንድም እህቱን የሚጠጣ ወተት እንድታገኝ ሲረዳ ያሳያል።



29-U



ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል፣ “ለራሳችንና ለልጆቻችን በሥራ እናምናለን . . . ልጆቻችን እንዲሰሩ ማሰልጠን አለብን፤ የቤትንና የአትክልት ቦታን ኋላፊነት መውሰድን መማር አለባቸው። ምንም እንኳን አስቸጋሪ ቢመስልም፤ ቤትን የፀዳና ንፁህ አድርገው የመጠበቅን ሥራ ልንሰጣቸው ይገባል። አትክልትን እንዲጠብቁ . . . ለልጆች ምድብ ሥራ መስጠት ይቻላል” ብለዋል (“The Stone Cut without Hands,” *Ensign,* May 1976, p. 5)።

ለራሱ ጥቀም ብቻ የሚሰራ ልጅ የቤተሰብ ኃላፊነትን ስሜት የሚያጣው ለምንድነው?

አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው ባደጉ ጊዜ ጠንክረው መሥራት አለባቸው ብለው ያስባሉ። ልጆቻቸው በቤት ውስጥ በሥራ እንዲረዷቸው አይፈልጉም። ሌሎች ልጆች ብዙ ለመርዳት በጣም ጨቅላ ናቸው ወይም አልሰለጠኑም ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ብዙዎች ልጆች በቤት ውስጥ እንዲያግዙ አስፈላጊ ነው ብለው ያስባሉ።

ስለሥራ የእነዚህ አመለካከቶች ውጤቶች ምንድናቸው?

እንዴት ልጆችን የሥራ ደስታን እንዲማሩ በቤተሰብ ላይ ኃላፊነት እንዲሰጣቸው ለማድረግ ሊያስደንቀን ይችል ይሆናል። በየቤተሰቡ ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸው፤ ነገር ግን ልጆች መሥራቱንና ኃላፊነት መውሰድን በብዙ መንገዶች መማር ይችላሉ።

ልጆችን እንዲሰሩ ለማስተማር የሚከተሉትን በመዘርዘር በጠመኔ ሰሌዳ ላይ ወይም በተለጠፈ ማስታወቂያ ላይ ያሳዩ፤

1. ለአንዳንድ አካላዊ ፍላጎታቸው እንዲጠነቀቁ አስተምሯቸው።
2. ትላልቅ ልጆች ትናንሽ ልጆችን እንዲያስተምሩና እንዲጠብቋቸው ይጠይቁ።
3. ለቤተሰብ እርሻ ወይም ንግድ እንዲጠነቀቁ ያስተምሯቸው።
4. የቤተሰብ ሥራ ፕሮጀክትን ያደራጁ።

### ለአንዳንድ አካላዊ ፍላጎታቸው እንዲጠነቀቁ አስተምሩአቸው።

ልጆችን እራሳቸው የፈጠሩትን ምስቅልቅል እንዲያስተካክሉና ለልብሶቻቸው እንዲጠነቀቁ ማስተማር አለብን። በቤት ውስጥ ለእርዳታ በተቀጣሪነት ወይም በአገልጋይነት አንዳንድ ሥራን የሚሰሩ ባሉበት ቦታም ቢሆን፤ አሁንም ልጆች ብዙ ሥራን መማር ይገባቸዋል። በአንድ ወቅት እነርሱም ይህን ሥራ ልጆቻቸውን ወይም የቀጠሯቸውን ሰራተኞቻቸውን ያስተምሩ ይሆናል። በሁሉም ቤት ያሉ ልጆች ራስን መቻልን መማር ይገባቸዋል። ስለሥራ ቀና ሃሳብ ማሳደግ ይገባቸዋል፤ እናም ሥራ የሚሰጠውን ትምህርት ይማራሉ።

ልጆችን ለራሳቸው አካላዊ ፍላጎት እንዲጠነቀቁ የሚያስተምሩ ሌሎች የተለያዩ መንገዶች ምንድናቸው?

### ትላልቅ ልጆች ትናንሽ ልጆችን እንዲያስተምሩና እንዲጠብቁ ጠይቋቸው።

ትላልቅ ልጆች ለታናናሽ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው በከፊል ኋላፊነት እንዲሰማቸው መማር አለባቸው። ወላጆች ለተወሰነ ጊዜ በማይኖሩበት ጊዜ ሊጠብቋቸው ይችላሉ። ከእነርሱ ጋር በማንበብ፤ በመዘመር፤ በመጫወት፤ እናም ሊያስተናግዱዋቸው ይችላሉ። ትላልቅ ልጆች በይበልጥ መልካም ምሳሌን ማስቀመጥ ይገባቸዋል። ቄስ አድነይ ኮማትሱ የምሳሌነትን ኃይል ተናግረዋል፤

“በቅርቡ፤ በፆምና ምስክርነት ጉባዔ፤ አንድ ወጣት የቤተክርስቲያኑ አባል ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ምስክርነቱን ሰጠ። ‘ወንድሜ ለእኔ ግሩም ምሳሌ ነበር። በክህነት ሥልጣኑ ውስጥ ጥሪውን በሚያጎላበት ጊዜ ታላቅ ለውጥን በወንድሜ ሕይወት ተገነዘብኩ። ወንድሜ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ለሥልጣን የበቃው በእግዚአብሔር ተጠርቶ እንደሆነ

አውቃለሁ። ተሞክሮዎቹ የተህትና አገልግሎት በመሆናቸው እናም ጌታን በትጋት በማገልገል፣ ተህትናን እና የተሟላ ደስታን ተለማምዷል። እንደ ወንድሜ መሆን እፈልጋለሁ’ ” በማለት ሲናገር የሁሉንም ልብ ነክቷል። (In *Official Report of the Korea Area Conference,* Aug. 1975, p. 4.)

ትላልቅ ልጆች ትናንሽ ልጆችን መርዳት የሚችሉበት ሌሎች መንገዶች ምንድናቸው?

ለቤተሰብ እርሻና ንግድ ጥንቃቄ እንዲረዱ አስተምሩአቸው።

እንደቤተሰብ አባላት፣ ልጆች በቤተሰብ ሥራ መካፈል አለባቸው። ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልዩ ኪምቦል የራሳቸውን የወጣትነት ልምዳቸውን ሲገልፁ።

“በአባቴ አመራር ሥር በሳሙና የፈረስ ዕቃዎችን በማጠብና ቀባት በመቀባት ስለነበረኝ ልምድ ተመስጋኝ ነበርኩ። የአጥር እንጨትን የውሃ ገንዳ፣ የሰረገላ አጥርን፣ ተሳቢ ሰረገላና የጭነት ፋርጎን፣ እናም በመጨረሻ ቤት መቀባትን ተማርኩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አልፎ አልፎ በእጄ ላይ ውሃ የቋጠረ ቁስል ሲሸፍነኝ፣ በነዚያ ተሞክሮዎች አላዝንም ነበር።” (In Conference Report, Apr. 1976, p. 172; “Family Preparedness,” *Ensign,* May 1976, p. 126.)

ዊሌ ሂሬይ የስዊድን፣ የጎተቦርግ ቤተሰብ የሆነ ሰው፣ ሰባት ልጆቻቸውን በተሳካ የቤተሰብ ንግድ አሳተፈዋል። “አባት፣ እናት፣ እና ልጆች . . . ከአስር እስከ አሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜ ጀምበር ከመውጣቷ በፊት ጋዜጣዎችን ያስረክባሉ። ደግሞም ፈረሶችን በማግራት ይሸጧቸዋል። በበጋ የልጆች ሰፊ እርሻና ከብት እርባታ ቦታ በስትሮምስታድ ከአራት እስከ ስድስት መቶ ልጆች ከስዊድን፣ ከኖርዌይ እና ፊንላንድ ይሰራሉ። ለአብዛኛው ሕዝብ ቀኑ ሲጀምር፣ የሂሬይ ቤተሰብ ለተወሰኑ ሰዓቶች እንቅስቃሴ ላይ ነበሩ። ከሥራና ትምህርት ቤት በኋላ ቀኑ በቤተክርስቲያን ሥራ ያበቃል። በሰኞ ማታ . . .በቤተሰብ ምሽት . . . ይዘምራሉ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችንም ይጫወታሉ። በጣም በሥራ ይጠመዳሉ እናም ይደሰታሉ ስለዚህም በህይወት ያለመደሰትን አያስቡትም።” (Edwin O. Haroldsen, “Changing Lives,” *Ensign,* June 1971, pp. 20–21.)

በቤተሰብ ንግድ ላይ በአንድነት መሥራት ልጆችን በቤተሰባቸው ውስጥ ጤናማ ኩራትንና አፈፃጸም እንዲያጎለብቱ መርዳት ይችላል። የገንዘብ ገቢ አግኝተው ለሚስዮናዊ ሥራና ለወደፊት ትምህርት ቤታቸው መቆጠብ ይችላሉ።

ልጆችን በቤተሰብ ንግድ ውስጥ ማጠቃለል ምን ሌላ ጥቅሞችን ያመጣል?

የቤተሰብ ሥራ ፕሮጀክቶችን ያደራጁ

የቤተሰብ ሥራ ፕሮጀክቶች ጥሩ ልምድንና ማኅበሮችን መስጠት ይችላሉ። ተሰጦዎን ወይም የቤተሰብ አባላትን ፍላጎት ማዕከል በማድረግ፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች ለሁሉም ሰው አስደሳች መሆን ይችላሉ። አብሮ በመሥራት ልጆች እና ወላጆች ይቀራረባሉ እናም የበለጠ ስለእርስ በርስ ይማማራሉ።

በአንድ ቤተሰብ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ስለሥራ ጥቅም መማራቸውን ይሰማቸው ነበር። የአባታቸውን ቢሮ ለማፅዳት የፅዳት ሰራተኛን በመቀጠር የልጆቹን የእድገት እድል እያሳለፉ እንደሆነ ተገነዘቡ። (እርሱም ሐኪም ነበር።)

በእያንዳንዱ ማለዳ፣ ቢሮን በማፅዳት በሚወስዱት ቋሚ ገቢ ስለማግኘታቸው፣ ልጆቹ ተደስተዋል። የቡድን ሥራ አስፈላጊ ሆኗል። በአንድ ጠዋት ወንዶች ልጆች የቤተሰብን ሥራዎች ለመርዳት ቤት በሚውሉበት ጊዜ የቤተሰቡ ልጃገረዶች ቢሮን ያፀዳሉ። በሚቀጥሉት ጠዋቶች ሥራቸውን በተረኛነት ይፈራረቃሉ።

"ፕሮጀክቱ ተጨማሪ ጥረትንና በወላጆች በኩል ያለውን ጊዜ ይጠይቃል፣ እናት በየጠዋቱ ልጆችን ወደ ቢሮ እንድትልክ ትጠየቃለች። ነገር ግን በልጆች ይገኝ የነበረው ጥቅም ከሚፈለገው ከተጨማሪ ጥረት ይልቅ የበለጠ ዋጋ ነበረው።" (Elwood R. Peterson, "Family Work Projects for Fun and Profit," *Ensign,* June 1972, p. 8.)

የዚህ ቤተሰብ ሥራ ፕሮጀክት ጥቅሞች ምን ነበሩ? (ልጆች ከአባታቸው ሥራ ጋር ተላምደዋል፣ ልጆች የአባታቸው ንግድ አካል እንደሆኑ ይገምታሉ፣ ልጆች ከሚያከናውኑት ዕለታዊ ተግባር አላቸው፣ ልጆች የተሰራውን ሥራ ለማየት ኃላፊነት ነበራቸው፣ ልጆች የአብሮ መሥራትን ጥቅም ተምረዋል።)

### ልጆች ሥራን መውደድን መማር ይችላሉ

ልጆች ሥራን ሲወዱ፣ በተሻለ መንገድ ጠንክረው ለመሥራት ጥረት ያደርጋሉ። ሥራን የማይወዱት ደግሞ በየጊዜው ራሳቸውን ያመካኛሉ። ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር በተመሳሳይ ኩባንያ ስለሚሰሩት ሁለት መልዕክተኛ ልጆች ልዩነታቸውን ይናገራሉ፣

"አንዱ ልጅ በሚከናወነው በሁሉም ነገር ደስተኛ ነበር . . . ሌሎችን በመርዳትና በማገልገል እናም የሚቻለውን በማድረግ ስለ ንግዱ ሥራ ለመማር ፈለገ . . . የሚቻለውን ያህል ተወዳዳሪ የሌለው መልዕክተኛ ልጅ ለመሆን ይሞክር ነበር . . . አንድ ድርጊቱን ያስተዋለው ተቀጣጣሪ ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ በጠራው ጊዜ እርሱ ለጥቂት ወራት ብቻ ከዚያ ነበር፣ በዚህ ዓይነት ለላቀ የኃላፊነት ደረጃ ደረሰ። ከዓመቱ መጨረሻ በፊት ሌላ አመርታ ነበረው፣ እናም በአስተሳሰቡ የተነሳ ዕድገቱ ቀጠለ። ከተፈለገው በላይ ለማድረግም ተዘጋጀ። በራሱ ኩባንያ በመደሰትና ግልጋሎትን በማበርከት በማንኛውም ሁኔታ እምነት ይጣልበት ነበር። ሌላኛው መልዕክተኛ ልጅ እዚያው መልዕክተኛ ሆኖ ቀረ . . . በእርግጥም፣ ኩባንያው በሥራ ችሎታው እንዳልተደሰተበት ተሰማው።" (*Seek Ye First the Kingdom of God,* pp. 236–37.)

በእነዚህ ልጆች የሥራ ስኬት ላይ ልዩነት ያደረገው ምንድነው?

ልጆች የሥራ ዋጋቸው የሌሎች ደስታ በሆነበት ጊዜ በሥራ ይደሰታሉ። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦማኬይ ይህን ምሳሌ ሰጥተዋል፣

ወጣት ሴት ልጃገረዶች በአረጋዊያን ቀን ሙሉ ቀናቸውን የሌሎችን ደስታና ምቾት በመሻት ሰዎችን ሲያገለግሉ አይቻለሁ። በአንድ ወቀት አስታውሳለሁ ከእነዚያ ወጣት ሴቶች በምሽት ወደቤት ስትመጣ በድንገት መድከሟን ተገነዘበች፣ በልጅ አልጋ ላይ ራሷን ወረወረችና፣ "ደክሞኛል፣ ነገር ግን ይህ በሕይወቴ ውስጥ አንዱ የደስታዬ ዕለት መሆኑን ታውቃላችሁ።" አለች። በሥራ ለሌሎች ደስታን የሚሰጥ ደስታ ነበራት።

"ሥራዎን መውደድን ይማሩ። "ይህ ሥራዬ ነው፣ ክብሬም ነው፣ አሳዛኝ ዕድሌ አይደለም" ማለትን ይማሩ።' " (*Stepping Stones to an Abundant Life,* pp. 115–16.)

ልጁ ሥራው ከተሳካለት እንደ አስደሳች ነገር ይሆንለታል። ልጁ ሥራ በጀመረበት በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ጊዜያት፣ አዋቂ ወይም ትልቅ ልጅ አሰራሩን እስኪለማመድ ድረስ ከእርሱ ጋር እንዲሰራ ያስፈልጋል። ከዚያም የልጁን የሥራ መሳካት መገንዘብና በታማኝነት

ጥረቱን ማወደስ አለብን። አንድ ልጅ ባደረገው ስህተት ላይ ብቻ ማተኮር በጣም ቀላል ነው፤ ምክንያቱም በሚቀጥለው ጊዜ የተሻለ እንዲያደርግ እንፈልጋለን። *ትክክለኛ* ነገሮችን በመስራታቸው ላይ ስናተኩር ልጆች አብዛኛውን ጊዜ መልካም ሥራን ይሰራሉ።

ስራን የበለጠ አስደሳች ማድረግ የምንችለው መዝሙር በመዘመር፤ ወይም ሥራን እንዲያውም ወደ ጨዋታ በመለወጥ የሰራን እንደሆነ ነው። ወላጆች ስለልጅነት ታሪካቸው ወይም ስለቀደሙት አያቶቻቸው ለልጆች መልሰው ማውራት ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ተግባሮች ሥራን አብሮ በመስራት የበለጠ ቀላል የሚያደርጉ ናቸው። ልጆች አልፎ አልፎ የዕረፍት ቀን እንደሚያሻቸው አይርሱ። በየሳምንቱ ከአሰልቺ ሥራቸው እንዲያርፉ ቢደረጉ፤ በሚቀጥለው ቀን በሥራው በይበልጥ ሊደሰቱ ይችላሉ፤ አሰልቺ ሥራዎቻቸው ከተገባደዱ በኋላ ለጨዋታም ሆነ ለሌሎች ተሳትፎዎች ለራሳቸው ጊዜን ይፈልጋሉ።

እህቶችን እንዴት ለቤተሰቦቻቸው ሥራን የበለጠ መደሰቻ እንዳደረጉ ይጠይቁ።

## ማጠቃለያ

ልጆቻችንን በተሳካ ሁኔታ እንዲሰሩ ለማስተማር፤ በራሳችን የሥራ ፍላጎት ደስተኞች መሆን ይገባናል። ምናልባት ልጆቻችንን ለመርዳት ከሁሉ የተሻለ መንገድ በራሳችን ሥራ ደስታን እንዲያገኙ ነው። ብርግም ያንግ እንደተናገሩት፤ “በዚህ ዓለም የእያንዳንዱ ሰው ደስታ የተመረኮዘው በሚሰራው ሥራ ላይ እና ሥራውን በሚሰራበት መንገድ ላይ ነው። (Quoted by Elwood R. Peterson, “Family Work Projects for Fun and Profit,” *Ensign,* June 1972, p. 9.)

## ሙከራ

ከእያንዳንዱ ልጆችዎ ጋር ይነጋገሩበት። ስለቤተሰብ ኃላፊነት ሃሳብዎንና ሃሳባቸውን ተወያዩበት። እያንዳንዱ ልጅ የሥራ ድርሻን እንዲወስድ እና እንዲጨርስ ይርዱ።

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች*፤ ምዕራፍ 27፤ “ስራና ግላዊ ኃላፊነት” የሚለውን ያንብቡ።
2. የጠመኔ ሰሌዳና ጠመኔን ያዘጋጁ፤ ወይም ልጆችን ሥራ ለማስተማር አራቱን (አማራጭ) መንገዶች በተለጠፈ ማስታወቂያ አማካይነት ያስረዱ።
3. የክፍሉ አባላት በዚህ ትምህርት ላይ ታሪክና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# ራስን መግዛትን ማስተማርና ማጐልበት

ትምህርት 30

የዚህ ትምህርት ዓላማ ራስን መግዛትን እንድናስተምርና እንድናሳድግ ለመርዳት ነው።

## መግቢያ

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ በዚህ አነጋገር ላይ እናታቸውን ይጠቀሳሉ፣

“ለልጆቿ፣ እና ለሚያውቋት ለሌሎች ሁሉ፣ ቀንጆና ግርማ ሞገስ ያላት ነበረች። በከፍተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ብትሆንም፣ ቁጡና በራሷ የምትተማመን ነበረች። ደብዛዛ ቡናማ ዓይኖቿ ሲታዩ የሚማርኩ ቢመስሉም ቀሉ፣ እርሷ ሁልጊዜ ራሷን በፍፁም ቁጥጥር ስር ታደርጋለች።” (*Secrets of a Happy Life,* p. 1.)

በቅዱሳን መጽሐፍት “በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል” (መጽሐፈ ምሳሌ 16፥32)። የሚል እናነባለን። ደግሞም “በፍቀር ትሞሉ ዘንድ ፍላጎታችሁን ሁሉ መቆጣጠር አለባችሁ” (አልማ 38፥12)።

ፍላጎታችንና ጥልቀ ስሜታችን፣ እንደ ኃይለኛ ስሜታዊ ፈረስ ናቸው። ፈረሶች ሳይገሩ፣ ያለልጓም እንደአውሬ እንዲጋልቡ ቢፈቀድላቸው፣ ወደፈለጉበት ይወስዱናል። አደገኛ ጎጂ ወደሆኑበት ሥፍራ ይወስዱናል። ነገር ግን ኃይለኛ ስሜት ስላለበት ብቻ ደህናውን ፈረሳችንን መጉዳት አይገባንም። በልጓም ብንቆጣጠረው፣ ፈረሱም በሚገባ ያገለግላል። እንደዚሁ ደግሞ፣ ፍላጎታችንን እና ስሜታችንን ከተቆጣጠርን፣ ከወንጌል ጋር በተቀናጀ ሁኔታ መምራትን እንማራለን። ከዚያም እነዚህ ስሜቶች አገልጋዮቻችን ይሆናሉ። የደስታና የፍቀርን ስሜት ለመጨመር ችሎታችንን ያሳድጋሉ።

## ራስን መግዛት ለዕድገታችን አስፈላጊ ነው

ጥምቀት የአዲስ ህይወት መጀመሪያችን ነበር። ዓላማዊነትን፣ ድካምን እና ኃጢአትን ለማሸነፍ አዳኛችንን መከተል ጀመርን። አዳኛችን እንዳስተማረን፣

“ማንም ሊከተለኝ ቢወድ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።”

“እናም ለሰው መስቀሉን መሸከም ማለት በሁሉም ራሱን መካድ፣ እናም ማንኛውንም ዓለማዊ ፍላጎት መካድ፣ እናም ትዕዛዛቴን መጠበቀ ነው።” (የማቴዎስ ወንጌል 16፥24፣ የዮሴፍ ስሚዝ ትርጉም ይመልከቱ።)

ደግሞም ሲያስተምር፣ “በጠበበው ደጅ ግቡ፣ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፣ መንገዱም ትልቀ ነውና፣ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፣

“ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነውና፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።” (የማቴዎስ ወንጌል 7፥13–14።)

በጠባቡ መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት ራስን መግታትንና መካድን ይጠይቃል። በጣም ፈታኝ ከሆኑት ነገሮች ውጭ ማከናወን ማለት ነው። እውነትን አውቀን በእርሱ ከኖርን ዋጋችን አርነት መውጣት ነው። (የዮሐንስ ወንጌል 8፥31–32 ይመልከቱ።)

የዮሐንስ ወንጌል 8፥31–32 አንብቡ። በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ፥ የወንጌል መሰረተ ሃሳብን መጠበቅ እንዴት አርነት ያወጣናል? እህቶች ስለዚህ ጥያቄ እንዲያስቡበት ይጠይቁ።

ፍላጎታችንን ስንቆጣጠር፣ እኛን ከሚቆጣጠሩ ስሜቶች ራሳችንን ነፃ እናደርጋለን። ለራሳችን ቁጣን፣ ምቀኝነትን፣ በቀልን፣ ራስ ወዳድነትን፣ ኩራትን፣ ፉከራን፣ ጥላቻን፣ እና የመሳሰሉትን ለመግለፅ ብንፈቀድ ያስሩናል። በቀጣይነት የበለጠ ኃይል ያገኛሉ። ከፀባያችን ጋር ይጣበቁና ሱስ ያስይዙናል። በዚህ ዓይነት መንገድ አርነታችንን ብቻ አናጣም፣ ነገር ግን ክብራችንንም ጭምር እናጣለን።

ፍላጎታችንን ስንቆጣጠር፣ ሊገዙን ከሚችሉት ፍላጎቶች ነፃ እንሆናለን። ለብዙ ምግብ፣ ወይም ለጎጂ ነገሮች እንደ ቡና፣ ሻይ፣ አልኮል መጠጥ፣ ወይም ትምባሆ፣ ፍላጎቶች ከተረታን በቁጥጥራቸው ስር ያደርጉናል። ሰውነታችን ፍላጐት ያድርበታል። ለእነርሱ ባሪያዎች እንሆናለን።

ለዓለማዊ ነገሮች መራብ (ቀድሞውኑ ለፍላጎታችን በቂ እያለን) በጣም ብዙ ለመተኛት ወይም በጣም ብዙ ለመዝናናት (እንደ ቴሌቪዥን አይነት ላሉት) መራብም ፍላጐቶች ናቸው። አግባብ ባለው ወሰን ውስጥ መጠበቅ ይገባቸዋል።

እህቶች የበለጠ ስለሚጥሩበት ፍላጎቶች፣ ስሜቶች፣ እና ሱሶች እንዲያስቡ አድርጉአቸው። ለእነዚህ ፍላጎቶች መሰጠት ሰንሰለትን በራሳችን ዙሪያ እንደማድረግ የሚያሳዩ እንደሆነ ጠይቋቸው። 2ኛ ኔፊ 9፥45 አንብቡ። የወንጌል መሰረተ ሃሳባችን መጠበቅ እንዴት ነፃ ያደርገናል?

ቸር፣ ጠቢቡ የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን ትዕዛዛትን ሰጠን። ከሃዘን ሊጠብቀን ይፈልጋል። እንዲባርከን ራስን መግዛትን እንድናገኝ ሊረዳን ይፈልጋል። የምግብ ፍላጎታችንን መቆጣጠር እንድናውቅ የፆም ህግን በከፊል ሰጠን። ከዚያም መንፈሳችን አካላችንን እንዲቆጣጠር ማድረግ እንችላለን። የራስ ወዳድነት ፍልጎታችንን እንድናሸንፍ ሊረዳን የአሥራት ሕግን በከፊል ሰጠን። ጉዳትን ከሚያስከተሉ ትምባሆ፣ አስካሪ መጠጦች፣ እና ዕፆች በከፊል ነፃ እንድንሆን የጥበብ ቃል ሰጥቶናል። አካላዊ ፍላጐታችንን እንድንቆጣጠር ሊረዳን የንፅህና ህግን ሰጠን። እርሱ የመሰረተልንን ደንቦች መጠበቅ ይገባናል። ትዕዛዛቱ ሁሉ ለመልካም ናቸው።

ዮሴፍ ስሚዝ "ምንም እንኳ ሁኔታዎች ከተከናወኑ ከረዥም ጊዜ በኋላ ውጤቱን ብናይም፣ ምንም ይሁን ምን፣ ማንኛውም እግዚአብሔር የሚፈልገው ትክክል ነው" ብሏል። (*History of the Church,* 5:135; *Teachings of the Prophet Joseph Smith,* p. 256.)

ራስን መግዛት ማግኘት ማለት ምንም ነገር ያለማድረግ ሊመስል ይችላል። ጠንካራና ምቹ ልምዶችን መቀረፅ ማለት ነው። በማለዳ በመነሳት፣ በየቀኑ ቅዱሳን መፅሃፍትን በማጥናት፣ ሥራችንን በትጋት ለመፈፀም መገፋፋት አለብን። ፕሬዚዳንት ኤን አልደን ታነር፥ "የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ስንጠብቅ ብቻ፣ በሁሉም ነገሮች ታዛዦች ስንሆን ብቻ፣ በዚህና በመጪው አለም ዘላለማዊ ሕይወትን ልናገኝ እንችላለን፣ እናም አለምን ለመልካም ልናዘጋጅ፣ እና በዚህም ምድር የእግዚአብሔርን መንግስት ለመገንባት መረዳት እንችላለን።" ብለዋል። ("Obedience," *Ensign,* Jan. 1974, p. 94.)

ራስን መግዛት ትዕዛዛትን ለመጠበቅ እንዴት ይረዳናል?

## ራስን መግዛትን ማግኘት

ራስን መግዛት የረዥም ጊዜ ክንዋኔ ነው። ወንጌልን እንደተረዳን፣ መሰረተ ሃሳቦቹን ለመጠበቅ እንፈልጋለን። በሕይወታችን ዘመን ውስጥ እያንዳንዳችን ራስን መቆጣጠርን ማግኘትን መጠበቅ አለብን።

ራስን መግዛትን ለማግኘት እንዴት እንደምንችል ቀደም ተከተሎቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ወይም በተለጠፈ ማስታወቂያ ላይ በመዘርዘር ይፃፉ፣

1. ራሳችንን ማወቅ።
2. እቅድን ማቀድ።
3. ለእርዳታ በጌታና በቅዱስ መፃህፍት ላይ መመካት።

### ራሳችንን ማወቅ

በህይወታችን ዘመን፣ አዲስ ሁኔታዎች ይገጥሙናል፣ እናም የበለጠ ስለወንጌል እናውቃለን። ከዚያም ስለ ድክመቶቻችንና ጥንካሬያችን እንገነዘባለን። ለምን እንደሚያስፈልጉንም መረዳት እንጀምራለን። ከመጥፎ ሱሶች መወገድና ጥሩዎቹን ማጎልበት እንፈልጋለን።

### እቅድን ማቀድ

ግባችንን እስከምናልምና ለመቀዳጀት እስከምንሰራ፣ እንደ ባህር ሞገድ ዓይነት ነን። በየአቀጣጫው እንገፋለን። ነፋሱ የማይገታ ፍላጎታችንና ስሜታችን ነው። ድክመታችንን ከመቆጣጠራችን በፊት በሚገባ የተገለጸ እቅድና በራስ መተማመን ሊኖረን ይገባል። ከዩናይትድ ስቴትስ እህት ኬይ ኒው ማን ስነ-ሥርዓት ከሌለው ፍላጎት ጋር ታግላለች፣

“የራሴ ክፉ ጠላት እንደነበርኩ ባወቀሁበት ጊዜ ካደጉት ልጆቼ ጋር ትልቅ ሴት ነበርኩኝ። እናም ይህንን ያስከተለው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ልነግራችሁ ፈራሁ! አንድ ቾኮሌት ሳጥን! ይኸውም በገና በዓል ወቀት ከሞላ ጎደል አንድ ሳጥን ሙሉ ቾኮሌት በላሁ . . .

“ቾኮሌትን መብላቴ የሚያሳየው ዝቀተኛነቴን ነበር። ፍፁም ተመሳሳይ ስሜቶች ያላጋጠመው ሰው የደረሰብኝን መግለፅ አይችልም፣ በቾኮሌት ጠገብኩ፣ ራሴን ተፀየፍኩ፣ ተጨነቀሁ እናም በአጠቃላይ ተስፋ ቆረጥኩ። በዚህ አሳዛኝ፣ መጥፎ ድክመት፣ ሰይጣን በእኔ ውስጥ በመሥራት ዝቅ አደረገኝ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ስሜቴና ሃሳቦቼ ብቃት የጎደላቸው ነበሩ።

“በመሆኑም በዚያ የገና በዓል ወቀት ያን ሁኔታ ዳግም በጭራሽ እንደማልለማመደው ወሰንኩኝ። ቁጭ አልኩና ለራሴ ደብዳቤ ጻፍኩ። በደብዳቤው እንደማልረሳቸው ስሜቴን ገለጽኩ፣ እናም ሙሉ በሙሉ በራሴ ፍላጎት ላይ ቁጥጥር ማድረግን ሳላገኝ ሌላ ዓመት ማለፍ እንደሌለብኝ ለራሴ ቃል ገባሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት እንደዚያ ያለ ለውጥ በራሴ ውስጥ አየሁ፣ በራስ መተማመኔም በየዕለቱ በውስጤ አደገ። ይህን ልዩ ጦርነት ከሞላ ጎደል ማሸነፌን አወቅሁ።” (“My Worst Enemy—Me!” *Ensign,* Feb. 1975, p. 62.)

እህት ኒውማን እቅድ ማቀድ እና በእቅዷ መጽናት እንደምትችል ባረጋገጠች ጊዜ እንዴት ተሰማት? እቅዷን ለራሷ ለማስታወስ ምን አደረገች?

### ለእርዳታ በጌታና በቅዱሳን መጽሐፍት ታመኑ

በመደበኛ ፀሎትና ቅዱሳን መጻሕፍትን በማንበብ፣ ፍላጎታችንን የተሻለ ለማድረግ ራሳችንን ማጠናከር እንችላለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ሰዎች ሕይወት የምንከተለው

ምሳሌ ይሆነናል። ራስን መግዛት እንድናገኝ ያስገነዝቡናል። እህት ኒውማን በየቀኑ ለአንድ ሰዓት በታማኝነት ቅዱሳን መጻህፍትን በማንበብ ራሷን አጠናከረች። “በዚያች ሰዓት ጊዜ ውስጥ ራሴን የማሸነፍ ፍላጎትን ተገነዘብኩ። በዚያች ሰዓት ጊዜ ውስጥ ወደኋላ የሚጎትቱኝን የረዥም ጊዜ ሱሴን ለማስወገድ ፍላጎትን አገኘሁ። ያም ምኞት በማይቀጠሩ ችግሮቼ ሁሉ ከእኔ ጋር ቀይቷል።” በማለት ተናግራለች። (“My Worst Enemy—Me!” *Ensign,* Feb. 1975, p. 63.)

አንዲትን እህት እንዴት ፀሎትና ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብ እንድትለወጥ እንደረዳት ይጠይቁ።

## ራስን መግዛትን ለልጆቻችን ማስተማር

ቤታችን ልጆቻችን የራስ ቁጥጥርን መማር የሚችሉበት የሥልጠና አካባቢ መሆን አለበት። ልጆቻችንን በሚገባ ማስተማር ካልቻልን፣ ወይም በጣም ከተቆጣጠርናቸው፣ ራሳቸውን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ አይማሩም። ልጆቻችንን የራስ ቁጥጥርን ስናስተምር ሥነሥርዓት ያለውን ሂደት በመከተል መሆን አለበት።

የሚከተሉትን ዝርዝር ደረጃዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ወይም በተለጠፈ ማስታወቂያ ላይ ይፃፉ፣

1. ወሰን ያድርጉ።
2. ልጆች የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን በስራ ላይ እንዲያውሉ ያስተምሩ።
3. ኃላፊነትን ለልጆች ይስጡ።

### ወሰኖችን ያድርጉ

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ እንዳስተማሩት፣

“በእኔ አስተሳሰብ . . . ለልጅ የመከተልን ደንብ ለማስተማር ጥሩ ጊዜ በሶስትና አምስት ዕድሜዎች መካከል ነው . . . እናት በእነዚህ ዕድሜዎች ልጅን ካልተቆጣጠረች፣ በኋላ ለመቆጣጠር ከባድ ችግር ያገኛታል . . . ለመገፋፋት እና ለመጎተት ወይም ለማጋዝ አይደለም . . . ትንሽን ልጅ እንዲያድግ ከደህንነት ወሰን ልቀ ፍጹም እስኪሄድ ነፃ ለማድረግ ነው። ከዚያም ያለ ቁጥጥር የሆነ ጨዋነት ያለው ፅኑ እጅ እንዲሰማው ይሁን።

“በአንድ ወቀት እህት ማኬይ እና እኔ ይህን ደንብ በተግባር በአራዊት መጠበቂያ ሲታይ አይቻለሁ . . . ትንሽ ዝንጀሮ ልክ መዳህ ስትማር አየን። እናት ተጠብቃታለች እናም ተመግባታለች። በመጀመሪያ እናት ትንሽ ልጇን በመደባበስ፣ እንድትተኛ ስትሞክር በማየታችን ደስ አለን። ነገር ግን ትንሿ ፍጡር ከእናቷ ተነጥላ የሸቦ ቤቱ ላይ መውጣት ጀመረች። እናት በእርግጥ በአደገኛው ሥፍራ እስክትደርስ ድረስ በዝምታ ተመለከተቻት። ከዚያም ደረሰችባትና መለሰቻት፣ እናም በተወሰነው የደህንነት ክልል ውስጥ እንድትጫወት አደረገቻት . . . ከዚያም በቀድሚያ የቤተሰብን አስተዋፅኦ የልጅ ደስታ ከደህንነት ወሰን ወዲያ ያለመሄድ እውነታን ለማድነቀ እንደሆነ አይተናል።” (*Stepping Stones to an Abundant Life,* p. 38.)

ከአምስት ዓመት ዕድሜ በፊት ልጆቻችንን መቆጣጠር ቢያቀተን እንኳ፣ መሞከሩን ለምን መቀጠል አለብን? ትምህርትና ቃልኪዳን 93፡40–44 ያንብቡ። እነዚህን ወንድሞች ጌታ ለምን ገሰፃቸው?

### ልጆችን የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን በሥራ ላይ እንዲያውሉ አስተምሯቸው

ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር እንዳሉት፣

“ልጆች እንዴት ትክክለኛውን ከስህተት እንደሚለዩ በራሳቸው አይማሩም። ወላጆች ኃላፊነትን እንዲቀበል የልጁን የዝግጅት ሁኔታ ሊወስኑ ይገባል . . .ስናስተምራቸው፣

ትክክለኛውን ማድረጋቸውን ለማየት ሥነሥርዓት የማስያዝ ሃላፊነት አለብን። ልጅ ከቆሻሻ ጋር ተሸፍኖ ከሆነ ልታጠብ ብሎ ለመወሰን እስኪያድግ መቆየት የለብንም። በታመመ ጊዜም መድሃኒቱን ልውሰድ ወይም አልውሰድ ብሎ ለመወሰን ወይም ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ቤተክርስቲያንም ልሂድ ወይም አልሂድ ብሎ ለመወሰን እስኪያድግ መቆየት የለብንም . . .

"ወላጆች ደግሞ ስለተከበረው ሃሳብ እነርሱ የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጆች የመሆናቸውን እውነታ እናም የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ለመከተል መምረጥ ለስኬታማነት ብቸኛ መንገድና በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የዘለዓለማዊ ህይወትን ደስታ እንደምናገኝ ገና በመጀመሪያ የሕይወት ዕድሚያቸው ወቀት ማስተማር አለባቸው። ሰይጣን ደግሞ በራሱ ትዕዛዝ በሚገለገልባቸው ወኪሎቹ ሁሉ እንዲሳሳቱ ለመፈተን እርግጠኛ መሆኑን፣ ሊያስኮበልላቸው፣ የእርሱ ምርኮኛ ሊያደርጋቸው እና ከታላቁ የዘለዓለማዊ ሕይወት መዳን ደስታ ሊያስቀራቸው እንዳይደሰቱ ለማድረግ ጥረት የሚያደርግ መሆኑን ማስተማር አለባቸው። (*Seek Ye First the Kingdom of God,* p. 87.)

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፃዲቁ የቤተመቀደስ አገልጋይ ስለ ኤሊ እናነባለን። የኤሊ ልጆች የአባታቸውን አርአያ አልተከተሉም። ይልቅም በጌታ ላይ ታላቅ ኃጢአትን ሰሩ። ኤሊ አስጠንቀቋቸዋል ነገር ግን ሊያስተዋቸው አልቻለም። በዚህም የተነሳ ጌታ አልተደሰተበትም እናም የጭካኔ ፍርድ አመጣበት።

1ኛ ሳሙኤል 3፥13 ያንብቡ። ጌታ ልጆቻችንን ከማስተማር በተጨማሪ ምን እንድናደርግ ይጠብቅብናል?

ልጆቻችን የሚከተሉትን አግባብ የሆነ አርዓያን ማኖር በጣም አስፈላጊ ነው። አመላችንን፣ ሌሎች ፍላጎታችንን እና ጥልቀ ስሜታችንን የማንቆጣጠር ከሆነ ምናልባት ልጆቻችንም የራሳቸውን አይቆጣጠሩም።

ቤታችንን የደስታ ቦታ ማድረግ ይገባናል። ልጆቻችን ደህንነት፣ ጥበቃ እና ፍቀር ሊሰማቸው ይገባል። በቤት ውስጥ ወንጌልን በመኖር ደስታን የማያገኙ ከሆነ፣ ከወንጌል ውጭ ይሆናሉ። ስለሆነም፣ ልጅ የማይታዘዝ ከሆነ፣ እንቀጣውና ከዚያ በኋላ የበለጠ ፍቀር ማሳየት አለብን።

ትምህርትና ቃል ኪዳን 121፥43–44 ያንብቡ። ከቀጣናቸው በኋላ ለልጆቻችን የበለጠ ፍቀር የምናሳያቸው ለምንድነው? (ምክንያቱም ልጁ እንደባላጋራ አድርጎ እንዳይገምተን ነው)

## ለልጆች ኃላፊነት ይስጡ

ቄስ ኤፍ ኤንዚዮ ቡስቼ እንዳሉት፥

"እኔና ባለቤቴ መንፈሳዊነትን በማጎልበት ሂደት፣ ልጆች ትክክለኛ መስሎ የሚሰማቸው እንዳለ ተስማማን እጥረትም ቢኖር . . . እናም ይቀር ለማለት፣ ይህን መረዳት የወላጆች ተግባር እንደሆነ እናምናለን። "አለበለዚያ ተስፋ የቀረጡ ይሆናሉ።" ቆላስያስ 3፥21 ይመልከቱ። በጎ ስጦታዎችን የማግኘት ትንሹ ጅምራቸው ሊታይ፣ ሊጠቀስ፣ እና ሊደነቀ ይገባል።

"ልጆቻችን ራስን ወደማክበር እንዲያመሩ መጣር አለብን . . . እናም አብዛኛውን ጊዜ ለራሳቸው እንዲፈርዱ እንተዋቸዋለን። አንድ ሰው ጥሩ አስተማሪ ያለመሆኑን የምንለካው ስህተቶች በማግኘትና፣ በመጠቀም እውነታ በመነሳት እንደሆነ ልምዱ አለን . . . በመሆኑም አንድ ልጅ ለራሱ ስህተት እየፈፀመ መሆኑን እንዲያውቀ በረዳው ጊዜ ሊገነዘብ ይችላል ማለት ነው። ልጁ ራሱ ስህተቶቹን ካስተዋለ፣ የመጀመሪያ እርምጃው ተወሰደ ማለት ነው።

“በአንድ ወቅት ልጃችን ካጠፋ በኋላ ቀጣቱን በራሱ ላይ እንዲወስን እንዴት እንደጠየቅነው አስታውሳለሁ። ለአንድ ወር ያህል ቴሌቪዥን ማየት እንዳይፈቀድለት ወስኖ ነገረን። ያ ውሳኔ ለእኛ በጣም ትልቅ የሚከብድ ሆኖ ታየን፤ ነገር ግን የሴት አያቱን በጎበኛቸው ጊዜ እርሷ ልጁን አንዳንድ የቴለቪዥን ፕሮግራሞችን እንዲከታተል ስትገፋፋው እርሱ አጥብቆ ሲቃወማት እንደነበር ስንረዳ ምንኛ ደስተኞች እንደነበርን ነው። ይህን ያደረገው እኛ ወላጆቹ እንኳን በፍፁም በማናውቀበት ሁኔታ በውሳኔው መፅናቱን ማለታችን ነው። ለወላጆች ልጃቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ ራሱን በሚገባ መምራቱን ከማየት ሌላ ታላቅ አስደሳች ነገር ያለ አይመስለኝም።” (“Provoke Not Your Children,” *Ensign,* Mar. 1976, pp. 41–42.)

ቄስ ቡስቼ ልጆቻቸውን ራስን መግዛት እንዲያገኙ እንዴት አበረታቷቸው? (በትዕግስት ደጋግመው ተመሳሳይ ስህተቶችን በማረም፣ የራሳቸውን ስህተቶች እንዲያውቁ በመርዳት፣ የራሳቸውን ቀጣት እንዲወስኑ በመርዳት፣ ከተቃራኒ ይልቅ ቀና የሆነ ጥረታቸው ላይ በማተኮር ራስን ማክበርን በራሳቸው እንዲገነቡ በማድረግ ነው።)

ቄስ ኤል ቶምፔሪ እንዳሉት፥

“የነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ ንግግር ስለ አስተዳደር መሰረተ ሃሳቦች በእርግጠኝነት ልጆቻችንን ይመለከታል፥ ‘ትክክለኛውን የመሰረተ ሃሳብ ግንዛቤን አስተምሯቸው እናም ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ አድርጉአቸው።” (As quoted by John Taylor in *Millennial Star,* 13:339.) በእርግጥ የትምህርት አሰጣጣችን በቂና ቀስበቀስ እምነትን ማፍለቁን እና በሕይወታቸው ዘመን ውስጥ ጌታን እንዲያምኑ ማድረጋችንን እርግጠኛ ለመሆን መጠንቀቅ አለብን። በመንፈሳዊነት እየጠነከሩ መሄድ በጀመሩ መጠን በሚገባ መሰልጠናቸውንም እርግጠኞች መሆን ይገባናል፤ እናም በውስጣቸው እያደገ ያለውን ሃይል ለመግለጽ ዕድል ልንሰጣቸው ይገባናል። እምነታችንንና መታመንን እናም ኃላፊነትን ልንሰጣቸው ይገባናል።” (In *Official Report of the São Paulo Brazil Area Conference,* Feb. 1975, pp. 11–12.)

## ማጠቃለያ

በራሳችንና በልጆቻችን ራስን መግዛትን ስንገነባ የወንጌል በረከቶችን ደስታ በበለጠ እናገኛለን። በልጆቻችን የግል ቁጥጥርን መገንባት ፍላጎታችንን ከመጫንና መታዘዝን ከማስገደድ ይልቅ የበለጠ ትዕግስትን ይወስዳል። ነገር ግን ልጁ በሚገባ እንደአዋቂ እንዲሆን እንፈልጋለን።

## ሙከራ

ስህተትን የመቆጣጠርን ግብ አልሙ። ልጅችዎን ለመርዳት ራስን የመግዛትን ሶስት ደረጃዎችን ይከተሉ። ይህንን ትምህርት በቤት ውስጥ ይከልሱ።

---

**የአስተማሪ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን፣* ምዕራፍ 4፣ “ለመምረጥ ነፃነት” የሚለውን ርዕስ ያጥኑ።
2. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን፣* ምዕራፍ 35፣ “መታዘዝ” የሚለውን ርዕስ ያጥኑ።
3. ስብሰባውን “በብርሃን እንድራመድ አስተምረኝ” በሚለው መዝሙር ለመክፈት ያቀዱ (*የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች*)።
4. በትምህርቱ የተጠቀሰውን ፖስተር ያዘጋጁ፣ ወይም ጥቁር ሰሌዳና ጠመኔን ያቅርቡ።
5. የክፍሉ አባላት በዚህ ትምህርት የተጠቀሰውን ታሪኮችና ጥቀሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# በቤታችን በጎና አበረታች ሁኔታን መፍጠር

ትምህርት 31

የዚህ ትምህርት ዓላማ በቤታችን ውስጥ የሚያበረታታ አካባቢን ለመፍጠር እንዲያነሳሳን ነው።

## የቤት ህይወት ታላቁ ተፅዕኖ

ትዕይንት 31-ሀ፣ እናትና ልጆቿ፣ እናም 31-ለ፣ እናት ለልጆቿ ስታነብ ያሳያል።

በቤት የምናባክነው ጊዜ በህይወታችን ውስጥ ታላቅ ተፅዕኖ አለው። እያንዳንዳችን በቤታችን ጥሩ ሁኔታ ሊሰማን ይችላል። በዚህም ሥፍራ ልጆቻችን ልምዶቻቸውንና ሃሳቦቻቸውን ያበጃሉ። ዶርቲ ሎው ኖልት ሲፅፍ፣

"ልጅ በትችት ከኖረ፣ ማውገዝን ይማራል።
ልጅ በጥላቻ ከኖረ፣ ፀብን ይማራል።
ልጅ በመሳለቅ ከኖረ፣ እፍረትን ይማራል።
ልጅ በእፍረት ከኖረ፣ የጥፋተኛነት ስሜትን ይማራል።
ልጅ በቻይነት ከኖረ፣ ትዕግስተኛነትን ይማራል።
ልጅ በመበረታታት ከኖረ፣ በራስ መተማመንን ይማራል።
ልጅ በምስጋና የኖረ ከሆነ፣ መደነቅን ይማራል።
ልጅ አድሎ በሌለበት ከኖረ፣ ፍትህን ይማራል።
ልጅ በመረጋጋት ከኖረ፣ እምነት እንዲኖረው ይማራል።
ልጅ በመስማማት ከኖረ፣ ራሱን መውደድን ይማራል።
ልጅ በተቀባይነትና በወዳጅነት ከኖረ፣ በዓለም ውስጥ ፍቅር መፈለግን ይማራል።"
("Children Learn What They Live," © 1963 by John Philip Co.; used by permission.)

እንደሴትነታችን መልካም ስሜትን በቤት ውስጥ ለመፍጠር ኃላፊነት አለብን። አብዛኛውን ጊዜ ከባሎቻችንና ከአባቶቻችን ይልቁ የሚበልጠውን ጊዜ እዚያ እናጠፋለን። እነዚህን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ እንችላለን፣ በቤታችን ውስጥ ፀብ ወይም ቁጣ አለን? ሌሎችን እንወነጅላለን ወይም እናሳዝናለን? አግባብ የሌላቸውን ቀልዶች እንናገራለን? በቤታችን ውስጥ መሣላ አለን? የተሰላቸ፣ ደስተኛ ያልሆነ፣ ወይም ዕፍረት የሌለው ሰው አለን? ለእነዚህ ስሜቶችና ድርጊቶች ኃላፊዎች ነን? ኃላፊዎች ከሆንን፣ ለሌሎች የቤተሰብ አባላት መጥፎ አርአያ እናኖራለን።

ትዕግስተኞችና ደስተኞች ነን? የቤተሰባችንን ስህተት በቁጣ ሳይሆን በፍቅር እናርማለን? ለተቀደሱ ነገሮች ክብርን እናሳያለን? በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት አለን? የየራሳችንን ችግሮች እንካፈላለን? በግልና በቤተሰብም ሆነን እንፀልያለን? እርስበርስ በጥንቃቄ እንደማመጣለን?

31-ሀ እናት እና ልጆቿ




Bible

እነዚህን ነገሮች ካደረግን፣ መንፈሳችንን የሚያነቃቃና ቤተሰባችንን የሚረዳ ስሜትን እየፈጠርን ነው።

የቤተሰብ አባላት በተፈጥሮ ቁንጅናን የሚወዱበትን ቤት መመስረት እንችላለን። ሰላም፣ ማስተዋል፣ እና ደስታ ካለን ሌሎች የቤተሰብ አባላትም ደግሞ ደስታ ይሰማቸዋል።

## ቤትን የመኖሪያ ቤት ማድረግ

እያንዳንዳችን ቤተሰባችንን የሚያነቃቃ ስሜትን በቤታችን ውስጥ መፍጠር አለብን። የወንጌል መሰረተሃሳቦችን እንዲጠብቁና ጊዜያቸውንና ተሰጧቸውን በሚገባ እንዲጠቀሙበት እንሻለን። ማንኛውም ሰው አዕምሮውንና አካሉን ሊጠቀምበት ይገባል። ለጥናት፣ ለመዝናኛ፣ እናም በቤታችን ለመደሰቻ የምንሰራቸውን ሥራዎች ማዘጋጀት አለብን። ከዚያም የቤተሰብ አባላት ሌላ ቦታ አይሄዱም ማለት ነው።

ቤት ሰዎች በሰላምና በደስታ የሚኖሩበት ሥፍራ ነው። ቤት ዋሻ፣ ድንኳን፣ ጎጆ፣ ዳስ፣ ትልቅ የጡብ ህንፃ ወይም ቤተመንግሥት መሆን ይችላል። የህንፃው ውበት ወይም ስፋት ቤት አያሰኘውም። ይልቁንም፣ ደስተኛ ሰዎች ቤትን ይመሰርታሉ።

በየቤታችን ጥሩ ስሜትን የሚያሳድሩ ምንድናቸው? መልሶቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ይወያዩባቸው። ደግሞም የሚከተሉትን ሃሳቦች ይጥቀሱ፥

1. ለሌሎች ሰዎች ስሜት ጥንቃቄን ማድረግ
2. የጌታን መንፈስ በማኖር
3. የመፈለግ ስሜት መኖር
4. መፀለይ
5. የቤተሰብ የቤት ምሽት ጊዜን ማድረግ
6. ቅዱሳን መጻሕፍትን ማጥናት

ደሃም ሆነን ወይም ሃብታም፣ ቤተሰቦቻችንን በቤታቸው በመኖራቸው እንዲደሰቱ ብዙ ነገሮችን ማድረግ እንችላለን። የቀልድ ተግባሮችን በማሰብ የቤተሰብ አባላትን ለማስተማርና ለማስደሰት ማሰብ እንችላለን።

እህቶችን በሚያድጉበት ጊዜ በቤታቸው ስለነበራቸው ደስታ ጊዜያቸው እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።

በጠመኔ ሰሌዳ ላይ፥ ሙዚቃን ይፃፉ። የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፥

"ፍሬድ በታዛዥነት ቁርሱን በላ እናም ከወንበሩ ላይ ተንሸራቶ ወደቀ።

" 'አሁን ወደ ጂሚ እናት ቤት ልሂድ?" ሲል ጠየቀ።

"እኔ ግን 'ፍሬድ፣ ትናንትና ከዚያም በፊት ባለው ቀን እነርሱ ዘንድ ነበርክ። ስለዚህ ዛሬ ጂሚ ራሱ ለምን እዚህ አይመጣም?' አልኩት።

" 'ኦ፣ እርሱ አልፈለገም'። ምንም እንኳን የስድስት ዓመት ልጅ ቢሆንም የፍሬድ ከንፈሮች ተንቀጠቀጡ። 'እናቴ፣ እባክሽ።'

" 'ልጄ ከእኛ ቤት በተሻለ የእነ ጂሚን ቤት ለምን ወደድህ?" ተከተልኩ። ፍሬድና ጓደኞቹ ሁሉ ሁልጊዜ ወደ እነ ጂሚ ቤት መሄድ እንደሚፈልጉ አሰብኩ።

" 'ለምን፣" በማመንታት ገለፀ፣ "ምክንያቱም የእነ ጂሚ ቤት የሚዘመርበት ቤት ነው።'

31-ለ እናት ለልጆቿ ስታነብ ያሳያል

"'የሚዘመርበት ቤት?" ብዬ ጠየቅሁት። 'አሁን እንዲህ ስትል ምን ማለትህ ነው?'

"'ደህና' ፍሬድ ለማስረዳት ቸገረው፤ 'የጂሚ እናት እየሰፋች ታዜማለች፤ እናም አኒም በማድቤት፤ ብስኩቶችን ስትቀራርጥ ታዜማለች፤ እናም የጂሚ አባት ሁልጊዜ ወደ ቤት ሲመጣ ያፏጫል።' ፍሬድ ለትንሽ ጊዜ ቆም አለና በመቀጠል፤ 'ምንጣፋቸው በሚገባ ተጠቅልሎ በመስኮት ውስጥ አበቦች አሉ። ልጆች ሁሉ የጂሚን ቤት ይወዳሉ፤ እናቴ።'

"'ልጄ መሄድ ትችላለህ፤" አልኩት በፍጥነት። እኔ እንዳስብበት እንዲሄድ ፈለግሁ።'

"በቤቴ ዙሪያ አየሁ። እንዴት አስደሳች እንደነበር ሁሉም ሰው ነገረኝ። የምስራቃዊ ዓለም ስጋጃዎች ነበሩ። ዋጋቸውን በየጊዜው እንከፍል ነበር . . . ለተከማቹት የቤት ቁሳቁሶችና ለመኪናም ደግሞ በዚያ ዓይነት እንከፍል ነበር። ምናልባት ለዚህ ይሆናል የፍሬድ አባት ወደ ቤት ሲገባ የማያፏጨው።

"እኔ ቀዳሚ ጧት አስር ሰዓት ሲሆንም ወደ እነ ጂሚ ቤት ሄድኩ። በማለዳው አጋማሽ ሚስስ በርተን በመቋረጧ ምንም ሊሰማት እንደማይችል ሆኖ ተሰማኝ በጭራሽ የምትጣደፍ አይመስልም። በራሷ ዙሪያ ፎጣ ጠምጥማ በር ላይ ተገናኘን።

"'ኦ! ግቢ። ልክ አሁን ሳሎኑን አጽድቼ ስጨርስ መጣሽ። በእርግጥ አይደለም፤ አላደናቀፍሽኝም። ይህን የራስ ሽፋን አውልቄ ወዲያውኑ እመለሳለሁ።'

"እርሷ እስክትመለስ በምጠብቀበት ጊዜ፤ በቤቱ ውስጥ ዙሪያውን ተመለከትኩ። መወልወያዎቹ ከሞላ ጎደል አርጅተዋል፤ ምንጣፎቹ . . .ወደ ኋላ ታስረዋል፤ የቤቱ ቁሳቁሶች አሮጌና እንከን ያለባቸው ነበሩ . . .ባለብሩህ መሸፈኛ ጠረጴዛው የተለያዩ ወቅታዊ መጽሔቶች ተቀምጦበታል። በመስኮት ውስጥ የተሰቀሉ በጣም ለም የሆኑ የተክሎች ቅርጫቶች አሉ . . .በጸሐያማው በኩል በተሰቀሉ የወፍ ጎጆዎች ወፎች ይዘምራሉ። በሚፈለገው ዓይነት በጣም የተመቻቸ ቤት።

"የማዕድ ቤቱ በር ተከፍቶ ነበር እናም፤ ሕጻኗን ጄሪን፤ በንፁህ ጠንካራ ወለል ላይ ተቀምጣ አኒን የምግብ ፍራፍሬዎችን ጫፍ በአንድ ላይ ስትቀነጥስ ስትመለከታት አየሁ። ተዘምር ነበር።

"ወ/ሮ ቡርተን ፈገግ እያለች ገባች። 'ደህና፤ ለአንድ ነገር መምጣትሽን አውቃለሁ ምክንያቱም፤ አንቺ በጣም ሰራተኛ የሆንሽ ሴት ነሽ፤ ምንድነው እሱ?' ብላ ጠየቀችኝ።

"'አዎን፤ የሚዘመርበት ቤት ምን እንደሚመስል ለማየት ነው የመጣሁት።' አልኳት በድንገት።

"ወይዘሮ ቡርተን ግራ የተጋባች ተመስላለች። 'ለምን፤ ምን ማለትሽ ነው?'

"'ፍሬድ እንደሚለው እዚህ መምጣትን ይወዳል ምክንያቱም አንቺ የመዝሙር ቤት አለሽ። ምን ማለቱም እንደሆን ማወቅ ጀመርኩ።'

"'ምን ግሩም አስተያየት ነው! የወ/ሮ ቡርተን ፊት ፈካ። 'ነገር ግን ቤቴ በእርግጥ ከአንቺ ጋር አይወዳደርም። ሁሉም ሰው አንቺ በከተማው በጣም አስደሳች ቤት አለሽ ይላል።'

"'ነገር ግን የመዝሙር ቤት አይደለም።' ስል ተቃወምኩ። . . .ቤትሽን እንዴት የመዝሙር ቤት እንዳደረግሽ ንገሪኝ።'

"'ደህና፣ በእርግጥ ማወቅ ከፈለገሽ" ብላ ወ/ሮ ቡርተን ፈገግ አለች። አየሽ ጆን ብዙ ክፍያ የለውም። ወደፊትም በጭራሽ የሚያገኝ አይመስለኝም። የዚያ ዓይነት ሰው አይደለም። በሆነ ቦታ ላይ መቁረጥ አለብን፣ እናም አስፈላጊ በማይሆኑበት ነገሮች ላይ ወስነናል . . . መጻሕፍት፣ መፅሔቶች እና ሙዚቃዎች አሉ . . . እነዚህ ልጆች ወደ ውስጥ ማስቀመጥ የሚችሏቸው ነገሮች ናቸው። በእሳት ወይም (የገንዘብ ችግሮች) አይነኩም። ስለሆነም አስፈላጊ ናቸው ብለን ወስነናል። በእርግጥ ጥሩ ጤናማ ምግብ ሌላው አስፈላጊ ነው . . .የልጆች ልብሶች በጣም ቀላል ናቸው . . .ነገር ግን ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ከተከፈለ፣ ለመወልወያና ለቁሳቁስ ምንም የሚተርፍ አይመስልም . . .ማስቀረት ከቻልን ወደ ዕዳ መግባት የለብንም . . .(ይሁንና) ደስተኞች ነን፣' ስትል አጠቃለለች።

"'አሃ፣ አልኩ በሐሳብ። ጂሪንና ፍሬድን በማዕዘን በኩል ተመለከትኳቸው። እነርሱም በክብሪት ሳጥን ባቡር ሰርተው ስንዴ ጭነውበታል። ጥሩ ተሳትፎን እያሰራጩ ነው ነገር ግን ስንዴው ንጹህና ጤናማ ነው።

"ወደቤት ሄድኩ። የምሥራቁ አገር መወልወያዬ መልኩ የለቀቀ ይመስላል። ምንጣፎቹን ወደ መስኮቱ ጫፍ ለቀም አድርጌ መለስኩ፣ ነገር ግን በሐር የግድግዳ ልባስ ጨርቅ ውስጥ ብርሃኑ ሲመጣ ዛይሉ የተሸፈነ ነበር (ቤቴ) የመዝሙር ቤት አይደለም። ቢሆንም እንዲዘመርበት ወስኛለሁ።" (May Morgan Potter, "The Singing House," as quoted by Reed H. Bradford, "Priorities," *Instructor,* Nov. 1969, pp. 410–415.)

"የመዝሙር ቤት" ምን ማለት ነው? ይህ ቤት ደስተኛ የሆነበት አንዳንድ ምክንያቶች ምንድናቸው?

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሙዚቃዎች በዓለም ውስጥ መንፈስን የሚቀሰቅሱ አይደሉም። አንዳንድ የሙዚቃ ፀሐፊዎች ወራዳ ወይም ለተቀደሱ ነገሮች ክብር የማያሳዩ ስሜቶች እንዲኖረን ይፈልጋሉ። እንደዚያ ያሉ ሙዚቃዎች የጌታ መንፈስ እንዳይኖረን ያግዱናል።

ስዕላዊ መግለጫ 31-ሐ አሳዩ፣ ይህች እናት የወንጌል መዝሙሮችን ለልጆቿ ገና በጅምር ለጋ ዕድሜያቸው ወቀት ስታስተምር ያሳያል። ትምህርትና ቃልኪዳን 25፡12 ያንብቡ።

ሙዚቃ ቤተሰብን በአንድነት እንዲቀራረቡ እናም ወደ ጌታም እንዲቀርቡ ያስችላል። እንደቤተሰብ መዝሙርን በአንድነት መዘመር ወደ ጌታ ያቀርበናል። ባህላዊ ሙዚቃዎች ቀድመ አያቶቻችን እንዴት እንደኖሩ ያስታውሰናል። ጥሩ ሙዚቃ ያነቃቃናል፣ እናም መንፈሳችንንም ይቀሰቅሳል። በመስማት፣ በመዘመር፣ እናም በየጊዜው በመጫወት መውደድን እንማራለን።

የሙዚቃ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ የቤተሰብ አባላትን ማበረታታት አለብን። የቤተክርስቲያኑ መሪዎች የሚከብደን እንኳን ቢሆን ይህን እንድናደርግ ይመክሩናል። እህት ማርግሪት ኤፍ ሎነር፣ የስዊስ ቤተክርስቲያን አባል፣
የሚከተለውን ታሪክ ይነግሩናል፥

"የእናቴ ቀንጆ ድምፅ በስዊዘርላንድ ጧት፣ ቀትርና ምሽት ቤታችንን ይሞላዋል። ምንም ዓይነት ግጥሙ ቤት የሚመታን ዜማ አታውቀም፣ ነገር ግን የጽዮንን መዝሙር ትዘምራለች . . . ከዚህም የተነሳ፣ እኔ እነዚህን ብሔራዊ መዝሙሮችን በጣም ትንሽ ልጅ በነበርኩ ጊዜ ብቻ እንኳ መዘመር ችያለሁ።

"ወላጆቼ ፒያኖ ሊገዙልኝ አልቻሉም፣ . . . ስለዚህ በየዕለቱ ለዛያ ደቂቃ ያህል በዝናብና በበረዶ ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል ከፊተኛው ክፍል ከዙሪች ቀርንጫፋችን አንዳንድ



አባላት ዘንድ ፒያኖውን ለመለማመድ በብርድ ውስጥ እጓዝ ነበር። በዚህ የተነሳ ወዲያው የሳምባ ምች ያዘኝ፣ በዚህን ጊዜ ቤተሰቦቼ ከአንዳንድ ዕቃዎቻቸው ውጭ ፒያኖ ሊገዙልኝ ሄዱ። ለሙዚቃ ትምህርቴ ገንዘብን ለማግኘት እናቴ በጎረቤት ሕንፃዎች ውስጥ ክፍሎችን ታፀዳ ነበር። በዚህ የመስዋዕትነት ውጤቶች፣ ሕይወቴ ከሙዚቃ ጋር በብዙ ምርጫ ውስጥ ማለፍ ችላለች።" ("With a Song on Your Hearth," *Ensign,* Aug. 1975, p. 27.)

በጥቁር ሰሌዳው ላይ፣ ጥበብን ይፃፉ።

በቤታችን ኪነጥበብን እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

ትዕይንት 31-መ፣ የዚህን ቤት ሁኔታ ጠቃሚነት ለማሳየት የተነሳውን ክርስቶስን ፎቶግራፍ ተጠቀመውበታል።

በቤታችን የምንጠቀምባቸው ፎቶግራፎች፣ ለቤተሰቦቻችን ምን ነገሮች ጠቃሚ እንደሆኑ ይናገራሉ። በፎቶግራፎች ዙሪያችንን መከበብ እንችላለን ያም ስለቤተሰቦቻችን፣ ቅድመ አያቶቻችን፣ እምነታችን እናም ስለግባችን ያስታውሰናል። እነዚህ ፎቶግራፎች የአዳኙ፣ የቤተመቅደሶች፣ የነቢያት ሊሆኑ ይችላሉ። ቤታችንን ፍጥረትን፣ ሰላምን፣ ውበትን፣ ታሪክን እና የመሳሰሉትን አንድንወድ በሚረዱን ደግሞ ማስጌጥ እንችላለን።

ቀለም በመቀባት፣ ምስል በመቀረጽ፣ የመርፌ ሥራ፣ እና ሽመና፣ በእጅ ሙያ ጥበባችን ቤታችንን ማስጌጥ፣ ችሎታን ማጎልበት እንችላለን። የቤተሰብ አባላትን በኪነጥበብ አቅርቦትና መሳሪያ በመስጠት ማበረታታት እንችላለን፣ ሥራቸውን በቤታችን በማሳየት ልናበረታታቸው እንችላለን። በፍፁም በእጅ ሙያ ውጤታቸው ወይም ጥረታቸው ልናፌዝባቸው አይገባንም። በቤተሰብ የቤት ምሽቶች፣ ሙያን የምንማርበት ሥፍራ ሊኖረን ይችላል። ሁሉም ሰው አንድን ቆንጆ ነገር ለመፍጠር በአንድነት መሥራት ይችላሉ። ከዚህም በሽተኛ ለሆነ ሰው ከቤት መውጣት ለማይችል፣ ወይም ብቸኛ ለሆነ ሰው መስጠት እንችላለን።

በጠመኔ ሰሌዳ ላይ፣ ፍጥረትን ይፃፉ።

የፍጥረትን ደስታን እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

ብዙዎቻችን የፍጥረትን ውበት ለማድነቅ በቂ ጊዜ አንወስድም። ነገር ግን በየጊዜው የጀምበር ጥልቀትን፣ የአበቦች ውበትን፣ በዛፎች ውስጥ የፀሐይ ሙቀትን፣ የባህር ቀንድ አውጣን፣ ወይም ልዩ ቀለም ያላቸውን ድንጋዮች አይተን ስንደሰት የጌታ መንፈስ ሊሰማን ይችላል። ስለ ፍጥረት አስደናቂነት ላይ መነጋገርና ለእግዚአብሔር የእጅ ጥበብ ሥራ ምስጋናን መስጠት እንችላለን።

አበቦችንና ተክሎችን ከቤት ውጭ ወይም በቤት ውስጥ በመተከል የፍጥረትን ውበት ወደ ቤታችን ለማምጣት እንችላለን። ከሞላ ጎደል ሁሉም ሰው ዛፎች መትከልን፣ ውኃ ማጠጣትን፣ እና በአፈር ውስጥ ዘልቀው ሲበቅሉ በማየት ይደሰታል። ጠጠሮችን በመልቀም፣ እና ቀጠላ ቀጠሎችን በማጥናት ልንደሰት እንችላለን። እንስሳትን ማርባትና መጠበቅ ስለ ትውልድ፣ ሕይወት እና ሞት ያስተምረናል። ፍቅርንና ግልጋሎትን መስጠትን ያስተምረናል። ማንኛውንም ስለፍጥረት ፍላጎት በቤተሰብ አባላት የታዩትን ማበረታታት አለብን።

በጥቁር ሰሌዳ ላይ፣ መፃሕፍትን ይፃፉ።

በቤታችን የጥሩ መፃሕፍትን ደስታ እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

31-ሐ ይህች እናት ለልጆቿ በጅምር ዕድሚያቸው ወቀት የወንጌል መዝሙሮችን ታስተምራለች


31-00

ልክ ጥሩ ምግብ አካላችንን እንደሚመግብ ያህል፣ ቅዱሳን መፃሕፍትንና ጥሩ መፃሐፍትን ማንበብም አዕምሮአችንን ይመግባሉ። መፃሕፍት እንደ ወዳጆች ናቸው። ወደ ላይ ሊያነሱን ወይም ወደታች ሊጥሉን ይችላሉ። ብልሆች ከሆንን፣ ጥሩ ሰዎች የሚያደርጉንን መፃሕፍት ብቻ እናነባለን። ጥሩ መፃሕፍት ጥሩ የሆነን ነገር፣ ቀንጆ እና እውነትን እንድናደንቅ ይረዱናል።

በቤተሰባችን ጥሩ መፃሕፍትን ለቤታችን በመምረጥ የማንበብ ፍላጎት እንዲኖራቸው ማግባባት እንችላለን። ከፍ ባለ ድምፅ ማንበብ እንችላለን። የሕይወታችንንና የቀድመ አያቶቻችንን ታሪኮች መንገር እንችላለን።

ትምህርትና ቃል ኪዳን 88፡118፤ 90፡15 ያንብቡ።

ቤተሰብዎን ለመርዳት ምን ዓይነት መፃህፍትን ወደ ቤት ያመጣሉ?

በጥቁር ሰሌዳ ላይ፣ መስተንግዶን ይፃፉ።

ለቤተሰቦቻችን ምን ዓይነት መስተንግዶ ልናደርግላቸው ይገባናል?

የተንቀሳቃሽ ፊልምና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እንደ መፃሕፍት ሊያግባቡን ይችላሉ። አንዳንዶቹ እውነተኛ መሰረተ ሃሳቦችን ያስተምሩናል አንዳንዶቹ የሚያስገርሙን ናቸው፣ አንዳንዶቹ ጊዜያችንን ያባክናሉ፣ አንዳንዶቹ ሃሰተኛ ሃሳቦችን ይሰጡናል። ቤተሰቦቻችን የትኞቹ ለጊዜያችን ይፈይዳሉ እናም የትኞቹ ያባክናሉ በሚለው መወሰን ይገባቸዋል። በርካታ ጎልማሶችና ልጆች አካላቸውንና አዕምሮአቸውን በማሻሻል የቲቪ ጊዜያቸውን በተሻለ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። “ማንኛውንም ባለጥሩ ምግባር፣ አስደሳች፣ ወይም የጥሩ ዘገባ ወይም ስለ ደግነት ማመስገን ካለ፣ እነዚህን ነገሮች እንሻለን።” (አስራሶስተኛው የእምነት አንቀፅ)።

በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሥርዓትን፣ ንጽሕናን፣ ይፃፉ።

በቂ ገንዘብ እንኳን ባይኖረንም አነስተኛ ውበት በቤታችን ሊኖረን ይችላል። ለቆሻሻ፣ ላልተጠገኑ፣ ወይም አስቀያሚ ለሆኑ ነገሮች መዘጋጀት የለብንም። አንዳንድ ጊዜ ቤታችንን ንፅህና በፅዳት በመጠበቃችን፣ ከሥራዎች፣ በትርፍ ጊዜ ከምንሰራቸው ሥራዎች፣ ወይም ፕሮጀክቶች መወገድ እንፈልጋለን። ቤታችን እንዳያስደስተን ምስቅልቅል መሆናቸውን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል ለመፍጠር ነፃነትን ይሻል። ሁሉንም ንብረትና የሌሎችን አባላትን ተግባራት ማክበር አለብን። እያንዳንዱ ልጅ ”ለገንዘቡ” የተለያየ ቦታ መሳቢያ ወይም ሳጥን ሊኖረው ይገባል።

## ማጠቃለያ

ውብና መንፈስን የሚቀሰቅስ ቤት ለቤተሰብ አባላት ቸል የማይሉትን ዝንባሌ የሚሰጥ ነው። እዚያ መሆንን ይፈልጋሉ። እዚያ ተሰጧአቸውንና የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ሥራቸውን ማሳደግና ማሳየት ይችላሉ።

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ፡ “በዚህ ምድራዊ ህይወት ከቤት ይልቅ ሌላ እውነተኛ ደስታ ሊገኝ የሚችልበት ሥፍራ እንደሌለ አውቃለሁ። ቤትን ትንሿ መንግሥተ ሰማይ ማድረግ ይቻላል፣ በእውነትም፣ መንግሥተ ሰማይ ቀጣይነት ያለው ተስማሚ ቤት እንደሆነ ይታየኛል።” (*Secrets of a Happy Life,* p. 18.) እያንዳንዳችን የዚያን ዓይነት ቤት ለመፍጠር ዕድሉና ውድድሩ አለን።

31-መ፣ የተነሳው ክርስቶስ ምስል የዚህን ቤት ሁኔታን ለማነሳሳት ጥቀም ላይ ውሏል።

"ውበት በሁሉም ዙሪያ አለ" የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ (*የወንጌል መሰረተ ሐሳቦች*).

## ሙከራ

የቤትዎን ስሜት ለማሻሻል በዚህ ሳምንት አንድን ልዩ ነገር ያድርጉ። እንደ ጅምር፣ የሚበልጠውን ጊዜ ፈገግታ ለማሳየት ይሞክሩ፣ ወይም አስተያየትዎን ያሻሽሉ። በሌላ ቤተሰብ አባላት ላይ ያደረሰውን ያስታውሱ።

የተፈጥሮ ጉዞን ወይም ከልጅዎ ጋር መደበኛ የንባብ ፕሮግራም ያቅዱ።

---

#### የመምህሩ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች*፣ ምዕራፍ 34፣ "ተሰጥዎአችንን ማሳደግ" የሚለውን ያጥኑ።
2. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች*፣ ምዕራፍ 36፣ "ቤተሰብ ዘለዓለማዊ መሆን ይችላል" የሚለውን ያጥኑ
3. የጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ያቀርቡ።
5. የክፍሉ አባላት በዚህ ትምህርት የተጠቀሰውን ታሪኮችና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# በቤታችን ውስጥ ወንጌልን መማር

ትምህርት 32

የዚህ ትምህርት ዓላማ ቤታችንን ለወንጌል መማሪያ ማዕከል ለማድረግ እንዲረዳን ነው።

## ወላጆች ልጆቻቸውን ማስተማር ይገባቸዋል

የነቢዩ ልጅ፣ ኤነስ፣ በየጊዜው አባቱ ስለዘለዓለማዊ እውነት የሚያደርውን ንግግሮች ሰምቷል። አንድ ቀን ለአደን ወደ ጫካ ሄደ። እዚያ በነበረ ጊዜ፣ "በየጊዜው አባቴ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲናገራቸው የሰማሁት ቃላቶች፣ . . . በልቤ ውስጥ በጥልቁ ሰምጠዋል። አለ።

"እናም ነፍሴ ተራበች፣ እናም በፈጣሪዬ ፊት ተንበረከኩ።" (ኤነስ 1፥3-4)

ኤነስ ወንጌልን በአግባቡ በቤቱ የተማረ ወጣት ነው። ብሉይ ኪዳን "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" (መፅሐፈ ምሳሌ 22፥6) ሲል ያስተምራል። እንደ ታማኝ ወላጆች ለእኛና ለሰማዩ አባታችን ከሚታዘዙ ከታማኝ ልጆች ጋር እንባረካለን። ጌታ ሁል ጊዜ መማር እንዳለብን አቀዶልናል። በየቤታችን የዘለዓለማዊ ዕድገት ልምድን በመመሥረት ወንጌልን ማጥናት እንችላለን።

## ቤታችን የመማሪያ ማዕከል ነው

ቤተሰብ በቤተክርስቲያንና በኅብረተሰብ ውስጥ ከሁሉም የበለጠ አስፈላጊ ድርጅት ነው። በሰለስቲያል መንግሥትም የሚኖር ብቸኛ ድርጅት ነው። በዚህ የተነሳ፣ ቤታችንን የወንጌል መማሪያ ሥፍራ ማድረግ ይገባናል። እንደ ወላጆች፣ ወንጌልን ለልጆቻችን የማስተማር ኃላፊነት አለብን። እኛ እና ልጆቻችን በአንድነት ማደግ እንችላለን።

ትምህርትና ቃል ኪዳን 68፥25–28 ያንብቡ። ልጆች ስለ ዓለም መሰረታዊ ዕውቀታቸውን የሚማሩት ከየት ነው? *ስለዘለዓለማዊ ሕይወትስ* እንዴት ሊማሩ ይችላሉ?

ልጆች *ስለዚህ* ሕይወት በቤታቸው፣ በትምህርት ቤት፣ እና ከጨዋታ ጓደኞቻቸው ይማራሉ። ነገር ግን ዘለዓለማዊ እውነትን ከትምህርት ቤት እና ከጓደኞቻቸው አይማሩም። ወላጆች ልጆቻቸውን ወንጌል ለማስተማር የተቀደሰ ኃላፊነት አለባቸው። ይህን ተግባር ስናከናውን፣ የጌታን ትዕዛዛት እየተከተልን ነው። ነገር ግን ልጆቻችንን ማስተማር ካልቻልን፣ በዘለዓለማዊ ሕይወት ውስጥ እናጣቸዋለን።

ልጆቻችንን በብርሃንና በእውነት ለማሳደግ ከልጆቻችን ጋር ሆነን ወንጌልን ማጥናት መጀመር አለብን። ንጉሥ ቢንያም ለወላጆች እንደተናገሩት፣

"ልጆቻችሁ . . . የእግዚአብሄርን ህግ እንዲተላለፉ አታድርጓቸው፣ እናም እርስ በርስ አይጣሉ፣ እና ዲያብሎስን አያገልግሉ . . .

"ነገር ግን ልጆቻችሁን በእውነትና ራሳቸውን መቀጣት በሚችሉበት መንገድ፣ እርስ በርስ እንዲዋደዱ፣ እርስበርስም እንዲረዳዱ ማስተማር አለባችሁ።" (ሞዛያ 4፥14–15።)

## ለቤተሰብ የወንጌል ጥናትን ስለማቀድ

ቤታችንን የወንጌል መማሪያ ለማድረግ፣ ዕቀድ ሊኖረን ይገባል። እያንዳንዱ ቤተሰብ በሚገባ ሊሰራባቸው የሚችለውን መንገድ መፈለግ አለበት።

እነዚህን ቀደም ተከተሎች እንደ ተወያያችሁባቸው በተለጠፈ ማስታወቂያ አሳዩ ወይም እያንዳንዱን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፏቸው፣

1. ለትምህርት ሁኔታዎችን ያመቻቹ።
2. ከቤተሰብ ጋር ይፀልዩ።
3. የተለየ እውነትን ለማስተማር ጥሩ ዕድል ይውሰዱ።
4. በየጊዜው ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት።
5. በቋሚነት የቤተሰብ የቤት ምሽትን ማከናወን።
6. ለልጆቻችን ምስክርነትን መስጠት።

### ለትምህርት ሁኔታዎችን ያመቻቹ

ልጆቻችን በቤት ከእኛ ጋር ለመነጋገር ነፃነት ሊሰማቸው ይገባል። ብዙ ቤቶች ልጆች ጥያቄዎችን እንዳይጠይቁና ስሜታቸውን እንዳይገልጹ ተፅዕኖ በማድረግ በማሳዘን በጭንቀት የተሞሉ ናቸው። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ ሲመክሩ፣ “ወላጆች . . . ጥያቄዎችን ለመመለስ ፈቃደኛነትን ማሳየት ይገባቸዋል። ጥያቄዎችን የሚጠይቀ ልጅ ለህይወትዎ ደስታ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው።” (*Gospel Ideals,* p. 480.) ልጆች በተለይ ስለወንጌል ጥያቄ እንዲጠይቁ ማበረታታት ይገባል። ሁልጊዜ መልሶችን ላናውቀ እንችላለን፣ ነገር ግን በአንድነት መማር እንችላለን።

የወንጌል ውይይቶችን በቤታችን እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

### ከቤተሰብ ጋር መፀለይ

ከቤተሰቦቻችን ጋር ስንፀልይ፣ ልናስተምራቸው እንችላለን። ተስፋችንን፣ ጭንቀታችንን እና እንከን የሌለበትን ሕይወታችንን ማስረዳት እንችላለን። ለቤተሰብ አባላትና ለሌሎች ስንፀልይ፣ ፍቅርን ማስተማርና ስለችግራቸውም ሊሰማን እንችላለን። የሰማዩ አባታችንን ስለበረከቱ ስናመሰግን፣ ልጆች ስለራሳቸው በረከቶች ደስ መሰኘት ይችላሉ። ከሰማዩ አባታችን ጋር መገናኘት እንደጀመርን፣ ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነትና ስለ እርሱ የሚሰማንን ፍቀር እናስተምራለን።

### “የማስተማሪያ አጋጣሚዎችን” ተጠቀሙባቸው

ዘወትር ወንጌልን በቤት ማስተማር እንችላለን። በምግብ ጊዜያት፣ ወላጆች እንዴት የዕለት ሁናቴ ከወንጌል መሰረተ ሃሳቦች ጋር እንደሚዛመድ ማሳየት ይችላሉ። ታሪኮችን ለትናንሽ ልጆች በመኝታ ጊዜ ከመፅሐፈ ሞርሞን፣ ከመፅሐፍ ቅዱስ ወይም ከራሳችን መንፈሳዊ ተሞክሮን መንገር እንችላለን። ከዕለት የቀዱሳን መፅሐፍት ምንባብ ታሪኮችን መንገር እንችላለን። እንደ የየዕለቱ ሁኔታዎች አነሳስ፣ ልጆቻችንን የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን እዲረዱ ማስተማር እንችላለን።

የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች ማስተማሪያ ሌላ ጊዜያት የትኞቹ ናቸው?

ስዕል 32-ሀ፣ ወንጌልና ሌላ ጥሩ መፅሐፍት ለቤተሰብ አባላት በመፅሐፍ መደርደሪያ ውስጥ እዲገኙ ማድረግ ይችላሉ።

32-ሀ፣ ወንጌልና ሌላ ጥሩ መፅሐፍት ለቤተሰብ አባላት
በመደርደሪያ ላይ እንዲዘጋጅ ማድረግ ይቻላል።



32-U

### ያለማቋረጥ ቅዱሳን መፅሐፍትን ያጥኑ

እኛ ሴቶች ቅዱሳን መፅሐፍትን እንድናጠና ተነግሮናል፣ "የኋለኛው ቀን ቅዱሳን እህቶች ሁሉ መደበኛ የቅዱሳን መጽሐፍትን እንዲያነቡ በውስጣቸው ያለውን ዘለዓለማዊውን እውነታ በልባቸው እንዲያገናዝቡ እንወዳለን።" (Bruce R. McConkie, "Drink from the Fountain," *Ensign*, Apr. 1975, p. 70.) አግባብነት ያለውን ምሳሌ ስናኖር፤ ልጆቻችንን ቅዱሳን መፅሐፍትን እንዲያነቡ ማስተማር ቀላል ይሆንልናል።

መደርደሪያ ወይም በቤት የመፅሐፍ መደርደሪያ በቤት ውስጥ የወንጌል ዕቃዎችን መያዝ ይችላል። መፅሐፍት፤ ምስሎች፤ የካሴት ቴፖችና ማጫወቻዎች፤ እና ሌላ ዕቃዎች ለሙሉ ቤተሰብ እዚያ ሊጠበቁ ይችላሉ። መደበኛ የቅዱሳን መጽሐፍትና *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች* ወይም ቴፖች በመፅሐፍት ቤታችን ውስጥ የሚገኙ መሰረታዊ መገልገያዎች መሆን አለባቸው። ከተቻለ፤ ለእያንዳንዱ ልጅ የመፅሐፈ ሞርሞንና መፅሐፍ ቅዱስን ልንገዛላቸው ይገባናል። ከዚያም ከእነርሱ ጋር እነዚህን መፅሐፍት የምናጠናበትን የተለየ ጊዜ ማቀድ አለብን። እኛ ከእነርሱ ጋር ካልሰራንና ምሳሌ ካልሆንናቸው ልጆቻችን ያጠናሉ ብለን መገመት አንችልም።

በግል ቅዱሳን መፅሀፍትን ለማጥናት መንገዶችን የሚዘረዝረውን የተለጠፈ ማስታወቂያን ያሳዩ። ወይም እነርሱ እንደ ተወያዩበት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፏቸው።

ቅዱሳን መፅሐፍትን ለማጥናት ብዙ መንገዶች አሉ። በግል ወይም በቤተሰብ ማጥናት እንችላለን። ለብቻ ቅዱሳን መፅሐፍትን ማጥኛ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ቅዱሳን መፃህፍትን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያንብቡ። በየቀኑ አንድ ወይም የበለጠ ምዕራፎችን ለማንበብ ይሞክሩ ወይም በየቀኑ ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች ያንብቡ።
2. ቅዱሳን መፃህፍትን በርዕስ (እንደ "ፀሎት" ወይም "ታዛዥነት" የመሳሰሉትን) ያጥኑ። ስለዚያ ርዕስ ማንኛውንም የተጠቀሱ መፃሕፍትን ይፈልጉ።
3. ለችግሮች መፍትሔዎችን ለመፈለግ ቅዱሳን መጽሐፍትን ያጥኑ።
4. መንፈስን የሚያነሳሱ የቅዱሳን መጽሐፍትን ዝርዝር ያዘጋጁ።
5. በመደበኛ የጥናት ዕቅድ የቅዱሳን መፃሕፍትን ማውጫ ይጠቀሙ።

የክፍል አባላት በግል ቅዱሳን መፃሕፍትን የሚያጠኑበት ሌላ መንገዶችን ሃሳብ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

ቤተሰቦች ቅዱሳን መፅሐፍትን ማጥናት የሚችሉበትን መንገዶች በተለጠፈ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ዘርዝረው ያሳዩ። ወይም እንድተወያዩበት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፏቸው።

ስዕል 32-ለ፤ እናት ከቅዱሳን መጻሕፍት ለልጆቿ ስታነብ ያሳያል፤ እናም 32-ሐ፤ ቤተሰብ መፅሐፈ ሞርሞንን ሲያነቡ ያሳያል።

ቅዱሳን መፅሐፍትን በቤተሰብ ማንበብ እንችላለን

1. ጠዋት ጠዋት አባት ለሥራ እና ልጆች ለትምህርት ከመሄዳቸው በፊት አሥራ አምስት ደቂቃ መድቡ።
2. በምሽት ልጆች ወደ መኝታቸው ከመሄዳቸው በፊት አጭር የጥናት ስብሰባ ማድረግ።
3. ከቅዱሳን መፅሐፍት ታሪኮችን ለወጣት ልጆች ያዘጋጁ እናም ይንገሯቸው።

32-ለ፤ እናት ከቅዱሳን መፅሐፍት ለልጆቿ ስታነብ።



32-ለ



4. የቅዱሳን መፃሕፍት ጥቅሶችን ይምረጡ እና በካርድ ላይ ይፃፏቸው። ካርዱን በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወይም ሁሉም ሰው ማየት በሚችልበት ቦታ በግድግዳ ላይ ይለጥፉ። በቃል እንዲያጠኗቸው የቤተሰብ አባላትን ያበረታቱ።
5. መሰረተ ሃሳቡን ለማስተማር ቅዱሳን መፅሐፍትን ይምረጡ። ከዚያም በትምህርት መልክ የተሰጠውን መሰረተ ሃሳብ እንዴት እንደሚተገብሩ ይወስኑ። ምሳሌዎች፣ ማቴዎስ 25፥31–40 አንብቡ፤ ከዚያም በኋላ ችግረኛ ቤተሰብን ይርዱ። ያዕቆብ 1፥27 ወይም ገላቲያ 6፥2፤ አንብቡ፤ ከዚያም አረጋዊን ሰው እርዱ።
6. ባለፈው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የቀረበው ንግግር ፅሑፍ ካለ ያንብቡ። በወንድሞች የቀረቡትን ሃሳቦች በተግባር ያሳዩ።
7. ከተቻለ ጥቅሶችን ከካሴት ቴፖች ያዳምጡ።

ምንም ዓይነት ዕቀድ ብንከተልም፤ ሁልጊዜ ቅዱሳን መፅሐፍትን በፀሎት መጀመር አለብን። የሰማዩ አባታችንን ለመመሪያና ለማስተዋል መጠየቅ አለብን። የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን በህይወታችን ውስጥ ለመተግበር ስላነበብነው ማሰብ አለብን።

ጳጳስ ኤች ብሩክ ፒተርሰን እንደሚሉት፣

“ማንኛውም ቤተሰብ ከዚህ ቤተክርስቲያን በየቀኑ ጊዜ ወስደው ከቅዱሳን መፅሐፍት የማያነቡ መኖር የለባቸውም. . . . መኖር አይገባቸውም . . .፤ እያንዳንዱ ቤተሰብ ይህን በራሱ መንገድ ማድረግ ይችላል።” (“Helps for Parents,” *Ensign,* May 1975, pp. 53–54.)

እንደ ቤተሰብ ቅዱሳን መፃሕፍትን ማጥናት ለምን አስፈላጊ ሆነ? ከክፍል አባላት ቅዱሳን መፃሕፍትን (በቻልተኝነት) ሳይሆን በሚገባ *የምታነብን* ይምረጡ። ዘዴዋን እንድታስረዳ ያድርጉአት። ስለ ቅዱሳን መፃሕፍት ያላትንም ስሜት ደግሞ እንድትገልጽ ይጠይቁአት።

## የቤተሰብ የቤት ምሽትን በመደበኛነት መቀጠል

የቤተሰብ የቤት ምሽት ልጆቻችንን የምናስተምርበት አንዱ ጥሩ ጊዜ ነው። (እያንዳንዱ ሰኞ ምሽት ለዚህ ተለይቶ ተቀምጧል።) ቤተሰብ የቤተሰብ የቤት ምሽት መምሪያ መፅሐፍ ካለ መጠቀም አለባቸው። የመምሪያ መፅሐፉ ከሌለ ቅዱሳን መሐፍትና *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን* ማጥናት፣ የወንጌል ቅጂ ድምፆችን ማዳመጥ፤ ወይም ስለ ቤተክርስቲያን የሚሰማንን ማካፈል አለብን። ልጆች በምሽቱ እንዲደሰቱ አስደሳች እና የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር ይረዳል። ከዚያም በበለጠ መሳተፍ ይፈልጋሉ። የቤተሰብ የቤት ምሽት ልጆች በማይገባቸው ስብከት የተሞላ መሆን የለበትም። ለማንኛውም ሰው በቀልድ መልክ መሆን አለበት።

## ለልጆቻችን ምስክርነትን መስጠት

በምግብ ሰዓት፤ ቅዱሳን መፅሐፍትን በምናጠናበት ጊዜ፤ በቤተሰብ የቤት ምሽት ወይም በወንጌል ውይይቶች ለልጆቻችን ምስክርነታችንን መስጠት አለብን። እንደሰሙንና በራሳቸው ዓይን ወንጌልን እንደምንጠብቅ ሲያዩን ለወንጌል ምስክርነታቸውን ያሳድጋሉ።

ዘዳግም 11፥19 ያንብቡ።

የክፍል አባላትን ወንጌልን ለልጆቻቸው ለማስተማር ያላቸውን ተሞክሮ እንዲያካፍሉ ያድርጓቸው።

32-ሐ፤ ቤተሰብ መፅሐፈ ሞርሞንን ሲያጠና።

### ወንጌልን ማጥናት በረከቶችን ያስገኛል

ወንጌልን ስናጠና፣ ከቤተሰቦቻችን ጋር እንባረካለን። ምስክርነታችንና ቤታችንም በጥንካሬ ያድጋል። ለችግሮቻችንም መፍትሔ እናገኛለን። ከክርስቶስ እና ከሰማዩ አባታችን ጋር በቀርበት ለመኖር የሞከርን ስለሆነ ደስተኞች እንሆናለን፣ እናም ላቀ ያለ ሰላምም ይኖረናል።

በጠዋት በማለዳ የቅዱሳን መፅሐፍትን ጥናት የምታካሂደው የቤተሰቡ እናት ስለበረከቶቻቸው ትናገራለች፣

"ከዚህ ከጠዋት ማለዳ ፕሮግራም ብዙ ጥቀሞች አሉ፥ ቅዱሳን መፅሐፍትን እና ትርጉማቸውን በሕይወታችን ውስጥ በተሻለ መረዳት፣ ቀኑን በህይወታችን ውስጥ በበለጠ በተደራጀ ሁኔታ በመጀመር . . .፣ የቤተሰብ ቁርስን በአንድነት መሳተፍ።

"ልጆቻችን ለራሳቸው፣ ለቤተሰባችን፣ እና ስለ ራሳቸው ዓለም ደህንነት የበለጠ በመተማመን በደስታ ወደ ትምህርት ቤት እንደሚሄዱ እርግጠኛ ነኝ።" (Geri Brinley, "Getting a Head Start on the Day," *Ensign,* Apr. 1977, p. 8.)

ቄስ ብሩስ አር ማኮንኪ ከእንደዚያ ዓይነቱ ጥናት ሌሎች በረከቶች እንደሚመጡ ተናገሩ፥

"በዚህ ሕይወታችን ሰላምና ደስታ እና ፍሰሃን እናም በመጪው ዓለም የዘለዓለማዊ ሕይወት ወራሾች ለመሆን እንፈልጋለን። ሰዎች ሊወርሱት የሚችሉት ሁለት ታላላቅ በረከቶች እነዚህ ናቸው። የዘለዓለማዊ ሕይወትን ቃላቶች እዚህና አሁን በማንበብና በመማር እናም ትዕዛዛትን በመጠበቅ ልናገኛቸው እንችላለን።" ("Drink from the Fountain," *Ensign,* Apr. 1975, p. 70.)

#### ሙከራ

በሁለቱም በግልና ከቤተሰብ ጋር ወንጌልን ለማጥናት ያቅዱ። በየዕለቱ የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን ለልጆችዎ ለማስረዳት አጋጣሚን ይፈልጉ።

### ተጨማሪ ጥቅሶች

ሮሜ 15፥4 (ቅዱሳን መጻሕፍት ተስፋን ይሰጣሉ)
2ኛ ጢሞቲዎስ 3፥14–17 (ቅዱሳን መጽሐፍት ለፍፁምነት ሊመሩን ነው)
2ኛ ኔፊ 4፥15 (ቅዱሳን መፃሕፍት ለትምህርትና ለትርፍ)
ት እና ቃ 1፥37 (ቅዱሳን መፅሐፍት እውነት እና ታማኞች ናቸው)

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ የተዘረዘሩትን ተጨማሪ ጥቅሶች ያንብቡ።
2. ወንጌልን በግል ለማጥናት በፖስተር ላይ ዝርዝር መንገዶቹን ያዘጋጁ፣ ወይም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ።
3. እንደቤተሰቦች ወንጌልን ለማጥናት በፖስተር ላይ ዝርዝር መንገዶችን ያዘጋጁ፣ ወይም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ።
4. የክፍሉ አባላት በዚህ ትምህርት የተጠቀሰውን ታሪኮችና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# ለማስተማር መዘጋጀት

ትምህርት 33

የዚህ ትምህርት ዓላማ ወንጌልን በብቃት ተዘጋጅተን ለማስተማር እንድንችል እንዲረዳን ነው።

## እርስ በርስ መማማር

ጌታ የቤተክርስቲያኑን አባላት እርስ በርስ እንዲማማሩ አዟል።

የክፍሉ አባል ትምህርት እና ቃል ኪዳን 80፥77–78 እንዲያነቡ ያድርጉ። ማንን ማስተማር አለብን?

ቤተሰባችንን፣ ጓደኞቻችንን፣ ጎረቤቶቻችንን፣ የሥራ ጓደኞቻችንን፣ የትምህርት ቤት ጓደኞቻችንን ማስተማር እንችላለን። በተደራጁ ክፍሎች የቤተክርስቲያን አባላትን ማስተማር እንችላለን። አባል ያልሆኑትንም ደግሞ ማስተማር እንችላለን።

33-ሀ፣ ስዕላዊ መግለጫ አሳዩ። ይህች እናት ሴት ልጇን የጫማ አስተሳሰርን ስታስተምር።

ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ፣ ጌታ ልጆቻችንን ወንጌልን እንድናስተምር ነግሮናል። በቤተሰብ የቤት ምሽት ወቅትና በሌላ ጊዜያት ልናስተምር እንችላለን። በተለይ እናት ልጆቿን በቤት ውስጥ ለማስተማር ብዙ አጋጣሚዎች አሏት።

የክፍል አባላት ልጆቻቸውን በማስተማር ስላላቸው ልምዶች እንዲናገሩ ያድርጉኣቸው።

ቄስ ቦይድ ኬ ፓከር እንዳሉት፥ "የምናደርጋቸው ብዙ ነገሮች ማስተማር ነው። ህፃናቶች ጫማቸውን እንዴት እንድሚያሥሩ ማሳየት፣ . . . ሴት ልጆችን በአዲስ የምግብ አሰራር መርዳት፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ንግግር ማድረግ፣ ምስክርነት መስጠት፣ የመሪዎች ስብሰባ መምራት፣ እና፣ በእርግጥ፣ ክፍልን ማስተማር—ይህ ሁሉ ትምህርት ነው፣ እናም ባለማቋረጥ እያከናወንን ነው. . . .

"በምንሰብክበት ጊዜ ወይም በምንናገርበት ጊዜ ወይም በስብሰባዎች መልስ በምንመለስበት ጊዜ እያስተማርን ነው።" (*Teach Ye Diligently,* pp. 2–3.)

በቤተክርስቲያን ውስጥ በተደራጁ ክፍሎች ብዙ የማስተማር ዕድሎች አሉ። ቄስ ቦይድ ኬ ፓኬር እንዳሳሰቡን፥

"እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባል የሕይወት ዘመኑን በሙሉ ለበጎ ምግባር ያስተምራል።

"በሁሉም የቤተክርስቲያኑ ድርጅት ውስጥ የሚያገለግሉ አስተማሪዎች አሉን. . . .

"ቤተክርስቲያኑ በቀጣይነት ወደፊት የሚራመደው በተከናወነው የማስተማር ኃይል ነው። ማስተማሩ በሚገባ ካልተከናወነ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ይሰናከላል።" (*Teach Ye Diligently,* pp. 2–3.)

አንዳንድ ጊዜ የምናስተምረው በክፍል ብቻ አይደለም። በክፍል ፋንታ አብረን በምንነጋገርበት ጊዜ ሊደረግ ይችላል። የሚቀጥለው ታሪክ የዚህ ምሳሌ ነው፥



“ጳጳስ ፍሬድ ካሩል እኔ በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የ14 ዓመት ዕድሜ ዲያቆን ሆኜ ቤተሰቦቼ ወደ እርሳቸው ዋርድ ሲዘዋወሩ ከእኔ ጋር ተዋወቁ። በግምት እኚህ ታላቅ ሰው በቀጥታ ያነጋገሩኝ ከሃምሳ ባልበለጡ ቃላት ነው፣ ከነዚህ ከፊሉ በአዕምሮዬ ውስጥ በማይፋቀ ሁኔታ ተቀርፀዋል። ይህ ግሩም ጳጳስ አንድ ቀን በፀጥታና በግል ስለሰጡኝ በእነዚያ ሃያ አምስቱ አስፈላጊ ቃላቶች በእኔ ላይ ስላላቸው አስገራሚው ተፅዕኖ እርግጠኛ ነኝ፣ አንተ በቤተክርስቲያናችን ስብሰባዎች እንዴት በአክብሮት የተሞላህ እንደሆንክ አገናዝብ ነበር። ሌሎች ልጆች እንዲከተሉት መልካም አርዓያ ሆነሃል።’ አሉኝ።

“ትንሽ ቃላቶች ናቸው፣ ነገር ግን፣ እንዴት ኃያል ናቸው! ለእኔ ከዚያን ጊዜ ከነበሩኝ ከብዙ መቶዎች የሥራ ምድብ ይልቅ የበለጠ በአዕምሮዬ ላይ የቀሩ ውጤቶች ናቸው። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ራሴን እንደልዩ አክባሪ አድርጌ አልገምትም ነበር። ጳጳሱ ካሩል ለክብር ያለኝን የመቆጠብ ፍርሃቴን በተሳሳተ መንገድ እንደወሰዱት አልጠራጠርም ያ ግን አያሳስብም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለ አክብሮት ትርጉም በህይወቴ ውስጥ መደነቅ ጀመርኩ። ወዲያው አክባሪ መሆን ጀመርኩ። ያም ሆነ ይህ ጳጳስ ካሩል አክባሪ እንደሆንኩ ቢያስቡም እንኳ በእርግጥም ነበርኩ! በጳጳሱ ካሩል እንዳስብ ስላደረጉኝ በውስጤ ማደግ የጀመረው ሃሳብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በማደግ በህይወቴ ውስጥ መሪ ተፅዕኖ ሆኗል።” (Lynn F. Stoddard, “The Magic Touch,” *Instructor,* Sept. 1970, pp. 326–27.)

የተደራጁ የክፍል አስተማሪዎች የክፍል አባላትን ለማግባባትና ለመምራት ብዙ ዕድሎች አላቸው። ጠንክረው ከሰሩ፣ የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ለማስተማር ጥሩ መንገዶች ያገኛሉ። ቄስ ቶማስ ኤስ ሞንሰን በእንደዚያ ያሉ አስተማሪዎች ተፅዕኖ ስር ስለመሆን ይናገራሉ፥

“በሰንበት ትምህርት ክፍላችን፣ ስለ ዓለም ፍጥረት፣ ስለአዳም ውድቀት፣ ስለ ኢየሱስ የመስዋዕትነት ክፍያ በተመለከተ አስተምራናለች። እንደ ክብር እንግዶች ሙሴን፣ ኢያሱን፣ ጴጥሮስን፣ ቶማስን፣ ጳውሎስን፣ እና ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ክፍሏ አምጥታለች። ባናያቸውም እንኳን፣ እንድናፈቅራቸው፣ እንድናከብራቸው፣ እናም እንድንከተላቸው ተምረናል።

“አንድ እሁድ ጥዋት በድንገት የክፍሉ አባል የሆኑት እናት መሞታቸውን እንዳስታወቀችን እንደዚያ ቀን የትምህርት አሰጣጧ የበለጠ ዘለዓለማዊ ሃይል አልነበረውም። በዚያን ጧት ቢሊ ቀርቶብን ነበር፣ ነገር ግን የቀረበትን ምክንያት አላወቅንም ነበር። ትምህርቱ ከመቀበል ይልቅ መስጠት ታላቅ በረከት ነው።’ በሚለው ርዕስ ላይ ያተኮረ ነበር።

“በትምህርቱ መሐከል፣ አስተማሪያችን መምሪያውን መፅሐፍ ዘጋች እና ለእግዚአብሔር ክብር አይናችንን፣ ጆሮአችንን፣ እና ልባችንን ከፈተን። ‘በክፍላችን ለግብዣ መዋጮ ምን ያህል ገንዘብ አለን?’ ስትል ጠየቀች።

“ . . . ‘አራት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም።’

“ከዚያም በፍፁም ጨዋነት አስተያየትዋን ስትሰጥ፥ ‘የቢሊ ቤተሰብ በድህነት እና በትካዜ ተጐድተዋል። ዛሬ ጧት የቤተሰቡን አባላት መጎብኘት እና የመዋጮ ገንዘባችሁን መስጠት ምን ይሰማችኋል?

33-ሀ ይህች እናት ሴት ልጇን የጫማ አስተሳሰርን ስታስተምር።

“ለዘወትር አነዚያን ሶስቱን ትንንሽ ቡድን የከተማ ረድፎችን በመራመድ በቢሊ ቤት በመግባት፣ እርሱን፣ ወንድሙን፣ እህቱን፣ እና አባቱን ሰላምታ የጠየቁትን አስታውሳለሁ። ትዝ ከሚለኝ በዚያን ጊዜ እናቱ ቤት አልነበሩም። ውድ የሆነ የፓርቲያችን የመዋጮ ገንዘብን የያዘ ነጩ ፖስታ በለስላሳ የአስተማሪያችን እጅ ወደ ችግረኛው ልበ ሰባራ አባት እጅ ሲተላለፍ በሁሉም ዓይን የተንፀባረቀውን እንባ ሁልጊዜ አስታውሳለሁ። ወደ ቤተክርስቲያኑ መንገዳችን በመያያዝ ከሞላ ጎደል በፈጣን እርምጃ ሄድን። ከዚህ ቀደም ከነበረን ይልቅ ልባችንን ቀለለን፣ ደስታችን የበለጠውን ሞላ፣ አስተውሎአችንም የበለጠ ጥልቀ ሆነ። በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላች በምህረት ወንዶችና ሴቶች ልጆቿን የመለኮታዊ እውነትን ዘለዓለማዊ ትምህርትን አስተምራለች፥ መስጠት ከመቀበል የበለጠ በረከት ነው።’ ” (“Only a Teacher,” *Ensign,* May 1973, p. 29.)

እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባል አስተማሪ ነው። ሁላችንም ሌሎችን ወንጌልን በቃላችንና በተግባራችን እናስተምራለን። በተጠመቅን ጊዜ፣ “በማንኛውም ጊዜና፣ በሁሉም ነገሮች፣ እናም በምንገኝበተ በሁሉም ሥፍራዎች፣ እስከ ዕለተ ሞታችን እንኳን ለአምላክ ምስክሮች በመሆን ለመቆም ቃል ገብተናል” (ሞዛያ 18፥9)። ከተጠመቅን በኋላ፣ ወንጌልን ለጎረቤቶቻችንና በምድር ላይ ለሚገኙት ሕዝቦች ሁሉ ማዳረስ ይገባናል። ልጆቻችንንና ሌሎች የቤተክርስቲያናችንን አባላትም ማስተማር ይገባናል።

## ጥናት እና ዝግጅት

ስዕላዊ መግለጫ 33-ለ አሳዩ አንዲት እህት ከቅዱሳን መጻሕፍት ስታስተምር።

ጥሩ አስተማሪዎች ለመሆን፣ በሚገባ መዘጋጀት ይገባናል። ሁላችንም የማስተማር ችሎታ አለን፣ ነገር ግን እያንዳንዳችን አሁንም ማሻሻል እንችላለን። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ እንዳሉት፥ “እርሱ ወይም እርሷ የማያውቁትን ነገሮች ማስተማር የሚችል መምህር አይኖርም። የማያየውንና የማይሰማውን ነገር ማስተማር የሚችል መምህር አይኖርም።” (*Treasures of Life,* p. 476.)

እርስዎ የሚከተሉትን ጥቀሶች ሲያነቡ የክፍሉን አባላት ስለ ትምህርቱ ዝግጅት ዛሳብ እንዲሰሙ ይጠይቋቸው፥

“የትምህርትዎ ዕቅድ የሚከናወንበትን የተወሰኑ ጊዜንና ቦታን ይምረጡ። አስፈላጊ መሳሪያዎችን፣ ቅዱሳን መፃህፍትን፣ የትምህርት መምሪያ መፅሃፍን፣ የተጠቀሱ መፅሐፍትን፣ ወረቀቶች፣ እርሳስ፣ ተዘጋጅቶ ይቀረብ. . . .

“እቅዱን . . . [በፀሎት] ይጀምሩ። ይህ የእርሱ [የጌታ] ወንጌል ነው፣ እርስዎ የእርሱን ልጆች የሚያስተምሩ መምህሩ ነዎት። መልዕክቱን እንዴት እንዲያስተምሩ እንደሚፈልግ ጌታን ይጠይቁ . . . ልዩ ፍላጎት ከተሰማዎ የጌታን መንፈስ ለማቀረብ ፀሎት ከፆም ጋር መጎዳኘት አለበት።” (*Teacher Development Program,* Basic Course, p. 133.)

ትምህርትን ለማዘጋጀት የሚፈልጉትን መሳሪያዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ። በሚዘጋጁበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብዎት?

የሚከተሉት ደረጃዎች ትምህርትን ለክፍል ለማዘጋጀት የቀረቡ ሀሳቦች ናቸው፥

1. ለትምህርቱ ግብ (ዓላማ) ያስቀምጡ።
   በአብዛኛው የቤተክርስቲያኑ መምሪያ መፅሐፍት፣ ይህ ግብ በትምህርቱ መግቢያ ላይ

33-ለ አንዲት እህት ከቅዱሳን መጽሐፍት ስታስተምር።



ተፅፏል። ግቡ የክፍሉ አባላት እንዲማሩ፣ እንዲያስታውሱ፣ እንዲያከናውኑ የሚፈልጉት አብይ ጉዳይ ነው። ትምህርቱን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ግብዎን ይፃፉና ያስቡበት።

2. የትምህርቱን መሳሪያ ይወቁ።
   የትምህርቱን መሳሪያ፣ ሁለቱንም ማለት የመምሪያ መፅሀፍና ቅዱሳን መፃህፍትን አስቀድሞ በሚገባ በማጥናትና የትኞቹ ነጥቦች ይበልጥ አስፈላጊ እንደሆኑ ይወስኑ። ዘወትር በፀሎት ይዘጋጁ።

3. ስዕላዊ መግለጫን በምርምርና በጥናት ያጠራቅሙ።
   የክፍሉ አባላት ማየት የሚችሉትን ነገሮች፣ በትምህርቱ ውስጥ ፍላጎትን ለመፍጠር ይጠቀሙ። ቁሳቁሶች፣ ሰንጠረዦች፣ ሥዕሎች፣ ወይም ሌላ ዕቃዎች ለትምህርት የሚረዱ ሥዕላ ሥዕሎች የማሳያ መረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በሁሉም ዕድሜ ያሉትን ሰዎች ለማስተማር በትምህርቱ ውስጥ ፍላጎትን መፍጠር አስፈላጊ ነው።

4. ለትምህርቱ መርጃዎችን እና ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።
   መሳሪያዎችን በትምህርት ውስጥ በሚያገለግሉበት አይነት ቀደም ተከተል ያስተካክሉ። አስቀድሞ ቀደም ተከተል ማስያዝ ግራ መጋባትን ለማስወገድ ይረዳል።

## የምናስተምራቸውን መውደድ

ቄስ ቦይድ ኬ ፓከር እንደሚሉት፡ “ጥሩ መምህር ትምህርቱን አስቀድሞ ያጠናል። ግሩም መምህር ደግሞ ተማሪዎቹን ያጠናል. . . . በቁምነገርና በዕቀድ ያጠናቸዋል . . . የተማሪዎችዎ ገፅታና ስሜት፣ በልብዎ ውስጥ ሊፈጠሩ ይችላሉ . . . እንደ መነሳሻ የሃሳብ ስሜት ሆኖ በጎቹን እንዲመግቡ . . . የጌታን ሥራ እንዲሰሩ የሚያስገድድዎት ፍቅር ነው።” (“Study Your Students,” *Instructor,* Jan. 1963, p. 17.)

የሚወደዱ ተማሪዎች የበለጠ በራሳቸው መተማመን ይኖራቸዋል። ራሳቸውን ለማሻሻል ይመኛሉ። የተወደዱ ተማሪዎች ሌሎችን እንዴት እንደሚወዱ ይማራሉ። ተማሪዎቻቸውን የሚወዱ አስተማሪዎች ከጌታ ጥሩ የሚያነሳሳ መንፈስን ያገኛሉ። የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት በበለጠ ይረዳሉ።

“በባህላዊ ሥነ ጥበብ ማስተማር ያልሰለጠነ መምህር እንኳን ያንን ተማሪ የሚወድና የሚያከብር ከሆነ እናም ግላዊ ፍላጎቱን የሚያሳየው ከሆነ በተማሪው ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል።

“አሰልቺ እና ምንም ደስ የማያሰኝ ነው ብዬ የምገምተው መምህር አንድ ቀን አግኝቶኝ እኔ እወደዋለሁ ብሎ ያሰበውን አንድ መፅሐፍ ሲሰጠኝ አስታውሳለሁ። እኔ በተለይ መፅሐፉን አልወደድኩም ነበር . . . ነገር ግን በዚያን ቀን በእኔ ላይ እንደዚያ ያለ ፍላጎት ላለው መምህር አዲስ አድናቆትን አተረፍኩ፣ እናም ከዚያም በኋላ እኔን ማስተማር ቻለ።” (William E. Berrett, “Teaching: An Extension of Your Personality,” *Ensign,* Apr. 1973, p. 61.)

ለክፍሉ አባላት እንደምንወዳቸው እንዴት ልናሳያቸው እንችላለን? በክፍል ውስጥ? ከክፍል ውጭ?

## ለመንፈስ መፀለይ

ስዕላዊ መግለጫ 33-ሐ አሳዩ፣ መምህርቷ ቅዱሳን መፃሕፍትን በሚያጠኑበት ጊዜ መመሪያ ለማግኘት ሲፀልዩ።

33-ሐ መምህርቷ ቅዱሳን መጽሐፍትን በሚያጠኑበት ጊዜ መመሪያ ለማግኘት ሲፀልዩ።



ፕሬዚዳንት ብርግም ያንግ እንዳሉት፣ "ከጥሩ መጽሐፍት፤ ወዘተ፤ ጥበብን ለማግኘት ማንኛውንም ጥረት ካደረግን በኋላ አሁንም ቀሪ የተከፈተ ምንጭ አለ፤ ' "ማንም ጥበብ ቢጎድለው እግዚአብሔርን ይጠይቅ።' " (*Discourses of Brigham Young,* p. 261.)

የማስተማር ተሰጥዎ የሚኖረን ከሆነ፤ ለሰማዩ አባታችን መፀለይ ይገባናል። ትምህርቱን ለማዘጋጀት ይረዳናል። ተማሪዎችን እንድናውቃቸውና እንድንወዳቸው ይረዳናል። እርዳታውን የምንሻ ከሆነ፤ በምናስተምርበት ጊዜ ከእኛ ጋር ይሆናል።

**ማጠቃለያ**

ወንጌልን ለልጆቻችን፤ ሌሎች የቤተክርስቲያኑ አባላት፤ እና አባል ላልሆኑትም በዓለም ውስጥ ላሉ ጎረቤቶቻችን ለማስተማር ኃላፊነት አለብን።

"ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ እንደተናገሩት፣ 'በዓለም ውስጥ የሰው ልጅን ነፍስ ከማሰልጠን በላይ የሆነ ታላቅ ኃላፊነት የለም።' በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ለሁሉም ወላጆችና አስተማሪዎች ታላቁ የግል መጋቢነትን ማስተማርና ማሰልጠን ነው።" (Vaughn J. Featherstone, "The Impact Teacher," *Ensign,* Nov. 1976, p. 103.)

ጌታ በውጤታማነት ለማስተማር እንድናዘጋጅ ይጠብቅብናል። ዝግጅት ማለት ማጥናት፤ መፀለይ እና በመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ማስተማር ነው።

**ሙከራ**

በዚህ ሳምንት የወንጌል መሰረተ ሃሳቦችን ለማስተማር ይምረጡ። የዕለት አጋጣሚዎችን ለማስተማር ይፀልዩ እና ያግኙ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ የጥረትዎን ደረጃ ያውጡ። የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብ ይጠቅማል።

**ተጨማሪ ጥቅሶች**

ዘዳግም 6፥5–6 (በሁሉም ጊዜያት ያስተምሩ)
ሞዛያ 4፥11–15 (ለልጆች ፍቀርን ያስተምሩ)
ት እና ቃ 42፥14 (በመንፈስ ብቻ ያስተምሩ)
ት እና ቃ 68፥25–28 (ልጆችን ለማስተማር ይዘዙ)
ሙሴ 6፥57 (ለልጆች ንሰሐን ለማስተማር ይዘዙ)

---

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፣

1. የክፍሉ አባላት ቅዱሳን መጻህፍትን ወደ ክፍል ይዘው እንዲመጡ ያሳስቡ።
2. ብዛት ያላቸውን የክፍሉን አባላት ልጆቻቸውን በማስተማር ስለልምዶቻቸው እንዲናገሩ ይመድቧቸው።
3. የክፍሉን አባላት በዚህ ትምህርት ታሪኮችን እና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# ከቅዱሳን መጽሐፍት ማስተማር

ትምህርት 34

የዚህ ትምህርት ዓላማ ከቅዱሳን መጽሐፍት ለማስተማር እንድንዘጋጅ ለመርዳት ነው።

## መግቢያ

ስዕላዊ መግለጫ 34-ሀ፣ አሳዬ ይህች መምህርት ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የተማረችውን ነገሮች ደግሞ ማገናዘብ እንደሚገባት ያሳያል፣ እናም ተዕይንት 34-ለ፣ ይህች እህት ከቅዱሳን መፃሕፍት ታስተምራለች፣ እናም ልጆችም በክፍሉ ውስጥ ሆኖ ለማመሳከር የራሳቸውን ቅዱሳን መጽሐፍትን መያዛቸውን ያሳያል።

ፕሬዚዳንት ጀ ሩበን ክለርክ ጁኒየር፣ በአንድ ወቅት ለቤተክርስቲያኑ መምህራን እንደተናገሩት፥ "ዛሬ . . . የእናንተ አስፈላጊው ተግባር፣ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ማስተማር ነው. . . . ይህን ወንጌል የምታስተምሩት እንደ ማስተማሪያ ምንጫችሁና ሥልጣኖቻችሁ በማድረግ መደበኛውን የቤተክርስቲያኑ ሥራዎች (ቅዱሳን መጽሐፍት) እና ሕዝቡን እንዲመሩ በዚህ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች በተናገሩት ቃል መሰረት ነው።" ("The Charted Course in Education" [an address given 8 Aug. 1983 to the Church seminary and institute leaders], pp. 10–11.)

በምናስተምርበት ጊዜ ያለን ታላቅ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ቅዱሳን መፅሐፍትን ማወቅና መጠቀም ነው።

ጌታ ቅዱሳን መጽሐፍትን የማወቀና የማስተማርን አስፈላጊነት አስተምሯል። ከትንሳኤው በኋላ ለኔፋይቶች፣ ያለው፣ "አዎን፣ እኔ የምሰጣችሁ ትዕዛዝ እነዚህን ነገሮች (ቅዱሳን መፃሕፍትን) በትጋት እንድትመረምሩ ነው" (3ኛ ኔፊ 23፥1)። ደግሞም ለሌሎች ወንጌልን እንዲያስተምሩ አዞአቸዋል። (3ኛ ኔፊ 23፥14 ይመልከቱ።) በትምህርትና ቃልኪዳን በብርታት በመሥራት ቅዱሳን መጽሐፍትን እንድንመራመር አዞናል። እነርሱ ስለእርሱ የሚመሰክሩ ስለሆኑ በታማኝነት ማስተማር አለብን። ቅዱሳን መፅሐፍት ማድረግ ያለብንን ሁሉንም ነገሮች ይዘዋል። (ት እና ቃ 1፥37 ይመልከቱ።)

ከቅዱሳን መጻህፍት በተጨማሪ፣ በአሁኑ ዘመን በሕያው ነብይ አማካይነት የጌታ ቃል አለን። የህያው ነብያት ቃሎች ደግሞ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ይወሰዳሉ። (ት እና ቃ 68፥1–4 ይመልከቱ።) የቤተክርስቲያኑ መምሪያ መፃሐፍት የነብያትን ቃሎችና ሌሎች ቅዱሳን መፃሕፍትን እንድንማር ይረዱናል።

የህያው ነቢይን ቃል ከየት ማግኘት እንችላለን?

34-ሀ፣ ይህች መምህርት ቅዱሳን መፃሕፍትን ማጥናትን ማወቀ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የተማረችውን ነገሮች ደግሞ ማገናዘብ እንደሚገባት ታውቃለች።

34-ለ፣ ይህች እህት ከቅዱሳን መፃሐፍት ስታስተምር፣ እናም ልጆች በክፍል ውስጥ ለማገናዘብ የራሳቸውን ቅዱሳን መጽሐፍት ይዘዋል።





## ቅዱሳን መጽሐፍትን በህይወታችን መተግበር

ሌሂና ቤተሰቡ በተስፋው ምድር በደረሱ ጊዜ፣ ኔፊ ወንድሞቹን ቅዱሳን መጽሐፍትን አስተማረ። ለሰዎቹ ሊገባቸው በሚችለው መንገድም አስተማራቸው። ከእርሱም ሲጠቀስ "ለጥቀማችን እና ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ፣ ቅዱሳን መፃሕፍትን ሁሉ በራሳችን መሰልኳቸው" (1ኛ ኔፊ 19፥23)።

ቅዱሳን መጽሐፍት "በሌሎች አገሮች በጥንት ህዝቦች መካከል የጌታን ሥራዎች" ያስተምሩናል (1ኛ ኔፊ 19፥22) ባለፉት ጊዜያት የተፃፉ ቢሆንም፣ ከእነርሱ ይጠቀሙና ይማሩ ዘንድ ሁሉንም ቅዱሳን መጽሐፍት ለራሱ ሕዝብ በማነፃፀር ተናገረ። (1ኛ ኔፊ 19፥23 ይመልከቱ።) ቅዱሳን መጽሐፍት አሁንም በእኛ ጊዜ ትርጉም ይሰጡናል። ነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ ቅዱሳን መጽሐፍትን የተሟላ ትርጉም እንዲኖራቸው ስለማድረግ አስተምሯል። "ቅዱሳን መጽሐፍትን መርምሩ፣ ነብያትንም ፈልጉና የትኞቹ ክፍሎች ለእናንተ እንደሆኑ ተማሩ" (*Teachings of the Prophet Joseph Smith,* p. 12)።

መልካም መምህራን ቅዱሳን መጽሐፍትን በዘመናዊ ሕይወት ያዛምዳሉ። የወቀቱን ክስተት እንድንረዳ እኛን ለመርዳት ሲሉ ያለፈውን ሁኔታ ይጠቀማሉ።

ስዕል 34-ሐ፣ ኔፊና ሌሂ ከሊያሆና ጋር እንደሆኑ ያሳያል።

የክፍሉ አባል 1ኛ ኔፊ 16፥9–12፣ 15–30 እንዲያነብ ያድርጉ።

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል ከዚህ ታሪክ ጋር በማጣቀስ ከመፅሐፈ ሞርሞን ሲናገሩ፥

"አባቱ ከድንኳኑ ደጃፍ በውጭ በኩል አንድ ነገር አግኝተው በመደሰት ትኩረት ሲሰጡ እንደሰማው ኔፊ አድርጋችሁ ራሳችሁን ማሰብ ትችላላችሁን? እርሱም . . . "ድቡልቡል ኳስ የሆነ መልካም ባለሙያ የሰራው፣" ያልተለመደ ባዕድ ነገር፣ ከጥሩ "መዳብ የተሰራ"፣ እናም ከዚህ ቀደም እንደዚህ ያለን ነገር በፍፁም ማንም ያላየው ነው። (1ኛ ኔፊ 16፥10) . . .

"የዚህን ያልተለመደ ኳስን ሥራ በሚገባ ጥንቃቄ . . . ብትመለከቱ፣ በእምነት እና በትጋት እናም ማዳመጥ መሰረት መሄድ ወደ ለለብዎት መንገድ አቀጣጫ አሰራሩን ያስገነዝብዎታል። (1ኛ ኔፊ 16፥28።) . . . በትኩረት አመለካከት "ለማንበብ ግልጽ የሆነ" የጌታን መንገዶች የሚገልፁ . . . ፅሁፎች ከኳሱ ላይ መኖራቸውን ቢገነዘቡ ምን ያስባሉ? እናም ይህ በቤተሰቡ "እምነትና ትጋት መሰረት" መመሪያው "ከጊዜ ወደ ጊዜ" በጌታ እንደተደረገው ተጨማሪ ጥያቄ ቢቀያየርስ? (1ኛ ኔፊ 16፥29።). . . .

"ኳሱ፣ ወይም ሊያሆናው . . . ሲተረጎም አቀጣጫን የሚያመልክት (ኮምፓስ) ማለት የሆነው . . .በጌታ የተዘጋጀ በተለይም ለሌሂ በምድረበዳ የሚሄድበትን አቀጣጫን ለማሳየት ነው። እያንዳንዳችሁ . . . የዚያን ዓይነት ኳስ እንዲኖራችሁ አትወዱምን? . . . ስለሆነም በስህተት ላይ በምትሆኑበት ጊዜ ትክክለኛውን መንገድና መልዕክቶቻችሁን ለመፃፍ ይጠቀማችኋል፣ በመሆኑም በተሳሳታችሁ ጊዜ ወይም በስህተት መንገድ ላይ በሆናችሁ ጊዜ ሁሉ ታውቃላችሁ?

34-ሐ፣ ኔፊና ሌሂ ከሊያሆና ጋር።



34-ሐ

“ያ፣ እናንተ ሁላችሁም አላችሁ። ጌታ ለሁሉም ሰው . . . በማንኛውም ጊዜ በተሳሳተ መንገድ መሄዱን ሲጀምር የሚናገረውን ህሊና ሰጥቶታል። የሚያዳምጥ ከሆነም ሁልጊዜ ይነግረዋል፣ ነገር ግን ሰዎች፣ በእርግጥ መልዕክቱን አዳምጠው እስከመጨረሻው በጭራሽ እስከ ማይዘግቡ ድረስ ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት ይችላሉ።

“እንደ ኮምፓስ ያለ አንድ ነገር እንደ ሊያሆና ያለ፣ በራሳችሁ ብልሃት እንዳላችሁ ማስታወስ ይገባችኋል። ይህ ለሁሉም ልጅ ተሰጥቷል . . . ሊያሆናውን በእርሱ ሥርዓት የሆነውን ካልተከተለ፣ በመጨረሻም ለእርሱ የሚነገር ድምፅ አይኖረውም። ነገር ግን ሁላችንም በትክክል የሚመራን ነገር እንዳለ ብናስታውስ፣ ህሊና የምንለውን የራሳችን ሊያሆና የሚነግረንን ብንሰማ . . . መርከባችን በተሳሳተ አቀጣጫ አይሄድም።” (In Conference Report, Oct. 1976, pp. 115–17; or *Ensign,* Nov. 1976, pp. 77–79.)

ፕሬዚዳንት ኪምቦል ቅዱሳን መጽሐፍትን በአሁኑ ወቀት ለእኛ እንዴት አዛመዱልን? የታሪኩ የትኛው ክፍል ነው ከእኛ ጋር የማይስማማው?

ቅዱሳን መጽሐፍትን ካወቅን፣ እውነተኛ መሰረተ ሃሳቦችን ከህይወታችን ጋር ማዛመድ እንችላለን። የሚከተሉት ምሳሌዎች አንዲት እናት ልጇቿን እንዴት ከቅዱሳን መፅሐፍት እንዳስተማረች ያሳያል።

በአንድ ምሽት በፀሎት ሰዓት የ4 ዓመቷ አን ፀሎት ማድረግ እንዳልፈለገች አስታወቀች። እናቷ አባበለቻት፣ ነገር ግን አን መፀለይን እምቢ አለች። ከዚያ በኋላ እናቷ ለአን የዳንኤልን ታሪክ ነገረቻት።

የተመደበን የክፍል አባል ዳንኤል 6፥1–23 እንዲያነብ፣ ወይም ታሪኩን እንዲናገር ያድርጉ።

ከዚያም እናት ለዳንኤል ፀሎት በጣም አስፈላጊው እንደነበር ገለፀችላት፣ በመፀለዩ እንኳን የሚሞት ቢመስለውም ፀለየ “አሁን ፀሎት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አውቀሻል፣ በፀሎትሽ አንድ ዓይነት እርዳታን ትፈልጊያለሽ?” በማለት አንን ጠየቀቻት።

ሌላ ጊዜ፣ አንና ጀኒፈር በመጯጯህ ይጣሉ ነበር። ሁለቱም አንድን ተመሳሳይ የሆነ አሻንጉሊት ይፈልጉ ነበር። እናቷ ወደ ልጇ መጥታ፣ “ለምን አሻንጉሊቱን በግማሽ ቆርጠን ለሁለታችሁም ቁርጥራጩን አንሰጣችሁም?” አለቻት።

አን “አይሆንም፣ በግማሽ አተቁረጪው።” አለች።

ጀኒፈር ግን “አዎን፣ ይሁን ይቀረጭ።” ስትል ጮኸች።

በዚህን ጊዜ እናት ስትመልስ፣ “የአን አሻንጉሊት ሊሆን ይገባል። እንዴት ማወቅ እንደምችል መገመት ትችያለሽ?” ከዚያም እርሷ ከልጃገረዶቹ ጋር በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 3፥16–27። የሚገኘውን ታሪክ በማንበብ ተወያዩበት።

የተመደበውን የክፍል አባል ከ1ኛ ነገሥት 3፥16–27 ያለውን ታሪክ እንዲያነብ ወይም እንዲናገር ያድርጉ።

ይህችን እናት ልጆቿን እንድታስተምር ቅዱሳን መፅሀፍት እንዴት አድርገው ረዷት? ሔኑስ 1፥2–5፣ ማቴዎስ 25፥1–13፣ እና ትምህርትና ቃል ኪዳን 40፥1–3 ያንብቡ።

**ቅዱሳን መጽሐፍትን ለማስተማር መዘጋጀት**

ፕሬዚዳንት ሐሮልድ ቢ ሊ እንደተናገሩት፣

“እኔ እንደምለው ሕዝባችንን በቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ መልሶቻቸውን እንዲፈልጉ ማስተማር አለብን . . . ነገር ግን መጥፎው አጋጣሚ ቢኖር ብዙዎቻችን ቅዱሳን መጽሐፍትን

አለማንበባችን ነው። በውስጣቸው ያለውን አናውቅም። እና ስለሆነም በቅዱሳን መፃሕፍቱ ማግኘት ስለምንችላቸው ነገሮች ግምቶችን እናደርጋለን። እኔ በዘመናችን ያለው አንዱና ታላቁ አደጋ ይህ ነው በማለት አስባለሁ።” (“Find the Answers in the Scriptures,” *Ensign,* Dec. 1972, p. 3.)

ቅዱሳን መጽሐፍትን እንድናጠና ማንም አያስገድደንም። እኛ ላለማጥናት ብዙ ምክንያቶችን ማግኘት እንችላለን። ለቅዱሳን መፃሕፍት ጥናት ማቀድ ያስቸግራል። በድንገተኛ ድርጊት ወይም በአጋጣሚ ማከናወን የለብንም። (በዚህ መመሪያ መፅሐፍ ትምህርት 32 ይመልከቱ።)

ቅዱሳን መጽሐፍት ላለማጥናት ምን ምን ዓይነት ምክንያቶች እንጠቀማለን? እነዚህን እንቅፋቶች እንዴት ማሸነፍ እንችላለን?

ከቅዱሳን መጽሐፍት ማስተማር ብንፈልግ፣ ልክ ባለማሰብ ከምናነባቸው ይልቅ የበለጠ ማድረግ ይገባናል።

የክፍል አባላትን ሞሮናይ 10፥3 እንዲያነቡ ያድርጉ። ሞሮናይ ከቅዱሳን መጽሀፍት ስለመማር ምን ይነግረናል?

ሞሮናይ፣ የቅዱሳን መጽሐፍትን እውነት ከተቀበልን በኋላ፣ በልባችን ልናገናዝባቸው እንደሚገባን ይነግረናል። ፕሬዚዳንት ማሪዮን ጂ ሮምኒ፣ “ቅዱሳን መጽሐፍትን እንዳነበብኩ፣ *ማገናዘብ* በሚለው ቃል ተቸገርኩ . . . መዝገበ ቃላት እንደሚለው *ማገናዘብ* ማለት በአዕምሮ ውስጥ መለካት፣ ስለነገሩ በጥልቀት ማሰብ፣ የሚታሰብበት፣ ከልብ ማሰላሰል . . .

“*ማገናዘብ*፣ በእኔ ስሜት፣ የፀሎት ዓይነት ነው። ቢያንስ ለጌታ መንፈስ አቀራረብ እንደሆነ ነው።” (In Conference Report, Apr. 1973, p. 117; “Magnifying One’s Calling in the Priesthood,” *Ensign,* July 1973, p. 90.)

ሞሮናይ 10፥3–4 ማገናዘብ እንዳለብን (እነዚህን ነገሮች በአእምሮአችን እንድናጠና) ይነግረናል። ከዚያም በኋላ የሰማዩ አባታችንን እውነት እንደሆኑ መጠየቅ አለብን። እርሱም እውነት መሆናቸውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንድናውቅ ያደርገናል።

## ማጠቃለያ

ቅዱሳን መጽሐፍትን ለማስተማር፣ በየጊዜው በማንበብ *መዘጋጀት* ይገባናል። ስላነበብነው በማሰብ *ማገናዘብ* ይገባናል። በእውነት፣ ከልብ *መፀለይ* ይገባናል። ከዚያም በኋላ ያወቅነውን እና በመንፈስ የተረዳነውን *መተግበር* ይገባናል። ይህን ካደረግን በኋላ፣ ቅዱሳን መጽሐፍትን በኃይል *ማስተማር* እንችላለን።

## ሙከራ

በዚህ ሳምንት አስፈላጊ ጥቅሶችን ምልክት ማድረግን ጀምሩ። ቅዱሳን መጽሐፍትን ከህይወታችሁ ጋር አነፃፅሩ። በቤተሰብ የቤት ምሽት፣ በምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ፣ ወይንም በሌላ በቤተሰብ ሁናቴዎች፣ ስለቅዱሳን መጽሐፍት ታሪኮች ተነጋገሩ። ከህይወታችሁም ጋር ቅዱሳን መጽሐፍትን አገናዝቡ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

2ኛ ኔፊ 4፥15–16 (ኔፊ ለቅዱሳን መፅሐፍት ያለው ፍቅር)
2ኛ ኔፊ 32፥3–7 (የክርስቶስን ቃል መመገብ)

## አልማ 37፥38–47 (አልማ ለልጁ ሂለማን ቅዱስ ትምህርት ሲሰጠው)
## ት እና ቃ 11፥21–22 (የእግዚአብሔርን ቃል ያግኙ)

**የመምህሩ ዝግጅት**

ይህን ትምህርት ከማቅረብዎ በፊት፥

1. *የወንጌል መሰረተ ሃሳቦች* ምዕራፍ 10፣ “ቅዱሳን መጽሐፍት” የሚለውን ያንብቡ።
2. የክፍል አባላትን ቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸውን ወደ ክፍል እንዲያመጡ ያሳስቧቸው።
3. የክፍሉ አባላት በዚህ ትምህርት የተጠቀሰውን ታሪኮችና ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቡ።

# በመንፈስ ቅዱስ ሃይልና ተፅዕኖ ማስተማር

ትምህርት 35

የዚህ ትምህርት ዓላማ ወንጌልን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ተፅዕኖ ለማስተማር እንዲረዳን ነው።

**መግቢያ**

ጌታ ስለ መንግስቱ እርስ በርሳችን እንድንማማር አዞናል (ት እና ቃ 88፥77 ይመልከቱ)። ለማስተማር፣ የተመለሰውን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ምስክርነት ሊኖረን ይገባል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ተፅዕኖ ማስተማር ይገባናል።

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ፥ "መምህራን፣ የትምህርታችሁን ዝግጅት በፀሎት ጀምሩ። ትምህርታችሁን ከልብ በሆነ ጸሎት ስጡ። ከዚያም እግዚብሔር መልዕክታችሁን . . . በመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ እንዲያደርስ ጸልዩ።" (*Gospel Ideals,* p. 223.)

ቄስ ሐርትማን ሬክተር፣ ጁኒየር፣ ስለ ፕሬዚዳንት ሐሮልድ ቢ ሊ ታሪክ ሲናገሩ፥

"ለፕሬዚዳንትነት ሹመት ከበቁ ከትንሽ ጊዜ በኋላ፣ . . . አንድ ጋዜጠኛ . . . ሲጠይቀ፣

" 'በአስተዳደርዎ ዘመን እንደቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንትነትዎ ምን ለማከናወን ያቀዳሉ? . . .'

"እርሳቸውም "ደህና" አሉ፣ በጌታ አማካይነት የጥንት መዝገቦችን እንዲጠብቀ ስራ በተሰጠው ጊዜ በታላቁ ነቢይ በተናገረው ቃል ብቻ ያንን ጥያቄ መመለስ እችላለሁ። እርሱም እንዲህ ብሏል፣

" 'እናም ማድረግ የሚገቡኝን ነገሮች አስቀድሚ ስላላወቀኩ፣ በመንፈስ ተመራሁ።" (2ኛ ኔፊ 4፥6) ("You Shall Receive the Spirit," *Ensign,* Jan. 1974, p. 106.)

እንደ መምህራን፣ እኛ ደግሞ በመንፈስ መመራት ይገባናል። ዛሳባችን የእግዚአብሔር ዛሳብ አይደለም። መንገዳችንም የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም። (ኢሳያስ 55፥8–9 ይመልከቱ።) የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለማስተማር የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሊኖረን ይገባል።

የክፍል አባሎችን ት እና ቃ 42፥12–14 እንዲያነቡ ይጠይቋቸው። እንድናስተምር የተነገረን ምንድነው? እነዚህን መሰረተ ዛሳቦች ከየት እናገኛቸዋለን? የምናስተምርበትን መንፈስ እንዴት እናገኛለን? የመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ ከሌለን፣ ለምን ማስተማር አይገባንም?

የመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ የአስተማሪውን ቃላት በአድማጮቹ ልብ ውስጥ በጥልቁ እንዲሰምጡ ያደርጋል፥ "አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሚናገርበት ጊዜ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መልዕክቱን ወደ ሰዎች ልብ ይወስዳል" (2ኛ ኔፊ፣ 33፥1)።

ስዕላዊ መግለጫ 35-ሀ፣ ንጉሥ ቢንያም ከከፍተኛ ግንብ ላይ ሆኖ ልጆቹን ሲያስተምር ያሳያል።


35-U

ንጉሥ ቢንያም ልዩ መመሪያዎችን ሊሰጣቸው ሕዝቡን በአንድነት ሰበሰበ። በመንፈስ ሊያጠናክራቸው ፈለገ።

ክፍሉን ሞዛያ 5፥1–2 እንዲያነቡ ይጠይቁ። ንጉሥ ቢንያም የተናገረውን ቃል ሕዝቡ እንዲያምኑ ያደረገው ምንድነው? ክፍሉ ሞዛያ 5፥3–4 እንዲያነብ ይጠይቁ። እምነታቸው እንዴት በልምዳቸው ላይ ተፅዕኖን ሊያደርግ ቻለ?

## የመንፈስ ቅዱስ መመሪያን ማግኘት

የሞዛያ ልጆች ወንጌልን በመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ አስተማሩ። እነርሱ ይህን መመሪያ ከብዙ ጥረት በኋላ አገኙ።

ክፍሉን አልማ 17፥2–3 እንዲያነብ ይጠይቁ። የሞዛያ ልጆች በኃይል ለማስተማር ሶስቱ የተከተሏቸው ደረጃዎች ምንድናቸው? ሶስቱን ደረጃዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ። (ቅዱሳን መፃሕፍትን አጠኑ፣ ጾሙ፣ እና ፀለዩ)

የጥናቱን ዝግጅት ከፈፀመ በኋላ፣ መምሕሩ መፀለይ ይገባዋል።

ፕሬዚዳንት ማሪዮ ጂ ሮምኒይ ስለሚስታቸው በመንፈስ የማስተማር ልምድ ይናገራሉ። ነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ አብንና ወልድን ያየበትን ራዕይ በተመለከተ ትምህርት ልትሰጥ ነበር። በክፍሏ ውስጥ አባል ያልሆነች የዩንቨርሲቲ ምሩቀ ነበረች። እህት ሮምኒይ ትምህርቷ በዚህች ምሁር ሴት ተቀባይነት አይኖረውም ስትል ፈራች፣ እናም እራሷም ብትሆን እውነት ነው ብላ ለማወቋ እርግጠኛ አልነበረችም።

ችግሩን ከእናቷ ጋር በመወያየት፣ እህት ሮምኒይ እንዲህ አለች፣ "'ያን ትምህርት መስጠት አልችልም። ዮሴፍ ስሚዝ ያንን ራዕይ እንዳየ አላውቅም።'

"እናቷ የተማሩ ሴት አልነበሩም፣ ነገር ግን ምስክርነት አላቸው። ለልጇ፣ 'ነብዩ እንዴት ራዕይ እንዳየ ታውቂያለሽ፣ አታውቂምን?' አለች

" 'አዎን፣ . . . ስለጥበብ ለእግዚአብሔር በመፀለይ አገኘ' . . .

"(እህት ሮምኒይ) ወደ ክፍሏ ሄዳ ሞከረች . . . ውጤቱ ያንን ትምህርት . . . በሚያሳምን ሁኔታ፣ በኃይል ከተፈጥሮ ችሎታዎቿ በላይ መስጠት ነበር። እንዴት ማድረግ ቻለች? አዎን፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሷ መጥቶ ለጥያቄዎቿ መልስ ሰጣት። በነፍሷ ውስጥ መቃጠልን አገኘች። ዮሴፍ ስሚዝ እስከሚያውቀው ድረስ ራዕይ ማየቱን አወቀች። ነብዩ ያየውን ተመሳሳይ ነገር በትክክል በዓይኗ አላየችም፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ዕውቀት ነበራት። ከዮሴፍ ስሚዝ መግለጫ ያየውን አወቀች፣ እናም ታሪኩ እውነት እንደነበረ ከመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ነበራት።" ("How to Gain a Testimony," *New Era,* May 1976, pp. 10–11.)

እህት ሮምኒይ ምን ደረጃዎችን ተከተለች? እነዚህን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከተዘረዘሩት ሶስቱ ደረጃዎች ጋር አያነፃፅሩም። ለብቻ ማጥናት ለምን በቂ አስተማማኝነት አልሰጣትም? እህት ሮምኒይ ያገኘችውን እማኝነት ምን ብለን እንጠራዋለን? (ምስክርነት)።

ዝምብሎ እውነትን በማንበብና የምታምኑት ሰው ይህ ነገር እውነት ነው ብሎ በመናገሩ መካከል ምን ልዩነት አለ? የክፍል አባላት ሞሮናይ 10፥4–5 እንዲያነቡ ያድርጉ። መንፈስ ቅዱስ እንዴት እውነትን ይነግረናል? ይህን ምስክርነት ለማግኘት ምን ማድረግ አለብን?

## ምስክርነትን መስጠት

በምስክርነት ማስተማር ማለት በዕውቀት ወንጌሉ እውነት መሆኑን ማስተማር ማለት ነው። በመንፈስ ምስክርነት፣ ሌሎች የተመለሰውን ወንጌል እንዲረዱ መርዳት እንችላለን። መንፈስ

35-ሀ ንጉስ ቢንያም ሕዝቡን ከከፍተኛ ግንብ ላይ ሆኖ ያስተምራል።

ቅዱስ የወንጌልን መሰረተ ሃሳቦች ለአድማጮች መመስከር ይችላል። (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥12–13 ይመልከቱ።)

ስዕላዊ መግለጫ 35-ለ፤ ሁለት ሚስዮናውያን በእውነት መርማሪ ቤት ደጃፍ እንዳሉ ያሳያል።

ቄስ ኣልቪን አር ዳየር የሚከተለውን ታሪክ ተናገሩ፥

"ሁለት ሚሲዮናውያን ጥቂት ከሰዓት ቀደም ብሎ በአንድ ቤት ደረሱ . . . ቤተሰቡ . . . ለምሽት እራት ይዘጋጁ ነበር። ሚሲዮናውያኑ በበር ለበር መልዕክታቸው ብዙም አልተሳካላቸውም። አንዲት ሴት በር መዝጋት ጀምራለች። ሚሲዮናውያኑ ውጭ ሆነው ስለ ወንጌሉ እውነተኛነትም መሰከሩ። ከሚስዮናዊያኑ አንዱ ሆነ ብሎ ድምፁን ከፍ በማድረግ ውስጥ ያሉት በሚሰሙበት ሁኔታ ተናገረ። ወንጌላውያኑ ከመግባት ይልቅ በፍጥነት ተመልሰው ሄዱ።

"ከመደዳው ሰፈር ገሚሱን ያህል እንደሄዱ አንድ ሰው ሲጠራቸው ሰሙ . . . አንድ ዕድሜው 14 ዓመት ገደማ የሆነው ወጣት ደረሰባቸው እና "አባቴ እንድትመለሱ ይፈልጋችኋል" አላቸው። ስለሆነም ወደ ቤት በፍጥነት ተመለሱ። አባት ቀደም ሲል በድጋሚ አንዱ ምስክርነቱን ሲሰጥ እስከሚሰማ ድረስ በበራፍ ላይ ሆነው በተናገሩት ስሜቱ እንዳልተነካ ተናገረ። "ባዕድ የሆነ ስሜት በላዩ መጣ፤ እናም እናንተን መልሰን በመሰደዳችን ስህተት መሥራታችንን አወቅሁ" አለ። ይህ የሚያነቃቃ ፍላጎት፤ በምስክርነትና በፅኑ እምነት የተከናወነው ይህን ቤተሰብ ወደ ጥምቀት መራው።" ("When Thou Art Converted," *Instructor,* July 1961, p. 225.)

አባት ሚስዮናውያንን እንዲመለሱ ለምን አደረገ?

ሁለቱ የተመደቡ አህቶች ወንጌልን በሚማሩበት ጊዜ እንዴት እንደተሰማቸው እንዲናገሩ ያድርጓቸው።

**ማጠቃለያ**

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንደ ወላጆችና አስተማሪዎች፤ የምናስተምራቸውን ሕይወት ለመለወጥ ተጠርተናል። ለውጥ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ነው። በመንፈስ ቅዱስ በማስተማር፤ እውቀትን፤ ማስተዋልን፤ ምስክርነትን እና እምነትን . . . በራሳችንና በምናስተምራቸውም ውስጥ እንጨምራለን። ብቁዎች መሆንና በመንፈስ ቅዱስ ለማስተማር መዘጋጀት ይገባናል። ይህን ካደረግን፤ እውነትን እናስተምራለን። የመንፈስ ቅዱስ መመሪያ የሚመጣው እንደ ጥናታችን፤ ፀሎታችን፤ እና የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንደጠበቅን ነው።

"እናም በእምነት ፀሎት መንፈስ ይሰጣችኋል፤ እናም መንፈስን የማትቀበሉ ከሆነ፤ ማስተማር አትችሉም። . . .

"በአጽናኙ ድምፃችሁን አንስታችሁ ትናገራላችሁ፤ ለእኔ መልካም እንደሆነ ትናገራላችሁ እናም ትተነብያላችሁ፤

"እነሆ፤ አጽናኙ ሁሉንም ነገሮች ያውቃልና።" (ት እና ቃ 42፥14፤ 16–17።)

35-ለ ሁለት ወንጌላዊያን በእውነት ፈላጊዎች በራፍ ላይ ሆነው



35-ለ

## ሙከራ

የመንፈስ ቅዱስ መመሪያን በማጥናት፣ በመፀለይ፣ እና በመፆም ይፈልጉ። እነዚህ ለማስተማር ለማዘጋጀት የሚረዱ ቀደም ተከተሎች ናቸው። ልጆችን፣ ጓደኞችን እና ጎረቤትን ለማስተማር አጋጣሚዎችንና ጥበብዎን ያስተውሉ።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

ሉቃስ 24፥32 (የደቀመዛሙርት ልብ በውስጣቸው ይቃጠላል)
ዮሐንስ 14፥26 (መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገሮች ያስተምራል)
2ኛ ኔፊ 32፥7–8 (መንፈስን ያዳምጡ)
ሞዛያ 23፥14 (መምህር የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን)
አልማ 5፥43-52 (አልማ ስለመንፈስ ቅዱስ ይመሰክራል)
ሞሮናይ 10፥7-10 (በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ስጦታ)

---

### የመምህሩ ዝግጅት

ይህን ትምህርት ከማቀረብዎ በፊት፥

1. የመንፈስ ቅዱስ እርዳታን ለማግኘት በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ቀደም ተከተሎች ይከተሉ።
2. ሁለት የክፍል አባላት ወንጌልን በሚማሩበት ጊዜ የተሰማቸውን እንዲናገሩ ይመድቧቸው።
3. የክፍሉ አባላት በዚህ ትምህርት ውስጥ ታሪኮችንና የቅዱሳን መጽሐፍት ጥቅሶችን እንዲያቀርቡ ይመድቧቸው።

## የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንቶች

### 1. ዮሴፍ ስሚዝ

የመጀመሪያው የዮሴፍ ስሚዝ፣ እና የሉሲ ማክ ስሚዝ ልጅ፣ በሻሮን ዊንድሶር አካባቢ በቨርሞንት ታህሳስ 23 ቀን 1805 ዓ.ም ተወለደ። በግንቦት 1829 ዓ.ም በአነ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣንን (በሐዋሪያት ተካነ) ተቀበለ። (ት እና ቃ 20፡2፣ 27፡12 ይመልከቱ)፣ በሚያዝያ 6 ቀን 1830 ዓ.ም እንደ የመጀመሪያ ቄስ በመሆን በ24 ዓመት ዕድሜው ተመረጠ፣ በሰኔ 3 ቀን 1831 ዓ.ም በሊይማን ዊት ለሊቀካህንነት ተሾመ፣ በጥር 25 ቀን 1832 ዓ.ም በአመሔርሰት በሎረን አካባቢ፣ በኦህዩ ጉባኤ እንደ ሊቀካህናት ፕሬዚዳንት ተመረጠ፣ በሰኔ 27 ቀን 1844 ዓ.ም በካርተጅ ወህኒ ቤት ካርተጅ ዛንኮክ አካባቢ በአሊኖይስ ውስጥ በ38 ዓመቱ ሰማዕት ሆነ።

### 2. ብርግሃም ያንግ

የዮሐንስ ያንግ እና የአቢጌል ሆዌ ያንግ ልጅ፣ በዊትንግሃም ዊንድሃም አካባቢ፣ በቨርሞትን፣ ሰኔ 1 ቀን 1801 ተወለዱ። በየካቲት 14 ቀን 1835 ዓ.ም በሶስቱ የመጽሐፈ ሞርሞን ምስክሮች በሐዋሪያነት ተካኑ፣ በሚያዝያ 14 ቀን 1840 ዓ.ም የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዚዳንት በመሆን ተመረጡ፣ በታህሳስ 27 ቀን 1847 በ46 ዕድሜአቸው የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት በመሆን ተመረጡ፣ በነሐሴ 29 ቀን 1877 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ፣ በ76 ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

### 3. ጆን ቴይለር

የጀምስ ቴይለር እና የአግንስ ቴይለር ልጅ። ታህሳስ 19 ቀን 1838 ዓ.ም በብርግሃም ያንግ እና ሄበር ሲ. ኪምቦል በሐዋሪያነት ተካኑ፣ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዝዳንት ጥቅምት 6 ቀን 1877 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ጥቅምት 10 ቀን 1880 ዓ.ም በ71 ዓመታቸው ተመረጡ፣ ሐምሌ 25 ቀን 1887 ዓ.ም በ78 ዓመታቸው ኬይስቪል፣ ደቪስ አካባቢ፣ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

### 4. ዊልፎርድ ውድሩፍ

የአፌክ ውድሩፍ እና ቡሉ ታምፕሰን ውድሩፍ ልጅ፣ በአቮን (ፋርሚንግተን)፣ ሐርት ፎርድ አካባቢ፣ ኮነክቲከተ መጋቢት 1 ቀን 1807 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋሪያነት ሚያዝያ 26 ቀን 1839 ዓ.ም በብርግሃም ያንግ ተካኑ፣ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዚዳንት ጥቅምት 10 ቀን 1880 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ሚያዝያ 7 ቀን 1889 ዓ.ም በ82 ዓመታቸው ተመረጡ፣ መስከረም 2 ቀን 1898 ዓ.ም በሳንፍራንሲስኮ አካባቢ፣ ካሊፎርኒያ በ91 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

### 5. ሎሬንዞ ስኖው

የኦሊቨር ስኖው እና የሮሲታ ሌኦኖራ ፔቲቦን ስኖው ልጅ በማንቱአ፣ ፓርተጅ አካባቢ፣ በኦሃዮ በሚያዝያ 3 ቀን 1814 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋሪያነት የካቲት 12 ቀን 1849 ዓ.ም በሄበር ሲ ኪምቦል ተካኑ፣ ለፕሬዚዳንት ብርግሃምያንግ በአማካሪነት ሚያዝያ 8 ቀን 1873 ዓ.ም ተመረጡ፣ ለፕሬዚዳንት ብርግሃም ያንግ ረዳት አማካሪነት ግንቦት 9 ቀን 1874 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዚዳንት ሚያዝያ 7 ቀን 1889 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት መስከረም 13 ቀን 1898 ዓ.ም በ84 ዓመታቸው

ተመረጡ፣ ጥቅምት 10 ቀን 1901 በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ ውስጥ በ87 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

**6. ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ**

የሃይረም ስሚዝና ሚሪ ፊልዲንግ ስሚዝ ልጅ በሩቅ ምዕራብ፣ ካልድዌል አካባቢ፣ ሙዙሪ፣ ሕዳር 13 ቀን 1838 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት እና በቀዳሚ አመራር አማካሪነት ሐምሌ 1 ቀን 1866 ዓ.ም በብርግሃም ያንግ ተሾሙ፣ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን አባል ጥቅምት 8 ቀን 1867 ዓ.ም ተካኑ፣ ነሐሴ 29 ቀን 1877 ፕሬዚዳንት ያንግ በመሞታቸው ከቀዳሚ አመራር አማካሪነት ለቀቁ፣ በጥቅምት 10 ቀን 1880 ዓ.ም የፕሬዚዳንት ጆን ቴይለር ሁለተኛ አማካሪ በመሆን ተመረጡ፣ ሐምሌ 25 ቀን 1887 ፕሬዚዳንት ቴይለር በመሞታቸው ከአማካሪነታቸው ሲለቁ፣ ሚያዝያ 7 ቀን 1889 ዓ.ም ፕሬዚዳንት ዊልፎርድ ውድሩፍ በሁለተኛ አማካሪነትም ተመረጡ፣ መስከረም 13 ቀን 1898 ለፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖው ሁለተኛ አማካሪ በመሆን ተመረጡ። በጥቅምት 6 ቀን 1901 ዓ.ም የፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖው ተቀዳሚ አማካሪ ሆነው ተመረጡ፣ ሆኖም ግን ይህን ማዕረግ ሳይረከቡ፣ ጥቅምት 10 ቀን 1901 ዓ.ም በፕሬዚዳንት ስኖው ሞት ምክንያት ሥልጣናቸውን ለቀዋል፣ ጥቅምት 17 ቀን 1901 በ62 ዓመታቸው የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት በመሆን ተመረጡ፣ ህዳር 19 ቀን 1918 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ ውስጥ በ80 ዓመታቸው አረፉ።

**7. ሒበር ጀዲ ግራንት**

የጀዲዲያ ሞርጋን ግራንትና ራሄል ሪድግዋይ አይቪንስ ግራንት ልጅ በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ በህዳር 22 ቀን 1856 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት ጥቅምት 16 ቀን 1882 ዓ.ም በጆርጅ ኦ. ካኖን ተሾሙ፣ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንት በመሆን ጥቅምት 23 ቀን 1916 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ ቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንት ህዳር 23 ቀን 1918 ዓ.ም በ62 ዓመታቸው ተመረጡ፣ በግንቦት 14 ቀን 1945 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ ውስጥ በ88 ዓመታቸው አረፉ።

**8. ጆርጅ አልበርት ስሚዝ**

የጆን ሄነሪ ስሚዝ እና ሣራ ፋር ስሚዝ ልጅ በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ ውስጥ ሚያዝያ 4 ቀን 1870 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት ጥቅምት 8 ቀን 1903 ዓ.ም በዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ ተሾሙ፣ በአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዚዳንት ሐምሌ 1 ቀን 1943 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት በግንቦት 21 ቀን 1945 ዓ.ም በ75 ዓመታቸው ተመረጡ፣ በሚያዝያ 4 ቀን 1951 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፣ ሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ ውስጥ በ81 ዓመታቸው አረፉ።

**9. ዴቪድ ኦ ማኬይ**

የዴቪድ ማኬይ እና ጄነት ኢቫንስ ኤቡንስ ማኬይ ልጅ፣ በሀንትስቪል፣ ዌበር አካባቢ፣ ዩታ ውስጥ በመስከረም 8 ቀን 1873 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት ሚያዝያ 9 ቀን 1906 ዓ.ም በዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ ተሾሙ፣ ለፕሬዚዳንት ሒበር ጀ. ግራንት ሁለተኛ አማካሪነት ጥቅምት 6 ቀን 1934 ዓ.ም ተመረጡ፣ ለፕሬዚዳንት ጆርጅ አልበርት ስሚዝ ሁለተኛ አማካሪነት ግንቦት 21 ቀን 1945 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንት መስከረም 30 ቀን 1950 ዓ.ም ተመረጡ፣ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ሚያዝያ 9 ቀን

1951 በ77 ዓመታቸው ተመረጡ፤ ጥር 18 ቀን 1970 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፤ ሶልት ሌክ አካባቢ በ96 ዓመታቸው አረፉ።

### 10. ዮሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ

የዮሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ እና ጁሊና ላምብሰን ስሚዝ ልጅ በሶልት ሌክ ሲቲ፤ ሶልት ሌክ አካባቢ ሐምሌ 19 ቀን 1876 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት ሚያዝያ 7 ቀን 1910 ዓ.ም በዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ ተሾሙ፤ ለአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን እንደ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት በመሆን መስከረም 30 ቀን 1950 ዓ.ም ተመረጡ፤ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንት ሚያዝያ 9 ቀን 1951 ዓ.ም ተመረጡ፤ እንደ ቀዳሚ አመራር አማካሪ ጥቅምት 29 ቀን 1965 ዓ.ም ተመረጡ፤ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ጥር 23 ቀን 1970 ዓ.ም በ93 ዓመታቸው ተመረጡ፤ በሐምሌ 2 ቀን 1972 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፤ ሶልት ሌክ አካባቢ፤ ዩታ ውስጥ በ95 ዓመታቸው አረፉ።

### 11. ሐሮልድ ቢንግሃም ሊ

የሳሙኤል ኤም ሊ እና ሉዊሳ ብንግሃም ሊ ልጅ፤ በክሊፍተን፤ ኦነይዳ ካውንቲይ፤ አይዳሆ ውስጥ መጋቢት 28 ቀን 1899 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት ሚያዝያ 10 ቀን 1941 ዓ.ም በሔበር ጀ ግራንት ተሾሙ፤ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንት ጥር 23 ቀን 1970 ዓ.ም ተመረጡ፤ ለፕሬዚዳንት ዮሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ ቀዳሚ አማካሪነት ጥር 23 ቀን 1970 ዓ.ም በ70 ዓመታቸው ተመረጡ፤ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ሐምሌ 7 ቀን 1972 ዓ.ም በ73 ዓመታቸው ተመረጡ፤ በታህሳስ 26 ቀን 1973 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፤ ሶልት ሌክ አካባቢ፤ ዩታ ውስጥ በ74 ዓመታቸው አረፉ።

### 12. ስፔንሰር ውሊ ኪምቦል

12. የአንድሪው ኪምቦል እና ኦሊቭ ውሊ ኪምቦል ልጅ በሶልት ሌክ ሲቲ፤ ሶልት ሌክ አካባቢ፤ ዩታ ውስጥ መጋቢት 28 ቀን 1895 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋሪያነት ጥቅምት 7 ቀን 1943 ዓ.ም በሔበር ጀ ግራንት ተሾሙ፤ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን እንደ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት በመሆን ጥር 23 ቀን 1970 ዓ.ም ተመረጡ፤ የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት በመሆን ታህሳስ 30 ቀን 1973 ዓ.ም በ78 ዓመታቸው ተመረጡ፤ ህዳር 5 ቀን 1985 ዓ.ም በሶልት ሌክ ሲቲ፤ ሶልት ሌክ አካባቢ፤ ዩታ ውስጥ በ90 ዓመታቸው አረፉ።

### 13. እዝራ ታፍት ቤንሰን

የጆርጅ ቲ ቤንሰን እና ሣራ ዱንክሌ ቤንሰን ልጅ፤ በዊትኔ፤ ኦኔኢዳ አካባቢ፤ አይዳሆ ውስጥ ነሐሴ 4 ቀን 1899 ዓ.ም ተወለዱ። በሐዋርያነት ጥቅምት 7 ቀን 1943 ዓ.ም በሔበር ጀ ግራንት ተሾሙ፤ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንት ታህሳስ 30 ቀን 1973 ዓ.ም በ74 ዓመታቸው ተመረጡ፤ እንደ ቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ህዳር 10 ቀን 1985 ዓ.ም በ86 ዓመታቸው ተመረጡ፤ ቤተክርስቲያን ጥቅምት 10, 1985 በ86፤ ግንቦት 30, 1994 በሶልት ሌክ ሲቲ፤ በሶልት ሌክ አካባቢ ዩታ በ94 ዓመታቸው ሞቱ።

## 14. ሀዋርድ ድብሊው ሀንተር

የጆን ዊልያም ሀንተር እና የኔሊ ማሪ ራምሰን ሀንተር ልጅ በቦይስ፣ አዳ አካባቢ፣ አይዳሆ፣ ጥቅምት 14, 1907 ተወለዱ። ጥቅምት 15, 1959 በዴቪድ ኦ ሚኬይ ሐዋርያ ሆነው ተሾሙ፤ ጥቅምት 10, 1985 በአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንቱን ተክተው ለመስራት ተሾሙ፤ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዚዳንት ሆነው ሰኔ 2, 1988፤ በ80 ዓመታቸው ተሾሙ፤ የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ሆነው ሰኔ 5, 1994 በ86 ዓመታቸው ተሾሙ፤ በመጋቢት 3 1995 በሶልት ሌክ ሲቲ፣ በሶልት ሌክ አካባቢ፣ ዩታ በ87 ዓመታቸው ሞቱ።

## 15. ጎርደን ቢ ሂንክሊ

ሰኔ 23, 1910 በሶልት ሌክ አካባቢ፣ ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ፣ ከብራያንት ኤስ ሂንክሊ እና ከአዳ ቢትነር ሂንክሊ ተወለዱ። ለአስራ ሁለቱ እንደ ረዳት ሆነው ሚያዝያ 1958 ተሾሙ፤ በዴቪድ ኦ ሚኬይ ጥቅምት 5, 1961 ተሾሙ፤ ሐምሌ 23, 1981 ለፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው እንደ አማካሪ ሆነው ተሾሙ፤ ታህሳስ 2, 1982 ለፕሬዚዳንት ኪምቦል እንደ ሁለተኛ አማካሪ ተመረጡ፤ ለእዝራ ታፍት ቤንሰን እንደ አንደኛ አማካሪ ሆነው ህዳር 10, 1985 ተሾሙ፤ ሰኔ 5, 1994 ለፕሬዚዳንት ሀዋርድ ደብሊው ሀንተር እንደ አንደኛ አማካሪ ሆነው ተሾሙ፤ መጋቢት 12, 1995፤ በ84 ዓመታቸው የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት ሆነው ተሾሙ።

# Sources Cited


Brown, Hugh B. *The Abundant Life.* Salt Lake City: Bookcraft, 1965.

Cannon, George Q. *Gospel Truth: Discourses and Writings of President George Q. Cannon.* Selected by Jerreld L. Newquist, Salt Lake City: Deseret News Press, 1957.

The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints. *Official Report of the First Mexico and Central America Area General Conference of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints.* Salt Lake City: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1973.

_____ *Official Report of the Korea Area Conference.* Salt Lake City: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1977.

_____ *Official Report of the São Paulo Area Conference.* Salt Lake City: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1977.

Clark, J. Reuben, Jr. "The Charted Course of the Church in Education." An address given on 8 Aug. 1938 to the Church seminary and institute leaders.

_____ *Immortality and Eternal Life,* vol. 2, Melchizedek Priesthood Course of Study. Salt Lake City: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1969.

Cowley, Matthew. *Matthew Cowley Speaks: Discourses of Elder Matthew Cowley of the Quorum of the Twelve of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1954.

Evans, Richard L. *Thoughts . . . for One Hundred Days.* Salt Lake City: Publishers Press, 1966.

Grant, Heber J. *Gospel Standards: Selections from the Sermons and Writings of Heber J. Grant.* Compiled by G. Homer Durham. Salt Lake City: Deseret News Press, 1969.

Hoole, Daryl V., and Ockey, Donette V. *With Sugar 'n Spice.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1966.

*Inspirational Missionary Stories.* Compiled by Leon R. Hartshorn. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1976.

Jensen, Margie Calhoun. *When Faith Writes the Story.* Salt Lake City: Bookcraft, 1973.

*Journal of Discourses.* 26 vols. London: Latter-day Saints' Book Depot, 1954-86.

Kimball, Spencer W. *Faith Precedes the Miracle.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1972.

_____ *The Miracle of Forgiveness.* Salt Lake City: Bookcraft, 1969.

_____ "We Should Be a Reverent People." Pamphlet published by The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1976.

Lee, Harold B. *Stand Ye in Holy Places: Selected Sermons and Writings of President Harold B. Lee.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1974.

_____ *Ye Are the Light of the World.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1974.

McConkie, Bruce R. *Mormon Doctrine,* 2nd ed. Salt Lake City: Bookcraft, 1966.

McKay, David O. *Gospel Ideals: Selections from the Discourses of David O. McKay.* Salt Lake City: Deseret News Press, 1953.

_____ *Secrets of a Happy Life.* Compiled by Llewelyn R. McKay. Salt Lake City: Bookcraft, 1967.

_____ *Stepping Stones to an Abundant Life.* Compiled by Llewelyn R. McKay. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1971.

_____ *Treasures of Life.* Compiled by Clare Middlemiss. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1962.

Packer, Boyd K. *Teach Ye Diligently.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1975.

Pratt, Parley P. *Key to the Science of Theology.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1938.

Rector, Hartman and Connie. *No More Strangers.* 3 vols. Salt Lake City: Bookcraft, 1976.

*Remarkable Stories from the Lives of Latter-day Saint Women.* 2 vols. Compiled by Leon R. Hartshorn. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1976.

Roberts, B. H. *A Comprehensive History of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints: Century One.* 6 vols. Provo, Utah: Brigham Young University Press, 1957.

Smith, Joseph. *History of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints.* 6 vols. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1951.

_____ *Teachings of the Prophet Joseph Smith.* Selected by Joseph Fielding Smith. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1965.

Smith, Joseph F. *Gospel Doctrine.* 5th ed. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1939.

*Speeches of the Year.* BYU devotional and fireside addresses, published annually by Brigham Young University Press, Provo, Utah.

*Stories of Insight and Inspiration.* Compiled by Margie Calhoun Jensen. Salt Lake City: Bookcraft, 1976.

Tanner, N. Eldon. *Seek Ye First the Kingdom of God.* Compiled by LaRue Sneff. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1973.

*Webster's New Collegiate Dictionary.* Springfield, Mass.: G&C Merriam Co., 1975.

Whitney, Orson F. *Life of Heber C. Kimball.* Salt Lake City: Bookcraft, 1945.

Widtsoe, John A. *Man and the Dragon and Other Essays.* Salt Lake City: Bookcraft, 1945.

_____ *Priesthood and Church Government.* Salt Lake City: Deseret Book Co., 1965 printing.

*The World Book Encyclopedia.* 1977 ed.

Young, Brigham. *Discourses of Brigham Young.* Compiled by John A. Widtsoe. 1971 ed. Salt Lake City: Deseret Book Co., 1954.






# የክፍል ማስታወሻዎችና የቤት ሥራዎች

# ስዕሎች

1. የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንቶች
   ዮሴፍ ስሚዝ
   ብርግሃም ያንግ
   ጆን ተይለር
   ዊልፎርድ ውድሩፍ
   ሎሬንዞ ስኖው
   ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ
   ሒበር ጄ ግራንት
   ጆርጅ አልበርት ስሚዝ
   ዴቪድ ኦ ማኬይ
   ዮሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ
   ሐሮልድ ቢ. ሊ
   ስፔንሰር ደብልው ኪምቦል
   እዝራ ታፍት ቤንሰን
   ሀዋርድ ደብልው ሐንተር
   ጎርደን ቢ. ሂንክሊ (በላይኛው በቀኝ ማዕዘን)
2. ቀዳሚ አመራር
   ፕሬዚዳንት ጎርደን ቢ. ሂንክሊ
   ፕሬዚዳንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን (በግራ በኩል)
   ቀዳሚ አማካሪ
   ፕሬዚዳንት ጄምስ ኢ ፋውስት (በቀኝ በኩል)
   ሁለተኛ አማካሪ
3. የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን
   ቦይድ ኬ ፓከር፣ ኤል ቶም ፔሪ፣ ዴቭድ ቢ. ሐይት፣ ኒል ኤ. ማክስዌል፣ ሩፐል ኤም ነልሰን፣ ዳሊን ኤች ኦክስ፣ ኤም. ሩሴል በላርድ፣ ዮሴፍ. ቢ ዊርትሊን፣ ሪቻርድ ጂ. ስኮት፣ ሮበርት ዲ. ሄልስ፣ ጄፍሪ አር. ሆላንድ፣ ሄንሪ ቢ. ኤይሪንግ
4. ኢየሱስ ክርስቶስ
5. ወደ ግብጽ ሽሽት
6. መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቀ
7. ክርስቶስ ሐዋርያትን ሲሾም
8. ኢየሱስ በጌተሰማኒ ሲፀልይ
9. ማሪያምና የተነሳው ጌታ
10. ኢየሱስ ቁስሉን ሲያሳይ
11. ሊሂና ሕዝቡ በተስፋው ምድር ሲደርሱ


12. ሞሮናይ ሰሌዳዎቹን በኩሞራ ተራራ ውስጥ ሲደብቅ
13. የሶልት ሌክ ቤተመቅደስ
14. የቤተመቅደስ መዘምራን
15. ልጁ ሲጠመቅ
16. ወጣቷ ሴት አባልነቷ ሲጸድቅላት















































የኋለኛው ቀን ቅዱሳን

# የኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተክርስቲያን

4 02311 13506 6
31113 506